# የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር

የዜግነት ክብር በኢትዮጵያችን ፀንቶ፣
ታዬ ሕዝባዊነት ዳር እስከዳር በርቶ::
ለሰላም፣ ለፍትህ ለሕዝቦች ነፃነት፣
በእኩልነት በፍቅር ቆመናል ባንድነት::
መሠረተ ፅኑ ሰብዕናን ያልሻርን፣
ሕዝቦች ነን ለሥራ በሥራ የኖርን::
ድንቅ የባህል መድረክ የአኩሪ ቅርስ ባለቤት፣
የተፈጥሮ ፀጋ የጀግና ሕዝብ እናት፣
እንጠብቅሻለን አለብን አደራ፣
ኢትዮጵያችን ኑሪ እኛም ባንቺ እንኩራ::

## ይህን መፅሐፍ በጥንቃቄ ያዝ/ያዢ



- ይህ መጽሐፍ የትምህርት ቤትህ/ቤትሽ ንብረት ነው፡፡
- መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይንም እንዳይጠፋ በጥንቃቄ ያዝ/ያዥ፡፡
- ቀጥሎ መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ የሚረዱ 10 ነጥቦች ቀርበውልሃል/ቀርበውልሻል፡፡

1. መጽሐፉን እንደ ኘላስቲክ፣ ጋዜጣ ወይንም መሰል ወረቀቶች በመጠቀም ሸፍን/ሸፍኝ፡፡
2. ምንጊዜም መጽሐፉን በንፁህ እና ደረቅ ቦታ አስቀምጥ/አስቀምጭ፡፡
3. መጽሐፉን በምትጠቀምበት/በምትጠቀሚበት ወቅት እጆችህ/እጆችሽ ንፁህ መሆን አለባቸው፡፡
4. በመጽሐፉ ሽፋን ላይ ወይንም በውስጥ ገፆች ውስጥ አትፃፍ/አትፃፊ፡፡
5. ለመጽሐፉ የገፅ ማስታወሻ መያዝ ሲያስፈልግ ቁራጭ ወረቀት ተጠቀም/ተጠቀሚ፡፡
6. ከመጽሐፉ ውስጥ ገፆችን ወይንም ስዕሎች በፍፁም ቀደህ/ቀደሽ አታውጣ/አታውጪ፡፡
7. የተቀደዱ ገፆች ሲኖሩ በማጣበቂያ ወይንም በኘላስተር ጠግን/ጠግኚ፡፡
8. መጽሐፉን ከትምህርት ቤት ቦርሳህ/ቦርሳሽ ውስጥ በምታስገባበት/በምታስገቢበት እና በምታስወጣበት/በምታስወጪበት ጊዜ ጥንቃቄ ውሰድ/ውሰጂ፡፡
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው በምታቀብልበት/በምታቀብይበት ወቅት ጥንቃቄ አድርግ/አድርጊ፡፡
10. አዲስ መፅሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ በምትጠቀምበት/በምትጠቀሚበት ወቅት በመጀመሪያ መጽሐፉን በጀርባው አስቀምጥ/አስቀምጭ፡፡ ቀጥሎ በአንድ ጊዜ ጥቂት ገፆችን ብቻ ግለጥ/ግለጭ፡፡ መጽሐፉ የሚታጠፍበት ገፅ ላይ በዝግታ ጫን በማድረግ አስተካክል/አስተካክይ፡፡ ይህም ሽፋኑ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዲቆይ ይረዳል::

# የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ

## 7ኛ ክፍል

ፀሐፊዎች፡-

1. አቶ ሸዋቀና ቸርነት
2. አቶ ቦጋለ ስብሃቱ
3. አቶ አሰግደው ተስፋዬ
4. አቶ ተስፋዬ ከፋለ
5. አቶ ጌታቸው በለጠ
6. ወ/ሮ ፀሐይ መሳኩ
7. ወ/ሮ ውዳሳት ገዳሙ
8. ወ/ሮ የዝና ወርቁ
9. ወ/ሮ አጋረደች ጀማነህ
10. አቶ ብቃለ ሥዩም
11. አቶ የሻው ተሰማ

አዘጋጆችና አርታኢአን፡-

አቶ ግርማ አለማየሁ
አቶ ዳንኤል አበበ
አቶ ቱጁባ በቃና

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

AL GHURAIR
PRINTING AND PUBLISHING LLC

© ትምህርት ሚኒስቴር
የመጀመሪያ እትም 2003 ዓ.ም

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

ISBN 978-99944-2-054-4

# ማውጫ

ገፅ

ምዕራፍ አንድ፡- ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ........ 1
ምዕራፍ ሁለት፡- የሕግ የበላይነት ........ 16
ምዕራፍ ሦስት፡- እኩልነት ........ 28
ምዕራፍ አራት፡- ፍትሐዊነት ........ 41
ምዕራፍ አምስት፡- የሀገር ፍቅር ........ 54
ምዕራፍ ስድስት፡- የኃላፊነት ስሜት ........ 67
ምዕራፍ ሰባት፡- ጠንካራ የሥራ ባህል ........ 76
ምዕራፍ ስምንት፡- ራስን መቻል ........ 87
ምዕራፍ ዘጠኝ፡- የቁጠባ ባህል ........ 98
ምዕራፍ አሥር፡- ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ........ 112
ምዕራፍ አሥራ አንድ፡- ዕውቀትን መሻት ........ 123

# ምሥጋና

ይህ መጽሐፍ ፕሪቱ የተጠበቀ ሆኖ እንዲወጣ በርካታ ሰዎች ያልተቆጠበ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል። Ms. Myra Murphy ለመጽሐፉ አዘጋጆች ተማሪ አሳታፊና ምቹ የሆነ የመጽሐፍ አዘገጃጀት ሥልጠና በመስጠት ከፍተኛ ድጋፍ አድረገዋል። Ms. Myra Murphy በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ወጪያቸውን የሸፈነው የአውሮፓ ዩኒየን በመሆኑ ከፍተኛ ምሥጋና ይገባዋል።

በመጽሐፉ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉትን የተለያዩ ምስሎች በመለገስ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ኤጄንሲ፣ የኢትዮጵያ ባህልና ቱሪዝም ኮሚሽን፣ በወቅቱ የነበረው የማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበርና የኢትዮጵያ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ላደረጉት ድጋፍ ምሥጋና ሊቸራቸው ይገባል።

በአጠቃላይ ትምህርት የሥርዓተ ትምህርት መመሪያ ውስጥ የሚገኘው የመማሪያ ማስተማሪያ አዘገጃጀት ዩኒት መጽሐፉን ለማሣተም የሚያስችል የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀትና ለዓለም ባንክ በመስጠት ላደረገው አስተዋጽኦ ሊመሰገን ይገባዋል።

በተለይም የቪኤሶ ኢትዮጵያ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አባል የሆኑት Mrs. Helen Papworth መጽሐፉን ከወትሮ ለየት ባለመልኩ ፎርማት በማድረግ ልዩ አድናቆት የሚሰጠው ተግባር በማከናወናቸው ሊመሰገኑ የሚገባ ሲሆን፤ የቪኤሶ ኢትዮጵያም የበጎ ፈቃደኞች ወደሚኒስቴር መሥሪያ ቤታችን በመምጣት ሙያቸውን እንዲያካፍሉን በማድረጉ ከፍተኛ ምሥጋና ስናቀርብ በከፍተኛ ደስታ ነው።

# ምዕራፍ አንድ

# ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረታዊ መርሆዎችን ታውቃለህ /ታውቂያለሽ፣
- የግለሰብና የቡድን ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶችን ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ፣
- የፌደራልና የክልል መንግሥታትን ተግባራት ትረዳለህ/ትረጃለሽ፣
- የመንግሥት የሥልጣን አካላት አወቃቀርን ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ፣
- ልዩነቶችን አቻችሎ አብሮ የመኖር ጠቀሜታን ትረዳለህ/ትረጃለሽ፣
- ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሀገሮች ያበረከተችውን አስተዋፅኦ ታውቃለህ/ ታውቂያለሽ፣

## 1.1 የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መርሆዎች

### 1.1.1 ነፃ የፖለቲካ ሥልጣን ውድድር

- *ነፃ የፖለቲካ ሥልጣን ውድድር ማለት ምን ማለት ነው? ጥቅሙስ ምንድን ነው?*

የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አንዱ መርህ ነፃ የፖለቲካ ሥልጣን ውድድር መኖር ነው:: ነፃ የፖለቲካ ሥልጣን ውድድር ሲባል በመጀመሪያ ደረጃ የሚያመለክተው የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ ቢያንስ ሁለት እና ከዚያ በላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም ከየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ያልወገኑ ግለሰቦችም ሕገመንግሥቱን አክብረው ለምርጫው መወዳደር እንደሚችሉ ነው::

ይህም መራጩ ሕዝብ የሚፈልገውን ፓርቲ ወይም ግለሰብ በነፃነት እንዲመርጥ የሚያስችለው ምቹ ሁኔታ መኖሩን ያመለክታል:: ሕዝቡ ከምርጫው በፊትም ሆነ በምርጫው ወቅት የፈለገውን እንዳይመርጥ የሚያስፈራው ማንኛውም ለምርጫ እንቅፋት የሚሆን ነገር እንዳይኖር በቂ ጥንቃቄ እና ዝግጅት ይደረጋል::

ሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲዎችም ሆኑ ግለሰቦች መራጩን ሕዝብ ቀርበው ማነጋገር ይችላሉ:: ሆኖም ጠብና ግጭትን የሚጋብዙ ንግግሮች ማድረግ ፈፅሞ ክልክል ነው:: ይልቁንም መራጮችም ሆኑ ተወዳዳሪዎች እርስ በእርሳቸው መከባበርና አንዱ የሌላውን የፖለቲካ አመለካከት ማክበርና መቻቻል ይጠበቅባቸዋል::

**መልመጃ 1**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልሱ::***

1. ነፃ የፖለቲካ ሥልጣን ውድድር የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አንዱ መሠረታዊ መርህ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?
2. ነፃ የፖለቲካ ሥልጣን ውድድር ማድረግ የሚያስፈልገው ለምንድንነው? ለምንስ ይጠቅማል?

### 1.1.2 የሕግ የበላይነት

- *የሕግ የበላይነት ስንል ምን ማለታችን ነው?*
- *የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አንዱና ዋናው መሠረታዊ መርህ የሕግ የበላይነት ነው የሚባልበትስ ምክንያት ምንድን ነው?*

የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሌላው መሠረታዊ መርህ የሕግ የበላይነት ነው:: ይህ መርህ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚቆምበት ምሰሶ ነው:: ምክንያቱም መርሁ ማንኛውም የመንግሥት አካል የሚወስነው ውሳኔ ሕግን መሠረት ያደረገ እንጂ ባለሥልጣኑ በሚፈልገው መልኩ ወይም ከሕግ ውጭ እንዳይሆን ለዜጎች ጥበቃ ስለ ሚሰጥ ነው:: ይህ መርህ ማንኛውም ሰው በሕግ ፊት እኩል መሆኑንም ያረጋግጣል:: ይህም በፆታ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በሃብት፣ በሥልጣን እና በመሳሰሉት ልዩነት ሳይደረግ ሁሉም ሰው እኩል መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው:: በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ማንኛውም ሰው የመንግሥት ባለሥልጣናትን ጨምሮ ለሕግ ተገዥ ይሆናሉ::

**መልመጃ 2**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

?

1. የሕግ የበላይነት የሚገለፅባቸውን ሁለት ምሳሌዎች በመጥቀስ አብራሩ::
2. የሕግ የበላይነት መርህ በተግባር ሥራ ላይ መዋሉ የሚሰጠውን ጥቅም አብራሩ::

### 1.1.3 ግልጽነትና ተጠያቂነት

ግልፅነት ማለት ምን ማለት ነው? ተጠያቂነትስ?

የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሦስተኛው መሠረታዊ መርህ በሕዝብ የሚመረጡትም ሆነ በመንግሥት የሚሾሙት ባለሥልጣናት ለሚሠሩት ሥራ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለባቸው መሆኑ ነው። የሚሠሩት ሥራ ሁሉ ለሕዝብ ግልፅ መሆን አለበት:: በዚህ መርህ መሠረት፡

1ኛ) ባለሥልጣናት የሚያሳልፉት ውሳኔም ሆነ የሚያከናውኑት ተግባር ሁሉ ለሕዝብ ግልፅ መሆን አለበት:: የሚያገለግሉት ሕዝቡን ስለሆነ የተሠጣቸውን ሥልጣን ለግል ጥቅማቸው ማዋል የለባቸውም:: በሥልጣናቸው አላግባብ ተጠቅመው ቢገኙ በሕግ ይጠየቃሉ፣ በወንጀልም ሊከሰ ሱና ሊቀጡ ይችላሉ::

2ኛ) በግልፅነት መርህ መሠረት የሀገርንና የሕዝብን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ናቸው ተብለው በምስጢር እንዲያዙ በሕግ ከሚደነገጉ ጉዳዮች በስተቀር፣ ሕዝቡ መንግሥት የሚሠራውንና የሚያደርገውን፣ ስለሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታ የማወቅ ወይም መረጃ የማግኘት መብት አለው::

ስለዚህ ባለሥልጣናትም ሆኑ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኞች የሚሠሩት ሥራ ሁሉ ለሕዝብ ግልፅ መሆን አለበት:: የሚወሰኑት ውሣኔዎች ለምን እንደተወሰኑና ማን እንደወሰናቸው ሕዝቡ ማወቅ አለበት:: በሀገር ውስጥ ስለሚከናወነው ማንኛውም ጉዳይ ሕዝቡ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል ማለት ነው::

መንግሥት እያከናወነ ያለውን ተግባር ለሕዝብ ካላሳወቀ ሕዝቡ ያ መንግሥት የሚሠራው ሥራ የሚበጀው ይሁን አይሁን ላይ ገንዘብ ይችላል:: ስለዚህም መንግሥት ውክልናውን በትክክል እየተወጣ ቢሆን እንኳን፣ ይኸው ለሕዝብ ግልፅ ባለመሆኑ ሕዝብ በመንግሥት ላይ እምነት ሊያጣ ይችላል:: በአጠቃላይ ሁሉም ዜጎች ባለ ሥልጣናትን ጨምሮ ለሚያከናውኑት ተግባር ግልፅና ተጠያቂ መሆን አለባቸው::

**መልመጃ 3**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልሱ::*

?

1. የግልፅነት እና የተጠያቂነት መርህ መገለጫ የሆኑ ሁለት ምሳሌዎችን አቅርቡ::
2. የግልፅነት እና የተጠያቂነት መርህ ተግባራዊ መሆን ያለው ጥቅም ምንድን ነው?
3. የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አንዱ መሠረታዊ መርህ የግልፅነትና የተጠያቂ ነት መኖር ነው የሚባልበትስ ምክንያቱ ምንድን ነው? ተወያዩበት::

### 1.1.4 የብዙሃን ድምፅ የበላይነት እና የአነስተኛው ቁጥር ድምፅ መከበር

- የብዙሃን ድምፅ የበላይነት ማለት ምን ማለት ነው?

የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሌላው መሠረታዊ መርህ የብዙሃን ድምፅ የበላይነት ነው:: የዴሞክራሲ ሥርዓት መገለጫ ከሆኑት ተግባራት ውስጥ፤

- ግልፅ ውይይት፣
- የሐሳብ ልውውጥ፣
- ክርክር ማካሄድ እና
- ለችግሮች ወይም ለልዩነቶች በሰላማዊ መንገድ እልባት መስጠት ይጠቀሳሉ::

ችግሮችን፣ ልዩነቶችን፣ ጥያቄዎችን ወዘተ... በመወያየት፣ ሃሳብ ለሃሳብ በመለዋወጥ፣ በመከራከር፣ በመጨረሻም በመግባባትና በስምምነት መፍታት የዴሞክራሲ ሥርዓት መታወቂያ ነው:: ሙሉ በሙሉ በመግባባትና በስምምነት መፍታት

ሲያቅት በድምፅ ብልጫ በመፍታት ውሳኔ ላይ መድረስ የግድ ይሆናል:: በልዩነቶቹ ወይም በችግሮቹ ላይ ሰፊና ጥልቅ ውይይት ይካሄዳል፣ ሁሉም ያለ ምንም ፍርሃት ወይም ይሉኝታ የሚያምነውን፣ ትክክለኛ ነው የሚለውን ሃሳብ፣ መፍትሄ፣ መልስ፣ ወዘተ... ያቀርባል፣ ደጋግሞ በመከራከር ለማሳመን ይሞክራል::

በዚህ ዓይነት የሁሉም ሃሳብ በደንብ ከቀረበና ከተደመጠ በኋላ ሁሉም ባንድ ሃሳብ ላይ ሊስማሙ ካልቻሉ የቀረቡት ሃሳቦች ለድምፅ ብልጫ ቀርበው ጥቂቶች ተቃውመው ወይም ድምፅ ሳይሰጡ ሆኖም አብዛኞቹ ከደገፉት የአብዛኛውን ድምፅ ድጋፍ ያገኘው ሃሳብ ይፀድቃል:: ይህ አሰራር ነው እንግዲህ የዴሞክራሲ ሥርዓት መርህ ነው የምንለው::

በዚህ ዓይነት መንገድ የተወሰኑ ጉዳዮች ተፈፃሚ ናቸው:: አንድ ሃሳብ ውይይት ተደርጎበት በድምፅ ብልጫ ከተወሰነ በኋላ ተወያይተው የአፀደቁት የደገፉትም ሆኑ ድምፅ ያልሰጡት ወይም የተቃወሙት ወገኖች ውሳኔውን ወደ ተግባር መተርጎም ይጠበቅባቸዋል::

በመሠረታዊ መብቶች ላይ የሚወሰኑ ውሳኔዎችን ለምሳሌ ህልውናን፣ ደህንነትን፣ ሰብዓዊ ክብርን፣ የሃሳብ፣ የእምነት፣ የንግግር፣ የፅሁፍ ወዘተ...ነፃነትንና የመሳሰሉትን የሚገድቡ ወይም የሚያሳንሱ ውሳኔዎችን ተግባራዊ አናደርግም በማለት ለመቃወም ይቻላል:: በዴሞክራሲ ሥርዓት ይህ የተፈቀደ ነው:: አነስተኛ ቁጥር ያለው ወይም ሃሳቡን ያልተቀበለው ወገን መሠረታዊ መብቶቹና ዴሞክራሲያዊ ነፃነቶቹ ሊገደቡበትና ሊሰረዙበት አይገባም:: እነዚህ ካልተከበሩ ዴሞክራሲ ሊኖር ስለማይችል የድምፅ ብልጫ ይሄንን ሊያጠፋው አይችልም። ይህ አነስተኛ ቁጥር ያለው ወገን መብቱ ከዴሞክራሲ ህልውና ጋር የተሳሰረ ስለሆነ ይሄንን በድምፅ ብልጫ ወስኖ ተግባራዊ ማድረግ ዴሞክራሲን ማጥፋት ማለት ነው::

**መልመጃ 4**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልሱ::***

?

1. የብዙሃን ድምፅ የበላይነት መርህን መገለጫ በምሳሌ አብራሩ::
2. የብዙሃን ድምፅ የበላይነት መርህ ተግባራዊ መሆን ያለው ጥቅም ምንድን ነው?
3. የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አንዱ መሠረታዊ መርህ የብዙሃን ድምፅ የበላይነት ነው የሚባልበትስ ምክንያቱ ምንድን ነው?

***የሚከተሉትን 4 ጉዳዮች በጥሞና አንብቧቸው::***

1. በአንድ የመንግሥት የልማት ድርጅት ውስጥ ሙስና እና ብልሹ አሠራር ነግሷል፣ ሠራተኞች አስተዳደራዊ በደል እየደረሰባቸው ነው፣ ወዘተ... የሚል ጥቆማ ለሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በመድረሱ ኮሚሽኑ ምርምራ አካሄደ:: በምርመራውም የድርጅቱ የበላይ ሃላፊ እና አስተዳዳሪው ጥፋተኞች መሆናቸውን የሚያሳዩ በቂ መረጃዎች በመገኘታቸው በቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ተደረጉ::
2. በአንድ የመንግሥት መ/ቤት ውስጥ የበላይ ሃላፊዎች የሠራተኞችን ሰብዓዊ መብቶች በየጊዜው ይጥሳሉ የሚል መረጃ ለጋዜጠኞች ደረሰ:: ጋዜጠኞችም መረጃው ምን ያህል እውነት እንደሆነ ለማጣራት በስልክም በአካልም እቦታው ድረስ በመሄድ ያደረጉት ሙከራ አልተሳካም:: ምክንያቱም የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ጋዜጠኞችን ለማናገር እንደማይፈልጉና በጉዳዩም ላይ ጋዜጠኞች ምንም እንደማያገባቸው ስለተናገሯቸው ነው::
3. በግንቦት 5ቀን 2000 ዓ.ም እና ግንቦት 12 ቀን 2000 ዓ.ም በተደረገው የማሟያ ምርጫ የተለያዩ ፓርቲዎች ተሳትፈዋል:: መራጩ ሕዝብም የፈለገውንና ያመነበትን ለመምረጥ በነፃና በሠላማዊ መንገድ ድምፁን ሲሰጥ ውሏል::

4. የአንድ መንደር ነዋሪዎች መብራትና የቧንቧ ውሃ ለማስገባት ገንዘብ አሰባሰቡ:: የተሰበሰበው ገንዘብ ግን መብራት ወይም ውሃ ብቻ ማስገባት የሚችል ነው:: ስለዚህ አንዱን መርጠው ማስገባትና ሌላውን በሚቀጥለው ዓመት እንደገና ገንዘብ ሰብስበው ማስገባት እንዳለባቸው አመኑ:: ሆኖም የትኛው ይቅደም እሚለው ላይ መስማማት አልቻሉም:: የተወሰነው ውሃ ይቅደም ሲል የተወሰነው መብራት በማለቱ በድምፅ ብልጫ ለመወሰን ተስማሙ:: በዚህም መሠረት ከ520 ሰዎች ውስጥ ውሃ ይቅደም ያሉት 130 ብቻ ሲሆኑ 390ዎቹ መብራት እንዲቀድም በመፈለጋቸው በዚህ ዓመት መብራት እንዲገባ በሠላማዊ መንገድ በድምፅ ብልጫ ወሰኑ::

**መልመጃ 5**

? *ከላይ ያነበባችኋቸውን እያንዳንዳቸውን ጉዳዮች ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መሠረት በማድረግ ተወያዩባቸው፤*

1. ከአራቱ የዴሞክራሲ ሥርዓት መርሆዎች ውስጥ የትኛውን የበለጠ ይመለከታል?
2. መርሆው በአግባቡ ተተገበረ ወይስ ተጣሰ?
3. መርሆው ተጥሷል የሚል ምላሽ ካለ ምን መደረግ ነበረበት?

## 1.2 ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች

### 1.2.1 የግለሰብ ሰብዓዊ መብቶች

- የግለሰብ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ከሚባሉት ውስጥ ሁለቱን ጥቀሱ::

*ሀ) በሕይወት የመኖር መብት፣*

ሰው ሌሎቹን መብቶቹንና ነፃነቶቹን ከመጠየቁ በፊት አስቀድሞ እርሱ ራሱ በሕይወት መኖር ይገባዋል:: በሕይወት የመኖር መብት ዋናና መሠረታዊ መብት ነው የሚባለውም ለዚህ ነው::

ሕይወት ለአንድ ጊዜ የሚኖር እንጂ እንደፈለጉ መሄድና መምጣት የሚቻልበት መንገድ አይደለም:: በመሆኑም የሰው ሕይወት እንደ ቀላል ነገር ሊታይ አይገባም:: ማንም ሆነ ማን ሕይወትን ሊሰጥ አይችልም፣ ሊሰጥ የማይችለውን ደግሞ መውሰድ አይገባውም፣ በመሆኑም የሰው ሕይወት ክቡርና ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነገር ነው::

ቢሆንም በሕግ የተከለከሉ ድርጊቶችን መፈፀም፣ በተለይ የሌሎችን ሕይወት ሆን ብሎ ማጥፋት፣ ሕብረተሰቡን በጣም ከፍተኛ አደጋ ላይ የሚጥል ወንጀል መፈፀም በሕይወት የመኖር መብትን ያሳጣል:: ምክንያቱም በፈፀመው ድርጊት በሕግ የሞት ቅጣት ሊፈፀምበት ስለሚችል ነው::

*ለ) በአካል ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የመጠበቅ መብት፣*

ይህ መብት በሕይወት ከመኖር መብት የሚመነጭ መብት ነው:: በሕይወት የመኖር መብት ተከብሮ የአካል ደህንነት መብት ካልተጠበቀ ትርጉም የለውም:: በአካሉ ላይ ኢሰብአዊ ድርጊቶች እየተፈፀሙበት መኖር የሚፈልግ ሰው የለም:: ስለዚህ የአካል ስቃይና ጉዳት የሌለበት ሕይወት ለሰው ልጆች በሕይወት እንደመኖር ሁሉ አስፈላጊ ነው::

*ሐ) ከሕግ ውጭ ያለመያዝ፣ ያለመከሰስና ያለመታሠር መብት፣*

ይህ መብት ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት መያዝም ሆነ መታሰር እንደሌለበት የሚያሳይ ነው:: በዚህ መሠረት ማንም ሰው ያለበቂ ማስረጃና በፅሑፍ ከተደገፈ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ውጭ ሊያዝ አይገባም::

**መልመጃ 6**

? *የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. የግለሰብ ሰብዓዊ መብቶች መከበር ለሰው ልጅ ምን ያህል አስፈላጊና ጠቃሚ ነው?
2. ሰብአዊ መብቶች በአግባቡ እንዲከበሩላችሁ ከእናንተ የሚጠበቀው ሚና ምን ድን ነው?

### 1.2.2 የቡድን ሰብዓዊ መብቶች

- የቡድን ሰብዓዊ መብቶች ከሚባሉት ውስጥ ሁለቱን ጥቀሱ::

*ሀ) የእኩልነት መብት፣*

የእኩልነት መብት ከመሠረታዊ መብቶች ውስጥ አንዱ ነው:: የእኩልነት መብት በእኩል ዐይን መታየት ነው:: የተለያዩ ብሄሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በአንድ ላይ በሚኖሩበት አገር የእኩልነት መብት መረጋገጥ የቡድን ሰብአዊ መብቶችን እንዲከበሩ ያገለግላል:: ይህም ለሠላም፣ ለዕድገትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መፋጠን አስተዋጽኦ ያበረክታል::

*ለ) የሃይማኖት፣ የእምነትና የአመለካከት ነፃነት፣*

የሃይማኖት፣ የእምነትና የአመለካከት ነፃነት ማለት የፈለጉትን ሃይማኖት ወይም እምነት የመቀበልና የመከተል ነፃነት ማለት ነው::

**የሃይማኖት እና የእምነት ነፃነት የሕዝብን ደህንነት፣ ሠላምን፣ የሌሎች ሰዎችን መሠረታዊ መብቶች ለማስከበር በሚወጡ ሕጎች ገደብ ሊጣልበት ይችላል::**

ማንም ሰው ከፍላጐቱ ውጭ የትኛውንም ሃይማኖት ወይም አምልኮ ለመከተል አይገደድም:: ለምሳሌ ሕፃናት ወደ አንድ የተወሰነ የሃይማኖት ትምህርት ቤት እንዲገቡ ሊገደዱ አይገባም::

**መልመጃ 7**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

?

1. የቡድን ሰብዓዊ መብቶች መከበር ያስገኘውን ጠቀሜታ አብራሩ::
2. በቡድን ሰብዓዊ መብቶች ላይ ገደብ ሊጣልባቸው ይችላልን? ለምን?

### 1.2.3 የግለሰብ ዴሞክራሲያዊ መብቶች

- የግለሰብ ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚባሉትን ጥቀሱ::

*ሀ) አመለካከትንና ሃሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት፣*

አመለካከትንና ሃሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት ለሰው ልጅ ሕይወትና ህልውና መሟላትና ለስብዕናው መዳበር አስፈላጊና መሠረታዊ ከሆኑት መብቶች አንዱ ነው::

ይህ መብት የራስን ሃሳብና አመለካከት የመግለፅ ብቻ ሳይሆን እኛ የምንፈልገውን ማንኛውንም መረጃ የመጠየቅና የማግኘት መብትንም የሚያጠቃልል ነው::

ስለዚህ ማንኛውም ሰው በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በፅሑፍ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሀሳብ መሰብሰብ እና ማሰራጨት ይችላል ማለት ነው::

**አመለካከትንና ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብት የሀገርን ደህንነት የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ሕጋዊ ገደብ ሊጣልበት ይችላል::**

*ለ) የመዘዋወር ነፃነት፣*

ይህ መብት በሀገር ውስጥ የመዘዋወር፣ ወደ ውጭ ሀገር የመሔድና የመመለስ፣ በፈለጉበትና በመረጡበት ስፍራ የመኖርን መብት የሚያካትት ነው:: በአንድ ስፍራ ወይም አካባቢ እንዲኖር የተገደበ ሰው የመዘዋወር ነፃነት የለውም:: በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚኖር ሰው በአብዛኛው እስረኛ ወይም ከእስረኛ የማይሻል ነው ለማለት ይቻላል::

**መልመጃ 8**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

?

1. የግለሰብ ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ለሰው ልጅ ምን ያህል አስፈላጊ እና ጠቃሚ እንደሆነ አብራሩ::
2. በእነዚህ መብቶች በአግባቡ ለመጠቀም ከእናንተ የሚጠበቀው ምንድን ነው?
3. በእነዚህ መብቶች ላይ ገደብ ሊጣልባቸው ይችላል? ለምን?

### 1.2.4 የቡድን ዴሞክራሲያዊ መብቶች

- የቡድን ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚባሉትን ጥቀሱ::

*ሀ) የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት፣*

የዜጎች መብቶች እንደሆኑ ከሚገለፁትና ሕዝቦችን የሚመለከቱ ናቸው ተብለው ከሚገለፁት መብቶች መካከል አንዱ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና እና ሕዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ነው:: ይህ መብት ህዝቦች በፍላጎታቸው በአንድነት እንዲኖሩ የሚያስችላቸው መብት ነው::

ይህ መብት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን የማስተዳደር፣ ባህልና ቋንቋቸውን የማሣደግና ከፈለጉም የራሳቸውን ነፃ አስተዳደር የመመሥረት መብት መጠቀምን ሁሉ ያጠቃልላል:: ከዚህ በተጨማሪ ለሕዝቡ የተረጋገጠለት ሌላው መብት በዴሞክራሲያዊ መብቱ ተጠቅሞ የመረጣቸውን የመንግሥት ባለሥልጣናት የመቆጣጠርና በእነሱ ላይ እምነት ባጣና አያስፈልጉኝም ባለበት ጊዜ ከሥልጣን በማውረድ በሌሎች የመተካት መብት ነው:: ሕዝቡ ይህንን መብቱን ለመጠቀም የሚያግደው ነገር መኖር የለበትም::

*ለ) የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ እና አቤቱታ የማቅረብ መብት፣*

የዜጎች ዴሞክራሲያዊ መብቶች መሰብሰብን፣ መደራጀትን፣ ሠላማዊ ሰልፍ በማድረግ ተቃውሞ መግለፅን ያጠቃልላሉ::

እነዚህ መብቶች መሠረታዊና ከፍተኛ ግበት የሚሰጣቸው ናቸው:: ሰዎች ለሕይወታቸው የሚያስፈልጋቸውን ለማሟላት በተለያዩ አቅጣጫዎች ተሰባስበውና ተደራጅተው የጋራ ችግሮቻቸውን በሕብረት መፍታት ይኖርባቸዋል::

ማንኛውንም ሰው ካለፍላጎቱ የየትኛውም ድርጅት አባል እንዲሆን ማስገደድ አይቻልም:: የመሰብሰብ፣ የመደራጀት፣ ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብቶችና ነፃነቶች የሌሎችን መብቶችና ነፃነቶች የሚጋፉ መሆን የለባቸውም:: በሕገ መንግሥትና በሌሎችም የሀገሪቱ ሕጎች ውስጥ የሰፈሩትን መብቶች ለመጣስ የሚደረግ መደራጀት ተቀባይነት የለውም::

**የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት የዜጐች ደህንነት ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ፣ የጦርነት ቅስቀሳዎችን እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል ሕጋዊ ገደብ ሊጣልበት ይችላል::**

*ሐ) የሕዝብ ሉዓላዊነት፣*

የሕዝብ ሉዓላዊነት ማለት የአንድ ሀገር ሕዝቦች የሥልጣን ምንጭና ባለቤት ናቸው ማለት ነው:: የሕዝብ ሥልጣን በሕግ ተደንግጎ የሚሰጥ ሳይሆን ከራሱ ከሕዝቡ የሚመነጭ ነው:: የሕዝብ ሉዓላዊነት አለ ለማለት የምንችለው ሕዝቡ የራሱን ዕድል በራሱ መወሰን ሲችል፣ የሚያስተዳድሩትን ተወካዮቹን መምረጥ ሲችል፣ በፈለገ ጊዜ ደግሞ ከሥልጣን ማውረድ ሲችል ነው:: የሕዝቦች ሉዓላዊነት መረጋገጥ ከምንም በላይ ለሁሉም የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ወሳኝ ነው::

**መልመጃ 9**


*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

?

1. የቡድን ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ለሰው ልጅ ምን ያህል አስፈላጊ እና ጠቃሚ እንደሆነ አብራሩ::
2. በእነዚህ መብቶች በአግባቡ ለመጠቀም ከእናንተ የሚጠበቀው ምንድን ነው?
3. በእነዚህ መብቶች ላይ ገደብ ሊጣልባቸው ይችላል? ለምን?

## 1.3 ልዩነቶችን ማቻቻል

### 1.3.1 ልዩነቶችን ማቻቻል አብሮ ለመኖር ያለው ጠቀሜታ



*ሥዕል 1.1 ክርስቲያንና ሙስሊም ተማሪ ጓደኞች በአንድ ላይ ሲያጠኑ*

1. ከላይ ያለውን ሥዕል በሚገባ ተመልከቱ:: በልጆቹ መካከል የሚታዩ ቢያንስ ሦሥት ልዩነቶችን አውጡ::
2. ሥዕሉ ምንን ያመለክታል? ምንስ ተገነዘባችሁ?

**አራቱ ጓደኞቹ፤**

ወልደ ገብርኤል የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ሲሆን ሔለን የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ ናት:: ሐሰን እና ሐዋ ደግሞ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው:: እነዚህ አራት ጓደኞች የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ በጣም የሚዋደዱ ጓደኞች ናቸው:: ክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ በጭራሽ አይለያዩም:: አብረው ያጠናሉ፤ አብረው ይጫወታሉ:: ጓደኝነታቸው በጣም ጥብቅ በመሆኑ ወላጆቻቸውን አስተዋውቀው በቤተሰብ ደረጃም ይጠያየቃሉ::

እነዚህ ጓደኞች በትምህርታቸውም ጥሩ ውጤት ለማምጣት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ:: ቅዳሜና እሁድ የጥናት ፕሮግራም አዘጋጅተው በየተራ አንደኛቸው ቤት እየተገናኙ ያጠናሉ:: ወላጆቻቸውም ጥናቱ እነሱ ቤት የሆነ ቀን ቁርስ፣ ምሣ፣ ሻይ እያዘጋጁ ያስተናግዷቸዋል::

ከዚህ በተጨማሪ የክርስቲያኖች የሃይማኖት በዓላት ገና፣ ጥምቀት፣ ፋሲካ በመጣ ቁጥር ሃሰን እና ሃዋ ከወላጆቻቸው ጋር እነ ሔለን እና እነ ወልደ ገብርኤል ቤት ሄደው እንኳን አደረሳችሁ በማለት መልካም ምኞታቸውን ይገልፁላቸዋል:: በተመሳሳይ መልኩ የሙስሊሞች በዓላት ኢድ፣ መውሊድና አረፋ በመጡ ቁጥር ሔለንና ወልደ ገብርኤል ከወላጆቻቸው ጋር እነ ሐሰን እና እነ ሐዋ ቤት ሄደው እንኳን አደረሳችሁ በማለት መልካም ምኞታቸውን ይገልፁላቸዋል::

የእነዚህ አራት ልጆች የጓደኝነት ፍቅር በጣም ጠንካራ በመሆኑ እና ምን ጊዜም ሳይለያዩ አብረው በመዋላቸው የአንድ ቤተሰብ አባላት ይመስላሉ::

ወላጆቻቸውም ሁሉንም ልጆች እንደራሳቸው ልጆች በመመልከት እንክብካቤ ያደርጉላቸዋል:: ይህ ግንኙነት እያደገ ሄዶ የልጆቹ ወላጆችም በክፉም ሆነ በደጉ የሚጠያየቁ፣ በችግር ጊዜም የሚረዳዱ ጥብቅ ዘመዳሞች ሆኑ::

**መልመጃ 10**

*ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. ከአራቱ ጓደኞች ተግባር ምን ተማራችሁ?
2. ከአራቱ ጓደኞች ቤተሰቦች ምን ተገነዘባችሁ?
3. እንደ አራቱ ጓደኞች ያለ ፍቅር ያላቸው ጓደኞች ታውቃላችሁ? የምታውቁ ከሆነ በአጭሩ በፅሑፍ ግለፁ::

ልዩነቶችን ማቻቻል አብሮ ለመኖር ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው:: ምክንያቱም ልዩነቶችን ማቻቻል በየትኛውም ቦታና በማንኛውም ጊዜ ለግለሰብም ሆነ ለቤተሰብ ብሎም ለኅብረተሰብ ሠላምን፣ ፍቅርን፣ እና መተሳሰብን ስለሚያሰፍን ነው::

ቤተሰብ የሕብረተሰብ ንዑስ ክፍል ነው:: የአንድ ቤተሰብ አባላት የተለያየ እምነት፣ አመለካከት እና ዝንባሌ ሊኖራቸው ይችላል:: እነዚህ ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆነው በሠላምና በፍቅር ለመኖር የሚችሉት ልዩነቶቻቸውን ማቻቻል ሲችሉ ነው:: ልዩነቶችን ማቻቻል ደግሞ የቤተሰቡ አባላት በመካከላቸው ያሉትን ልዩነቶች በወንድማ ማችነት እና በእህትማማችነት እንዲሁም በመግባባት መንፈስ አክብረው እንዲቀበሉ ያደርጋቸዋል:: የቤተሰቡ አባላት እርስበርሳቸው አንዱ

የሌላውን ልዩነት በአክብሮት መቀበላቸው በሠላም እና በፍቅር አብረው እንዲኖሩ ያስችላቸዋል፡፡

በሕብረተሰቡ ውስጥ ደግሞ ልዩነቶችን ማቻቻል የእርስ በእርስ ግንኙነት እንዲዳብር እና በጋራ መሥራት እንዲኖር ያስችላል፡፡ በሕብረተሰቡ አባላት መካከል ፀብ እና ግጭት እንዳይፈጠር ተቀራርቦ መነጋገር፣ መወያየት እና መደራደር ብሎም አለመግባባቶችን በሠላማዊ መንገድ መፍታት እንዲችሉ ይረዳል፡፡

ልዩነቶችን ማቻቻል ሕብረተሰቡ በልዩነቶች ውስጥ አንድነት ፈጥሮ በሠላምና በፍቅር አብሮ መኖር እንዲችል ያደርጋል፡፡ አንድነት ፈጥሮ በሠላምና በፍቅር አብሮ መኖር መቻል ደግሞ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

**መልመጃ 11**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው፡፡***

1. ልዩነቶችን ማቻቻል ማለት ምን ማለት ነው?
2. ከሌሎች ጋር ብዙ ልዩነቶች እያሉን በሰላም አብረን ስመኖር የምንችለው እንዴት ነው?
3. በሠላምና በፍቅር አብሮ መኖር ምን ጠቀሜታዎች አሉት?

## 1.4 የመንግሥት ተግባራት

### 1.4.1 የኢትዮጵያ የፌደራል መንግሥት ተግባራት

- ከኢትዮጵያ የፌደራል መንግሥት ተግባራት ውስጥ ቢያንስ ሦሥቱን ጥቀሱ፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት የሚያከናውናቸው በርካታ ተግባራት አሉት፡፡ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) ሕገመንግሥቱን ይጠብቃል ይከላከላል፣
ለ) የሀገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ የማሕበራዊና የልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ዕቅድ ያወጣል፣ ያስፈፅማል፣
ሐ) የሀገርና የሕዝብ የመከላከያና የደህንነት እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት የፖሊስ ኃይል ያደራጃል፣ ይመራል፣
መ) ብሔራዊ ባንክን ያስተዳድራል፣ ገንዘብ ያትማል፣ ይበደራል፣ የውጭ ምንዛሪና የገንዘብ ልውውጥን ይቆጣጠራል፡፡ ክልሎች ከውስጥ ምንጮች ስለሚበደሩበት ሁኔታ ሕግና መመሪያ ያወጣል፣
ሠ) የውጭ ግንኙነት ፖሊሲን ይወስናል፣ ፖሊሲውንም ያስፈፅማል፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ይዋዋላል፣ ያፀድቃል፣
ረ) የአየር፣ የባቡር፣ የባሕር መጓጓዣ፣ የፖስታና የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች እንደዚሁም ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ክልሎችን የሚያገናኙ አውራ መንገዶችን ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣
ሰ) ወደ ሀገር የመግቢያና የመውጫ ጉዳዮችን ስለስደተኞችና ስለ ፖለቲካ ጥገኝነት ይወስናል፣ ይመራል፡፡

*(የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 51)*

**መልመጃ 12**

***የሚከተለው ጥያቄ ላይ ተወያዩ፡፡***

1. ከፌደራል መንግሥት ዋና ዋና ተግባራት ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን ምረጡና ለምን የፌደራል መንግሥት ተግባራት እንደሆኑና የክልል መንግሥታት ተግባራት ሲሆኑ የማይችለበትን ምክንያት እያነሳችሁ ተወያዩ፡፡

### 1.4.2 የክልል ብሔራዊ መንግሥታት ተግባራት

- ከክልል ብሔራዊ መንግሥታት ተግባራት ውስጥ ቢያንስ ሦሥቱን ጥቀሱ፡፡

የክልል ብሔራዊ መንግሥታት የሚያከናውኗቸው በርካታ ተግባራት አሏቸው፡፡ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳደር ያዋቅራሉ፣ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ይገነባሉ፣
ለ) የክልል ሕገመንግስትና ሌሎች ሕጎችን ያወጣሉ፣ ያስፈጽማሉ፣

ሐ) የክልሉን የኢኮኖሚ የማሕበራዊና የል ማት ፖሊሲ ስትራቴጂና ዕቅድ ያወጣሉ፣ ያስፈጽማሉ፣
መ) የፌደራሉ መንግሥት በሚያወጣው ሕግ መሠረት መሬትና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተ ዳድራሉ፣
ሠ) ለክልሉ በተወሰነው የገቢ ምንጭ በክልል ደረጃ ግብርና ታክስ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፣ የክልሉን በጀት ያወጣሉ፣ ያስፈፅማሉ።
ረ) የክልሉን መስተዳድር ሠራተኞች አስተዳደ ርና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ሕግ ያወጣሉ፣ ያስፈፅማሉ፣ ሆኖም ለአንድ የሥራ መደብ የሚያስፈልጉ የትምህ ርት፣ የሥልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ከአጠቃላይ የሀገሪቱ መመዘኛዎች ጋር የተቀራረቡ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል።
ሰ) የክልሉን የፖሊስ ኃይል ያደራጃሉ፣ ይመ ራሉ፣ የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ያስጠ ብቃሉ።

**መልመጃ 13**

*የሚከተለው ጥያቄ ላይ ተወያዩ።*

? ከክልል መንግሥት ዋና ዋና ተግባራት ውስጥ ቢያንስ ሦሥቱን ምረጡና ለምን የክልል መንግሥት ተግባራት እንደሆኑ፣ የፌደራል መንግሥት ተግባራት ሲሆኑ የማይችሉበት ምክንያት ምን እንደሆነ ተወያዩበት።

### 1.4.3 የከተማ አስተዳደርና ተጠሪነት

- የከተማ አስተዳደር ማለት ምን ማለት ነው?

በየክልሉ እራሣቸውን በራሣቸው የሚያስተዳ ድሩ ሕጋዊ እውቅና የተሰጣቸው ከተሞች አሉ። ከተሞች ተጠሪነታቸው ለመረጣቸው ሕዝብ ሆኖ የራሣቸው ምክር ቤቶች አሉዋቸው። ከዚህም በላይ የሥራ አስፈፃሚዎች ያሉዋቸው ሲሆን፣ በሥራ አስፈፃሚዎቹ የተመረጡ ከንቲባዎች የከ ተሞቹን የለትተለት ሥራ ይመራሉ። የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች ከመረጣቸው ሕዝብ በተጨማሪ ተጠሪነታቸው ለፌዴራል መንግሥቱ ነው።


አዲስ አበባ የፌደራል መንግሥቱ መቀመጫና የሀገሪቱ ዋና ከተማም ናት። ከተሞች የአስ ተዳደር እርከኖች አሉዋቸው። ለምሣሌ በአዲስ አበባ በከተማ ደረጃ የከተማው ምክር ቤት፣ ዝቅ ብሎ የክፍለ ከተማ ምክር ቤቶች፣ ከዚያም የቀበሌ ምክር ቤቶች አሉ። ምክር ቤቶቹን የሚ መሩ የሥራ አስፈፃሚዎች አሉ።

**የቡድን ሥራ፣**

ከመምህራችሁ ጋር በመነጋገር በምትመሠርቱት ቡድን በመሆን በዕጣ የሚደርሳችሁን
ሀ) የፌደራል መንግሥት ተግባራት፣
ለ) የክልል መንግሥታት ተግባራት ወይም
ሐ) አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ተጠሪነታቸው ለፌደራል መንግሥት የሆነበትን ምክን ያት በተመለከተ ማብራሪያ አዘጋጁና አቅርቡ።

## 1.5 የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የሥልጣን አካላት

- ከዚህ በታች ያለውን ሥዕል ደብተራችሁ ላይ ገልብጡና በተሰጡት ምሳሌዎች መሠረት በቅንፍ ውስጥ ያሉት የጥያቄ ምልክቶች የሚወክሏቸውን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መን ግሥትን የሥልጣን አካላት አስፍሩ።




*ሥዕል 1.2 የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የሥልጣን አካላት*

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ሦሥት የሥልጣን አካላት አሉት:: በተመሳሳይ መልክ የክልል መንግሥታትም ሦሥት የሥልጣን አካላት አሏቸው:: እነሱም ሕግ አውጪው፣ ሕግ አስፈፃሚው እና ሕግ ተርጓሚው ናቸው::

## 1.5.1 ሕግ አውጪ

ሕግ አውጪው የፌደራሉ መንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሲሆን እሱም የፌደራሉ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው:: የክልል መንግሥት ከፍተኛው የሥልጣን አካል የክልል ምክር ቤት ነው:: **በፌደራል ደረጃ** ሕግ አውጪው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው:: **በክልል ደግሞ** ሕግ አውጪው የክልል ምክር ቤት ነው:: በዘህም መሠረት የሕግ አውጪው ተግባር በሀገሪቱና በክልሎች ተግባራዊ ሊሆኑ የሕዝቡን ሠላምና ፀጥታ ሊያስከብሩና ሊያስጠብቁ የሚችሉ ሕጎችን ማውጣትና ማፅደቅ ነው:: ሕጎቹም አዋጆች፣ ደንቦችና፣ መመሪያዎች ወዘተ... ሊሆኑ ይችላሉ::

## 1.5.2 ሕግ አስፈፃሚ

**በፌደራል ደረጃ** ሕግ አስፈፃሚው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው:: **በክልል ደረጃ ደግሞ** ሕግ አስፈፃሚው የክልል መስተዳድር ነው:: የሕግ አስፈፃሚው ዋና ተግባራት ሕግ አውጪው የሚያወጣቸውን ሕጎች ተፈፃሚ ማድረግ ነው:: በዚህ መሠረት ሕጎቹ በትክክልና በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል:: እነዚህንም ተግባራት ለማከናወን ልዩ ልዩ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን፣ የፖሊስ ሃይል፣ የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤቶችና የማረሚያ ቤቶችን ያዋቅራል፣ ሥራቸውንም ይከታተላል:: በፌዴራል ደረጃ ዋናው አስፈፃሚ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይመራል:: በክልል ደረጃ ደግሞ ዋናው አስፈፃሚ በክልሉ ፕሬዝዳንት ይመራል።

## 1.5.3 ሕግ ተርጓሚ

**በፌደራል ደረጃ** ሕግ ተርጓሚው የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሆኖ በውስጡም በየደረጃው የተዋቀሩ ፍርድ ቤቶችን ያጠቃልላል:: በክልል ደግሞ ሕግ ተርጓሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሆኖ በሥሩም በየደረጃው የተዋቀሩ ፍርድ ቤቶችን ያጠቃልላል::

ይህ አካል በሕግ አውጪውም ሆነ በሕግ ተርጓሚው የወጡ ሕጎችን በመተርጎም በሀገሪቱ ውስጥ የሚፈለገው ሠላምና ፀጥታ እንዲሰፍን የሚያግዝ ነው:: የሕግ ተርጓሚው ዋና ተግባር በሕጉ መሠረት የዳኝነት አገልግሎት መስጠት ነው::

ከላይ እንደተገለፀው በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሕግን የማውጣት፣ ሕግን የማስፈፀምና ዳኝነት የመስጠት ተግባራት በተለያዩ ተቋማት ይካሄዳል:: ከዚህም በላይ በዚህ የሥልጣን ክፍፍል አንዱ አካል በሌላው የሥልጣን ክልል ውስጥ ጣልቃ እንዳይገባና ሁሉም በየራሱ የሥልጣን ገደብ ውስጥ የተጣለበትን ኃላፊነትና ግዴታ እንዲወጣ የሚያደርግ መርህ ነው:: የመንግሥት ሥልጣን በሦስት የተከፋፈለበት ዋናው ምክንያት ሥልጣን አንድ ቦታ ላይ እንዳይከማች ለማድረግና አምባገነንነትን ለመከላከል ነው::

ይህ መርህ ፍርድ ቤቶች፣ ሕግ አውጭ ምክር ቤቶችና ሕግ አስፈፃሚ ተቋማት አንዳቸው በሌላው ሕጋዊ ሥልጣን ላይ ጣልቃ ሳይገቡ እየተጠባበቁ በሕገመንግሥቱ መሠረት የተጣለባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ያስችላል:: ይህም ሥልጣን በአንድ አካል ላይ ብቻ እንዳይከማችና አምባገነንነት እንዳይሰፍን ይከላከላል::

**መልመጃ 14**

? *በሚከተለው ጥያቄ ላይ ተወያዩ::*

**በዴሞክራሰያዊ ሥርዓት ውስጥ ሦስት የመንግሥት የሥልጣን አካላት እንዲኖሩ ለምን አስፈለገ?**

## 1.6 የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት

### 1.6.1 ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሀገራት ያደረገችው አስተዋፅኦ



*ሥዕል 1.3 ኢትዮጵያ የወጭ ግንኙነት ውል ስትፈራረም*

- ከዚህ በላይ ከሚታዩት ፎቶዎች ምን ትረዳላችሁ?
- ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሀገራት ስላደረገችው አስተዋፅኦ የምታውቁትን ያህል ጥቀሱ::

ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ሥር የወደቁ የአፍሪካ ሀገሮችን ከቅኝ ተገዢነት እንዲላቀቁ ምሳሌ ሆናለች:: ሠላምን በማስከበር ተግባርም በአህጉሪቱ ውስጥ በስፋት በመሳተፍ አስተዋጽኦ አበርክታለች:: ለነፃነት በተደረገው የአፍሪካውያን ትግል ወቅት የነፃነት ኃይሎች በኢትዮጵያ ውስጥ ወታደራዊ ሥልጠና እንዲያገኙ በማድረግና የሠራዊት ድጋፍ በመስጠት ረድታለች::

በአፍሪካ በሠላም ማስከበር እንቅስቃሴዎች ውስጥም ከፍተኛ ሚና እየተጫወተች ትገኛለች:: ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያ የሠላም አስከባሪ ሠራዊት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰላም ተልዕኮ አጋር በመሆን በኮንጐ፣ በሩዋንዳ፣ በቡሩንዲና በላይቤሪያ እየተወጣ ያለውን አኩሪ ተልዕኮ መጥቀስ ይቻላል::

የኢትዮጵያ ሠራዊት በሰላም ማስከበር ተልዕኮ መሳተፍ ብቻ ሳይሆን በየሄደባቸው ሀገሮች በጦርነት የተፈናቀሉ ዜጎችን መልሶ በማቋቋምና በመደገፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረገ ነው:: ይህም ኢትዮጵያ የምትኮራበት የሠላምና የልማት ተልዕኮ ያነገበ ሠራዊት እንዳላት ያሳያል:: በአጠቃላይ በ1950ዎቹ በኮሪያ የሠላም አስከባሪ ኃይል አሰማርታ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን አፍሪካውያን የሚኮሩበትን አመርቂ ተልዕኮ ፈፅሞ መመለሱ ይታወቃል:: ይህም በራሱ የኢትዮጵያን ተቀባይነትና ለሠላም እና ለአፍሪካ መረጋጋት ያላትን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ተጨባጭ ተግባር ነው::

**መልመጃ 15**

? ***የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመከፋፈል ለእያንዳንዱ የተለያዩ ምንጮችን በመጠቀም (ቤተመፃሕፍት፣ የታሪክ መምህር፣ ወዘተ.) ከሁለት ገፅ ያልበለጠ ዘገባ አቅርቡ::***

1. **የኢትዮጵያ ሠራዊት ከአሁን በፊት ሠላም ለማስከበር የዘመተበትን አንድ ሀገርም ረጡና ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ያካተተ ፅሑፍ አዘጋጁ::**

**ሀ) የዘመተበት ወቅት መቼ እንደነበር፣**
**ለ) ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት ምን ምን እንደነበሩ፣**

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የዴሞክራሲ ሥርዓት በርካታ መሠረታዊ መርሆዎች አሉት፡፡ ዋና ዋናዎቹ ነፃ የፖለቲካ ሥልጣን ውድድር፣ የሕግ የበላ ይነት ግልጽነትና ተጠያቂነት ናቸው፡፡

ልዩነቶችን ማቻቻል አብሮ ለመኖር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ልዩነቶችን ማቻቻል በየትኛውም ቦታ እና በማንኛውም ጊዜ የሰው ልጅ በልዩነቶች ውስጥ አንድነት ፈጥሮ በሠላምና በፍቅር አብሮ መኖር እንዲችል ያደርጋል፡፡

የፌደራል መንግሥት የሚያከናውናቸው በርካታ ተግባራት አሉት፡፡ ዋና ዋናዎቹ ሕገመንግሥቱን መጠበቅና መከላከል፣ የሀገርና የሕዝብ የመከላከያና የደህንነት እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት የፖሊስ ኃይል ማደራጀትና መምራት፣ ብሔራዊ ባንክን ማስተዳደር፣ ገንዘብ ማተም፣ መበደር፣ የውጭ ምንዛሪና የገንዘብ ልውውጥን መቆጣጠር፣ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲን መወሰን፣ የአየር፣ የባቡር፣ የባሕር መጓጓዣ፣ የፖስታና የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ማስፋፋት፣ ወደ ሀገር የመግቢያና የመውጫ ጉዳዮችን ስለ ስደተ ኞችና ስለ ፖለቲካ ጥገኝነት መወሰን ናቸው፡፡

የክልል ብሔራዊ መንግሥታት የሚያከናውኗቸው በርካታ ተግባራት አሏቸው፡፡ ዋና ዋናቹ ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መሥተዳደር ማዋቀር፣ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ዴሞክራሲዊ ሥርዓት መገንባት፣ የክልል ሕገመንግሥትና ሌሎች ሕጎችን ማውጣት፣ የክልሉን የፖሊስ ኃይል ማደራጀት፣ መምራት፣ የክልሉን ሰላምና ፀጥታ ማስጠበቅ ናቸው፡፡

ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ሶስት የሥልጣን አካላት አሉት፡፡ ይህ በመሆኑም የፌዴራል መንግሥቱም ሆነ የክልል መንግሥታት በየደረጃቸው ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈፃሚ እና ሕግ ተርጓሚ አካላት አሏቸው፡፡

ኢትዮጵያ በምትከተለው የውጪ ግንኙነት የአፍሪካ ሀገራት ከቅኝ ግዛት እንዲላቀቁ ከፍተኛ ጥረት ከማድ ረጓም በላይ በሠላም ማስከበር ተግባር ውስጥ በንቃት በመሳተፍ በርካታ የማይደናቁ አስተዋፅኦች አበር ክታለች፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**ፌዴራሳዊ፣** ራሳቸውን በራሳቸው በሚያስተዳድሩ የክልል መንግሥታት ሕብረት የተዋቀረ መንግሥት፡፡

**ዲሞክራሲያዊ፣** ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን የሕዝብ የሆነበትና ሥልጣኑም ሕዝቡ በነፃ በመረጣቸው ተወካዮች አማካይነት ተግባራዊ የሚሆን፡፡

**ሪፐብሊክ፣** በሕዝብ ምርጫ የተመሠረተ መንግሥት፡፡

**የፕሮቶኮል ስምምነት፣** በሀገሮች መካከል የሚደረግ የትምህርት፣ የባህል፣ የኢኮኖሚ፣ ወዘተ ስምምነት፡፡

**ሳንሱር፣** የፅሑፍና የኤሌክትሮኒክስ መልዕክቶች ለሕዝብ ከመቅረባቸው በፊት በፖለቲካና በሞራል በኩል የሚያስከትሏቸው ችግሮች እንዳሉ ለማጣራት የሚደረግ ቅድመ ምርመራ ወይም ቁጥጥር፡፡

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ፡፡*

### I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ፡፡

1. በዴሞክራሲ ሥርዓት በሥልጣን ላይ ያሉ መሪዎች በምርጫ መሸነፍን በፀጋ ይቀበላሉ፡፡
2. በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ በሕይወት የመኖር መብት በምንም ምክንያት ገደብ አይጣልበትም፡፡
3. በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ሰዎች ለፈለጉት ሕጋዊና ሰላማዊ ዓላማ ሁሉ መሰባሰብ ይችላሉ፡፡
4. ልዩነቶችን ማቻቻል አንዱ የሌላውን አመለካከት በአክብሮት መቀበል፣ መተሳሰብ፣ መተባበር እንዲኖርና ሠላምና ፍቅር እንዲሰፍን ይረዳል፡፡
5. የውጭ ግንኙነት ፖሊሲን መወሰን፣ ፖሊሲውንም ማስፈፀም፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መዋዋልና ማፅደቅ የክልል መንግሥት ተግባር ነው፡፡

### II. በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን በ "ሀ" ሥር ካሉት ሥር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚቆምበት ምሰሶ፣ | ሀ) የሕግ በላይነት። |
| 2. በማሕበር የመደራጀት መብት፣ | ለ) የግለሰብ ሰብዓዊ መብት። |
| 3. በሠላማዊ መንገድ የመሰብሰብ መብት | ሐ) የቡድን ሰብዓዊ መብት። |
| 4. የሃይማኖት መብት፣ | መ) የግለሰብ ዴሞክራሲያዊ መብት። |
| 5. የብሔሮች፣ የብሔረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት፣ | ሠ) የቡድን ዴሞክራሲያዊ መብት። |
| 6. ሀሳብን በነፃ የመግለፅ መብት፣ | |
| 7. በሕይወት የመኖር መብት፣ | |

### III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ባለሥልጣናት የሚያሳልፉት ውሳኔ የሕዝብን እንጂ የእነርሱን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ መሆን የለበትም የሚለው መርህ የትኛው ነው?
   - ሀ) ግልፅነት፣
   - ለ) ተጠያቂነት፣
   - ሐ) የሕግ የበላይነት፣
   - መ) ሁሉም ልክ ነው።
2. የፌደራል መንግሥት ሥልጣንና ተግባር ያልሆነው የቱ ነው?
   - ሀ) ገንዘብ ማተም፣
   - ለ) ብሔራዊ ባንክን ማስተዳደር፣
   - ሐ) የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን ማካሄድ፣
   - መ) ከልሎችን መምራት።

3. ልዩነቶችን ማቻቻል ለምን ይጠቅማል?
   ሀ) የእርስ በእርስ ግንኙነት ለማዳበር፣
   ለ) በጋራ ውጤታማ ሥራ ለመሥራት፣
   ሐ) በልዩነቶች ውስጥ አንድነትን ፈጥሮ በሠላም ለመኖር፣
   መ) አለመግባባቶችን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት፣
   ሠ) ሁሉም መልስ ነው።

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ።

1. ዋና ዋናዎቹ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መርሆዎች ----------------፣---------------- እና -------------------------- ናቸው።
2. ሦስቱ የመንግሥት የሥልጣን አካላት -------------፣------------እና ------------ናቸው።

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ።

1. ሦስቱ የመንግሥት የሥልጣን አካላት እነማን ናቸው? የመንግሥት የሥልጣን አካላት ሦስት መሆናቸው ፋይዳው ምንድን ነው? በምሳሌ አስረዱ።
2. የፌደራል መንግሥትንና የክልል መንግሥታትን ተግባራት አነፃፅሩ።

# ምዕራፍ ሁለት

# የሕግ የበላይነት


**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- የሕገመንግሥትና የሌሎች ሕጐችን ምንነት ታውቂያለሽ/ ታውቃለህ፣
- የሕግ ክለሳ መገለጫዎችንና ያለውንም ጠቀሜታ ታውቂያለሽ/ ታውቃለህ፣
- የመንግሥስትና የሕዝብ ተመራጮች ሥልጣ ናቸው በሕግ የተገደበ መሆኑን ትረጂያለሽ/ ትረዳለህ፣

## 2.1 ሕገመንግሥት

### 2.1.1 የፌደራል ሕገመንግሥት ምንነት

- *የኢትዮጵያ ሕገመንግሥት ለምን ፌዴራላዊ ሕገመንግሥት ነው ተባለ?*





መግቢያ

እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦች ፣ ሕዝቦች ፦

በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም ፣ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገታችን እንዲፋጠን ፣ የራሳችንን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን ፣ በነፃ ፍላጎታችን ፣ በሕግ የበላይነት እና በራሳችን ፈቃድ ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ በጋራ ለመገንባት ቆርጠን በመነሳት ፤

ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ፣ የግለሰብና የብሔር/ብሔረሰብ መሰረታዊ መብቶች መከበራቸው ፣ የፆታ እኩልነት መረጋገጡ ፣ ባሕሎችና ሃይማኖቶች ካለአንዳች ልዩነት እንዲራመዱ የማድረጉ አስፈላጊነት ጽኑ እምነታችን በመሆኑ ፤

ኢትዮጵያ ሀገራችን የየራሳችን አኩሪ ባሕል ያለን ፣ የየራሳችን መልክዓ ምድር አሰፋፈር የነበረንና ያለን ፣ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በተለያዩ መስኮችና የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረን አብረን የኖርንባትና የምንኖርባት ሀገር በመሆንዋ ፣ ያፈራነው የጋራ ጥቅምና አመለካከት አለን ብለን ስለምናምን ፤

መጪው የጋራ ዕድላችን መመስረት ያለበት ከታሪካችን የወረስነውን የተዛባ ግንኙነት በማረምና የጋራ ጥቅማችንን በማሳደግ ላይ መሆኑን በመቀበል ፤

5

*ሥዕል 2.1 የፌዴራል ሕገመንግሥት የበላይ ሕግ ነው፡፡*

የፌደራል ሕገመንግሥት በፌደራል የመንግሥት አስተዳደር ሥርዓት የሚተዳደሩ ሀገሮች የሚመሩበት የሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ ነው፡፡ በፌደራል ሥርዓት በሚተዳደሩ ሀገሮች ውስጥ ከአንድ በላይ ሕገመንግሥቶች ይኖራሉ፡፡ ይህም ማለት ፌዴራል መንግሥቱን የመሠረቱት ክልላዊ መንግሥታት የየራሳቸው ሕገ መንግሥት ሲኖራቸው፣ ማእከላዊ ወይም ፌዴራላዊ መንግሥት ተብሎ የሚጠራው የራሱ ሕገመንግሥት ይኖረዋል፡፡

የፌደራል ሕገመንግሥት ፌደራል መንግሥቱን በመሠረቱት አባል ክልሎች ስምምነት የተዘጋጀና የፀደቀ የጋራቸው የሆነ ገዢ ሰነድ ነው፡፡ ስለዚህ በፌደራል መንግሥቱ ውስጥ ላሉ ክልሎች የበላይ ሕግ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በዚህ መሠረት የክልል ሕገመንግሥቶችና ሌሎች ሕጎችና ደንቦች የፌደራል መንግሥቱን ሕገመንግሥት የሚፃረሩ መሆን የለባቸውም፡፡

በአጠቃላይ የፌዴራል ሕገመንግሥት በፌደራል አስተዳደር የሚመራ ሀገር ዋና መተዳደሪያ ሕግ ነው፡፡ ስለሆነም በዚሁ ሕገ መንግሥት የሀገሮቹ ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ መርሆዎች የሚገለፅበት ሀገራዊ መተዳደሪያ ሰነድ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ሕገመንግሥቱ የሌሎች ሕጐችና ደንቦች ሁሉ መነሻ ነው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ የፌደራል ሥርዓቱን መከተል ከጀመረችበት ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ በሀገሪቱ በሚኖሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ስምምነት የፀደቀ የፌዴራል ሥርዓትን የሚያንፀባርቅ ሕገ መንግሥት አላት፡፡ ይህ ሕገመንግሥትም የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ክልሎችም የራሳቸውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ ሁኔታ ያዘጋጁት ነገር ግን የፌደራል ሕገመንግሥቱን የማይቃረን የየራሳቸው ሕገመንግሥት አላቸው፡፡

"ሕገመንግሥቱ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ነው፡፡ ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር፣ እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገመንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

*/የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገመንግሥት አንቀፅ 9 ተ.ቁ 1 /*

**መልመጃ 1**

***ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡***

1. በሀገራችን ስንት ሕገመንግሥቶች አሉ?
2. በሀገራችን ከአንድ በላይ ሕገመንግሥት ካሉ ለምን ሊኖሩ እንደቻሉ አብራሩ፡፡
3. ከሕገመንግሥቶች ሁሉ የበላይ ሕግ የሆነው የቱ ነው?
4. በፌደራሉ መንግሥት ሕገመንግሥትና በክልሎች ሕገመንግሥቶች መካከል ልዩነቶች ቢፈጠሩ ተቀባይነት የሚኖረው የትኛው ነው? ለምን?

## 2.1.2 የፌደራል ሕገመንግሥት አስፈላጊነት

- *የፌደራል ሕገ መንግሥት ጠቀሜታን ዘርዝሩ፡፡*

*የፌዴራላዊ የመንግሥት አስተዳደር አንዱ መለያ ባህሪ በፌደራሉ መንግሥትና በክልል መንግሥታት መካከል የሚኖር የሥልጣን ክፍፍል ነው፡፡ የፌደራሉ ሕገ መንግሥት የነዚህን ሁለት አካላት የሥልጣን ልዩነት፣ አንድነት እና ግንኙነት በግልፅ ለይቶ ያመላክታል፣ ያስቀምጣልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፌደራል ሕገመንግሥት አስፈላጊ የሚሆነው የሚከተሉትን ዓላማዎች ለማሟላት ነው፡፡*

- ሕዝቦች የራሳቸውን ጉዳይ ራሳቸው እንዲወስኑ፣ ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ፣
- የአስተዳደር ተቋማትንና የፍትሕ አካላትን አገልግሎቶች በቅርበት እንዲያገኙ፣
- ሕዝቦች በተለያዩ የአስተዳደር እርከኖች የመሳተፍና የመወከል መብቶቻቸውን ለማጎልበትና በክልል እና በፌደራል ደረጃ የሚኖራቸውን ውክልናና ተሳትፎን ለማጠናከር፣
- በክልሎች መካከል የተመጣጠነ እድገት እንዲኖር ለማድረግ፣
- በሕዝቦች መካከል መፈቃቀድና፣ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት ለማጎልበት፣
- በፌዴራል መንግሥትና በክልል መንግሥታት መካከል የሥልጣንና የሀብት ክፍፍልን ፍትሐዊና ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ ለመወሰን፣
- የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን የሥልጣን ሉአላዊነትን ለማረጋገጥ፣
- የመንግሥት ሥልጣንና ኃላፊነቶችን፣ የሥልጣን ሽግግርን፣ የዜጎችን መብቶችና ነፃነቶች፣ የሕዝቦችን ውክልና ወዘተ. ለማረጋገጥ ናቸው፡፡

**መልመጃ 2**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልሱ፡፡***

1. በሀገራችን የሚገኙት ብሄራዊ የክልል መንግሥታት የጋራ ሕገመንግሥት ባይኖራቸው ኖሮ ምን ዓይነት ችግሮች ሊከሰቱ ይችል ነበር?
2. ሕገመንግሥት በክልልና በፌደራል ደረጃ መኖሩ ምን ምን ጥቅሞችን ያስገኛል?
3. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታ የራሳቸው ሕገ መንግሥት ኖሯቸው የጋራ የሆነ ሰነድ ባይኖራቸው ሊከሰት የሚችለውን ሁኔታ አስረዱ፡፡

## 2.1.3 የሕግ ከለላ ለዜጐች የሚሰጠው ጥቅም

- *ሰዎች ሲጣሉ ወይም በደል ሲፈፀምባቸው ወደ ሕግ ቦታ ውሰዱኝ ብለው የሚማፀኑት ለምን ይመስላችኋል?*

**ከድርና ጫኔ፤**

*ከድርና ጫኔ በትምህርት ቤታቸው ውስጥ በልዩ ልዩ መንገድ ሙስና እንደሚፈፀም ደርሰውበታል፡፡ ታዲያ ሁለቱም በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚፈፀመውን ሙስና ለማጋለጥ ከወሰኑ በኋላ በአንድ የጋራ ሃሳብ ላይ ሊደርሱ አልቻሉም፡፡*

*ከድር ሙስናን ስናጋልጥ ትምህርት ቤቱ የሕግ ከለላ ካላደረገልን ልንጐዳ እንችላለን ሲል ጫኔ ደግሞ ሙስናን ለማጋለጥ ምንም የሕግ ከለላ አያስፈልግም ይላል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ሃሳብ እንድታካፍላቸው የቅርብ ጓደኞቻቸውን ሸጌን ጠየቋት፡፡*

**መልመጃ 3**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. እናንተ በሽጌ ቦታ ብትሆኑ ምን ዓይነት መፍትሄ ትሰጣላችሁ?
2. ድርጊቱን በማጋለጣቸው ምክንያት ጉዳት እንዳይደርስባቸው የሕግ ከለላ መስጠት ያለበት ማን ነው?
3. በትምህርት ቤታችሁ የሚታዩ ጥፋቶችን ለሚጠቁሙ፣ ለሚያጋልጡ ተማሪዎች ት/ቱ የሕግ ከለላ እንደ ሚያደርግ እና እንደማያደርግ ጠይቃችሁ ያገኛችሁትን ምላሽ ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡

የሕግ ከለላ ማለት በዜጐች መካከል ልዩነት ሳይደረግ ለሕይወታቸውና ለንብረታቸው ሕጋዊ ጥበቃና ዋስትና መስጠት ማለት ነው፡፡ የሕግ ከለላ ማለት ሀብትና ኃይል ያላቸው ሰዎች በገንዘብም ይሁን በጉልበት በሌሎች ዜጐች ላይ በደል እንዳይፈጽሙ መከላከል ማለት ነው፡፡

የሕግ ከለላ ዜጐች በሙሉ ነፃነት ከቦታ ቦታ እንዲንቀሳቀሱ እንዲሁም በመረጡትና በፈቀዱት የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እና የማሕበራዊ ጉዳዮች ውስጥ እንዲሳተፉ ሙሉ መብት ይሰጣል፡፡ የሕግ የበላይነት በሕገመንግሥቱ ለሰፈሩት ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ማስከበሪያ መሣሪያም ሆኖ ያገለግላል፡፡

**መልመጃ 4**

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡***

1. የሕግ ከለላ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ዜጐች የሕግ ከለላ የሚያስፈልጋቸው ለምንድን ነው?
3. የፌዴራል ሕገመንግሥት ለሕጻናት የሚሰጠውን የሕግ ከለላ ዘርዝሩ፡፡

## 2.2 ሥነምግባር

### 2.2.1 ሕብረተሰቡ ከተማሪዎች የሚጠብቀው ሥነ ምግባር

የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ ገልብጡ፡፡ በማስከተልም በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ ተመሥርታችሁ ሕብረተሰቡ ከእናንተ የሚጠብቀውን መልካም ሥነምግባር በተመለከተ /√/ ምልክት በማድረግ አመልክቱ፡፡

ሥነምግባር፣ አንድ ሰው ካለበት አካባቢ አንፃር

| ዕሴቶች | መልካም ሥነምግባር | መልካም ያልሆነ ሥነምግባር |
|---|---|---|
| አቅመ ደካሞችን መርዳት፡፡ | | |
| አካባቢን በራስ ተነሳሽነት ማጽዳት፡፡ | | |
| የአካባቢን ችግር በጋራ ለመፍታት ጥሪ ሲቀርብ ቀድሞ በአርአያነት መገኘት፡፡ | | |
| ታላላቆችን ማክበር፣ ታናናሾችን መንከባከብ | | |
| ለተቸገረ ሰው ያለንን ማካፈል | | |
| በአውቶብስ ላይ ለአቅመደካሞች ወንበር መልቀቅ | | |
| የትርፍ ሰዓት ጊዜን ሁሉ በጨዋታ ማሳለፍ፡፡ | | |
| መምህራንን ማክበር | | |
| ሕገወጥ ተግባራት ሲፈጸሙ አለመቃወም፡፡ | | |
| ሕገወጥ ድርጊት ውስጥ አለመግባት | | |
| ፈተናን ከሌሎች አለመኮረጅ | | |
| የሌሎች ሰዎችን መብት አለመንካት | | |

ማድረግ የሚገባውንና የማይገባውን፣ ጥሩና መጥፎ፣ ትክክል የሆኑትንና ያልሆኑትን ተግባራት የሚመዘንበት መርህ ነው፡፡

በአንድ በሕብረተሰብ ውስጥ መልካም ሥነምግባር በሚጠፋበት ጊዜ ራስ ወዳድነት፣ ሥርዓት አልበኝነት፣ ሌብነት፣ አጭበርባሪነት ወዘተ... እየተስፋፉ ይሄዳል፡፡ ከዚህም የተነሣ ሕብረተሰቡ ከማደግ ይልቅ በድህነት እንዲጎሳቆል ምክንያት ይሆናል፡፡ ከሀገራችን የዳበረ ባህል ውስጥ አብሮ መብላት፣ የተቸገረን መርዳት፣ አረጋውያንና ታላላቆችን ማክበር፣ በደስታና በሀዘን ጊዜ መረዳዳት የመሳሰሉት መልካም እሴቶች ናቸው፡፡

ሕብረተሰባችን ተማሪዎች ሀገር ተረካቢ ዜጎች መሆናቸውን በመረዳት በሥራቸውና በተግባራቸው የመልካም ሥነምግባር አርአያ የሆኑ ሰዎችን ፈለግ እንዲከተሉ ይፈልጋል፡፡ ተማሪዎች

ሥራን የሚያከብሩ፣ ታማኞች፣ ሀቀኞች በሰፈርና በአካባቢያቸው የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚጥሩ፣ ኃላፊነትን የሚቀበሉና ግዴታቸውን በአግባቡ የሚወጡ፣ ሕዝባቸውንና ሀገራቸውን የሚወዱ፣ የሌሎችን መብት የሚያከብሩ፣ ወዘተ. ምግባርን እንዲላበሱ ይፈልጋል።

ስለዚህ ተማሪዎች እነዚህን እና ሌሎች የመልካም ሥነምግባር መገለጫ እሴቶችን ሊከተሉና ጠብቀው ሊያቆዩአቸው ይገባል። ይህ ሲሆን ነው ሀገራችን ካለችበት ከፍተኛ ኋላቀርነት እና ድህነት ልትላቀቅ የምትችለው። ይህን ማድረግ የሚችሉት ደግሞ የሀገሮቹ ዜጎች እንጂ ሌሎች እንዳልሆኑ ተማሪዎች አጥብቀው ሊገነዘቡት የሚገባ ጉዳይ ነው፡

**መልመጃ 5**

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡***

1. በአካባቢያችሁ መልካም ሥነምግባር ያላቸው ልጆች በታላላቆች ሲመረቁ ወይም ከሥነ ሥርዓት ውጪ በሆኑ ልጆች ደግሞ ነዋሪው ሲያዝንባቸው ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? እስኪ የሰማችሁትን ምርቃቶችና እርግማኖች ከነምክንያታቸው ግለፁ፡፡
2. አንዳንድ ሰዎች «ስወላጅ መታዘዝ» «ታላቅን ማክበር» ድሮ ቀረ ሲሉ ይሰማል፡፡ እናንተ በዚህ ሐሳብ ትስማማላችሁ? ለምን? ምክንያታችሁን ግለጹ፡፡

| ምሣሌ ምርቃት | ምክንያት | እርግማን | ምክንያት |
|---|---|---|---|
| እደግ | ታላላቆች ሲልኩት እሺ በማለቱ | አትደግ | ሴቶች ልጆችን በመንገድ ስለሚተናኮል |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

## 2.3 የሥልጣን ገደብ

### 2.3.1 በመንግሥት ባለሥልጣናት ላይ የሥልጣን ገደብ የመጣል አስፈላጊነት

- *የመንግሥት ባለሥልጣን የሚባሉት ሰዎች የትኞቹ ናቸው?*
- *በመንግሥት ባለሥልጣናት ላይ የሥልጣን ገደብ መጣል ለምን ያስፈልጋል?*

**ዮትም ጌታ፤**

አቶ የትምጌታ የአንድ መሥሪያ ቤት ኃላፊ ናቸው። በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ባሉት ማናቸውም ሥራዎች ጣልቃ በመግባት ይታወቃሉ። ሠራተኛ እንዲቀጠር የሚያዙት፣ ለአዳዲስ ተቀጣሪዎች ፈተና የሚያወጡት እሳቸው ናቸው። እንዲሁም በመሥሪያ ቤቱ ትጉህ ሠራተኞችን መርጦ ለሽልማት በሚያበቃው ኮሚቴ ውስጥ ሰብሳቢም ናቸው። እሳቸውም ሁለት ጊዜ ትጉህ ሠራተኛ ተብለው ተሸልመዋል።

ለመሥሪያ ቤቱ የሚያስፈልጉ ዕቃዎች የሚገዙበትን ቦታዎች የሚወስኑት፣ የተገዙትንም ዕቃዎች ጥራት የሚያረጋግጡት እሳቸው ናቸው። ከዚህም የተነሣ በአቶ የትምጌታ ላይ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ሁለት ዓይነት አስተያየቶች ይሰጣሉ።

አንደኛው አቶ የትምጌታ ብቻቸውን ሆነው ይህንን ሁሉ ሥራ በመሥራታቸው ሊመሰገኑ፣ ሊሸለሙም ይገባል የሚል ሲሆን ሌላው ደግሞ አቶ የትምጌታ የሥልጣን ገደብ ካልተደረገባቸው ችግሮች መከሰታቸው አይቀርም የሚል ነው።

**መልመጃ 6**

***ከላይ በቀረበው ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. ከተሰጡት ሁለት ዓይነት አስተያየቶች የትኛውን ትደግፋላችሁ? ምክንያታችሁን ግለፁ፡፡
2. እነዚህ ኃላፊዎች ካላቸው ሥልጣንና ተግባር ሁለቱን ብቻ ጥቀሱ፡፡
3. አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን ሥልጣኑና ኃላፊነቱ በሕግ ገደብ ባይደረግበት ሊደርሱ የሚችሉትን ሶስት ችግሮች ጥቀሱ፡፡

በመንግሥት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ለመሥራት፣ ሥራን ለመምራት እና ለማስተዳደር በመንግሥት የተሾሙ፣ በሕዝብ የተመረጡ የሥራ ኃላፊዎች የመንግሥት ባለ ሥልጣናት ይባላሉ፡፡ እነዚህ የመንግሥት ባለሥልጣናት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችላቸው በሕግ የታወቀ በቂ ሥልጣን ይሰጣቸዋል፡፡ ስለዚህ ባለሥልጣናቱ ሥልጣን ቢኖራቸውም መሥራት የሚገባቸው በሕግ ተወስኖ በተሰጣቸው የሥልጣን ገደብ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን የተሰጣቸውን የሥልጣን ገደብ አልፈው ቢገኙ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

ለምሣሌ አንድ ባለሥልጣን ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ዜጎችን በቁጥጥር ሥር እንዲውሉና እንዲቀጡ ማድረግ አይችልም፡፡ ይህን ካደረገ የሥልጣን ገደቡን አለፈ ማለት ነው፡፡ በመንግሥት ባለ ሥልጣናት ላይ የሥልጣን ገደብ መጣል የሚያስፈልገውም፤

- የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዳይጣሱ፣
- የሕግ የበላይነት እንዳይሸረሸር፤
- የግልጽነትና የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲሰፍን፣
- ሕብረተሰቡ ተገቢ አገልግሎት እንዲያገኝ፤
- አድሎአዊ አሠራሮችን፣ ሕገወጥነትንና ሥርዓተ አልበኝነትን ለመከላከል ወዘተ... ናቸው፡፡

**መልመጃ 7**

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጡ፡፡***

?

1. **የትምህርቱን ሥራ ስመሥራት ስመምራት በመንግሥት የተሾሙ የትምህርት ቤታችሁ የሥራ ኃላፊዎች እነማን ናቸው?**
2. **እነዚህ ኃላፊዎች ካላቸው ሥልጣንና ተግባር ሁለቱን ብቻ ጥቀሱ፡፡**
3. **አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን ሥልጣኑና ኃላፊነቱ በሕግ ገደብ ባይደረግበት ሲደርሱ የሚችሉትን ሶስት ችግሮች ጥቀሱ፡፡**

## 2.4 ምስጢር

### 2.4.1 የቤተሰብ ምስጢር

- «የቤታችን ገመና እንዳይወጣ» ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ሰምታችሁ ከሆነ በምሣሌ ለማስረዳት ሞክሩ፡፡
- «ምስጢር የባቄላ ወፍጮ አይደለም» የሚባለው ለምንድን ነው?

***ከታች በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን ጉዳዮች በመመርምር የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1ኛ. ከቀረቡት አራት ጉዳዮች መካከል የቤተሰብ ምስጢር የሆኑትን ለዩ፡፡

2ኛ. የቤተሰብ ምስጢር የሆኑበትን ምክንያት አብራሩ፡፡

3ኛ. ምስጢሩ ቢወጣ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ዘርዝሩ፡፡

4ኛ. ከቀረቡት አራት ጉዳዮች መካከል የቤተሰብ ምስጢር ሊሆኑ የማይችሉትን ለይታችሁ ምክንያታችሁን አቅርቡ፡፡

| | |
|---|---|
| 1 | በመስኮት ወደ ውጪ በመመልከት ላይ እያለች በድንገት በልጆቿ የተወረወረ ድንጋይ የሌላ ሰው የቆመ መኪና መስታወት ሲሰብር ተመለከተች፡፡ ድርጊቱን ከሷ ሌላ ያየ አልነበረም፡፡ |
| 2 | የ14 ዓመቱ ልጅ ሽንቱን መቆጣጠር ስለማይችል አልጋው ላይ ይሸናል፤ ጉዳዩ በቤተሰብ ምስጢር ሆኖ ተይዟል፡፡ |
| 3 | በወላጆቿ መካከል ከፍተኛ አለመግባባት በመከሰቱ ትምህርቷን መከታተል አልቻለችም፣ ትተክዛለች፣ አልፎ አልፎም ታለቅሳለች፡፡ ሁኔታው ያሳሰባቸው የቅርብ ጓደኛዋ እና መምህሯ ምን እንደደረሰባት በተደጋጋሚ ስለጠየቋት ጉዳዩን ነገረቻቸው፡፡ |
| 4 | አንድ ቤተሰብ በሎተሪ ዕጣ ግማሽ ሚሊዮን ብር ደርሶታል፡፡ ይህ ጉዳይ ምስጢር ሆኖ በቤተሰቡ ተይዟል፡፡ |

ብዙ ቤተሰቦች ስለ እለት ከእለት ኑሯቸው፣ ስለ ልጆቻቸው አስተዳደግ፣ ትምህርት፣ ሥራ፣ ስለ ማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ወዘተ… ይወ ያያሉ፣ ይመካከራሉ፡፡ አልፎ አልፎም በቤተሰብ አባላት፣ በባልና በሚስት፣ በወላጆች፣ በወንድ ማማቾችና በእህትማማቾች ወዘተ… መካከል አለመግባባቶች እና ግጭቶች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ ታዲያ እነዚህን በቤተሰብ ውስጥ የሚያጋጥሙ ጉዳዮችን ለሌሎች መናገር አስነዋሪ ምግባር ነው፡፡

የቤተሰብ ምስጢር በቤተሰብ አባላት ብቻ ተጠ ብቆ የሚቆይ ለቤተሰቡ ሠላም፣ ደህንነት እና መሻሻል አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን ያካትታል፡፡ የቤተሰብ ምስጢር ለሌሎች ሰዎች የማይጠቅም ይልቁንም በቤተሰቡ ላይ ጉዳት ወይም ችግር ሊያስከትል የሚችል ጉዳይ ሊሆን ይችላል፡፡

የቤተሰብን ምስጢር መጠበቅ የአንድ መልካም ዜጋ መገለጫ ባህርይ ነው፡፡ እነዚህ ባህሪዎች ማደግ የሚገባቸው በቤተሰብ ውስጥ ነው፡፡ የቤ ተሰብን ምስጢር መጠበቅ የተለማመደ ወጣት ወደፊት በሀገርና በመሥሪያ ቤት ደረጃ የሚያ ውቃቸውንም ሆነ በሌላ አጋጣሚ ያገኘውን ምስ ጢር የመጠበቅ ጠንካራ ባህሪ ይኖረዋል፡፡ በዚ ህም ታማኝና ሀቀኛ ዜጋ ይሆናል፡፡

ይሁንና አንዳንድ ጊዜ ምስጢር ያልሆኑ ነገ ሮች ምስጢር ናቸው ተብለው በቤተሰብ መካከል ተጠብቀው የሚቆዩበት ሁኔታዎችም አሉ፡፡ ለም ሣሌ ያታዊ ጥቃቶች፣ የአካልና የአእምሮ ችግር ያለባቸውን ህፃናትና ተገቢ ባልሆነ ቅጣት የተ ጐዳ ህፃንን መደበቅ ወዘተ… ምስጢር ተብለው ሊያዙ ይችላሉ፡፡ እነዚህ መሰል ጉዳዮች ምስ ጢር ተደርገው መያዛቸው ተገቢ ካለመሆኑም በላይ የወንጀል ድርጊት የሚሆኑበትም ሁኔታ አለ፡፡

ስለዚህ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባላት የቤተሰብ ምስጢር የሆኑ ጉዳዮችንና ምስጢር ያልሆኑትን መለየቱ ተገቢ ነው፡፡

**መልመጃ 8**

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡***

**?**

1. የቤተሰብ ምስጢር ማለት ምን ማለት ነው?
2. የቤተሰብ ምስጢር መጠበቅ ያለበት ማን ነው?
3. ምስጢርን መጠበቅ ለምን ያስፈልጋል?

### 2.4.2 የቤተሰብን ምስጢር አለመጠበቅ የሚያስከትለው ጉዳት

- የቤተሰብን ምስጢር አለመጠበቅ ምን ጉዳት ያስከትላል?
- በቤተሰብ ምስጢር አለመጠበቅ ምክንያት ችግር ውስጥ የገቡ ቤተሰቦችን ታውቃላ ችሁ? ካወቃችሁ ምስጢሩ በመባከኑ የተ ፈጠረውን ችግር ለጓደኞቻችሁ አካፍሉ፡፡

**ቁልፉ፤**

እነ ሚሚ ቤታቸውን ከቆለፉ በኋላ መክፈቻውን በቤታቸው በራፍ ከሚገኘው ሙቀጫ ሥር አስ ቀምጠው ይሄዳሉ፡፡ ቀድሞ ወደ ቤት የመጣ የቤተሰቡ አባል የቤቱን መክፈቻ ቁልፍ ከሙቀ ጫው ሥር ነው የሚያገኘው፡፡ ለረጅም ጊዜ ይህን ምስጢር ከቤተሰቡ አባል ውጭ ማንም የሚያውቅ አልነበረም፡፡

ይሁን እንጂ ከእለታት አንድ ቀን ሚሚ የቤታ ቸው መክፈቻ ቁልፍ የሚቀመጥበትን ምስጢር ለጓደኞቿ ስትናገር ምስጢሩ በአካባቢው በነበሩ ሌቦች ጆሮ ገባ፡፡ በተከታዩ ቀንም የቤታቸው ንብ ረት በሙሉ ተዘረፈ፡፡ በዚህ የተነሳም በቤተሰቡ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደረሰ፡፡

ሊሰሩ የታሰቡ ዕቅዶች ሁሉ ከንቱ ሆነው ቀሩ፡፡ ይህ ጉዳት የደረሰውም «የቁልፉን» ምስጢር በመ ታወቁ መሆኑን ጉዳዩን የተከታተሉት የፀጥታ ኃይሎች አረጋገጡ፡፡

## መልመጃ 9

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

?

1. የቀልፉ ምስጢር እንዴት ሲባክን ቻለ?
2. ወደፊት የዚህ መሰል ሌሎች ምስጢሮች ችግር እንዳያደርሱ በቤተሰብ ውስጥ ምን መደረግ አለበት?
3. ለችግሩ መከሰት ምክንያት እነማን ናቸው?

## መልመጃ 10

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን ስጡ፡፡***

?

1. የቤተሰብ ምስጢር የሚባሉት እንዴት ያሉ ጉዳዮች ናቸው?
2. የቤተሰብ ምስጢር በመባከኑ ምክንያት ሊፈጠሩ ይችላሉ ብላችሁ የምትገምቷቸውን ችግሮች ዘርዝሩ፡፡

## 2.5 ሙስና

### 2.5.1 ሙስና በመንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት

- በአካባቢያችሁ በሚገኙ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ ሊፈጸሙ የሚችሉ የሙስና ተግባራትን ግለጹ፤
- የእናንተን ወይም የቤተሰባችሁን ጉዳይ ለማስፈፀም ወደ አንድ መሥሪያ ቤት ሄዳችሁ ተጉላልታችሁ ታውቃላችሁ? ከሆነ ሁኔታውን ለጓደኞቻችሁ አካፍሏቸው፡፡

### ኮሚቴው፤

አንድ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት እድሜያቸው ከ16 ዓመት በላይ የሆኑ ሁለት ተማሪዎችን በክረምት የእረፍት ጊዜያት በድርጅቱ ውስጥ በጊዜያዊነት ተቀጥረው እንዲሰሩ ለትምህርት ቤት እድል ሰጠ፡፡ በወጣው መስፈርት መሠረት ሥራውን ለመሥራት የሚመረጡት ተማሪዎች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሆነው የዓመቱ የክፍል አማካኝ ውጤታቸው 85% እና ከዚያ በላይ የሆነ እና በክፍል ደረጃቸው ከ1ኛ-3ኛ የወጡ መሆን አለባቸው፡፡

ትምህርት ቤቱም ለዚህ የሥራ እድል ተማሪዎችን አወዳድሮ የሚለይ ኮሚቴ አቋቋመ፡፡ ነገር ግን ኮሚቴው ለውድድር ማስታወቂያ ሳያወጣ በሚከተለው መሠረት አምስት ልጆችን ብቻ ለውድድር አቀረበ፡፡

ኮሚቴው ከላይ ከቀረቡት አምስት ልጆች መካ

| ስም | የክፍል ደረጃ | ዕድሜ | የክፍል ደረጃ | የ8ኛ ክፍል ውጤት |
|---|---|---|---|---|
| በላይ ግርማ | 9 | 16 | 1ኛ | 90% |
| ዘሪቱ ሞላ | 10 | 17 | 5ኛ | 88% |
| ጫልቱ አገኘ | 9 | 17 | 1ኛ | 92% |
| ሀሰን ዳንቻ | 10 | 15 | 1ኛ | 94% |
| ደንድር ገዳ | 9 | 15 | 4ኛ | 86% |

ከል የአንዱን የኮሚቴ አባል ልጅ የሆነችውን ዘሪቱ ሞላን እና የሌላው የኮሚቴ አባል የወንድም ልጅ የሆነችውን የደንድር ገዳን ስም ለድርጅቱ አስተላለፈ፡፡ ልጆቹም ተቀጥረው መስራት ጀመሩ፡፡

ነገር ግን የትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ተወካይ ውድድሩ ከመጀመሪያው አንስቶ የአሰራር ግድፈት ያለበት መሆኑን ጠንክሮ በመከራከሩ ምክንያት ጉዳዩን የሚያጣራ ኮሚቴ ተቋቋመ፡፡ ኮሚቴውም ጉዳዩን በመመርመር ላይ ይገኛል፡፡

## መልመጃ 11

### ከላይ በቀረበው ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

?

1. በምንባቡ መሠረት ሙስና ተፈጽሟል አልተፈፀመም?
2. ሙስና ተፈጽሞ ከሆነ ምን ዓይነት ሙስና ነው የተፈፀመው?
3. ሙስና የፈፀሙት እነማን ናቸው?
4. በሙስናው ተጐጂ የሆኑት እነማን ናቸው?
5. ትክክለኛው አሠራር ምን መሆን ነበረበት ትላላችሁ?

ሙስና በተለያዩ ቦታዎች ሊከሰት የሚችል ወንጀል ነው፡፡ ሙስና የተመደቡበትን የመንግሥት ሥራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰው ወይም ለቡድን ጥቅም ማስገኘት፣ ጉቦ መቀበል፣ በሥልጣን ያለአግባብ መጠቀም፣ የመንግሥትን ንብረት ለግል ጥቅም ማዋል፣ በዝምድና መስራትና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ እነዚህ የሙስና ተግባራት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ ሊፈፀሙ የሚችሉ ሕገ ወጥ ድርጊቶች ናቸው፡፡

ለሙስና መፈፀም ምክንያት ከሚሆኑት ነጥቦች መካከል ግልጽ የሆኑ ሕጐች፣ የአሠራር መመሪያዎች አለመኖር ነው:: ለምሣሌ አንድ ተገልጋይ ጉዳዩን ለማስፈፀም የመሥሪያ ቤቱን አሠራር ደንብ እና የሚሄድበትን ቢሮ ካላወቀ የሚፈልገውን አገልግሎት ለማግኘት ይቸገራል፡፡ በመሆኑም ከምንገላታ በማለት በሕጋዊ መንገድ ማግኘት የሚገባውን አገልግሎት በሕገ ወጥ መንገድ ክፍያ ለመክፈል ወይም ለአገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች ጉቦ ለመስጠት ይገደዳል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግልጽ መመሪያና አሠራር ቢኖርም አንዳንድ ሠራተኞች ሆን ብለው ባለጉዳዮችን በማጉላላት ወይም ጉዳዩን በማጓተት ተገልጋዩ ጉቦ እንዲሰጣቸው የሚያመቻቹበት ሁኔታም አለ፡፡

አንዳንድ ጊዜ ለሥራ በተሰጠ መኪና መነገድ፣ ለሥራ የተሰጠን የቢሮ ቁሳቁሶችን ለግል ጥቅም ማዋል፤ መውሰድ የሥራ ሰዓትን የግል ሥራን ለመሥራት መጠቀም የመሳሰሉት የሙስና ተግባራት ናቸው፡፡

ለሕዝብ የተመደበን እና በሕዝብ ስም የተሰበሰበን ገንዘብና ንብረት ለግል መበልፀጊያ የማድረግ ተግባር በአንዳንድ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በተደጋጋሚ የሚታዩ የሙስና ድርጊቶች ናቸው፡፡

በዝምድናና በወዳጅነት መሥራት ሌላው የሙስና መፈፀሚያ መንገድ ነው፡፡ ይህ የሙስና ዓይነት አድልዎ በመሥራት፣ በአምቻ ጋብቻ፣ በዝምድና ወዘተ... ባለ መብት ያልሆነውን ሰው በመጥቀምና ሌላውን በመጉዳት የሚፈፀም ነው፡፡ ለምሳሌ ሥራ ለመቀጠር የሚሰጥ ፈተናን ለተፈታኝ ወይም ለዘመድ ቀድሞ በመንገር ለሥራው ተገቢ ያልሆነ ሰው እንዲያልፍ በማድረግ ማለፍ ያለበት የሚጎዳበት አድሎአዊ አሠራር የሙስና አንዱ ገፅታ ነው፡፡

## መልመጃ 12

### የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

?

1. የሚፈፀሙ የሙስና ድርጊቶች የምትሏቸውን ዘርዝሩ፡፡
2. በቡድን ሆናችሁ ቀጥሎ ከተከረዘሩት መሥሪያ ቤቶች አንዱን በመምረጥ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ሙስና ሲፈፀም የሚያሳይ ድራማ አቅረቡ፡፡
   ሀ. ሆስፒታል፣
   ለ. ትምህርት ቤት፣
   ሐ. መብራት ኃይል፣
   መ. ቀበሌ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ለአንድ ሀገር እድገትና ደህንነት የሕግ የበላይነት መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ ለሕግ የበላይነት መከበር ደግሞ የሕጐች ሁሉ የበላይ የሆነው ሕገመንግሥት መከበር አለበት፡፡ ሕገመንግሥስት የሕጐች ሁሉ የበላይ እንደመሆኑ ለሌሎች ሕጐች መነሻ ሕግ ነው፡፡ በፌዴራል አስተዳደር የሚመሩ የተለያዩ ማሕበረሰቦች መብቶቻቸው ተጠብቀው፣ ተቻች ለውና ተፋቅረው እንዲኖሩ በጋራ የሚመሩበት የፌደራል ሕገመንግሥት ያስፈልጋቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥትም ይህንኑ አረጋግጧል፡፡

በዜጐች መካከል ልዩነት ሳይደረግ ለሕይወታቸው፣ ለሀብታቸው፣ ለመብቶቻቸውና ለማንኛውም ደህንነታቸው ሕጋዊ ጥበቃ ወይም ዋስትና ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህም የሕግ ከለላ ይባላል፡፡

ሕብረተሰቡ ከወጣት ተማሪዎች መልካም ሥነምግባር ይጠብቃል፡፡ ከነዚህም መካከል ሥራን ማፍቀርና ማክበር፣ በአካባቢን ማክበር፣ በአካባቢ ለሚፈጠሩ ችግሮች መፍትሄ ለመፈለግ ግንባር ቀደም መሆን፣ አካባቢን በራስ ተነሣሽነት ማጽዳት፣ ታላላቆችን መርዳት፣ ለተቸገረ ማካፈል፤ ትሁትና ታማኝ መሆንና የመሳሰሉትን ባህሪያት ከወጣት ተማሪዎች ይጠበቃሉ፡፡

ባለሥልጣናት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ያሉ ሥራዎችን ለመሥራት፣ ለማሠራትና፣ ለመምራት በመንግሥት የሚሾሙ ወይም በሕዝብ የሚመረጡ የሥራ ኃላፊዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ባለሥልጣናት ውሣኔ ሰጪ እንደመሆናቸው ከተሠጣቸው ሥልጣንና ኃላፊነት ውጭ እንዳይሰሩና በደል እንዳይፈጽሙ ሥልጣናቸው በሕግ የተገደበ ነው፡፡

በቤተሰብ አባላት ብቻ ተጠብቆ የሚቆይ ምስጢር የቤተሰብ ምስጢር በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ ምስጢር ከቤተሰብ አባል ወጪ ከወጣ በቤተሰቡ ላይ ወይም በቤተሰቡ አባል ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡

ሌላው ለሕግ የበላይነት አለመከበር ምክንያት የሚሆነው ሙስና ነው፡፡ የተመደቡበትን የመንግሥት ሥራና ኃላፊነት ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰው ወይም ለቡድን ጥቅም መጠየቅ፤ ጉቦ መቀበል፤ በሥልጣን መነገድ፤መስረቅ፤ በዝምድና መሥራትና የመሳሰሉት የሙስና ተግባራት ናቸው፡፡ አሠራሮችን ግልጽ ባለማድረግ፣ ባለጉዳዮች በማጉላላት፣ ሚስጢርን በማባከን በዝምድናና በትውውቅ በመሥራት ሙስና ሊፈፀም ይችላል፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

| | |
|---|---|
| **የፌዴራል ሕገመንግሥት፣** | በፌዴራላዊ አስተዳደር የሚመሩ የተለያዩ ማህበረሰቦች፣ ጥቅሞቻቸውና መብቶቻቸው ተጠብቆላቸው ተቻችለውና ተከባብረው እንዲኖሩ በጋራ የሚመሩበት ሕገ መንግሥት:: |
| **የሕግ ከለላ፣** | በዜጐች መካከል ልዩነት ሳይደረግ ለሕይወታቸው፣ ለንብረታቸው፣ ለመብቶቻቸውና ለማንኛውም ደህንነታቸው የሚደረግ ሕጋዊ ጥበቃ:: |
| **የመንግሥት ባለሥልጣን፣** | በመንግሥት መሥሪያ ቤት የመንግሥት ሥራ ለመሥራት፣ ለማሠራትና ለመምራት በመንግስት የሚሾሙ ወይም የሚመረጡ የሥራ ኃላፊዎች:: |
| **መንግሥታዊ ተቋማት፣** | የመንግሥትን ሥራ ለመሥራት የተቋቋሙ መሥሪያ ቤቶች:: |
| **መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣** | በእርዳታ ወይም በስጦታ በሚገኝ ገንዘብ የሚተዳደሩ ሕዝብን ለማገልገል የሚቋቋሙ አትራፊ ያልሆኑና በመንግሥት የማይመሩ ድርጅቶች:: |
| **የሥልጣን ገደብ፣** | ሥልጣንና ኃላፊነትን የሚጠቀም በሕግ የተደገፈ የሥልጣን ኃላፊነት ክልል ወይም ገደብ:: |
| **የቤተሰብ ምስጢር፣** | በቤተሰብ አባላት ብቻ ታውቆ ለሁል ጊዜ ተጠብቆ የሚቆይ ጥብቅ ጉዳይ:: |

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ፡፡*

## I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ፡፡

1. የክልል ሕገመንግሥታት በምንም ዓይነት መንገድ ከፌዴራል ሕገመንግሥቱ አይቃረኑም ፡፡
2. በመንግሥት ባለሥልጣናት ላይ የሥልጣን ገደብ ከተደረገላቸው ለዜጐች የሕግ ከለላ ማድረግ አያስፈልግም፡፡
3. በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለሥልጣናት ለሚፈጽሙት የሕግ መተላለፍ ተግባር በሕግ ሊጠየቁ አይችሉም፡፡

## II. በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የተያዙ ሰዎች የቀረበባቸው ክስና ምክንያት ወዲያውኑ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲነገራቸው መብት አላቸው፣ | ሀ. የህጻናት መብት የሕግ ከለላ፡፡ |
| 2. ሥራን ለመሥራትና ለማሠራት በሕግ የተከለለና የተሰጠ ኃላፊነት፣ | ለ. የሴቶች መብት የሕግ ከለላ፡፡ |
| 3. በትምህርቱ፣ በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎች እንዲሰራ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ፣ | ሐ. የተያዙ ሰዎች መብት የሕግ ከለላ፡፡ |
| 4. የውሸት ደረሰኝ በማቅረብ ከመሥሪያ ቤት ክፍያ መቀበል፣ | መ. የሥልጣን ገደብ፡፡ |
| 5. ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጐች፣ ወጐችና ልማዶች፣ | ሠ. ሙስና፡፡ |

## III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ትክክለኛው ቅደም ተከተል የቱ ነው?
   - ሀ. የትምህርት ቤት ደንብ ⟶ የፌዴራል ሕገመንግሥት ⟶ የክልል ሕገመንግሥት ⟶ የትምህርት ቢሮ መመሪያ
   - ለ. የት/ቢሮ መመሪያ ⟶ የክልል ሕገ መንግሥት ⟶ የት/ቢሮ ደንብ ⟶ የት/ቤት ደንብ
   - ሐ. የፌዴራል ሕገ መንግሥት ⟶ የክልል ሕገ መንግሥት ⟶ የት/ቢሮ መመሪያ ⟶ የትምህርት ቤት ደንብ
   - መ. የት/ቤት ደንብ ⟶ የክልል ሕገመንግሥት ⟶ የት/ቢሮ መመሪያ ⟶ የፌዴራል ሕገመንግሥት

2. ከሚከተሉት ውስጥ የቤተሰብ ምስጢር ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. የባልና ሚስት ምስጢር፣ ሐ. የጓደኛና የግል ምስጢር፣
   ለ. የእህትና የወንድም ምስጢር፣ መ. የአባትና የእናት ምስጢር።
3. ከተማሪዎች የማይጠበቀው ሥነምግባር የቱ ነው?
   ሀ. በአካባቢ ልማት መሣተፍ፣ ሐ. አካባቢን በጋራ ማጽዳት፣
   ለ. መንገድ ዘግቶ ማውራት፣ መ. ታናናሾችን መርዳት።

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ።

1. ዜጎች ለንብረታቸው፣ ለመብታቸውና፣ በሠላም ወደፈለጉበት ሥፍራ ለመዘዋወር የሕግ __________ ያስፈልጋቸዋል።
2. የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ከተሰጣቸው ሥልጣን ውጭ አልፈው እንዳይሠሩ __________ ማድረግ ተገቢ ነው።
3. __________፣__________እና__________ ሕብረተሰቡ ከተማሪዎች የሚጠብቃቸው የመልካም ሥነምግባር መገለጫዎች ናቸው።

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ።

1. በፌደራል አስተዳደር የሚመሩ ማሕበረሰቦች ለምን የፌዴራል ሕገመንግሥት ያስፈልጋቸዋል?
2. የፌደራል እና የክልል ሕገመንግሥቶች የሚዛመዱበትን መንገድ ግለጹ።
3. በባለሥልጣናት ላይ የሕግ ገደብ ማድረግ ለምን ያስፈልጋል?
4. የቤተሰብ ምስጢር የሆኑትን ምስጢር ካልሆኑት እንዴት መለየት ይቻላል?
5. በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ሙስና ከሚፈፀምባቸው መንገዶች ሁለቱን ግለፁ።

# ምዕራፍ ሦስት

# እኩልነት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶችን ታውቃለህ/ ታውቂያለሽ::
- ሴቶችና ወንዶች በሁሉም መብቶች እኩል መሆናቸውን ትረዳለህ/ ትረጃለሽ::
- የአካል ጉዳተኞችን የእኩል ተጠቃሚነት መብቶች ትገነዘባለህ/ ትገነዘቢያለሽ::

## 3.1 የእኩልነትና የእኩል ተጠቃሚነት መብት

- የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በእኩልነት መኖራቸው ምን ጥቅም አለው?

**የየሺእመቤትና የአሰፋ ውይይት፤**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት ሁሉም ዜጎች በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውን ደንግጓል:: እንዲሁም ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች የተለየ እገዛና ድጋፍ እንዲሰጥ የሚያስችሉ ድንጋጌዎችም አሉ:: ይህንን ጉዳይ በተመለከተ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የሆኑት የአሰፋና የሺእመቤት በክፍል ውስጥ በክርክር መልክ ሀሳባቸውን በየተራ እንደሚከተለው ገልጸው ነበር::

**አሰፋ፣** ሕገመንግሥቱ ሁሉም ዜጎች እኩል መሆናቸውን ስላረጋገጠ ሳንበላለጥ በእኩል መታየት አለብን:: ምክንያቱም ለአንዱ ልዩ ድጋፍ ተደርጎ ለሌላው ከተከለከለ አድሎ አለ ማለት ነው:: ይህ ደግሞ የሕገ መንግሥቱን መርህ የሚቃረን ነው:: በዚህ የተነሳ ሃሳቡን አልቀበለውም በማለት ሐሳቡን ገለፀ::

**የሺእመቤት፣** በሕገመንግስቱ የሁሉም ሰዎች እኩልነት መደንገጉ ይታወቃል:: ይህ እንዳለ ሆኖ ግን በጎጂ ድርጊቶች፣ በታሪክ፣ በፆታና በሌሎች ምክንያቶች የተፈጠሩ ጉዳቶችንና አድሎዎችን ለማስተካከል ሲባል ልዩ ድጋፍ መደረጉ ተገቢ ነው:: ይህም የእኩልነትና የእኩል ተጠቃሚነት መብቶችን የበለጠ ተግባራዊ ለማድረግ ያግዛል በማለት አስረዳች::

**መልመጃ 1**

***ከላይ በቀረበው ውይይት መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. ከአሰፋና ከየሺእመቤት የመከራከሪያ ሀሳቦች መካከል የትኛውን ትደግፋላችሁ? ምክንያታችሁን አስረዱ::
2. በሕገመንግሥቱ የተለያዩ አንቀጾች ውስጥ ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞችና ለአንዳንድ ክልሎች የተለየ ድጋፍ መደረግ እንደሚገባው ተደንግጓል:: ይህንን ከእኩልነት መብት አንጻር እንዴት ታዩታላችሁ?

የእኩልነት መብት ሲባል የሰው ልጆች ሰብዓዊ መብቶች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በተግባር መከበር እንዳለባቸው የሚያመለክት ሀሳብ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ የግለሰቦችም ሆነ የቡድኖች ዴሞክራሲያዊ መብቶች በሕገመንግሥት ውስጥ በተቀመጡት መሰረት ሳይሸራረፉ ሊተገበሩ እንደሚገባ ያመለክታል::

በፌደራል ሕገመንግሥት ውስጥ ማንኛውም ሰው ሊከበሩለት የሚገቡ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በማያሻማ መልኩ ሰፍረው ይገኛሉ:: ይህም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ከእነዚህ የእኩልነት መብቶች ተጠቃሚ እየሆኑ እንደሚገኙ ያሳያል::

ማንኛውም ዜጋ ተመሳሳይ መብት፣ እድልና ጥቅም ሲያገኝና ተመሳሳይ ጥበቃ ሲደረግለት የእኩል ተጠቃሚነት መብቱ በተግባር ይረጋገጣል፡፡ ሁሉም ሰው በሕግ ፊት እኩል ሲታይና የሀገሪቱን ሀብት በእኩልነት መጠቀም ሲችል የእኩል ተጠቃሚነት መብት በተግባር ይረጋገጣል፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግሥት የግለሰብንና የቡድንን ኢኮኖሚያዊ ማሕበራዊና ባህላዊ መብቶች እንዲሁም የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦችን መብቶች በዝርዝር ደንግጓል፡፡ ይህም የእኩል ተጠቃሚነት መብት በሀገራችን ውስጥ ዋስትና ማግኘቱን ያመለክታል፡፡

**መልመጃ 2**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. በአካባቢያችሁ የእኩልነት መብቶች ምን ያህል ተግባራዊ እየሆኑ ይገኛሉ?
2. በሕገመንግሥቱ የተደነገገውን አንቀፅ 25ን መሠረት በማድረግ የእኩልነትን መብት ምንነት አስረዱ፡፡
3. የእኩል ተጠቃሚነት መብት የማክበርን አስፈላጊነት አብራሩ፡፡

### 3.1.1 የብሔሮች፣የብሔረሰቦችና የሕዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶች መገለጫዎች



*ሥዕል 3.1 የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች*

- ከሥዕሉ ምን ተገነዘባችሁ?
- ሀገራችን ኢትዮጵያ የሕዝቦች ሙዚየም ናት ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

**«የሄሴ ሕዝቦች»**

የሄሴ ህዝቦች በአንድ የዞን መስተዳድር ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የሄሴ ብሔረሰብ አባላትም በዞኑ ሦስት ተጎራባች ወረዳዎች ውስጥ በስፋት ይኖራሉ፡፡ ሄሴዎች የራሳቸው ታሪክ፣ ቋንቋና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች አሏቸው፡፡ በአንድ ወቅት የሄሴ ብሔረሰብ አባላት ተሰብስበው በአንድ ዞን ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር የእኩልነት መብታቸውን መጠቀም እንዲችሉ በተወካዮቻቸው አማካኝነት ለክልሉ ምክር ቤት ጥያቄያቸውን አቀረቡ፡፡

በምክር ቤቱ ውስጥ ከብሔረሰቡ ተወካዮች አንዷ የሆኑት ወ/ሮ አትጠገብ «እኛ በፌዴራል ሥርዓት በዴሞክራሲ የምንመራ ነን፣ ስለዚህ ራሳችንን በራሳችን የማስተዳደር መብት በሕገመንግሥቱ ተሰጥቶናል፡፡ በአካባቢያችን የተፋጠነ ልማት ለማምጣት ተደራጅተን መንቀሳቀስ አለብን» በማለት ሃሳባቸውን ለምክር ቤቱ ገለጹ፡፡ አንድ የምክር ቤቱ አባል ግን «አዲስ ዞን ሆናችሁ ስትቋቋሙ ከሌሎች ተለይታችሁ ለመኖር ቢከብዳችሁ እና የአካባቢያችሁ ነዋሪዎች ሰበብ እየፈለጉ ቢያጠቋችሁስ?» ሲሉ ጥያቄ አዘል ሀሳብ ሰነዘሩ፡፡

ሌላው በምክር ቤቱ የሄሴዎች ተወካይ የሆኑት አቶ ሁሴን «የራስን እድል በራስ መወሰን የሕዝቦች መብት ነው፡፡ በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ ሕዝቦች እኩልነታቸው ከተከበረላቸውና ከታወቀላቸው አብረውና ተባብረው መኖርን ይመርጣሉ እንጂ ጠላቶች ሊሆኑ ስለማይችሉ ጥቃት ይደርስብናል በማለት ልንፈራ አይገባንም፡፡» በማለት አስተያየታቸውን ገለጹ፡፡

የሄሴ ብሔረሰብም በተወካዮቹ ያቀረበው ጥያቄ በምክር ቤቱ ከፍተኛ ድምጽ አግኝቶ ከፀደቀ በኋላ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ተላከ፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤትም ጉዳዩን በሕገመንግሥቱ መሰረት ከመረመረ በኋላ ተቀብሎ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጠ፡፡

**መልመጃ 3**

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

?

1. የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ምን ጥቅም ያስገኛል?
2. የሄሴ ሕዝብ ራሱን በራሱ ስማስተዳደር ያቀረበው የመብት ጥያቄ በምን ሁኔታ ተግባራዊ ሆነ?
3. አብሮና ተባብሮ ስመኖር መከበር ያለባቸው መብቶችን ዘርዝሩ፡፡

በኢትዮጵያ ሕገመንግሥት ውስጥ የጎላ ስፍራ ከተሰጣቸው መብቶች መካከል የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብቶች ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ከነ ዚህም መብቶች መካከል የራስን ነፃ መንግሥት እስከ መመሥረት የሚዘልቅ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት አንዱ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሉዓላዊ ሥልጣናቸውን በመጠቀም የፌደራሉን መንግሥት መስርተዋል፡፡ የፌደራል አወቃቀር ሥርዓትን እውን በማድረግም በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት ፈጥረዋል፡፡ ለዚህም የጋራ ቃልኪዳን ሰነድ የሆነውን ሕገመንግሥት አጽድቀዋል፡፡ የእኩልነት መብቶቻቸው ስለተረጋገጠ ላቸው ኢትዮጵያ በጋራ የሚኖሩባትና የሚጠቀሙባት ሀገር ሆናለች፡፡

ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ከማስተዳደራቸው በተጨማሪ በፌደራሉ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮችና የፌደሬሽን ምክር ቤቶች ውስጥ ተመጣጣኝ ውክልና እንዲኖራቸው መደረጉ ሌላው የእኩልነት መብት መገለጫ ነው፡፡

**መልመጃ 4**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደራቸው የሚያስገኙላቸውን ጥቅሞች ዘርዝሩ፡፡
2. የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የእኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶች እንዴት እንደተከበሩ ግለጹ፡፡

## 3.2 የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቋንቋዎችና፣ የሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች እኩልነት መከበር አስፈላጊነት

- በአንድ አገር ውስጥ አለመረጋጋትንና ብጥብጥን ሊያነግሱ የሚችሉ ሁኔታዎች ምን ምን ይመስሏችኋል?

በሀገራችን ባለፉት የረጅም ዘመናት ታሪክ ውስጥ በተለያዩ ጨቋኝ መንግሥታት አገዛዝ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ታሪኮቻቸው፣ ቋንቋዎቻቸውና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎቻቸው ተንቀውና ተረስተው ኖረዋል፡፡ በእነዚህም ምክንያቶች ሀገራችን ሠላሟ ተናግቶ፣ ልማቷና እድገቷ ተጓትቶ ቆይታል፡፡

ትክክለኛ ባልሆኑ ተፅዕኖዎች ምክንያትም የሕዝቦች ማንነት ተዋርዶ ቆይቷል፡፡ በርካታ ዜጎችም በሥርዓቶቹ ኢ-ዴሞክራሲያዊ የመብት ረገጣዎች ሰለባ ሆነዋል፡፡ ለዚህ ማሳያ ከሚሆኑት ድርጊቶች መካከል በሀገራችን ታሪክ “ቀይ ሽብር” ተብሎ የሚታወቀው በደርግ ዘመን የተካሄደው ጭፍጨፋ አንዱ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ከ80 በላይ የሚሆኑ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም ቋንቋዎቻቸው ይገኛሉ፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግሥት መሠረት ሁሉም እኩል ናቸው፡፡ በርካታ ቋንቋዎችና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች ባሉባት ሀገር የነዚህ መብቶች እኩልነት መከበር ዘላቂ ሠላም ለማምጣት፣ ልማትና እድገትን ለማፋጠን እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

**መልመጃ 5**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***


?

1. የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች መብቶችን በተሟላ መልኩ ማክበር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ዘርዝሩ፡፡
2. የመብቶች አለመከበር ምን ምን ጉዳቶችን ሊያስከትል ይችላል?
3. «ቀይ ሽብር» ስለተባለው ዘግናኝ ጭፍጨፋ ከመጽሐፍ በመፈለግ ወይም የታሪክ መምህራችሁን ጋብዛችሁ በመጠየቅ ተወያዩ፡፡ ከዚያም ያሳችሁን አስተያየት ለጓደኞቻችሁ ግለጹላቸው፡፡

## 3.3 የፆታ እኩልነት

### 3.3.1 የሴቶች የእኩልነት መብት





*ሥዕል 3.2 ወንድና ሴት በምርምር ሥራ ላይ*

- ከዚህ በላይ ካለው ሥዕል ምን ተገነዘ ባችሁ?

**"ከታላላቅ ሥራዎች ጀርባ ታላላቅ ሴቶች አሉ" በሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ አንድ የውይይት መድ ረክ ተካሂዶ ነበር:: የውይይቱ ጭብጥ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ሰፍሮ ይገኛል:: በተለይም ሦስት ተናጋሪዎች በውይይቱ ያቀረቧቸው ፍሬ ሃሳቦች የሚከተሉት ናቸው::**

*ተናጋሪ 1፣* "ይህች ዓለም ውብ እንድትሆን ሴቶች ምክንያት ናቸው:: ይፋ ወጥቶ አይነገ ርም እንጂ ከእያንዳንዱ ሥራና ውጤት በስተጀርባ እኛ ሴቶች አለንበት፣ ከወ ንዶች ጋር አብረን ተራምደናል:: እየተራ መድንም ነው::"በማለት ሴቶች ታላላቅ ሥራዎችን መሥራታቸውንና እየሠሩ መሆናቸውን አስገንዝበዋል::

*ተናጋሪ 2፣* "ሴቶች ብቃትና ችሎታ እንዳላቸው አያነጋግርም:: በሀገርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ውጤታማነታቸውን አሳ ይተዋል:: በተለይ በአሁኑ ወቅት የሴ ቶች ብቃት በከፍተኛ ደረጃ እየታየ የመ ጣበት ጊዜ ነው:: በየጊዜው የሚወጡ አዳዲስ ሕጎችና ፖሊሲዎችም በወንዶ ችና በሴቶች መካከል የሚታዩ ልዩነቶ ችን እያጠበቡ መጥተዋል:: ሴቶች ብቃ ትና ችሎታቸውን ለማውጣት በዋነኝ ነት ራዕይ ሊኖራቸው ይገባል:: ይህንን ለማዳበርም ሆነ ራሳቸውን ለመለወጥ፣ መማርና ሌሎች ብቁ የሚያደርጓቸውን መንገዶች መከተል ይገባቸዋል::" ሲሉ አስረድተዋል::

*ተናጋሪ 3፣* "ታላቅ ሴት ራዕይዋን የምታውቅ፣ ለአላማዋ መስዋዕትነት ለመክፈል ቁር ጠኝነት ያላት፣ በባህሪዋ ትሁት እና ታማኝ ናት::" በማለት አብራርተዋል::"

***ምንጭ: አዲስ ዘመን መጋቢት 13 ቀን 2000 ዓ.ም ገጽ 13 ለማስተማር እንዲስማማ ሆኖ የተወሰደ::***

**መልመጃ 6**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

**?**

1. "ይህች ዓለም ውብ እንድትሆን ሴቶች ምክንያት ናቸው::" የሚለ ውን አባባል እንዴት ተረዳችሁት? በማብራራት ግለጹ::
2. ያለሴቶች እኩል ተሳትፎ ስኬታማ ልማት ማምጣት የሚቻል ይመስላ ችኋል? ለምን?
3. በአካባቢያችሁ ታላላቅ ስራዎችን የሠ ሩና አርአያ የሆኑ ሴቶችን ታውቃላ ችሁ? ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው::

ሴቶች በማንኛውም ጉዳይ ከወንዶች እኩል ናቸው:: በኢትዮጵያ ሕገመንግሥት ወንዶችና ሴቶች በጋብቻ፣ በትዳርና በቤተሰብ ህይወት፣ በንብረት አጠቃቀም፣ በስራና በሌሎችም መብቶች እኩልነታቸው ተረጋግጧል::

**ሴት ከወንድ እኩል መሥራት፣ መፍጠርና መምራት ትችላለች::**

**መልመጃ 7**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::*

1. ሴቶች ከወንዶች እኩል የአእምሮ ብቃት አላቸው በሚለው ሃሳብ ላይ ያላችሁ አስተያየት ምንድን ነው?
2. የሴቶች እኩልነት እንዲከበር ከእያንዳንዳችሁ ምን ይጠበቃል?

### 3.3.2 የሴቶች የእኩልነት መብት መገለጫዎች

- *የሴቶች የእኩልነት መብቶች በምን በምን ይገለፃሉ?*

በአንድ ወረዳ ውስጥ ነዋሪ የሆነው ወጣት ብርሃኑ ተገኝ የአካባቢው ነዋሪ የሆነችውን ቆንጆ ልጅ ለማግባት በመፈለግ የልጅቷን ቤተሰቦች በሽማግሌዎች ያስጠይቃል:: የልጅቷ ቤተሰቦችም ጥያቄውን ተቀብለው ለመስማማት ፍላጎት ያሳዩ ቢሆንም ልጅቷ ፈቃደኛ አልነበረችም::

ልጅቷ በዚህ እድሜዋ በዚህ ዕድሜዋ ቤተሰቦችዋ ልጅህን ለልጃችን ተባብለው በተሰማ መብት ቃል ያለ ዕድሜዋ ጋብቻ ከመፈፀም ይልቅ ለትምህርቷ ቅድሚያ መስጠት እንደምትፈልግ አስረዳች::

ቤተሰቦችዋ ግን የልጅቱን ሀሳብ ከመቀበል ይልቅ ቀድሞ የገቡትን ቃል መጠበቅ ህፃኗ ለያለዕድሜ ጋብቻ እንድትጋለጥ ማስገደዳቸው አልቀረም::

በአንድ በኩል ወጣት ብርሃኑ ሕፃኗን አስገድዶ ለመውሰድ ሲዶልት በሌላ በኩል ወላጆችዋ የያለዕድሜ ጋብቻ መፈፀም ተሯሩጠዋል:: ነገር ግን የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ለህፃኗ የሕግ ከለላ በመጠየቁ የፍትህ ጽ/ቤት በጉዳዩ ደርሶ ልጅቱን ወደ ትምህርት ገበታዋ አረጋግቶ በመመለስ ትምህርቷን በመከታተል ላይ ትገኛለች::

**መልመጃ 8**

*ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩባቸው::*

1. ከቀረበው ምንባብ ምን ተገነዘባችሁ?
2. በወጣት ብርሃኑ ላይ የተበየነው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተገቢ ነው ትላላችሁ? ለምን?
3. ያለ ዕድሜ ጋብቻ የገጠማት አንዲት ህፃን በንደኛችዋ አማካይነት ወደ ሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት መምህሯ በመምጣት ብታማክር ምን ምክር የሚለግሷት ይመስላችኋል?
4. የሴቶች የመማር መብት በአንጉልና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዳይደና ቀፍ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

ባለፉት ዘመናት በሀገራችን የሴቶችን መብቶች ከወንዶች መብቶች ያሳነሱ በርካታ ልማዳዊ ድርጊቶችና አሠራሮች ተንሰራፍተው ቆይተዋል:: አሁን በአንፃራዊ መልኩ ለውጥ እየታየ ቢሆንም ገና ሊሠሩ የሚገባቸው በርካታ ሥራዎች አሉ:: ዛሬም ቢሆን ሴትን የሚያንኳስሱ፣ መብቷን የሚፈታተኑና በተፅዕኖ ውስጥ እንድትሆን የሚያደርጉ ድርጊቶችና አሠራሮች ሙሉ በሙሉ አልተወገዱም:: በቀጣይ እነዚህን ኋላ ቀር አስተሳሰቦችና ድርጊቶች በመታገል የሴቶችን እኩልነት ማክበርና ማስከበር የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ሊሆን ይገባል::

**ሴት ልጅን ማስተማር ሕብረተሰብን ማስተማር ነው::**

በኢትዮጵያ ሕገመንግሥት በተደነገገው መሠረት ሴቶች በጋብቻ፣ ንብረት በማፍራት፣ እኩል የሥራ ክፍያ በማግኘትና በሌሎችም ጉዳዮች ከወንዶች እኩል መብት አላቸው:: ከዚህም በተጨማሪ በበታችነት ያለመታየት፣ ከጎጂ ባህል ተፅዕኖ የመላቀቅ፣ ከሚጨቁኑ ሕጎችና ልማዶች የመጠበቅ ሙሉ መብት አላቸው::


**መልመጃ 9**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

?

1. ሴቶች ከወንዶች እኩል የሆኑባቸውን ጉዳዮች በመዘርዘር አስረዱ::
2. በአካባቢያችሁ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጎጂ ድርጊቶችንና የሚነገሩ ጸያፍ አባባሎችን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ::
3. በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጎጂ ድርጊቶችንና አሠራሮችን ስመከላከል ከእናንተ ምን ምን ተግባራት ይጠበቃሉ? በመዘርዘር አስረዱ::

## 3.4 የአካል ጉዳተኞች መብቶች፤



*ሥዕል 3.3 ተገቢው እገዛ ከተደረገላቸው የአካል ጉዳተኞች ሲያከናውናቸው የማይችሏቸው ሥራዎች የሉም*

- ከዚህ በላይ ካለው ሥዕል ምን ተገነዘባችሁ?

### ትንሹ ወጌ፤

ወጌ የ12 ዓመት ታዳጊ ወጣት ሲሆን የሚኖረው ከእናቱ ጋር ነው:: አባቱን በሞት የተነጠቀው ገና በልጅነቱ ነበር:: ወጌን ጓደኞቹ "ትንሹ ወጌ" በሚለው ቅጽል ስሙ ይጠሩታል:: ይህ ስም ሰውነቱ ቀጫጫ በመሆኑ በወላጅ እናቱ የወጣለት ነው::

«ትንሹ ወጌ» የ1ኛ ክፍል ተማሪ በነበረበት ወቅት መንገደኛ ሰዎች ከትምህርት ቤት ሲመለስ አታለው በመስረቅ ራቅ ወዳለ ስፍራ ወሰዱት:: ሁለት አይኖቹንም በማጥፋት ለልመና ተግባር ይጠቀሙበት ጀመር:: በየሰፈሩና በየቤተ ክርስቲያኑ እየዞረ ለምኖ ያገኘውን ለአሳ ዳሪዎቹ ያስረክባል::

ኑሮውም በጣም የማይመችና አስጨናቂ ሆነበት:: በዚህ ሁኔታ እያለ አንድ ቀን አምልጦ በመጥፋት መንገድ እየጠየቀ በቅን ሰዎች እርዳታ ወደ እናቱ ቤት ደረሰ:: እናቱንም ሲያገኛት በሀዘን ምክንያት ተቆራምዳና በሽተኛ ሆና ነበር:: ኑሮዋም ያልተስተካከለና ከእጅ ወደ አፍ ሆኖ አገኘው:: «በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ» እንዲሉ መከራው ተደራረበበት::

ወጌ ግን በደረሰበት ችግር እና በእናቱ መጎሳቆል ተስፋ ሳይቆርጥ ትምህርቱን ለመማር ወሰነ:: በዚሁ መሠረት በአቅራቢያው ወደሚገኝ አንድ ትምህርት ቤት በመሄድ ትምህርቱን ለመማር እንዲፈቀድለት አመለከተ:: ትምህርት ቤቱ ግን ወጌን ተቀብሎ ማስተናገድ እንደማይችል አሳወቀው:: ወጌም ተስፋ ሳይቆርጥ ጥረቱን በመቀጠል በአካባቢው ወደሚገኘው የአካል ጉዳተኞች መብት ተከራካሪ ድርጅት በመሄድ ጉዳዩን አስረዳ::

ድርጅቱም የአካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ሰው መብት ያላቸው በመሆኑ ትምህርት ቤት ገብቶ መማር እንዲችል ድጋፍ እንደሚያደርግለት ገለጸለት:: በዚሁም መሠረት ድርጅቱ ከአካባቢው የትምህርት ቢሮ ጋር በመሆን የወጌ መብት እንዲከበርለትና ሁኔታዎች እንዲመቻቹለት አደረገ:: ወጌም ያጋጠሙት ፈተናዎች ሁሉ ሳይበግሩት መብቱ እንዲከበርለት ጥረት በማድረጉ ትምህርቱን በጥሩ ሁኔታ እየተከታተለ ይገኛል::

**መልመጃ 10**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. «ትንሹ ወገኔ» ያጋጠሙት ችግሮች በሕይወቱና በትምህርቱ ላይ የፈጠሩትን እንቅፋቶች በማብራራት አስረዱ፡፡
2. ወገኔ ትምህርቱን እንዲቀጥል ከጎኑ በመሆን ያበረታታው ድርጅት ሚናውን ምን ያህል የተወጣ ይመስላችኋል?
3. ትምህርት ቤቱ በመጀመሪያ ወገኔን ሳስመቀበል የወሰነው ውሳኔ እንዴት ሲቀየር ቻለ?
4. እናንተ በአካባቢያችሁ እንደ ወገኔ ያሉ የአካል ጉዳተኞችን ለመርዳት ምን ምን ተግባራትን ማከናወን ይጠበቅባችኋል?

አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ዜጋ መብቶቻቸው በተሟላ መልኩ ሊከበሩላቸውና በቂ እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ መንግሥትም የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን የሀገሪቱ አቅም በሚፈቅደው ደረጃ በማቋቋምና በመርዳት እንክብካቤ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡ መብቶታቸውም ከተከበሩላቸው ለሀገር የሚጠቅም ውጤታማ ሥራ መሥራት ይችላሉ፡፡

### 3.4.1 የአካል ጉዳተኞችን መብት አለማክበር የሚያስከትለው ጉዳት

- የአካል ጉዳተኞችን መብት በተገቢው ሁኔታ አለ ማክበር ምን ምን ጉዳቶችን ያስከትላል?

የአካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ሙሉ አካል እንዳለው ሰው ሙሉ ክብር ያላቸውና በየትኛውም የሕይወት ዘርፍ ውጤታማ ሥራ ሊያከናውኑ የሚችሉ ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ በሀገራችን ለውጦች እየታዩ ቢሆንም በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሰው መድሎ እና መገለል ገና አልተቀረፈም፡፡

ዝቅተኛ ግንዛቤ ያላቸው ሰዎች አካል ጉዳተኝነትን ከመጥፎ እድልና ከእርግማን ጋር ሲያያይዙት ይስተዋላሉ፡፡ በዚህም የተነሳ የአካል ጉዳተኞች ለኢኮኖሚያዊ ችግሮችና ለማሕበራዊ መድሎዎች የተጋለጡ ናቸው፡፡

አንዳንዶቹ በቤተሰቦቻቸው ሳይቀር በደል ይደርስባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ ከመከልከል አንስቶ ማንም ሰው እንዳያያቸው በቤት ውስጥ ይደብቋቸዋል፡፡ ይህም ከሌሎች ችግሮች ባሻገር ቁጥራቸው ትንሽ የማይባል የአካል ጉዳተኞች የትምህርት እድል እንዳያገኙ አድርጓል፡፡

የአካል ጉዳተኞችን ማግለልና ከማሕበራዊ ግንኙነቶች ማራቅ ቤተሰብንም ሆነ ሀገርን በከፍተኛ ሁኔታ ይጎዳል፡፡ ምክንያቱም በእምቅ ችሎታቸውና ተሰጦአቸው ከመጠቀም ይልቅ የማምረት ብቃታቸው ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደርጋል፡፡ ይህም የሀገርን እድገት ወደኋላ ይጎትታል፡፡ ድህነትም እንዲስፋፋ በማድረግ ሕዝብን ይጎዳል፡፡

የአካል ጉዳተኞችን መብቶች አለማክበር በአጠቃላይ በሀገርና በሕዝብ ላይ የተወሳሰቡ ችግሮችን ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም ቤተሰብም ሆነ ማሕበረሰብ ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡ ሁሉም ዜጋ የአካል ጉዳተኞችን የመንከባከብ ኃላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል፡፡

**መልመጃ 11**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. አካል ጉዳተኞችን ማግለል የሚያስከትሏቸው ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ምን ምን ሲሆኑ ይችላሉ?
2. ለአካል ጉዳተኞች ሊደረጉላቸው የሚገቡትን ድጋፎች በመዘርዘር አስረዱ፡፡
3. የአካል ጉዳተኞችን መብት ለማስከበር የእናንተ ኃላፊነትና ድርሻ ምን ሊሆን ይችላል?
4. የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ማክበር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ አብራሩ፡፡

### 3.5 የሃይማኖት እኩልነት መከበር ያለው ጠቀሜታ

- የሃይማኖት እኩልነት መብት መከበር ምን ጠቀሜታ ያስገኛል?


የሃይማኖት እኩልነት መብት መከበሩ በአንድ ሀገር ውስጥ የዴሞክራሲ ሥርዓትን ለማጠናከር፣ ሠላምን ለማስፈን፣ ልማትንና እድገትን ለማፋጠን ይጠቅማል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ማንኛውም ዜጋ የፈለገውን ሃይማኖት የመከተል

*መብቱና ነፃነቱ ከተከበረለት ለሀገሩ ያለው ፍቅርና ስሜት እያደገ ይመጣል። ለሀገሩ ያለው ፍቅር ሲያድግ ደግሞ ሀገሩን ለማልማትና ደህንነቷንም ለማረጋገጥ ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል። ሀገር የምትገነባው የዜጐች የእኩልነት መብቶች ሳይነጣጠሉ ሙሉ በሙሉ ሲታወቁና ሲከበሩ ብቻ ነው።*

*ማንኛውም ሰው ሃይማኖቱን በሠላማዊ መንገድ ማስተማርና ተከታይ ማፍራት ይችላል። ከዚህ ውጭ የትኛውንም ሃይማኖት በግድ ለማስለወጥ መሞከር ግን የሃይማኖት እኩልነት መብትን መፃረርና መጋፋት ይሆናል። ይህም የሀገሪቱን ሕገ መንግሥት መፃረር ነው። ይህ ደግሞ የሕዝብን ሠላም ያደፈርሳል። የእድገትና የልማት ተስፋን ያጨልማል። በሕዝቦችም መካከል መተማመን እንዳይኖር ያደርጋል።*

*የሃይማኖት እኩልነት መከበር ለአንድ ሕዝብ ወይም ሀገር ልማትና ብልጽግና ወሳኝ ነው። የሁሉም ሃይማኖቶች እኩልነት በሕግ ፊት ከተረጋገጠ ሠላማዊ ኑሮ ይሰፍናል፣ መተሳሰብና መደጋገፍ ይኖራል፣ ለጋራ ፍላጎትና ጥቅም በጋራ ለመሥራት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል። ይህ ሁኔታ ሲኖር ደግሞ ሕዝቦች በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ጠንካራ አንድነት እንዲፈጥሩ ማድረግ የጋራ እሴቶቻቸውን እንዲያሳድጉ ያስችላል።*

*የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት ማንኛውም ሰው የመሰለውን ሃይማኖት እንዲከተል ይፈቅዳል። ይህንን ነፃነት በኃይልም ሆነ በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ እንደማይቻልም ተደንግጓል። ይሁን እንጂ በአንቀጽ 27/5 እና በአንቀጽ 90/2 መሠረት የሃይማኖት መብቶች ሊገደቡ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች ተቀምጠዋል። በዚሁ መሠረት የሕዝብን ደህንነት፣ ሠላምን፣ ጤናን፣ ትምህርትን፣ የሕዝብ ሞራልንና የሌሎች ዜጎችን መብቶች የሚጎዳ ሁኔታ ሲፈጠር እምነትን የማራመድ ነፃነት ሊገድብ ይችላል።*



*ሥዕል 3.4 በኢፌዴሪ ሕገመንግሥት የሃይማኖቶች እኩልነት የተረጋገጠ ነው*

**መልመጃ 12**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

1. ማንኛውም ሰው የመሰለውን ሃይማኖት እንዲከተል መፈቀዱ ምን ምን ጥቅሞችን ይሰጣል?
2. በኢፌዴሪ ሕገመንግሥት መሠረት የሃይማኖት ነፃነቶች ሲገደቡ የሚችሉባቸው ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር አስረዱ፡፡
3. መደበኛ ትምህርት የሚሰጡ ተቋማት ከሃይማኖታዊ ትምህርት ተፅዕኖ ነፃ መሆን አለባቸው የሚለውን ሀሳብ እንዴት ትመለከቱታላችሁ?
4. የሃይማኖት እኩልነት መብት መከበር የሚያስገኘውን ጠቀሜታዎች ዘርዝሩ፡፡
5. የሃይማኖት እኩልነት ባልተከበረበት ሁኔታ ምን ምን ችግሮች ይከሰታሉ?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የሰው ልጆች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሳይሸራረፉ ሊከበሩ ይገባል፡፡ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ተመሳሳይ መብትና ጥቅም ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ የእኩልነት መብቶቻቸው ሲረጋገጡላቸው ከሀገራቸው ሃብት ሚዛናዊ ጥቅም ሲያገኙ ይችላሉ፡፡ በሀገራችን የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን የእኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶችን አረጋግጧል፡፡

በዚህም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደርና የራሳቸውን መንግሥት እስከ መመሥረት የሚደርስ ሙሉ መብታቸው ተከብሮላቸዋል፡፡ ባለፉት የፖለቲካ ስርአቶች እነዚህ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ተረስተውና ተንቀው ቆይተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን የታሪካቸው፣ የሃይማኖቶቻቸውና ሌሎች የባህላዊ መገለጫዎቻቸው እኩልነት በሕገመንግሥቱ ተረጋግጧል፡፡ ይህም ለሀገሪቱ ልማት፣ እድገትና ብልጽግና የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

በማንኛውም መብት ረገድ ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸው፡፡ ሴቶች በአእምሮአዊ ብቃታቸው ከወንዶች አያንሱም፡፡ ከወንዶች እኩል መሥራት፣ መማር እና ማምረት ይችላሉ፡፡ ስለዚህም ኋላቀርና የተዛቡ አመለካከቶችን በመታገል የሴቶችን መብቶች ማክበርና ማስከበር ትወልድን ብሎም ሀገርን ይጠቅማል፡፡

የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ማክበር ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡ አካል ጉዳተኞች አስፈላጊው ድጋፍ ከተደረገላቸው እንደማንኛውም ሰው ሀገርን ለማልማትና የሕዝቦችን እድገት ለማፋጠን ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ቤተሰብም ሆነ የትኛውም ማሕበረሰብ አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡ መንግሥትም የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ለአካል ጉዳተኞች እንክብካቤ በማድረግ ድጋፉን አጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**ሉዓላዊነት፣** የበላይ ሥልጣን ባለቤትነት፣ የመጨረሻ የፖለቲካ ውሳኔ ሰጭነት ስልጣን። በኢትዮጵያ የዚህ ስልጣን ባለቤቶች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ናቸው።

**ራዕይ፣** አንድ ሰው በሕይወቱ የሚኖረው ዓላማ፣ ሲደርስበት የሚያስበውና ሲያሳካው የሚገባው ግብ።

**ፀያፍ፣** አሳፋሪ፣ የማይገባ፣ የማይጠቅም።

**ብይን፣** የፍርድ ቤት ወሳኔ፣ ሕጋዊ ውሳኔ።

**ግብረአበር፣** በወንጀል ተግባር ላይ አብሮ የተሰማራ፣ ድርጊቱን አብሮ የፈፀመ ተባባሪ።

**አሳዳሪ፣** ኃላፊነት ወስዶ አንድን ሰው በቤቱ የሚያኖር ወይም የሚያስተዳድር።

**መቆራመድ፣** መቸገር፣ መጎሳቆል፣ መሰቃየት።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

## I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ፡፡

1. የእኩልነት መብቶች በተግባር ከተረጋገጡባቸው ሰነዶች አንዱ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ነው፡፡
2. በኢትዮጵያ ሕገመንግሥት ከሠፈሩት የእኩልነት መብቶች መካከል የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች መብቶች መሠረታዊ መብቶች ናቸው፡፡
3. ባለፉት የረጅም ዘመናት ታሪክ ውስጥ ሕዝቦች ባህሎቻቸውና ቋንቋዎቻቸው በመከበራቸው ሀገራችን የበለፀገች ሆና ቆይታለች፡፡
4. በኢትዮጵያ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የሴቶች ሚና ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር ደካማ ነው፡፡
5. የአካልና የአእምሮ ጉዳተኝነት በመጥፎ እድልና በእርግማን አማካኝነት የሚመጣ ነው፡፡

## II. በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ራስን በራስ የማስተዳደር መብት፣ | ሀ. የሕዝብና የመንግሥት የጋራ ኃላፊነት፡፡ |
| 2. ቀይ ሽብር፣ | ለ. ጎጂና ኋላቀር ድርጊቶች፡፡ |
| 3. ጠለፋና ያለዕድሜ ጋብቻ፣ | ሐ. የሕዝቦች ሉዓላዊ ስልጣን፡፡ |
| 4. አካል ጉዳተኞችን መንከባከብ፣ | መ. በዜጎች ላይ የደረሰ ዘግናኝ ጭፍጨፋ፡፡ |

## III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡

1. የእኩልነት መብት ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች፣
   ለ. በሕገመንግሥት ውስጥ የተቀመጡ የዴሞክራሲ መብቶች፣
   ሐ. በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ሃብቶችን ሚዛናዊ በሆነ መልኩ መጠቀም፣
   መ. መልሱ አልተሰጠም፡፡
2. የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች መብቶች ከሆኑት የማይካተተው የትኛው ነው?
   ሀ. ራስን በራስ የማስተዳደር ሉዓላዊ ሥልጣን ፣
   ለ. በሕዝብ ተወካዮችና በፌደሬሽን ምክር ቤቶች ተመጣጣኝ ውክልና ማግኘት፣
   ሐ. የሌላውን ባህልና ቋንቋ ማዋረድና ማንቋሸሽ፣
   መ. በመቻቻልና በመከባበር በአንድነት መኖር።

3. ወንዶችና ሴቶች እኩል ከሆኑባቸው የሕይወትና የኑሮ አቅጣጫዎች መካከል የሚጠቀሰው፣
   ሀ. በጋብቻና በቤተሰብ ሕይወት፣
   ለ. በንብረት አጠቃቀምና በሥራ፣
   ሐ. ንብረት በማውረስና በማስተላለፍ፣
   መ. ሁሉም ትክክል ናቸው።
4. ከሚከተሉት መካከል ስለ ሴቶች ብቃትና ችሎታ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. እስከ አሁን የተከናወኑ ታላላቅ ስራዎች በወንዶች ብቻ የተሰሩ ናቸው፣
   ለ. ሴቶች በውሳኔ ሰጭነትና በአመራር ከወንዶች እኩል ብቃት አላቸው፣
   ሐ. ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ የማግኘት መብት አላቸው፣
   መ. ሴቶች በትምህርት ብቃታቸው ከወንዶች አያንሱም።
5. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የአካል ጉዳተኞች፣
   ሀ. ተገቢውን ክብርና እንክብካቤ በበቂ ሁኔታ እያገኙ ናቸው፣
   ለ. ለብዙ ጊዜ ማሕበራዊ መገለልና መድሎ ሲደርስባቸው ኖረዋል፣
   ሐ. ቁጥራቸው ጥቂት ስለሆነ እርዳታ አያስፈልጋቸውም፣
   መ. የትምህርት እድል በከፍተኛ ሁኔታ አግኝተዋል።

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ።

1. ሀገራችን ኢትዮጵያ የሕዝቦች የአንድነት ____________________ ነች።
2. ኢትዮጵያውያን ሁሉ እኩል መሆናቸው የተረጋገጠበት ሰነድ ________________ ይባላል።

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልሱ።

1. የእኩልነት መብት ማክበር አስፈለጊነትን አስረዱ።
2. "ያለሴቶች ተሳትፎ ልማትን ማረጋገጥ አይቻልም።" ሲባል ምን ማለት እንደሆነ አብራሩ።
3. ለአካል ጉዳተኞች ሊደረጉላቸው የሚገቡ እንክብካቤዎችን በመዘርዘር አስረዱ።

# ምዕራፍ አራት

# ፍትሐዊነት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቂ/ ስታጠናቅቅ፤***

- በዜጎች መካከል ከአድሎ የፀዳና ፍትሐዊ አሠራር ሲኖር እንደሚገባ ታውቂያለሽ/ ታውቃለህ፡፡
- የፍትሕ አካላትን የፍርድ አሰጣጥ ሂደት ትገነዘቢያለሽ/ ትገነዘባለህ፡፡
- የአገልግሎት ተቋማት ፍትሐዊ ሥርጭት ምንነትን ትረዳለሽ/ ትረዳለህ፡፡

## 4.1 ከአድሎ የፀዳና ፍትሐዊ የሆነ አሠራር መኖር

- ከአድሎ የፀዳ ፍትሐዊ አሠራር ማለት ምን ማለት ነው? አድሎአዊ አሠራርን የሚገልፁ ድርጊቶች ናቸው የምትሏቸ ውን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ፡፡

### የወንጪት ቀበሌዎች፤

በአንድ ወቅት የወንጪት ቀበሌዎች በአካባቢው ሕዝቦች ተወዳጅ ነበሩ፡፡ ለዚህ መልካም ዝና ካበቋቸው ተግባሮች መካከል ዋናው ቀበሌዎቹ ለአካባቢው ሕብረተሰብ የንግድ፣ የእደ ጥበባት እና የትምህርት ማዕከል ሆነው ማገልገላቸው ነበር፡፡ ብዙዎች የአጎራባች አካባቢ አዛውንቶች ለቀበሌዎቹ ነዋሪዎች መልካም ትውስታ አላቸው፡፡ በዚህም ምክንያት “መኖር በወንጪት” እስከ መባል ተደርሶ ነበር፡፡

ነገር ግን ላለፉት አስርተ ዓመታት በተለያዩ ምክንያቶች ቀበሌዎቹ ቀድሞ የነበራቸውን የኢኮኖሚ እና የባህል ማዕከልነት ክብርና ዝናን አጥተዋል፡፡ ሥርቶ ለመኖርም አስፈሪ አካባቢዎች ናቸው እስከመባል ደርሰዋል፡፡

ከሁለት ዓመታት ወዲህ ግን የወንጪት ቀበሌዎች እንደገና ማንሰራራት ጀምረዋል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በነዋሪዎች ከፍተኛ ጥረት በተወሰኑ ቀበሌዎች የተጀመሩት የማሕበረሰብ የውይይትና የምክክር ጉባዔዎች በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡ ለቀበሌዎቻቸው መዳከምና ሠላም መደፍረስ ምክንያት በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሕዝቡ በግልፅ ተወያይቶ የችግሩ መንስዔ ምን እንደሆነ ለመለየት ቻሉ፡፡ ዋና መንስዔዎቹም በሕብረተሰቡ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ስር ሰደው የነበሩት አድሎአዊ አሠራሮችና የፍትሕ መጓደል መሆናቸው ተረጋገጠ፡፡ በውይይቶቹም መሰል ችግሮች ዳግመኛ እንዳይከሰቱ የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ተስማሙ፡፡

ሠላምን ለማስፈን ዋና ስልት ተደርጎ የተወሰደው ከቤተሰብ እስከ መንግሥት ተቋማት ፍትሐዊነትን የሚያጎለብቱ ሥራዎችን መሥራት መልካም አማራጭ መሆኑ ታመነበት፡፡ ለዚህም ተግባራዊነት ከአዛውንቶች፣ ከሴቶች፣ ከወጣቶች፣ ከመንግሥት ሠራተኞች፣ ከሃይማኖቶች እና ከጎሳ መሪዎች የተውጣጡ አባላት ያሉበት ኮሚቴ ተቋቋመ፡፡

ከኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት መካከል የእርቅና የይቅርታ መድረኮችን ማካሄድ እና በሕብረተሰቡ ውስጥ የሠላምና የፍትሕ ትምህርቶችን ማስፋፋት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ በተጨማሪም በሕዝብ እና በቤተሰብ አስተዳደር፣ በመሬት ክፍፍል፣ በሀብት አጠቃቀም፤ ወዘተ... አድሎአዊነትን ማስወገድ፣ ፍትሐዊ አሠራር የሚሰፍንበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት የኮሚቴው ተግባሮች ናቸው፡፡

እነዚህ ዕቅዶች ተግባራዊ መሆን እንደ ጀመሩ በወንጪት ቀበሌዎች ውስጥ የሠላም ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ መሻሻል አሳየ፡፡ በዚህም ምክንያት ቀደም ሲል ያጡትን የንግድ፣ የጥበብ እና የትምህርት ማእከልነት እንደገና

መልሰው ለመቆጣጠር ቻሉ፡፡ በተፈጠረው ሠላምና መረጋጋት ምክንያት የቀበሌዎች ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆኑ አጎራባች ሕዝቦችም ተጠቃሚ መሆን ጀመሩ፡፡ በዚህም ምክንያት የወንጪት ሕዝቦችና አጎራባቾቻቸው ከመድሎ የፀዳና ፍትሐዊ አሠራር መኖር ለእድገትና ለሠላም መስፈን ያለውን ጥቅም በሚገባ ተገነዘቡ፡፡

**መልመጃ 1**

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. የወንጪትን ቀበሌዎች ለውድቀት የዳረጋቸውን ችግሮች ዘርዝሩ፡፡
2. ከአድሎ የፀዳና ፍትሐዊ አሠራርን ለማስፈን በቀበሌ ነዋሪዎች የተከናወኑ ተግባራትን ዘርዝሩ፡፡ በዚህ ሂደት በጣም ጠቃሚ ነው የምትሉት ተግባር የትኛው ነው?
3. ከአድሎ የፀዳ ፍትሐዊ አሠራር መኖር በሀገር ደረጃ ያለውን ጥቅም ግለፁ፡፡

ከአድሎ የፀዳና ፍትሐዊ አሠራር መኖር በተለያዩ መንገዶች ሊገለፅ ይችላል፡፡ ዜጎችን በእኩልነት ማስተናገድ ወይም ማገልገል እና የሰዎችን መብቶች ማክበር የፍትሐዊ አሠራር ዋና መገለጫ ነው፡፡ የመንግሥት ባለስልጣናት እና የመንግሥት ሠራተኞች የተሰጣቸውን ኃላፊነት በቅንነትና፣ በሀቀኝነት ሲወጡ እንዲሁም ከመድሎ በፀዳ መልኩ ሕብረተሰቡን ሲያገለግሉ ፍትሐዊ አሠራር ይሰፍናል፡፡

በአጠቃላይ ከአድሎ የፀዳ አሠራር መኖር ማለት ሕብረተሰቡ አድሎ የማይፈፅም፣ አድኣዊ አሠራርን የሚጠላ እና በግልፅ የሚቃወም ሆነ ማለት ነው፡፡ የፍትሐዊ አሠራር መኖር በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፣

**የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን ያጠናክራል፣** ከአድሎ የፀዳ/ፍትሐዊ/ አሠራር መኖር የዜጎችን የእኩልነት መብት በማረጋገጥ የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡ ከአድሎ የፀዳ አሠራር እና ዴሞክራሲ በብዙ መንገድ የተቆራኙ ሀሳቦች ናቸው፡፡ አንድን ሀገር ዴሞክራሲያዊ ነው ከሚያሰኙት ጉዳዮች መካከል የመንግሥት አስተዳደር ፍትሐዊ አሠራርን ተግባራዊ ሲያደርግ ነው፡፡

**ዘላቂ ሠላምን ያሰፍናል፣** ከአድሎ የፀዳ ፍትሃዊ አሠራር መኖር ለሕዝቦች አለመግባባቶችና ለግጭቶች ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን በመከላከል የሕብረተሰቡ ግንኙነቶች ጤናማና ቀጣይነት ያላቸው እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ዜጎች ለሕግ ተገዥ እንዲሆኑ እና ሌሎችን የሚጎዱ ድርጊቶችን እንዳይፈፅሙ መከላከያ መሣሪያ በመሆን ያገለግላል፡፡ በዚህም በሀገር ላይ ዘላቂ ሠላም እንዲሰፍን የላቀ ሚና ይጫወታል፡፡

**ፈጣን ልማትን ያረጋግጣል፣** ከአድሎ የፀዳ ፍትሐዊ አሠራር ዜጎች አቅማቸው በሚፈቅደው እና በመረጡት የሥራ መስክ እንዲሰማሩ በማስቻል መብታቸውን ያረጋግጣል፡፡ በዚህም ለሀገር የጋራ ልማት እንቅ ስቃሴዎች ላይ በንቃት የመሳተፍ መብታቸውን ስለሚያስከብር ለሀገር እድገትና ልማት ከፍተኛ አስተዋፅኦ የማበርከት ስሜታቸው ከፍተኛ ይሆናል፡፡

**መልመጃ 2**

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡***

1. ከአድሎ የፀዳና ፍትሃዊ አሠራር ለፈጣን ልማት ያለው አስተዋፅኦ ምንድን ነው?
2. ከላይ ከተቀመጡት ነጥቦች በተጨማሪ የዴሞክራሲ ሥርዓትና ከአድሎ የፀዳ ፍትሃዊ አሠራር ያላቸውን ትስስር ዘርዝሩ፡፡
3. ከአድሎ የፀዳ አሠራር እና ሠላም ያላቸውን ተያያዢነት አብራሩ፡፡

## 4.2 አድሎአዊ አሰራሮች የሚያስከትሏቸው ችግሮች

- አድሏዊ አሠራሮች ያስከትሏቸዋል የምትሏቸውን ችግሮች ዘርዝሩ።

### አድሎአዊ አሠራር እና መዘዙ፤

ለረጅም ዘመናት በአንድ ሀገር የሚተዳደሩ አምስት ብሄረሰቦች ነበሩ፡፡ እነዚህ ብሄረሰቦች ምንም እንኳን በአንድ አስተዳደር ቢመሩም በመካከላቸው ፍቅርና ሠላም አልነበረም፡፡ በይበልጥም ከአምስቱ ብሔረሰቦች መካከል ሁለቱ ይህ ነው የማይባል ግፍ እና በደል ይፈፀምባቸው ነበር። እንደዚሁም በብዙ ነገሮች ተገልለውና ተጨቁነው ኖረዋል፡፡

በሀገር ላይ ለሚከሰቱ ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሠራሽ ችግሮች እንደ ዋና ምክንያት የሚጠቀሱት እነዚያው መከረኛ የሆኑት ሁለቱ ብሄረሰቦች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ የዝናብ እጥረት እና ድርቅ ቢያጋጥም፣ ወረርሽኝ በሽታ ቢነሳ ወዘተ… "እነዚህ እርጉም እና እርኩሶች በፈፀሙት ሀጢያት ነው ይህ ሁሉ ቁጣ የደረሰው" በሚል በእነሱ ማመካኘት የተለመደ ነበር፡፡

በዚህም የተነሳ ችግሮች ባጋጠሙ ቁጥር በሁለቱ ብሄረሰቦች ላይ የሚደርሰው መከራ እጅግ የከፋ ነበር፡፡ ቤታቸው ይቃጠላል፣ ንብረታቸው ይዘረፋል፡፡ ከሚኖሩበትም አካባቢ ይፈናቀላሉ፡፡ ከብሄረሰቦቹ ጋር ጋብቻ መፈፀምም ሆነ አብሮ መብላትና መጠጣት እንደ ሀጢያት ይቆጠር ነበር፡፡

በብሄረሰቦች ላይ የሚፈፀሙ የእነዚህ ዓይነት አስከፊ ድርጊቶች ቀስ በቀስ እየቀነሱ ቢሄዱም ከማንኛውም የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ የተገለሉ ነበሩ፡፡ በሚኖሩበት አካባቢም ምንም ዓይነት የማሕበራዊ አገልግሎት እና የመሰረተ ልማት አውታሮች አልተዘረጉም፡፡ በነዚህና በሌሎች መድሎአዊ ተግባራት የተነሳ ሁለቱ ብሄረሰቦች በተለያዩ ዘዴዎች ተቃውሟቸውን ይገልጹ ነበር፡፡ ለምሳሌ የአካባቢያቸውን የተፈጥሮ ሀብቶችን አይንከባከቡም፡፡ ለሚኖሩበት አካባቢም ሆነ ለሀገር የባለቤትነት እና የተቆርቋሪነት ስሜት አልነበራቸውም፡፡ ደኖችን በመመንጠርና በማቃጠል ይታወቃሉ፡፡ የዱር እንስሳትንም በማጥፋት የሚወዳደራቸው አልነበረም፡፡ በተለያዩ ጊዜያት ከውጪ የሚመጣ ወራሪ ኃይልን ሲተባበሩና ሲደግፉ ኖረዋል፡፡

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ደግሞ በብሄረሰቦች የሚደረጉት ተቃውሞዎች እጅግ እየከፉና እየተጠናከሩ መሄድ ጀምረዋል፡፡ በመንግሥት ላይ ከማመፅ አልፈው የተደራጀ የትጥቅ ትግል ማድረግ ጀመሩ፡፡ ሥልጣን ላይ ያለው አካል አመፁን ለመቆጣጠር ያደረጋቸው የኃይል እርምጃዎች የረባ ፋይዳ አልነበራቸውም፡፡ ከዕለት ወደ ዕለት ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ አስቸጋሪ ሆነ፡፡ የንግዱ እንቅስቃሴ አደጋ ላይ በመውደቁ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ታየ፡፡ ቀድሞውንም እንደነገሩ የነበረው ፀጥታና ሰላም በመጥፋቱ የሰዎች ስደትና መፈናቀልም ከእለት ወደ እለት እየጨመረ ሄደ፡፡

**መልመጃ 3**

*በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. ከምንባቡ ውስጥ አድሏዊ አሠራሮችን የሚገልፁ ድርጊቶችን ዘርዝሩ፡፡
2. ሁለቱ ብሄረሰቦች ከውጪ ወራሪዎች ጋር መተባበራቸው ትክክል ነው ትላላችሁ? ለምን? ይህን ድርጊት ለመፈፀም ምክንያታቸው ምን ሊሆን ይችላል?
3. ሁለቱ ብሄረሰቦች ለአካባቢያቸውም ሆነ ለሀገራቸው የባለቤትነትና የተቆርቋሪነት ስሜት የማይሰማቸው ለምንድን ነው?

አድሎአዊ አሰራሮች ከሚያስከትሏቸው ችግሮች መካከል የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

ሀ/ ዜጎች ለሥራ የሚኖራቸው የተነሳሽነት ስሜት መጥፋት እና የምንቸገረኝ ስሜት መስፋፋት፣ በማንኛውም አካባቢ እና ደረጃ የሚፈፀሙ አድሎአዊ ድርጊቶች የተለያዩ ችግሮችን ያስከትላሉ:: ለምሳሌ የዜጎችን ሀገራዊ ስሜት ያዳክማል፣ ለሕዝብ ንብረት የመቆርቆር እና ለሚኖሩበት ሀገር እና አካባቢ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ስሜት ስለሚጠፋ ለሚደርሱ ጥቃቶችና ጉዳቶች ግድ አይኖራቸውም:: አድሎአዊ አሠራር የዜጎችን የሥራ ተነሳሽነት ስሜት በመጉዳት የምንቸገረኝ እና የምንአገባኝ አስተሳሰብን ያስፋፋል::

ለ/ ለአመፅ መነሳሳት እና የሠላምና መረጋጋት መደፍረስ፣ አድሎአዊ አሠራሮች ከሚያስከትሏቸው አደጋዎች መካከል ሕዝብ በመንግሥት ላይ እንዲነሳ ምክንያት መሆናቸው ነው:: አመፅን በማስፋፋት ሕግና ሥርዓት እንዲሸረሸር በማድረግ ሠላምና መረጋጋት እንዳይኖር ያደርጋል:: ውሎ አድሮም ሀገርን እስከ መበተን የሚያደርስ አደጋ ሊያሰከትል ይችላል::

**መልመጃ 4**

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ::***

1. በአካባቢያችሁም ሆነ በሀገር ደረጃ አድሎአዊ አሠራሮችን ለመከላከል መደረግ አለባቸው የምትሏቸውን ተግባራት ዘርዝሩ::
2. ከላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች በተጨማሪ የአድሏዊ አሠራሮች መስፈን በሀገር ደረጃ ሊያስከትሏቸው የሚችሉ መሠረታዊ ችግሮችን ዘርዝሩ::

## 4.3 ማሕባራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት

### 4.3.1 የማሕበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፍትሐዊ ሥርጭት

- የማሕበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?
- የማሕበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፍትሐዊ ሥርጭት ማለት ምን ማለት ነው?

**የካኖ ግዛት፤**

ኮረብቲትና ወርካምቢት ካኖ በምትባል ትንሽ ሀገር ውስጥ የሚገኙ ጎረቤታማ ክልሎች ናቸው:: ሁለቱ ክልሎች በብዙ ነገሮች ይመሳሰላሉ:: በመልከዓ ምድራዊ አቀማመጥና በአየር ንብረታቸው ተመሳሳይነት አላቸው:: ከዚህም ባሻገር በሕዝብ ብዛት ተቀራራቢ ናቸው:: የክልሎቹ ተመሳሳይነት በርካታ በመሆኑ አንዱን ከሌላው ለመለየት ያስቸግራል:: ነገር ግን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የሁለቱ ክልሎች ልዩነት እየጎላ መምጣት ጀምሯል:: ለልዩነታቸው ምክንያት የሆነውም የማሕበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሥርጭት አለመመጣጠን ነው። ይህንኑ ልዩነት ቀጥሎ ካለው ሰንጠረዥ መረዳት ይቻላል::

| የክልሎች ስም | የሕዝብ ብዛት | የቀበሌ ጽ/ቤቶች | ትምህርት ቤቶች | የጤና ተቋማት | የግብርና ተቋማት |
|---|---|---|---|---|---|
| ኮረብቲት | 80,000 | 25 | 46 | 26 | 18 |
| ወርካምቢት | 75,000 | 12 | 14 | 10 | 2 |

**መልመጃ 5**

***ከላይ የቀረበውን ሠንጠረዥ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ለዚህ ዓይነት ማሕበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሥርጭት ልዩነት መንስኤ ናቸው የምትሏቸውን ነጥቦች ዘርዝሩ፡፡
2. ፍትሐዊ ያልሆነ የማሕበራዊ ተቋማት ሥርጭት እንዴት ሊስተካከል እንደሚችል ተወያዩበት፡፡
3. የማሕበራዊ ተቋማት ሥርጭት ያለመመጣጠን ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ዘርዝሩ፡፡

ማሕበራዊ ተቋማት ለአንድ ሕብረተሰብ ህልውና አስፈላጊ ከሚባሉት ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ፡፡ ስለዚህ ዜጎች ከተቋማቱ ተገቢ አገልግሎት እንዲያገኙ የተቋማቱን ሥርጭት ፍትሐዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

የማሕበራዊ ተቋማት ፍትሐዊ ሥርጭት ማለት ከቦታ ቦታ ልዩነት ሳይደረግ በሁሉም ቦታዎች በተመጣጠነ መልኩ የተቋማቱ መገኘት ማለት ነው። ስለዚህ ሥርጭታቸው በአንዱ አካባቢ የተሟሉ በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ ያልተሟሉ ወይም በአንዱ አካባቢ ጥቂት በሌላ አካባቢ በጣም ብዙ መሆን የለባቸውም፡፡

ባለፉት ዘመናት በሀገራችን ይገኙ የነበሩት የማሕበራዊ ተቋማት ሥርጭት ከአካባቢ አካባቢ በገጠርና በከተማ ከፍተኛ ልዩነት ይስተዋልባቸው ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን ይህን የተዛባ ሥርጭት ለማስተካከል ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

ይሁንና የተቋማቱን ሥርጭት ፍትሐዊ በማድረጉ ሂደት ዜጎች ተገቢውን ድጋፍ እና ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**መልመጃ 6**

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡***

1. በአንድ ሀገር ውስጥ የሚታየው የማህበራዊ ተቋማት ሥርጭት የተዛባ ከሆነ ሊከሰቱ ይችላሉ የምትሏቸውን ጉዳቶች ዘርዝሩ፡፡
2. የማሕበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሥርጭትን የማስተካከል ኃላፊነት የማን ነው?
3. የማሕበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ሥርጭት ፍትሐዊ ለማድረግ ያስፈልጋሉ የምትሏቸውን ጉዳዮች ጥቀሱ፡፡

## 4.4 በየደረጃው የሚገኙ የፍትሕ አካላት

### 4.4.1 በአካባቢ የሚገኙ የፍትሕ አካላት ፍትሐዊ አሠራር አስፈላጊነት

- *በአካባቢያችሁ የሚገኙ የፍትሕ አካላትን ስም ዘርዝሩ፡፡*
- *የፍትሕ አካላቱ አሠራር ፍትሐዊ መሆን ለምን ይጠቅማል?*

**የባህላዊ የፍትሕ አካላት ጠቀሜታ፤**

እያንዳንዱ ሕብረተሰብ የራሱ የሆኑ የተለያዩ የፍትሕ ማስፈኛ ተቋማት ሊኖሩት ይችላል፡፡ እነዚህ የፍትሕ ተቋማት ባህላዊ እና ዘመናዊ ተብለው ይከፈላሉ፡፡ ለምሳሌ በሀገራችን ብዙ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ብሄሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከጥንት ጀምሮ የየራሳቸው ባህላዊ የግጭት ማስወገጃ እና የፍትሕ ማስፈኛ ተቋማት አሏቸው፡፡

ምንም እንኳን የተቋማቱ መጠሪያ ከቦታ ቦታ ቢለያይም በሕብረተሰቡ ውስጥ ለሚከሰቱ የመብት ጥሰቶች እና በደሎች መፍትሄ በመስጠት፣ ሠላምና ፀጥታን ለማስፈን ከፍተኛ ሚናን ይጫወታሉ፡፡

“የሀገሩን ሰርዶ በሀገሩ በሬ” እንደሚባለው እነዚህ ባህላዊ ተቋማት የአካባቢውን ባህልና ወግ

መሠረት አድርገው ለህብረተሰቡ ፍትሕ በመስጠት ያገለግላሉ፡፡ በዚህም በአሁኑ ወቅት ባህላዊ የፍትሕ አካላት ያላቸው ተቀባይነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ይገኛል፡፡



*ሥዕል 4.1 ባህላዊ የፍትሕ ተቋም በሥራ ላይ*

ሆኖም በአንዳንድ ባህላዊ የፍትሕ ተቋማት ውስጥ የሚታዩ አሠራሮችን ከዘመናዊ የፍትሕ አሠራር ጋር ማጣጣም ተገቢ ነው፡፡ ለምሳሌ ከፆታ አንፃር ከጋብቻ ጋር በተያያዘ ሴቶች ላይ ለሚደርሱ በደሎች ተመጣጣኝ ፍርድ ያለመስጠት፣ አልፎ አልፎ ሥልጣንና ሀብት ወይም ተሰሚነት አለው ተብሎ ለሚታመን ወገን የማዳላት አዝማሚያ በአንዳንድ ባህላዊ የፍትሕ ተቋማት ሲንፀባረቁ ይስተዋላሉ፡፡ በተጨማሪም የተበደለን ሰው እንደ በደሉ መጠን ተገቢ ፍትሕ እንዲያገኝ ያለማድረግ የመሳሰሉት አሠራሮች ሊሻሻሉ የሚገባቸው ናቸው፡፡

**ትክክለኛና ከወገናዊነት የፀዳ ዳኝነት እንዲኖር ማድረግ፣** የፍትሕ አካላት ተቀዳሚ ተግባር በሕብረተሰቡ ውስጥ በሚፈጠሩ ፍትሕነክ ጉዳዮች ላይ ፍትሐዊ ውሳኔዎችን ማስተላለፍ ነው፡፡ ይህን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ ትክክለኛና ከወገናዊነት የፀዳ ዳኝነት መስጠት ሲቻል ብቻ ነው፡፡

በውሳኔ አሰጣጡ ሂደትም ዳኞች ውሳኔ ሲያስተላልፉ በንፁህ ህሊና እና ሕግና ደንብን ተከትለው መሆን ይኖርበታል፡፡

**ዘላቂ ሠላምን ማስፈንና ፈጣን ልማትን ማረጋገጥ፣** ፍትሐዊ አሰራር የእኩልነት መብቶች ማስከበሪያ መሳሪያ ነው፡፡ ፍትሐዊ አሠራር የመብት ጥሰቶችንና በደሎችን በማስወገድ ሠላምና ፀጥታን ያሰፍናል፡፡ የሠላምና የፀጥታ መስፈን የሀገር እድገት እንዲፋጠን የላቀ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ ፍትሐዊ አሠራሮች የሕይወትና የንብረት ዋስትናን በማስከበር ዜጎች በልማት ሥራዎች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ እድል ይሰጣል፡፡

በዚህም ምክንያት የሀገር እድገት እንዲፋጠን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ ፍትሐዊ አሠራር የሀገር ሀብትን ከብክነትና ከምዝበራ በመከላከልና ማሕበራዊ ተቋማት እና መሠረተ ልማቶች እንዲስፋፉ በማድረግ ረገድ የሚያበረክተው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡

**መልመጃ 7**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. በምትኖሩበት ሕብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ የፍትሕ አካላትን ዘርዝሩ፡፡
2. ባሕላዊ የፍትሕ አካላቱን ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን በመለየት ሪፖርት አቅርቡ፡፡

በአካባቢ የሚገኙ የፍትሕ ተቋማት ፍትሕን በማስፈኑ ሂደት ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፣

**መልመጃ 8**

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡***

?

1. የፍትሕ አካላት በየደረጃው መቋቋማቸው ምን ጥቅም አለው?
2. የፍትሕ ተቋማት ፍትሐዊ አሠራሮችን እንዳ ይከተሉ የሚያደርጓቸውን ምክንያቶች ዘርዝሩ፡፡

## 4.5 መብቶች ሲጣሱ እና ፍትሕ ሲጓደል መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች

### 4.5.1 መብቶችን የማስከበር እና ፍትሕን የማስፈን እርምጃዎች

- *መብቶች ሲጣሱ እና ፍትሕ ሲጓደል መብትን ለማስከበር ምን ዓይነት እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው ትላላችሁ?*

**መብቶችን ለማስከበር እና ፍትሕን ለማስፈን የዜጎች ሚና፤**

*መብቶች በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች፣ በተለያዩ ምክንያቶች ሊጣሱ ይችላሉ፡፡ ፍትሕን ለማስፈን የፍትሕ ተቋማት በየደረጃው መዋቀራቸው እና ሕግና ደንብ መኖሩ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ በእርግጥ ፍትሕን ለማስፈን የፍትሕ ተቋማት መኖር ወሳኝ ነው።*

*ነገር ግን ፍትህን በዘላቂነት ለማስፈን ከዜጎች የሚጠበቁ ብዙ ኃላፊነቶች አሉ፡፡ እያንዳንዱ ዜጋ የራሱ መብት እንዲከበርለት የሚፈልገውን ያህል የሌሎችን መብት ማክበሩ ተገቢ ነው፡፡ "በራስህ ላይ እንዲደረግ የማትፈልገውን በሌሎች ላይ አታድርግ" የሚለውን ወርቃማ አባባል ማስታወስ ተገቢ ይሆናል፡፡*

*ሆኖም በተለያዩ ምክንያቶች የመብት ጥሰትና የፍትሕ መጓደል ድርጊቶች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ዜጎች ጉዳዩን ለሚመለከተው የፍትሕ አካል የማቅረብ መብት እንዳላቸው ሊረዱት ይገባል፡፡*

*ይህን በሁለት መንገድ መግለፅ ይቻላል፡፡ አንደኛው በራስ ላይ የደረሰን የመብት ጥሰት ለሚመለከተው የፍትሕ አካል ማሳወቅ ነው፡፡ "በሽታውን ያልተናገረ መድሃኒት አይገኝለትም" እንደሚባለው ዜጎች በመንግሥት ተቋማት በባለሥልጣናትም ሆነ በግለሰቦች የደረሰባቸውን በደል ለሚመለከተው የፍትሕ አካላት ካላቀረቡ መፍትሄ አያገኙም፡፡*

*"ሁለተኛው በራስ ላይ የደረሰን ብቻ ሳይሆን በሌሎች ላይ የሚፈፀሙ የመብት ጥሰቶችን ወይም የፍትሕ ጉድለቶችን ለተገቢ የፍትሕ አካል የማቅረብ ልምድ ሊያጎለብቱ ይገባል፡፡" የሚል ነው፡፡*

**መልመጃ 9**

? *ከላይ የቀረበውን ጽሑፍ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄ ዎች መልሱ፡፡*

1. ፅሁፉን መሠረት በማድረግ ፍትሕን በማስከበሩ ሂደት የዜጎችን ኃላፊነቶች ዘርዝሩ፡፡
2. በእናንንተ ደረጃ ፍትሕን በማስከበሩ ሂደት መወጣት ያለባችሁን ድርሻ ግለፁ፡፡

*መብቶች ሲጣሱና ፍትሕ ሲጓደል የሚከተሉትን ሕጋዊ እርምጃዎች መከተል ጠቃሚ ነው፤*

*ሀ/ መብትን የማስከበር ነፃነትን መጠቀም፣ ማንኛውም ዜጋ የሚፈፀምበትን አድሎአዊ እና የመብት ጥሰቶች በመቃወምና ለሚመለከተው ክፍል በማሳወቅ የደረሰው በደል እንዲስተካከል ወይም ተገቢ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ ነፃነት አለው፡፡ ማንም ሰው የራሱን መብት ካላስከበረ ማንም ሊያስከብርለት አይችልም፡፡*

*ለ/ ክስ ማቅረብ፣ ዜጎች በራሳቸውና በሌሎች አካላት መብታቸው ካልተከበረላቸው የደረሰባቸውን የመብት ጥሰት፤ ለሚመለከተው የፍትሕ አካል ማቅረብ አለባቸው፡፡ በእርግጥ ጉዳዮቹ የሚቀርቡበት የፍትሕ አካላት ደረጃ እና ዓይነት እንደ ጉዳዮቹ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ሁሉንም ጉዳዮች ለከፍተኛ መንግሥታዊ የፍትሕ አካላት ከማቅረብ በፊት የአካባቢያዊ የፍትሕ ተቋማትን በመጠቀም መፍትሄ መፈለግ ጠቃሚ ነው፡፡*

ሐ/ **የይግባኝ መብትን መጠቀም፣** አብዛኛውን ጊዜ በፍርድ ቤት የፍትሕ አሰጣጥ ሂደት ውሳኔ ለመርካት ካልተቻለ ይግባኝ ማለት የተለመደ አሠራር ነው፡፡ አንድ የበታች ፍርድ ቤት ለምሳሌ የወረዳ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ያልረካ ባለ ጉዳይ ጉዳዩን ለሚቀጥለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት አለው፡፡ ይህም የይግባኝ መብት ይባላል፡፡

ስለሆነም ይግባኝ ማለት አንድ ባለ ጉዳይ በመጀመሪያ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ከበላዩ ላለው ፍርድ ቤት ጉዳዩ እንደገና እንዲታይለት የመጠየቅ መብትን የሚገልፅ ነው፡፡ ይግባኝ የሚጠይቀው ወገን ፍርድ የተፈረደበት ሰው ብቻ አይደለም፡፡

የተወሰነው ውሳኔ አንሷል፤ እንደደረሰብኝ በደል ተገቢ ማካካሻ አላገኘሁም በማለት የተፈረደለትም ቢሆን ቅሬታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉዳዩን በሚገባ ከመረመረ በኋላ ቀድሞ የተሰጠውን ውሳኔ ሊያፀድቀው፣ ሙሉ በሙሉ ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**መልመጃ 10**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

1. ሰዎች ለምን የይግባኝ ሥርዓትን ይጠቀማሉ?
2. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የፍትሕ ተቋማትን በመጎብኘት ወይም በመጠየቅ የይግባኝ ሥርዓት መብትን በማስከበርና ፍትሕን በማስፈን ያለውን ጠቀሜታ የቡድን ሪፖርት አቅርቡ፡፡

## 4.6 ግብር

### 4.6.1 የግብር ከፋዮች መብት፣ ግዴታዎች እና የሕብረተሰብ ኃላፊነት

- የግብርን ጠቀሜታ ወይም አስፈላጊነት ዘርዝሩ፡፡
- ግብር ከፋዮች ምን መብት አላቸው? ግዴታቸውስ ምንድን ነው?




*ሥዕል 4.2 ማንኛውም ዜጋ ከሚያገኘው ገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት*

**የማህበረሰብ ውይይት፤**

የአዲስ ከተማ ቀበሌ ነዋሪዎች ዛሬ ያደረጉት ውይይት ያተኮረው በግብር አሰባሰብ ዙሪያ ነው፡፡ ገለፃውንም ያደርጉት ከግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት የተወከሉት ወ/ሪት ተናኘ እና አቶ መገርሳ ናቸው፡፡ የቀበሌው ሊቀመንበር እንግዶቹን ካስተዋወቁ በኋላ ውይይቱ በባለ ሙያዎች ገለፃ ተጀመረ፡፡ የውይይቱ ሂደት አጠር ብሎ በሚከተለው ሁኔታ ቀርቧል፡፡

አቶ መገርሳ፣ “እንደምን አደራችሁ ወገኖቼ? እኛ ዛሬ እዚህ የተገኘነው ስለ ወቅታዊ የግብር ሁኔታ ውይይት ለማድረግ ነው፡፡ ባለፈው ውይይታችን ስለ ግብር ምንነትና ጠቀሜታ መወያየታችንን ታስታውሳላችሁ፡፡

እንደምታውቁት ግብር ለሀገራችን አዲስ ነገር አይደለም፡፡ ግብር ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ በሕግ በተወሰነው መሠረት ለመንግሥታቸው የሚከፍሉት ገንዘብ ነው፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ ሕብረተሰቡ ግብር ለልማት፣ ለእድገት፣ ለብልፅግና የሚከፈል መዋጮ መሆኑን እየተረዳው መጥቷል፡፡ ስለዚህ ግብር ለሀገር ልማትና እድገት ከገቢ ላይ የሚከፈል ገንዘብ መሆኑን በመረዳት እያንዳንዳችን የሚጠበቅብንን ግብር በወቅቱ የመክፈል የውዴታ ግዴታ አለብን፡፡" በማለት የመግቢያ ንግግር ካደረጉ በኋላ፣ የእለቱ ውይይት የሚያተኩረው ግብርን በመክፈሉ ሂደት የግብር ከፋዮች ግዴታዎች ላይ መሆኑን አብራሩ፡፡

**የተሳታፊ ጥያቄ፣** "አሁን የተገለፀልንን ማብራሪያ በግልፅ ተረድቻለሁ፡፡ ነገር ግን በግብር አከፋፈል ሂደት የዜጎች ኃላፊነትና መብት ምን እንደሆነ ቢብራራልን!"

በነዚህና በሌሎች የግብር ከፋዮች ግዴታና መብቶች በቀረቡ ጥያቄዎች ዙሪያ ሰፊ ውይይት ተካሄደ፡፡ ከተሰጡት ገለፃዎች መካከል ወ/ሪት ተናኘ ዜጎች ያላቸውን መብቶችና የሚጠቅባቸውን ግዴታዎች በተመለከተ የሰጡት ማብራሪያ በሚከተለው ሁኔታ ቀርቧል፡፡

***ሀ/ የግብር ከፋዮች ግዴታዎች፣***

- ግብር መክፈል ግዴታ መሆኑን በማወቅ በወቅቱና በፍላጎት መክፈል፣
- ለግብር አሰባሰብ የሚበጁ መረጃዎችን በሀቀኝነት መስጠት፤
- ግብር ያልተከፈለበትን ዕቃ ወይም ንብረት አለመሸጥ ወይም አለመግዛት። የግብርን አከፋፈል ሥርዓት ከማደናቀፍ መቆጠብ የሚሉት በዋናነት የተጠቀሱ ነበሩ፣

***ለ/ የግብር ከፋዮች መብቶች፣***

- የተጣለባቸውን ግብር መጠን የመጠየቅ፣ የማጣራት፣ ቅሬታ ካለ ቅሬታን የማቅረብ፣
- አገልግሎት መስጫ ተቋማትን እኩል የመጠቀም፣
- ከግብር የሚሰበሰብ ገንዘብ ለምን ተግባር እንደሚውል የመጠየቅ እና የማወቅ የሚሉት የሚጠቀሱ ናቸው፣

***ሐ/ ከሕብረተሰቡ የሚጠበቁ ግዴታዎች፣***

- ግብርን በአግባቡ መክፈል፣
- በሕገወጥ መንገድ የሚገቡ እና ግብር ያልተከፈለባቸውን ንብረቶች አለመሸጥ፣ አለመግዛት፣ ህገወጥ ንግድ የሚያካሂዱ አካላትን መቃወም፣
- ግብር የሚያጭበረብሩ እና የማይከፍሉትን ማጋለጥ፣ መቃወም፣ ለግብር አሰባሰብ የሚረዱ በቂ መረጃዎችን መስጠት የሚሉት በወ/ሪት ተናኘ የተጠቀሱት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በዚህም መሠረት የቀበሌው ነዋሪዎች ግብር የሕብረተሰብ እና የሀገር እድገት መሠረት ስለ መሆኑ የነበራቸው ግንዛቤ ይበልጥ ዳበረ፡፡ ስለግብር ምንነትና አስፈላጊነት የበለጠ በመረዳታቸው ግዴታቸውን በአግባቡ ይወጡ ጀመር፡፡ በዚህ በጎ ተግባራቸውም ተሸላሚ በመሆን ለሌሎች በምሳሌነት የሚጠቀሱ ሆኑ፡፡

**የቡድን ሥራ፣**

1. "መንግሥት ከሕዝቡ እንደ ገቢው መጠን የሰበሰበውን ግብር መልሶ ለሕዝቡ አገልግሎት በማዋል በአጠቃላይ ዜጎቹ እንዲጠቀሙ ያደርጋል" በሚለው አባባል ትስማማላችሁ? በቡድን ተወያዩና ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡
2. ከታች ያለውን ሀሳብ በመገንዘብና ሌሎችንም በመጠየቅ የቀረቡትን ጥያቄዎች ሥሩ፡፡

ወ/ሮ ራውዳ በዓመት አርባ ሺ ብር ግብር ይከፍላሉ፡፡ አቶ ሽኩር በዓመቱ የከፈሉት የግብር መጠን ሶስት ሺ ብር ሲሆን አቶ ደቻሳ የከፈሉት አንድ ሺ ብር ነው፡፡ አቶ ደረጀ ግን ምንም ዓይነት ግብር አልከፈሉም፡፡ ይባስ ብሎ በመንግሥት ይደጎማሉ፡፡ ይህ የግብር አሰባሰብ ሁኔታ ትክክል ነው በማለት ባለሙያዎቹ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

ሀ/ በግብር አሰባሰቡ ላይ የተሰጠው የባለሙያ አስተያየት ትክክል ነው? ለምን?

ለ/ ዜጎች ከመንግሥት የሚያገኙት አገልግሎት እንደሚከፍሉት የግብር መጠን መለያየት አለበት? ለምን?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች የሚፈፀሙ አድሏዊ አሠራሮች በሀገር ሠላም እና እድገት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡ ስለዚህ በሕብረተሰቡ ውስጥ ከአድሎ የፀዱና ፍትሐዊ ሥርዓትን ማስፈን የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ ከአድሎ የፀዳና ፍትሐዊ የሆነ አሠራር ለዴሞክራሲ ሥርዓት መጎልበት፣ ለዘላቂ ሠላም እና ለፈጣን ልማት መረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡

ከአድሎ የፀዳ ሥርዓት የማሕበራዊ ተቋማት ሥርጭት ፍትሐዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በሕብረተሰቡ ውስጥ ዘላቂ ሠላምንና ከወገናዊነት የፀዳ የዳኝነት ሥርዓትን ለማስፈን በየደረጃው የሚገኙ የፍትሕ አካላትን ፍትሐዊነት ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም በላይ ከአድሎ የፀዳና ፍትሐዊ የሆነ አሠራር እንዲጎለብት ዜጎች ሕጋዊ የፍትሕ ማስከበሪያ ሥርዓቶችን መከተል አለባቸው፡፡

ከአድሎ የፀዳና ፍትሐዊ ሥርዓት በሰፈነበት ሕብረተሰብ ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች ግብር ለምንና ለማን እንደሚከፈል በሚገባ ያውቃሉ፡፡ በዚህም መሠረት የሚጠበቅባቸውን የግብር ግዴታ በወቅቱ ይወጣሉ፡፡ በዚህ ተግባራቸውም ለሀገር ልማትና እድገት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

| | |
|---|---|
| ግብር /ቀረጥ፣ | ከተለያዩ የንግድ እንቅስቃሴዎች የሚሰበሰብ ገንዘብ። |
| ድጎማ፣ | የበጀት ጉድለትን ለማስተካከል የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ። |
| ጉባኤ፣ | ብዙ ሕዝብ ተሳታፊ የሚሆንበት የውይይት መድረክ። |
| ፈጣን ልማት፣ | የሕብረተሰቡን ሕይወት የሚለውጥና የሀገርን እድገት የሚያፋጥን ልዩ ልዩ ተግባር። |
| ለሕግ ተገዢ መሆን፣ | በሥራ ላይ ያሉ ህጎችን፣ ደንቦችንና ሕብረተሰቡ የተቀበላቸውን አሠራሮች ተግባራዊ ማድረግ። |

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ፡፡*

### I. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ፡፡

1. የማሕበራዊ ተቋማትን ሥርጭት ፍትሐዊ ማድረግ አይቻልም፡፡
2. በሀገራችን ባለፉት ሥርዓቶች የነበረው የተቋማት ሥርጭት ፍትሐዊነት የጎደለው ነበር፡፡
3. በአድሎአዊ አሠራር ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮች ያን ያህል ጎጂ አይደሉም፡፡
4. የፍትሕ አካላት በየደረጃው መዋቀራቸው በርካታ ጥቅሞች አሉት፡፡
5. ግብር መክፈል የዜጎች መብትም ግዴታም ነው፡፡

### II. በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉትጋር አዛምዱ፡፡

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| 1. የተነሳሽነት ስሜት ማጣት፣ | ሀ. ግብር በወቅቱ መክፈል። |
| 2. የግብር ከፋዮች ግዴታ፣ | ለ. ግብር። |
| 3. በፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ቅሬታ ማቅረብ፣ | ሐ. ይግባኝ። |
| 4. የእድገት መሰረት፣ | መ. የፍትህ መጓደል። |
| 5. ከፍተኛ የፍትህ አካል፣ | ሠ. ቀበሌ። |
| | ረ. ጠቅላይ ፍርድ ቤት። |

### III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡

1. የተቋማት ፍትሐዊነት የሚገለፀው ከሚከተሉት ድርጊቶች በአንዱ ነው፤
   - ሀ. ከቦታ ቦታ ያላቸውን ሥርጭት በማስተካከል፣
   - ለ. እኩል አገልግሎት የማግኘት መብታቸውን በማስጠበቅ፣
   - ሐ. ለኃላፊዎችና ለባለሀብቶች ቅድሚያ በመስጠት፣
   - መ. ‹ሀ› እና ‹ለ› መልሶች ናቸው።
2. ከሚከተሉት ውስጥ ዜጎች ፍትሕን ለማስከበር ሲሉ መጠቀም የሌለባቸው ድርጊት የቱ ነው?
   - ሀ. ክስ ማቅረብ፣
   - ለ. ይግባኝ ማቅረብ፣
   - ሐ. በጉልበት መጠቀም፣
   - መ. ሁሉም መልስ ናቸው።
3. ከሚከተሉት አካላት መካከል አንዱ የፍትሕ ውሳኔ ማስተላለፍ ተቀዳሚ ድርሻው አይደለም?
   - ሀ. ቀበሌ፣
   - ለ. ፍርድ ቤት፣
   - ሐ. ፖሊስ ጣቢያ፣
   - መ. የትምህርት ተቋም።

4. የፍትሕ ተቋማት በየደረጃው መቋቋማቸው ምን ጥቅም አለው?
   ሀ. ገንዘብንና ጉልበትን ይቆጥባል፣ ሐ. ችሎትን በቅርበት ያስችላል፣
   ለ. ጊዜን ይቆጥባል፣ መ. ሁሉም መልስ ነው።
5. የአድሏዊ አሠራሮች ውጤት ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. የተነሳሽነት ስሜት መጉደል፣ ሐ. ሠላምና መረጋጋት መስፈን፣
   ለ. ተስፋ መቁረጥ፣ መ. የእርስ በእርስ ግንኙነት መላላት።

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ፡፡

1. የዜጐች ሕጋዊ የመብት ማስከበሪያ መንገዶች ________እና________ ናቸው፡፡
2. በሀገር ላይ የሚገኙ የማሕበራዊ ተቋማት ሥርጭት __________ ሊሆን ይገባል፡፡
3. በሕብረተሰቡ ውስጥ ለሚፈጠሩ የፍትሕ ችግሮች መፍትሔ የሚሰጡ የፍትሕ አካላት ________እና ________ በሚሉ ተከፍለው ይገለፃሉ፡፡

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. ከአድሎ የፀዳ ፍትሐዊ አሠራር እንዲሰፍን የዜጐች ኃላፊነቶች ናቸው የምትሏቸውን ሀሳቦች ዘርዝሩ፡፡
2. በሚከተሉት ተቋማት ውስጥ አድሏዊ አሠራሮች የሚያስከትሏቸውን ችግሮች ዘርዝሩ፡፡
   ሀ) በት/ቤት፣
   ለ) በቤተሰብ፣

# ምዕራፍ አምስት

# የሀገር ፍቅር

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- የሕዝብንና የሀገርን ትክክለኛ ታሪኮችና ባህሎች ጠንቅቆ በመገንዘብ አዲሱን የሀገር ፍቅር ስሜት ታዳብራለህ/ ታዳብሪያለሽ።
- የጋራ ደኅንነትን ሊያናጉ የሚችሉ አፍራሽና ጐጂ ልማዶችን ትዋጋለህ/ትዋጊያለሽ።

## 5.1 የሀገር ፍቅር

### 5.1.1 የአዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት መገለጫዎች

- የሀገር ፍቅር ስሜት መገለጫ ሊሆኑ ከሚችሉት መካከል ጥቂቱን ዘርዝሩ፡፡

**የሀገር ታሪክ፤**

የ "ሕያው ተስፋ" ትምህርት ቤት የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ስለ ሀገራቸው ታሪክ ገለፃ እንዲሠጧቸው አንድ የታሪክ ምሁር ጋብዘዋል፡፡ ምሁሩ ገለፃ እንዲሰጡበት የተሰጣቸው ርዕስ "አዲሱን የሀገር ፍቅር ስሜት ማዳበር" የሚል ነው፡፡ ምሁሩ ገለጻቸውን እንዳጠናቀቁ ተማሪ ዎች የተለያዩ ጥያቄ ዎችን አቀረቡላቸው።

**ጥያቄ፣** እንድጠይቅ ስለተፈቀደልኝ አመሠግናለሁ። ለመሆኑ የሀገር ፍቅር ስሜትን አዲስና አሮጌ ብለን እንዴት ልንከፍለው እንችላለን?

**መልስ፣** ጥያቄው መሠረታዊ ነው። ከአሁን በፊት በነበሩት ሥርዓቶች እንዲዳብር ይፈለግ የነበረው የሀገር ፍቅር ስሜት በዋነኛነት የሕዝቦችን ታሪክ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ አመለካከትና ሥነ-ልቦናን ማዕከል ያደረገ አልነበረም። ይልቁንም በበርካታ አጋጣሚዎች ስለ ሀገር ፍቅር ስሜት ሲገለፅ የኖረው የሀገሪቱ ተፈጥሯዊ የመልክዓ ምድር አቀማመጥ ማለትም፤ ወንዙን፣ ተራራውን፣ እፅዋዕቱን፣ ወዘተ ማዕከል በማድረግ ነበር፡፡ አዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት መዳበር አለበት የሚባለው ይህንን አንድ አቅጣጫ ብቻ የሚያንፀባርቅ አመለካከትን በማረም ብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ያማከለ የሀገር ፍቅር ስሜት ነው፡፡

**ጥያቄ፣** እያንዳንዱ ዜጋ አዲሱን የሀገር ፍቅር ስሜት በተግባር ማሳየት የሚኖርበትስ እንዴት ነው?

**መልስ፣** አዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት መዳበር የሚገባው ቤተሰብን ከመውደድና ከማክበር ጀምሮ ነው፡፡ ከዚያም ከፍ ሲል የአካባቢንና የሀገርን ታሪክ በሚገባ ማወቅና ማክበር ከዜጎች ሁሉ ይጠበቃል፡፡ የሀገር ታሪክ የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች ታሪክ ነው፡፡ የሀገር ፍቅር የሚገለጸው እያንዳንዱ ዜጋ የአቅሙን ያህል ለሕዝብ ጠቃሚ የሆኑ አርአያነት ያላቸውን ተግባሮች በማከናወን ጭምር ነው፡፡ የራሱን ባህልና ታሪክ የሚያከብር ዜጋ የሌሎች ወገኖቹን ቋንቋ፣ ባህልና ታሪክ ያከብራል፡፡

**ጥያቄ፣** ካሁን ቀደም የተዛባውን የሕዝቦችን ታሪክ እንዴት ማስተካከል እንችላለን?

**መልስ፣** ቀደም ባሉት ሥርዓት መንግሥታት የነበሩ መሪዎች ቅድሚያ ይሠጡ የነበረው ለራሳቸው ክብር፣ ዝናና ሥልጣን እንጂ የሕዝብን ታሪክ ማዕከል በማድረግ አልነበረም። በነገሥታቱ የአገዛዝ ሥርዓት ወቅት ወታደራዊ የሥልጣን ምንጩ ሕዝብ ሳይሆን በዘር ሐረግ የሚገኝ ተደርጎ ይታመን ነበር፡፡ በኋላም የመጣው ወታደራዊ አገዛዝ የሕዝቦችን ታሪክ ወደ ጐን

በመተው ትኩረት ሲሰጥ የነበረው ለመሬቱ፣ ለወንዙ፣ ለሸንተረሩ ወዘተ... ብቻ ነበር። በመሆኑም በእነዚህ ሥርዓቶች ውስጥ የተጻፉት አብዛኞቹ ታሪኮች የሕዝቦችን ታሪክ ማዕከል አድርገው የተጻፉ አልነበሩም። ይህ ችግር የሚስተዋለው በጽሑፍ በቀረቡት ታሪኮች ላይ ብቻ ሳይሆን በልማድ ይነገሩ በነበሩ አፈ-ታሪኮች ጭምር ነበር። በተያያዝነው አዲሱ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ ግን ትክክለኛው የሕዝቦች ታሪክ ሲጻፍ ስህተቶቹ እየታረሙና እየተስተካከሉ ይሄዳሉ፡፡ ይህ ሲሆን አዲሱና ሕዝብን ማዕከል ያደረገ ታሪክ መጻፍ ብቻ ሳይሆን አዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት በብሔሮች፣ በብሔረሰቦችና በሕዝቦች ውስጥ ዳብሮ ይሰርፃል፡፡

**መልመጃ 1**

***ከላይ የቀረበውን ገለፃ መነሻ በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. የታሪክ ምሁሩ በገለፃቸው ውስጥ የጠቀሱት አዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት በዋነኛነት የሚገለፀው በምን በምን ተግባራት ነው?
2. አድልዎ የሌለበት የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች ታሪክ በትክክል የሚጻፈው እንዴት ነው?

ለአዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት መገለጫ ከሆኑት መካከል ለሕግና ደንብ ተገዥ መሆን፣ የሌሎችን ሰዎች መብቶች ማክበር፣ ኃላፊነትን በብቃት መወጣት፣ አርአያነት ያላቸው ተግባራት መፈፀምና የሀገርን ሉዓላዊነት ክብር ማስጠበቅ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሳቸው ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ታሪክ፣ ሥነ-ልቦናዊ አመለካከትና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች አላቸው። በሕዝቦች ታሪክ ውስጥ ጐልቶ መታየት የሚገባው የመሪዎች ታሪክ፣ ወይንም ሥልጣን የጨበጠው ፓርቲ ታሪክ ሳይሆን የራሱ የሕዝቡ ታሪክ መሆን ይገባዋል። አንዳንድ ታሪኮች ተዛብተው ሲጻፉና ሲነገሩ በቸልታ መታለፍ አይገባቸውም፡፡ የተዛቡ ታሪኮች ሲነገሩ ስህተቱን ፊት ለፊት በመንገርም ሆነ በመረጃ አስደግፎ በጽሑፍ በማስፈር ማረም ሀገሬን እወዳለሁ ከሚል ዜጋ ይጠበቃል፡፡ ይህም የአዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት መገለጫ አንዱ መንገድ ነው፡፡

**መልመጃ 2**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

?

1. ስለ ሀገር ፍቅር ሲወሳ በዋነኛነት መታሰብ ያለባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?
2. የተዛቡ ታሪኮች ተጽፈው ወይንም በቃል ሲነገሩ ስንሰማ ሀገሩን እንደሚወድ ዜጋ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?

## 5.2 አፍራሽና ጐጂ ተግባራት

### 5.2.1 በአካባቢያችን የሚታዩ አፍራሽና ጐጂ ተግባራት



*ሥዕል 5.1 አፍራሽና ጐጂ ተግባራትን መቃወም ሀገሩን ከሚወድ ዜጋ ሁሉ ይጠበቃል*

- ሥዕሎቹ ምን መልዕክት ያስተላልፋሉ?
- በሥዕሎቹ ላይ የተገለፁትን ዓይነት ተግባሮች የሚፈፅሙ ወጣቶች እናንተ አካባቢ አሉ? ካሉስ በምን በምን ጐጂ ተግባራት ላይ የተሠማሩ ናቸው?

## አውጫጭኝ፤

በአንድ ሰፈር ውስጥ ሕዝቡን ያስቸገሩ ሦስት ሌቦች ነበሩ። እነዚህ ሌቦች ቤት በመዝረፍ፣ የአካባቢውን ሕብረተሰብ ንብረት በማበላሸት፣ የሕዝብ ማመላለሻ መኪኖችን በማስቆምና የመንገደኞችን ንብረት በመዝረፍ፣ ሴቶችን አስገድዶ በመድፈርና ሌሎችንም ብዙ ጥፋቶች አድርሰዋል። ለምሳሌ፤ የውሃ ቧንቧ ከመሬት ውስጥ ቆፍረው በማውጣት ይሠርቃሉ፣ የመብራትና የስልክ ገመዶችን እየቆራረጡ በመውሰድ በሀገር ሃብት ላይ ከፍተኛ ወንጀል ይፈፅማሉ።

የእነዚህ ሌቦች የጥፋት ሥራ ያስመረረው የአካባቢው ነዋሪ ተደጋጋሚ ምሥጢራዊ ስብሰባ በማድረግ ሌቦቹን ለማጋለጥ ይወስናል። ይሄው ምሥጢር እንዲጠበቅም ሕዝቡ ቃል ገብቷል፡፡ ምሥጢሩን ያወጣ ሰው እንዲቀጣ ሕብረተሰቡ በአንድ ድምፅ ተስማምቷል፡፡

ስብሰባው በሚደረግበት ቀን እንደማንኛውም የአካባቢው ነዋሪ ሌቦቹ በስብሰባው ላይ እንዲገኙ ይጠሩ ወይንስ አይጠሩ በሚለው ሃሣብ ላይ ነዋሪው ተወያይቶ የተለያዩ ሃሣቦች ቀርበዋል። ከነዋሪዎቹ አንዳንዶች "ሌቦቹ ራሳቸው በተገኙበት ስብሰባ ላይ ብናጋልጣቸው በኋላ ሊያጠቁን ስለሚችሉ እነርሱ በሌሉበት ብንጠቁማቸው ይሻላል" የሚል ሃሣብ ሰነዘሩ። አንዳንድ ነዋሪዎች ግን ቁርጠኛ አቋም በመውሰድ "ሌቦቹ በስብሰባው ላይ ተገኝተው ጥፋታቸው በዝርዝር ይገለፅላቸው። ጥፋታቸውን ካመኑና የበደሉትን ሕብረተሰብ በይፋ ይቅርታ በመጠየቅ ወደ ሠላማዊ ሕይወት የሚመለሱ ከሆነና የሰረቋቸውን ንብረቶች በሙሉ ለመመለስ ከተስማሙ ምህረት ሊደረግላቸው ይገባል።

በሌብነት ተግባራቸው እንቀጥላለን ብለው ከወሰኑ ግን ለሕግ አሳልፈን እንሰጣቸዋለን" በማለት ሀሳብ አቀረቡ። የተወሰኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ግን "የሕዝብን ንብረት ሲያወድሙና ሲዘርፉ ከኖሩ ሌቦች ጋር መደራደር ስለማይገባ ሌቦቹ በስብሰባችን ላይ እንዲገኙ ካደረግን በኋላ የፊጥኝ አስረን ለሕግ ማቅረብ አለብን" የሚል አቋም ወሰዱ።

### መልመጃ 3

*ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. ሌቦቹ በሕብረተሰቡ የጋራ መገልገያ ንብረቶች ላይ የፈፀሙት የስርቆሽ ተግባር ሕዝብንና መንግሥትን ሲጐዳ የሚችለው እንዴት ነው?
2. የአካባቢው ሕዝብ ሌቦቹን ለማጋለጥ ባቀረባቸው ሦስት የመፍትሔ ሃሣቦች ላይ በቡድን ተወያዩ? የትኛው የመፍትሔ ሃሣብ የተሻለ ነው? ለምን?
3. በጋራ መገልገያ ንብረቶች ላይ አንዳንድ አጥፊዎች ጉዳት ሲያደርሱ እያስተዋልን "እኔን አይመለከተኝም" ብሎ ማለፍ ምን ውጤት ሊያስከትል ይችላል? በቡድን ተወያዩበት፡፡

በአካባቢያችን የሚታዩ ጐጂና አፍራሽ ተግባራትን መቃወም ብሎም ተባብሮ ማስወገድ ከእያንዳንዱ ዜጋ ይጠበቃል፡፡ የጋራ ንብረቶች በአንዳንድ ግዴለሽ ግለሰቦችና በአጥፊዎች ሲበላሹ እያስተዋለ፤ "ምን አገባኝ" የሚል ሰው ጉዳቱ ዞሮ ዞሮ ከእርሱም ዘንድ መድረሱ አይቀርም። ምክንያቱም በንብረቶቹ የሚገለገለው ሕብረተሰቡ ስለሆነ ጉዳቱ ለሁሉም ስለሚተርፍ ነው፡፡ እነዚህን መሰል አፍራሽና ጐጂ ተግባራትን በጋራ መከላከል ከእያንዳንዱ ዜጋ ይጠበቃል፡፡


### መልመጃ 4

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. ከአፍራሽና ጐጂ ተግባራት ነፃ የሆነ አካባቢ እንዴት መፍጠር ይቻላል? በቡድን ተወያዩበት?
2. በአካባቢዬ የሚታዩ አፍራሽና ጐጂ ተግባራትን ለመግታት የእኔ ድርሻ በሚል ርዕስ አጭር ጽሑፍ በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## 5.3 የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፤


### 5.3.1 ለሀገራችን ልማት የወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ድኅነትን በመዋጋት በኩል ያላቸው ሚና፣



*ሥዕል 5.2 ተግቶ መሥራት ያሸልማል*



*ሥዕል 5.3 ጠንክሮ በመሥራት ድህነት ይወገዳል*



*ሥዕል 5.4 ለሀገር እድገት ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ ማደረግ አለበት*

- ሥዕሎቹ በጋራ እንዲያስተላልፉት የተፈለገው መልዕክት ምንድን ነው?

- በአንድ ሀገር ውስጥ የድህነት መገለጫ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች ምንድን ናቸው?

### የአዲስ መንደር ወጣቶች፤

ቁጥራቸው ሰላሣ የሚሆነው የአዲስ መንደር ወጣቶች ለብዙ ዓመታት ሥራ አልነበራቸውም። ያለ ሥራ በመቀመጥ የወጣትነት ዕድሜያቸውን እያባከኑ ያሉት እነዚህ ወጣቶች መንግሥት ያመቻቸውን ዕድል በመጠቀም ከድህነትና ከሥራፈትነት ራሳቸውን ለማላቀቅ መሰባሰብና መደራጀት እንዳለባቸው ተስማሙ።

በስምምነታቸው መሠረትም አንድ "እምቢ ለድህነት" የሚባል ማሕበር አቋቋሙ። በማኅበራቸው አማካይነትም በአካባቢያቸው ከሚገኝ የብድር ተቋም ገንዘብ በመበደር አባላቱን በሦስት የሥራ ዘርፎች መድበው የሥራ እንቅስቃሴአቸውን በጥሩ የሥራ መንፈስ ጀመሩ፡፡

የመጀመሪያው ቡድን እንዲሠራ የተመደበው የአካባቢውን ነዋሪ የስልክ፣ የውሃና የመብራት ወርሃዊ ሂሣብ ሰብስቦ በመክፈል መጠነኛ የአገልግሎት ገቢ ማስገኘት ነው፡፡

የሁለተኛው ቡድን አባላት ደግሞ ከአካባቢው ነዋሪዎች ቤት ደረቅ ቆሻሻ እየሰበሰቡ በማስወገድ ወርሃዊ የአገልግሎት ክፍያ እንዲያገኙ ማድረግ ነው።

ሦስተኛው ቡድን በአካባቢው የሚገኘውን የኅብረተቡን የገበያ ማዕከል በማጽዳትና ፀጥታ በማስጠበቅ ሥራ ላይ ተመደበ።

የአዲስ መንደር፤ "እምቢ ለድህነት ማኅበር" አባላት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ የሥራ እንቅስቃሴ አድርገው ባስመዘገቡት ውጤት ከሦስት የተለያዩ ተቋማትና ከመኖሪያ አካባቢያቸው የቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤት ተሸላሚ ለመሆን በቅተዋል። በዚህም በወጣቶቹ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ሊታይ ችሏል።

## መልመጃ 5

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ወጣቶቹ ቀደም ብለው ይኖሩበት በነበረው ሁኔታ ቢቀጥሉ ውጤቱ ምን ሊሆን ይችል ነበር?
2. የወጣቶቹን የሥራ ተነሳሽነትና ሥራ ፈጣሪነት እንዴት ተመለከቱታላችሁ? በአካባቢያችሁ ይህንን መሰል ሥራ የሚሠሩ ወጣቶች አሉ? ካሉስ በምን የሥራ ዘርፍ ነው የተሰማሩት?
3. ብዙ ወጣቶች ሥራ ማግኘት እንደማይቻል በመግለፅ ሲያማርሩ ይደመጣል። እንደነዚህ ዓይነት ወጣቶች ቢገጥሟችሁ ምን መልስ ትሰጧቸዋላችሁ? በቡድን ተወያዩበት።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ድሃ ከሚባሉት ሀገራት አንዷ ናት። ከዚህ ድህነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመውጣት እውነተኛ የሀገር ፍቅር ስሜት ያለውና በሥራ የሚያምን ትውልድ ሊገነባ ይገባል።

የሀገሪቱን የድህነት ገጽታ ለመለወጥ መንግሥት የተለያዩ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። እነዚህን የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ወደ ተግባር ለመለወጥም መንግሥትና ሕዝብ የተቻላቸውን ጥረት በማድረጋቸው የሀገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት ለተከታታይ ዓመታት በተሻለ ደረጃ ላይ ደርሷል።

በተለይም የኢኮኖሚ ስትራቴጂው አካል የሆነው የግብርናው ዘርፍ ያስገኘው ውጤት በአርአያነት የሚጠቀስ ነው። የሀገሪቱ አርሶ አደሮችና ኢንቬስተሮች በግብርናና በሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ሽልማቶችን አግኝተዋል።

ሀገራችን በምትመራበት የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረት ድህነትን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማሸነፍ እያንዳንዱ ዜጋ የድርሻውን ማበርከት ይጠበቅበታል፡፡ እያንዳንዱ ዜጋ ሀገሪቱ የምትመራባቸውን የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መረዳትና ለተግባራዊነታቸው ጠንክሮ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ ፖሊሲዎቹና ስትራቴጂዎቹ ድክመት ካለባቸውም እንዲሻሻሉና እንዲታረሙ አስተያየት መስጠት የዜጎች ሁሉ ግዴታ ነው።

## መልመጃ 6

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. መንግሥት ከነደፋቸው ዋና ዋና የልማት ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች መካከል የተወሰኑትን በመዘርዘር ስላስገኙት ተጨባጭ ውጤት በቡድን ተወያዩ?
2. ከሀገራችን ድህነትን ለማስወገድ ከእያንዳንዱ ዜጋ ምን ይጠበቃል?

### 5.3.2 የጋራ ችግሮችን ለማስወገድ የበጎ ፈቃደኝነት ሚና

- የጋራ ችግሮች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?

**ቀዳሚ ነኝ እኔ፤**

ለወገኔ ችግር ለወገኔ ብሶት፣
ቀዳሚ ነኝ እኔ ለድርሻዬ አቅርቦት።
ለአካባቢ ሠላም ዘብ አድራለሁኝ ቆሜ፣
ወገኔን ይመቸው በዕውቀት በድካሜ።
ብልፅግና እንዲሠፍን ችግር ከእኛ ርቆ፣
እኔ አለሁ ለወገን ያበርታኝ መርቆ፡፡
ይሄው በፈቃዴ ራሴን አቀረብኩኝ፣
በጋራ ችግር ላይ ልዘምት ጨከንኩኝ፡፡

## መልመጃ 7

***ከላይ የቀረበውን ግጥም መነሻ በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. ግጥሙ ሊያስተላልፍ የፈለገው ዋና መልዕክት ምንድን ነው?
2. በግጥሙ ውስጥ "እኔ" እያለ የሚናገረው ባለታሪክ ምን ምን የበጐ ፈቃደኝነት አገልገሎት ለመስጠት ነው ቃል የገባው?
3. በትምህርት ቤታችሁ አባል የሆናችሁበት የበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት ካለ ስለሚሠጠው አገልግሎት ተወያዩበት፡፡ የአገልግሎቱ ጠንካራና ደካማ ጐኖችስ ምንድን ናቸው?

ልማትን ለማፋጠን መንግሥት የሚያወጣቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በዜጎች የበጐ ፈቃድ አገልግሎት መደገፍ ይኖርባቸዋል። በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩ ችግሮችን መፍታት የሚቻለው በመንግሥት

ጥረት ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ ራሱ በበጐ ፈቃደኝነት ዕውቀቱን፣ ገንዘቡንና ጊዜውን ለጋራ ዕድገትና ልማት ማበርከት ሲችል ነው። ለምሣሌ በአንድ ሠፈር ውስጥ የእሣት አደጋ ቃጠሎ ቢነሣ የእሳት አደጋ መከላከያ መኪና እስኪመጣ አይጠበቅም።

የአካባቢው ሕዝብ በሚቻለው ዘዴ ሁሉ ተረባርቦ እሣቱን በቁጥጥር ሥር ማዋል ይኖርበታል። አደጋው ባደረሰው ጥፋት የተጐዱ ነዋሪዎች ቢኖሩም ለተጐጂዎቹ ቀጣይነት ያለው የመቋቋሚያ ድጋፍ እስኪገኝ ድረስ ፈጣንና ጊዜያዊ ርዳታ የሚያደርገው የአካባቢው ሕዝብ ነው። እነዚህን የመሳሰሉ የጋራ ችግሮችን ራሱ ኀብረተሰቡ ተረባርቦ ማስወገድ ካልቻለ የመንግሥትን ድጋፍ መጠበቁ ብቻ በራሱ መፍትሔ አይሆንም፡፡

በግለሰብም ደረጃ የበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት ማበርከት ከእያንዳንዱ ዜጋ ይጠበቃል፡፡ በተጠናከረ ሁኔታ የበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት ሚናን ለመወጣትም በቅርባችን ከሚገኙ ተቋማት ጋር መሥራት ይቻላል። ለምሣሌ፤ በቀይ መስቀል ማኅበር አባል በመሆን ማኅበሩ በሚያከናውናቸው ተግባራት ውስጥ በቅንነትና በተነሳሽነት በማገልገል ወይንም በልዩ ልዩ ሰብዓዊ ተግባሮችና በልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በበጐ ፈቃደኝነት በመንቀሳቀስ ለኅብረተሰቡ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ተግባር ማከናወን ይቻላል።

**መልመጃ 8**

### *የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

?

1. በአካባቢያችሁ የበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ካሉ በመዘርዘር የአገልግሎታቸውን ዓይነት ግለፁ?
2. የአካባቢያችሁ ኅብረተሰብ በበጐ ፈቃደኝነት ያከናወናቸውን ተግባሮች በተመለከተ ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡
3. እናንተስ በአካባቢያችሁ የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት ተሳትፋችሁ ታውቃላችሁ? ካልተሳተፋችሁስ ለምን? ተወያዩበት፡፡

## 5.4 ዜግነት፤

### 5.4.1 የዜጐች መብትና ግዴታ፣

"ሀገሬ ለእኔ ምን አደረገችልኝ ማለት ብቻ ሳይሆን፤ እኔ ለሀገሬ ምን አደረኩላት ብላችሁ ጠይቁ፡፡" (የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆን ኤፍ ኬኔዲ)

- ከላይ የቀረበው አባባል ምን መልዕክት ያስተላልፋል?

### የተሣታፊያን አስተያየት፤

አቤል፣ ፋላስ፣ ሐረጐትና ዝናሽ የትምህርት ቤታቸው የሥነዜጋ እና ሥነምግባር ትምህርት ክበብ ኮሚቴ አባላት ናቸው። ከሁለት ቀናት በፊት "የዜጐች መብትና ግዴታ" በሚል ርዕስ የክርክር ፕሮግራም አዘጋጅተው ነበር። የዕለቱን ክርክር በተመለከተ የኮሚቴው አባላት በጽሑፍ የደረሳቸውን የተሳታፊያን አስተያየት በጋራ እያነበቡ ነው።

ከአንድ ተማሪ የተላከው አስተያየት እንዲህ የሚል ነው፤ "...ክርክሩን በጣም ወድጄዋለሁ። የዜግነት ግዴታችንን መወጣት የሚገባን ሁኔታዎች በተረጋጉ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሀገር በችግር ላይ ስትሆን ጭምርም መሆን እንደሚገባው አምናለሁ፡፡ እያንዳንዱ ዜጋ መብቱን መጠየቅ ብቻ ሳይሆን ግዴታውንም መወጣት አለበት፡፡ ለምሳሌ በአካባቢያችን አንድ ችግር ሲከሰት ተረባርበን ችግሩን ማስወገድ ይገባናል፡፡ ይህንን አስተያየት የፃፍኩት በክርክሩ ላይ እነዚህ ነጥቦች ስላልተነሱ ነው።"

ሁለተኛው ደብዳቤ እንዲህ ይላል፤ "ትናንት የተደረገው የተሟሟቀ ክርክር ጅምሩ ጥሩና አበረታች ነው። ነገር ግን ተከራካሪዎቹ ማንሣት የሚገባቸውን በርካታ ነጥቦች ያነሱ አልመሰለኝም። ለምሣሌ፤ አንዳንዱ ሰው በሕገ ወጥ መንገድ እየከበረ እኔ ብቻ የዜግነት ግዴታዬን መወጣት አለብኝ ብዬ ባስብ ምን ትርጉም ይኖረዋል፡፡ ስለዚህም በሕገ ወጥ መንገድ ለመክበር የሚሞክረውን ሰው በግልፅነት ማጋለጥና ከስህተቱ እንዲመለስ ማድረግ የሁላችንም ኃላፊነት መሆን እንዳለበት አምናለሁ፡፡"

ሦስተኛው አስተያየት የሚከተለው ነው። “አንድ ሰው ጥሩ ሥራ ሠርቶ የዜግነቱን ድርሻ ሲወጣ ብዙም ሲመሰገን አይታይም። ስህተት ፈፅሞ ከተገኘ ግን ግዴታውን አልተወጣም ተብሎ ሲኰነን ይታያል። ይህ ለምን ይሆናል? አመሰግናለሁ።” የክርክሩ አስተባባሪ ኰሚቴ አባላት እነዚህንና ሌሎችንም በርካታ አስተያየቶች ካነበቡ በኋላ በሚቀጥለው የክርክር ፕሮግራም ላይ አስተያየቶቹን አጠቃለው እንደሚያቀርቡ በመስማማት ተለያዩ።

## መልመጃ 9

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

1. የመጀመሪያው አስተያየት ሰጪ እንዳለው የዜግነት ግዴታችንን መወጣት የሚገባን መቼ ነው? ተጨማሪ ምሳሌዎችን እየጠቀሳችሁ በቡድን ተወያዩ፡፡
2. ሁለተኛው አስተያየት ሰጪ እንደጠቀሰው ብዙ ሰዎች ሕግን በማክበር የዜግነት ግዴታቸውን በሚገባ ሲወጡ አንዳንዶቹ ግን ሕገወጥ ተግባራትን በመፈፀም ኑሮአቸው ሲሳካ መታየቱ አግባብ ነው?
3. የዜግነት መብትና ግዴታውን የሚወጣ ሰው እንዴት መመስገን እንደሚገባውና ግዴታውን የማይወጣ ከሆነ ደግሞ እንዴት ሲታረም እንደሚገባ በምሣሌዎች እያስደገፋችሁ በቡድን ተወያዩ፡፡

እያንዳንዱ ዜጋ ሰብዓዊ ፍጡር በመሆኑ ብቻ ሊከበሩለት የሚገቡ መብቶች አሉት። ለምሣሌ፤ ዜጐች ሁሉ በሀገራቸው በነፃነት የመኖር መብት አላቸው፡፡ ማንም ዜጋ ከሕግ ውጪ ሊታሠርና ሊከሰስ አይገባም፡፡ የሃይማኖትና የእምነት ነጻነቱ ይከበርለታል። ይህ እንዳለ ሆኖ ሀገራችን እያራመደች በአለችው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የአስተዳደር ዘይቤ የዜጐች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በአግባቡ የተከበሩ ናቸው። ለአብነት ያህልም ሃሳብን በነጻነት የመግለፅ፣ ማንኛውንም አመለካከት በነፃነት የማራመድ፣ የመሰብሰብ፣ ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ፣ አቤቱታ የማቅረብ፣ ራስን የማስተዳደር መብት በዋናነት ይጠቀሳሉ። ሆኖም የዜጐች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ ዜጋ ግዴታውን መወጣትም ይጠበቅበታል፡፡

ማንኛውም ዜጋ ሰብዓዊም ሆነ ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ እንዲከበሩለት የሚፈልገውን ያህል እርሱም የሌሎችን መብት ማክበር ግዴታው ነው። ለምሣሌ አንድ ልጅ ወላጆቹ፣ አሳዳጊዎቹ ወይንም ረዳቶቹ አቅማቸው የፈቀደውን ያህል መሠረታዊ ፍላጎቶቹን እንዲያሟሉለት መጠየቅ መብቱ ሲሆን፤ እርሱ ደግሞ በቤተሰቡ ውስጥ የሚሰጠውን ኃላፊነት መወጣት ግዴታው ነው።

እያንዳንዱ ዜጋ በመብቱ በመጠቀም በአካባቢ በሚደረጉ ማኅበራዊ ጉዳዮች ውስጥ በንቃት መሳተፍ ይኖርበታል፡፡ ለጋራ ንብረት ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግና ሀገሪቱ ከእሱ የምትፈልገውን ሁሉ ማሟላትም የኃላፊነቱ አንዱ ገፅታ ነው፡፡

በአንጻሩም ለአካባቢ የልማት ዕቅዶች ማስፈፀሚያ ድጋፍ እንዲደረግ መንግሥትን መጠየቅ የዜጐች መብት ሲሆን ዜጐችም የድርሻቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ከፀጥታ ኃይሎች ጐን በመሆን የአካባቢን ሠላምና ደኅንነት በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲጠበቅ እያንዳንዱ ሰው ድርሻና ኃላፊነት አለበት፡፡

## መልመጃ 10

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ዜጐች ለመብታቸው ብቻ ትኩረት ሰጥተው ግዴታቸውን ባይወጡ ምን ሊከተል ይችላል?
2. በዜግነቴ ልጠይቃቸው የሚገቡ መብቶችና ልወጣቸው የሚገቡ ግዴታዎች ናቸው የምትሏቸውን ሦስት ያህል ነጥቦች ግለጹ፡፡

## 5.5 ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ

### 5.5.1 የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በታሪክ ያስፈባቸው ሂደቶች



*ሥዕል 5.5 ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ የሉዓላዊነታችን መገለጫ ነው*

- ሥዕሉ ለእናንተ የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድን ነው?

### ኩመራ አፍንጬና አባባ ጉዳ፤

አባባ ጉዳ ኩልፌ እየተባለ በሚጠራው ሰፈር ነዋሪ ሲሆኑ በጨዋታ አዋቂነታቸውና በታሪክ እውቀታቸው የአካባቢው ነዋሪ ሁሉ በጣም ይወዳቸዋል፡፡ የኩመራ አፍንጬ ቤተሰቦችና አባባ ጉዳ ጉረቤታሞች ስለሆኑ ኩመራ አፍንጬ ሁል ጊዜም አባባ ጉዳን ለማግኘት ዕድል አለው፡፡ ሁለቱ ሲገናኙ የሚያወሩት ቁምነገር ነው፡፡ ኩመራ አፍንጬና አባባ ጉዳ ስለ ሰንደቅ ዓላማ ያደረጉት ውይይት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ኩመራ አፍንጬ፣** አባባ ጉዳ የሀገራችን ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ከመጀመሪያ ጀምሮ ቀለሙ፤ እንዳዛሬው ሁሉ አረንጓዴ ብጫና ቀይ ነበር?

**አባባ ጉዳ፣** አረንጓዴ ብጫና ቀዩ ቀለማት ረጂም ታሪክ ያላቸው ቢሆንም በዚሁ የረጂም ታሪክ ጉዞ ውስጥ ግን አንዳንዴ ቀለማቱና አቀማመጣቸው ተለዋውጠው ነበር፡፡

**ኩመራ አፍንጬ፣** የተለዋወጡት የሰንደቅ ዓላማው ቀለማት ብቻ ናቸው ወይንስ ዓርማውም ተለዋውጧል?

**አባባ ጉዳ፣** አዎን ዓርማውም ሲለዋወጥ ኖሯል፡፡ ለምሳሌ የቅርቡን እንኳ ብጠቅስልህ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በብሔራዊው ሰንደቅ ዓላማ ላይ የነበረው ዓርማ በትከሻው ላይ ሰንደቅ ዓላማ የተሸከመ አንበሳ ነበር፡፡ የዓርማው ትርጉምም የነገሥታቱ የሥልጣን አመጣጥ ከሰለሞናዊ ነገድ መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ በደርግ የአገዛዝ ዘመን ደግሞ የአንበሳው ዓርማ ተነስቶ የሶሻሊዝምን ፍልስፍና የሚያሳይ ዓርማ በሰንደቅ ዓላማው ላይ ተለጠፈበት፡፡

የደርግ መንግሥት ከሥልጣን ተወግዶ የኢህአዴግ መንግሥት ሀገር መምራት ከጀመረ በኋላ ደግሞ የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ዕኩልነት የሚያንፀባርቀው ጨረር የሚፈነጥቀው ባለ አምስት ጫፍ የኰከቡ ዓርማ በብሔራዊ ዓርማነት ፀደቀ፡፡

**ኩመራ አፍንጬ፣** አባባ ጉዳ ሁሉንም አብራርተው ስላስረዱኝ አመሰግናለሁ፡፡

**አባባ ጉዳ፣** መልካም ነው አፍንጬ ተጨማሪ መጋለጫ ከፈለግህ የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት መምህርህን ብትጠይቅ በሚገባ ያስረዱሃል፡፡

**መልመጃ 11**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. ከኩመራ አፍንጬና ከአባባ ጉዳ ውይይት ምን ተገነዘባችሁ?
2. የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ቀለማትና ዓርማው በረጂም ዘመናት የታሪክ ሂደት እንዲለዋወጡ የተደረገው ለምን ይመስላችኋል?
3. ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና ብሔራዊ ዓርማ የማይለያዩበት ምክንያት ምን ሲሆን እንደሚችል ተወያዩበት፡፡

ቀለማት ዛሬ የምናውቃቸው ሦስት ቀለማት ማለትም አረንጓዴ፣ ብጫና ቀይ ብቻ አልነበሩም፡፡ የታሪክ ተመራማሪዎች እንዳረጋገጡት በተለያዩ ዘመናት መሪዎች ሥልጣን ሲይዙ የተለያዩ ዓይነት ቀለማት ያላቸው ሰንደቅ ዓላማዎች ያውለበልቡ ነበር፡፡ ለምሳሌ በዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ዘመን ይውለበለብ የነበረው የሰንደቅ ዓላማ ቀለማት ደማቅ ቀይ፣ ነጭና ሰማያዊ የነበረ ሲሆን

በአጼ ዮሐንስ ዘመንም እንዲሁ አረንጓዴ ብጫና ቀይ ቀለማት ያሉት ሰንደቅ ዓላማ ይውለበለብ እንደነበር አንዳንድ የታሪክ መረጃዎች ይጠቁማሉ::

ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ጥቅምት 25/1882 ዓ.ም ንጉሠ ነገሥት ተብለው ዘውድ ከደፉ በኋላ አረንጓዴ ብጫና ቀዩ ቀለማት (አንዳንዴ አቀማመጡ ቢዘበራረቅም) የሰንደቅ ዓላማው ቀለማት ግን እንዳለ ቀጥለዋል:: በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመንም አረንጓዴ፣ ብጫና ቀዩ ሰንደቅ ዓላማችን በስፋት ይውለበለብ ነበር::

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ኅብረ ቀለማትና አቀማመጥ ምን መምሰል እንደሚገባው ለመጀመሪያ ጊዜ በሕግ ተደንግጐ ሊወጣ የቻለው በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በ1948 ዓ.ም. በተሻሻለው ሕገመንግሥት ነበር::

ቀደም ሲል የተጠቀሱት ነገሥታት በሰንደቅ ዓላማው ላይ፣ "ሞአ አንበሳ ዘእምነ ነገደ ይሁዳ" ወይንም "አሸናፊው የይሁዳ ነገድ አንበሳ" የሚለውን የዘር ግንዳቸውን የሚወክልላቸው ዓርማ ነበራቸው:: በዘመነ ደርግም እንዲሁ አረንጓዴ ብጫና ቀዩ ሰንደቅ ዓላማችን ቀለማት እንዳሉ ቢቀጥሉም ዓርማው ግን የወቅቱን የሶሻሊዝም ፍልስፍና እንዲወክል ታስቦ ተለውጧል::

አሁን በተያያዝነው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ደግሞ አረንጓዴ፣ ብጫና ቀዩ ቀለማት እንዳሉ ሆነው እኩል ርዝመት ባላቸው መስመሮች የተሰራው የኮከቡ ዓርማና የሚፈነጥቀው ጨረር የብሔሮች የብሔረሰቦችና የሕዝቦችን እኩልነት እንዲያንፀባርቅ ሆኖ የተዘጋጀ ነው::

**መልመጃ 12**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

?

1. ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በነበሩት ሦስት ሥርዓቶች በብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማችን ላይ የነበረው ብሔራዊ ዓርማ እንዴት ይለዋወጥ እንደነበር ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት::
2. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ከጥንት ጀምሮ አረንጓዴ፣ ብጫና ቀይ ቀለማት ነበሩት ብሎ ለሚከራከር ሰው ምን መልስ ትሰጣላችሁ?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

አዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት መገለጫ በዋነኛነት የብሔሮችን፣ የብሔርሰቦችንና የሕዝቦችን ታሪኮችና ባህሎችን ማዕከል በማድረግ ሲሆን ሀገርን መውደድና ሕዝብን ማክበር የሚገለፀው ደግሞ ለሕግና ደንብ ተገዢ በመሆን ነው። የራሳችን መብት እንዲጠበቅ የምንፈልገውን ያህል የሌሎችንም መብት ልንጠብቅ ይገባል። ሀገሩን የሚወድ ሰው የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ይወጣል፣ ለኅብረተሰቡም አርአያነት ያላቸው ተግባራትን ይፈፅማል። የሀገሩንና የሕዝቡን ትክክለኛ ታሪኮችና ባህሎች መገንዘብ፣ የተዛቡ ታሪኮችንም ማስተካከል የእያንዳንዱ ዜጋ ድርሻ ነው።

አዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት የሚጀምረው አካባቢን በሚገባ በማወቅና የጋራ መገልገያ መሣሪያዎችን በጥንቃቄ በመያዝና በመንከባከብ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ለሀገራችን ልማት መፋጠን የወጡ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ድህነትን በመዋጋት በኩል ያላቸው ሚና የላቀ ቢሆንም በበጐ ፈቃደኝነት ተሳትፎ ካልተደገፉ የተጠበቀው ውጤት ላይመዘገብ ይችላል። ይህንን ውጤታማ ተግባር ለማከናወን ደግሞ ዜጐች ሁሉ መብትና ግዴታቸውን በሚገባ ሊገነዘቡ ይገባል፡፡

ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማችን ለሀገራችንና ለሕዝባችን ያለንን ፍቅርና አክብሮት መግለጫ ብቻ ሳይሆን የረጂም ዘመናት ታሪካችን ምስክርና ምልክትም ጭምር ሲሆን ተገቢው አክብሮትና ክብር ሊሰጠው ይገባል፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**ፖሊሲና ስትራቴጂ፣** ለሀገር ልማት አፈፃፀም ውጤታማነት መንግሥት የሚያወጣው ሕግ፣ የሚደነግገው ደንብና መመሪያ፡፡

**አውጫጭኝ፣** ቀደም ያለው ማኅበረሰብ ወንጀለኞችን ወይንም አጥፊዎችን ከመሃከሉ አጋልጦ ለፍርድ የሚያቀርብበት ባህላዊ ሥርዓት ሲሆን "አውጣጡልኝ" ከሚለው ቃል የተገኘ ነው፡፡

**ሉዓላዊ መንግሥት፣** የዳር ድንበሩ ክብር በዓለም አቀፍ የተከበረለት ነፃ መንግሥት።

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::*

## I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::

1. የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች ታሪክ እንዳይዛባ ለማድረግ እያንዳንዱ ዜጋ ድርሻ አለው።
2. ለሕግና ደንብ ተገዥ ለመሆን እያንዳንዱ ዜጋ የሕግ ዕውቀት አያስፈልገውም።
3. መብታችንን ከመጠየቅ በፊት ግዴታችንን መወጣታችንን ማረጋገጥ አግባብ ነው።
4. ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማችን የነፃነታችንና የረጂም ታሪካችን ምስክር ነው፡፡
5. እያንዳንዱ ዜጋ የአቅሙንና የዕውቀቱን ያህል ለኅብረተሰቡ አርአያነት ያለው ተግባር ሊፈፅም ይገባል።
6. በሀገራችን የተዛቡ ታሪኮችን የማስተካከል ኃላፊነት የታሪክ ምሁራን ድርሻ ብቻ መሆን ይገባዋል።

## II. በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ካሉትጋር አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. በነፃነት ሃሣብን መግለፅ፣ | ሀ. ምሥጢርን መጠበቅ። |
| 2. መብትና ግዴታን ማወቅ፣ | ለ. ጐጂ ተግባር። |
| 3. የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ | ሐ. አፍራሽ ተግባር። |
| 4. አንዱ የታማኝነት መገለጫ፣ | መ. አርአያነት ያለው ተግባር። |
| 5. ራስን ለባዕድ ሱስ ተገዥ ማድረግ፣ | ሠ. ድህነትን የማስወገጃ ስልቶች። |
| 6. የሀገርን በጐ ገጽታ ማጉደፍ፣ | ረ. ዴሞክራሲያዊ መብት። |
| 7. የጋራ መገልገያን መንከባከብ፣ | ሰ. የዜጐች ኃላፊነት። |

## III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::

1. የአዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት መገለጫ ከሆኑት መካከል፤
   ሀ. የተዛቡና ያልተዛቡ ታሪኮችን ለይቶ መረዳት፣
   ለ. ለሕግና ደንብ ተገዢ መሆን፣
   ሐ. አርአያነት ያለውን ተግባር ማከናወን፣
   መ. ሁሉም መልስ ሊሆን ይችላል።
2. አፍራሽና ጐጂ ተግባራትን መከላከል ያስፈለገበት ምክንያት፤
   ሀ. የእያንዳንዱ ዜጋ የግል ኃላፊነት ስለሆነ ነው፣
   ለ. የኅብረተሰቡ የጋራ ኃላፊነት በመሆኑ ነው፣
   ሐ. የሕግ አስከባሪው አካል ድርሻ ብቻ ስላልሆነ ነው፣
   መ. ሁሉም መልስ ይሆናል።

3. ለሀገራችን ልማት የተነደፉ ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች፤
   ሀ. ተግባራዊ የሚሆኑት በመንግሥት ጥረት ብቻ ነው፣
   ለ. መውጣታቸው ብቻ ለውጤታማነት በቂ ነው፣
   ሐ. መሻሻል አይገባቸውም፣
   መ. ለተግባራዊነታቸው የመንግሥትና የዜጎች የጋራ ጥረት ወሳኝ ነው።
4. የዜጎችን መብትና ግዴታ በተመለከተ ትክክለኛው ሃሳብ የትኛው ነው?
   ሀ. የዜጎች መብት በሕገመንግሥቱ ተረጋግጧል፣
   ለ. የዜጎች መብትና ግዴታ በተግባር መፈተን አለበት፣
   ሐ. መብቱና ግዴታውን ሁሉም እንዲያውቀው መደረግ አለበት፣
   መ. ሁሉም መልስ ሊሆን ይችላል።

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ፡፡

1. ከሀገራችን ድህነት እንዲወገድ እያንዳንዱ ዜጋ መንግሥት ለሚያወጣቸው ________እና __________ተፈፃሚነት የድርሻውን ሊወጣ ይገባል።
2. በራስ አነሳሽነት የሚፈፀም ተግባር__________ ተብሎ ይታወቃል።

## V. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልሶች ስጡ፡፡

1. የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች በጥንቃቄ ጉድለት ቢበላሹ በኅብረተሰቡ ላይ ምን ችግር ሊከተል ይችላል? በምሣሌ አብራሩ፡፡
2. መንግሥት ለሚነድፋቸው የልማት ሥራዎች የበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት እንዴት ሊያግዝ ይችላል?

# ምዕራፍ ስድስት

# የኃላፊነት ስሜት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** *ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቂ/ ስታጠናቅቅ ፤*

- የተለያዩ የኃላፊነት ዓይነቶችንና ደረጃ ዎችን ታውቃለህ/ታውቂያለሽ፣
- የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን የመንከባከብ ኃላፊነትሽን/ኃላፊነትህን ትረጂያለሽ/ትረዳለህ፡፡
- ራስን ከኤች.አይ.ቪ ኤድስ የመጠበቅ አስፈላጊነትን ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ፡፡

## 6.1 ኃላፊነትን መወጣት

### 6.1.1. የኃላፊነት ዓይነቶችና ደረጃዎች



*ሥዕል 6.1 በጎዳር 12 በባህላዊው የጽዳት ዘመቻ ቀን ኅብረተሰቡ ቆሻሻ በማስወገድ ላይ*

- ከሥዕሉ  ምን ተገነዘባችሁ?

**ትውስታ፤**

እኔ የምሠራው በጉምሩክ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ነበር፡፡ በአንድ ወቅት አንድ ባራቶሎ የሚባል ጣሊያናዊ የ30 ሚሊዬን ብር የግብር ዕዳውን እንድሰርዝለት ይፈልግና ወደኔ ይመጣል፡፡ ለዚህም ተግባሬ "ሶስት ሚሊዬን ብር እንዲሁም ገልባጭ መኪናና ቪላ ቤት ልሰጥህ ዝግጁ ነኝ" ይለኛል፡፡ እኔም ግብር ለሀገራችን ኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ነውና በምንም ዓይነት አስተያየት አይደረግልህም፡፡ ይህ ደግሞ የሀገራችን ሕግ ነው እለዋለሁ፡፡

ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ አማላጅ እንዲሆነው አንድ ትልቅ ባለሥልጣን ይልክብኛል፡፡ ለዚህ ሰው የመለስኩለት፣ "ተምረን ተምረን ሀገር እን ሽጥ ነው የምትለኝ?" የሚል ነበር፡፡ እሱም "እን ደደረቅህ ትቀራታለህ፣ መንግሥት እንደሆነ እንደ አሮጌ ቅርጫት ወርውሮ ይጥልሃል፡፡" አለኝ በን ዴት፡፡ የእኔም መልስ "ግዴለህም ሀገሬ ረድኤቷ ይበቃኛል፡፡" ነበር፡፡

ጉዳዩ እየተካረረ በመሄዱ ጣልያናዊው ሥራ አስኪያጅ የኩባንያው ሸሪክ ለሆኑት ለልዕልት ተናኘ ወርቅ ያመለክታል፡፡ እሳቸውም "ታመምኩ በልና ሆስፒታል ተኛ፣ ጃንሆይ እንዲጐበኙህ አደርጋለሁ፣" ሲሉ መከሩት፡፡ ባራቶሎም እንዳሉት ሆስፒታል ገባ፡፡

ልዕልት ተናኘወርቅም ጃንሆይ እንዲጐበኙት አደረጉ፡፡ ጃንሆይም፣ "መኪና ገጭቶህ ነው እንዲህ የሆንከው?" ሲሉ ጠየቁት፡፡ ባራቶሎም፣ "ጃንሆይ እኔን የገጨኝ መኪና ሳይሆን ሀገር ውስጥ ገቢ ነው፡፡" ሲል መለሰ፡፡ ጃንሆይም "አንተ ጉዳዩን ለኛ ተወው፣ አሁን ታክመህ ውጣ፡፡" ይሉና ይሄዳሉ፡፡ በ1965 ዓም አጋማሽ ላይ "ጥብቅ ምስጢር" የሚል ደብዳቤ ደረሰኝ፡፡ "ባራቶሎ እስከዛሬ ያለበት ዕዳ ተሰርዟል" ይላል፡፡

ከጥቂት ጊዜ በኋላ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም ጃንሆይ ከሥልጣን ወረዱ፡፡ ወደ ቢሮ ስሄድ ባራቶሎን አገኘሁት፡፡ "ደብዳቤ አልደረሰህም?" አለኝ፡፡ እንዳልደረሰኝ ነገርኩት፡፡ ሆኖም ሀገር ወዳድ ለሆኑ አንድ የገንዘብ ሚኒስቴር ባለሥልጣን ያበሳጨኝን ጉዳይ ገለጥኩላቸው፡፡ እሳቸውም ሀሳቤን ደገፉልኝ፡፡ ክስ እንዲመሰረትበት ሆኖ ከብዙ የፍርድ ቤት ውጣ ውረድ በኋላ ቱጃሩ ባለኩባንያ ጣልያናዊ ዕዳውን እንዲከፍል ተፈረደበት፡፡

*(ከገቢ ለልማት ቅጽ 4 ቁጥር 4 ጥር 2ሺ መጽሔት የተወሰደ፡፡)*

**መልመጃ 1**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. የባራቶሎን ጉቦና ምልጃ ያልተቀበሉት ባለሥልጣን ተግባር ምንን ያመለክታል?
2. ለሀገሩ ልማትና ለወገኑ ብልጽግና የሚሠራ ዜጋ ከዚህ ታሪክ ምን ይማራል?
3. የጉቦና ምልጃን ጉዳት ከጋራ ጥቅም አኳያ ግለጹ፡፡

ኃላፊነትን መወጣት፣ መሠረታዊ ግቡ ልማትና የሀገር ብልጽግና ነው፡፡ በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ሥራ የእድገት መሠረት ነው፡፡ ማኅበረሰቡም የሥራን ኃላፊነት የመቀበልና በአጥጋቢ ውጤት የማከናወን የዜግነት ግዴታ አለበት፡፡ ኃላፊነትን መቀበል አንድን ተግባር ለማከናወን እንዳሰበ የሚያመላክት ሲሆን ኃላፊነት መወጣት ደግሞ ውጤታማ መሆንን ያሳያል፡፡

ኃላፊነት በግልና በጋራ የሚፈፀም የተግባር ክንዋኔ ነው፡፡ የግል ኃላፊነት እያንዳንዱ ሰው ሊወጣው የሚገባውን ኃላፊነት ያመለክታል፡፡ የግል ኃላፊነት ከእያንዳንዱ ግለሰብ እንደ ዕድሜው፣ ችሎታው፣ ሥልጣኑ ወዘተ... የሚጠበቅ ሕጋዊና ሞራላዊ ግዴታ ነው፡፡ ግለሰቡ ይህን ኃላፊነት ባይወጣ ራሱ ከመጐዳቱም ባሻገር ኅብረተሰቡንም ሆነ ሀገሩን ሊጐዳ ይችላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች ለጋራ ኑሮ አመቺነት በሚጠቀሙባቸው ጉዳዮች ላይ የሚወስዱት እርምጃ የጋራ ኃላፊነት ይባላል፡፡ ለምሳሌ፣ የሀገርን ሉዓላዊነት መጠበቅ፣ የመንግሥትንና የሕዝብን ንብረቶች ከብክነትና ከጥፋት መከላከል፣ ሽብርተኝነትን መዋጋት፣ ወንጀልን መከላከል እና የመሳሰሉት በጐ ተግባራት ሁሉ የግል ብቻ ሳይሆኑ የጋራ ኃላፊነቶች ናቸው፡፡

ኃላፊነት አንድን ሕጋዊ ተግባር በአግባቡ የመፈፀም ግዴታ ሲሆን፣ ዓይነትና ደረጃዎች አሉት፡፡ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ሰዎች እንደሙያቸው ዓይነትና የትምህርት ደረጃ በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ይሠማራሉ፡፡ እንደተሠማሩበት የሞያ መስክም ኃላፊነታቸው ይለያያል፡፡ ለምሳሌ እያንዳንዱ ዜጋ የሀገሩ ሕልውናና ዕድገት ይመለከተዋል፡፡ ሆኖም ዕቅዶችንና ሕግጋትን በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግረገድ፤ የሀገሪቱ ሕልውናና እድገት እውን እንዲሆን የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የበለጠ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በሌላም በኩል አንድ ሐኪም ሙያዊና ሞራላዊ በሆነ ኃላፊነት ሕሙማንን ለመርዳት ከጤናረዳቱ የላቀ ኃላፊነት አለበት፡፡ የመማር-ማስተማር ሂደትም በተጣጣመ መልኩ እንዲከናወን ከት/ቤት አስተዳደር ፀሐፊ ይልቅ የርዕሰ መምህሩ ኃላፊነት የጐላ ነው፡፡ ሆኖም በማንኛውም የሥራ መስክ ውጤት ለማምጣት፣ ልዩ ልዩ የኃላፊነት ሥራዎች በደረጃቸውና በዓይነታቸው አስፈላጊዎች ናቸው፡፡

**መልመጃ 2**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. ኃላፊነት ማለት ምን ማለት ነው?
2. የጋራ ጥቅም የሚያስገኙ ጉዳዮችን በጋራ ማከናወን ምን ዓይነት ኃላፊነት ነው?
3. የኃላፊነት ዓይነትና ደረጃ ሲባል ምንን ለማመልከት ነው?
4. ኃላፊነትን መቀበልና ኃላፊነትን መወጣት ልዩነታቸው ምንድን ነው?
5. የግል ኃላፊነቱን የማይወጣ ግለሰብ የሚጐዳው ማንን ነው?

## 6.2 ቃልኪዳን

- *ቃልኪዳን ምንድን ነው?*

### የቃልኪዳን ሙዳይ፤

የመስከረም ወር ሁልጊዜም የብሩህ ራዕይ መስኮት ነው፡፡ ት/ቤቶች በሙሉ ኃይልና ዝግጅት ሥራ የሚጀምሩት በዚሁ ወር መባቻ ላይ ሲሆን፣ የአጀማመሩ ሥነ ሥርዓት በምስራቅ ጮራ ት/ቤት ልዩ ውበት አለው፡፡ ሁሉም ክፍሎች አልፈዋቸው ለመጡት ክፍሎች የአደራና የቃልኪዳን ችቦ ያቀብላሉ፣ እነሱም እንዲሁ ከበላይ ካሉት ክፍሎች ይቀበላሉ፡፡

በተማሪዎች ካውንስልና በት/ቤቱ አስተዳደር ስምምነት መሠረት ለየክፍሎቹ በአንድ ዓመት የትምህርት ጊዜ ውስጥ የሚሠሯቸው ተግባራት ተወስነዋል፡፡ የሚከናወኑት ተግባራት በክፍሎች ደረጃ እንደሚከተለው ተገልጸዋል፡፡

***7ኛ ክፍል*** ዓመቱን በሙሉ የት/ቤት ግቢ ጽዳት፣

***8ኛ ክፍል*** የአበባና የሣር ቦታዎች እንክብካቤ፣

***9ኛ ክፍል*** የውሀ አጠቃቀምና የመፀዳጃ አካባቢዎች ንፅህና ቁጥጥር

***10ኛ ክፍል*** ለቀይ መስቀልና በጐ አድራጐት ክበባት ድጋፍ የገቢ ምንጭ ማስገኘት (ከጓሮ አትክልት ልማት፣ ስፖርት ትያትር ገቢ ወዘተ...)

***11ኛ ክፍል*** የት/ቤቱን ግቢ የስፖርትና ማረፊያ ቦታዎች መከለል፣ ማስዋብ መሰለፊያና መተላለፊያ መንገዶችን ቀለም መቀባት፣

***12ኛ ክፍል*** የወላለቁ ዴስኮችንና ወንበሮችን ከባለሙያ ጋር መጠገን፣ የተቀደዱ መጻሕፍትን መጠረዝ፣ የመታሰቢያ ዛፎችን መትከልና ዓመቱን በሙሉ እንክብካቤ ማድረግ፣ ናቸው፡፡

ሁሉም ክፍሎች የተቀበሉትን ኃላፊነት በስኬታማነት ለማጠናቀቅ ቃልኪዳን ይገባሉ፡፡ ከመማር ማስተማሩ ሂደት በተጓዳኝ ቃልኪዳንን በውጤት ለማሳየት ከመስከረም በኋላ ጤናማ ውድድርና እንቅስቃሴ በት/ቤቱ ውስጥ ይደራል፡፡ የተሰጠውን አደራ በገባው ቃል ኪዳን መሠረት በአጥጋቢ ውጤት ያከናወነ ክፍል ደግሞ የጋሻና የዋንጫ ሽልማት ይሰጠዋል፡፡

በምሥራቅ ጮራ ት/ቤት የሚንቀሳቀሰው አየር ንፁህና የሚያዝናና ነው፡፡ ምክንያቱም ግቢው በልምላሜና በንፅህና የተያዘ በመሆኑ ነው፡፡ የተሰባበሩ ወንበሮች፣ የተበሳሱ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣ ቀለማቸው የተጋጠ ግድግዳዎች አይታዩም፡፡ የሁሉም ክፍል ተማሪዎች በተቀበሉት አደራ "የኔ ንብረትና ሀብት ነው" በሚል የኃላፊነት ስሜት ቃልኪዳናቸውን ለመጠበቅ ይሠራሉ፡፡

በት/ቤቱ ግቢ በረድፍ ተተክለው ጥላ በመሆንና የአካባቢውን የአየር ሁኔታ በማስተካከል የሚያገለግሉት ዛፎችም ለትምህርት ቤቱ ልዩ ውበት አጐናጽፈውታል፡፡

በምሥራቅ ጮራ ት/ቤት የሚከናወን ሌላም ዐቢይ ተግባር አለ፡፡ በቀይ መስቀልና በጐ አድራጐት ክበባት መሪነት በዓመት ሁለት ጊዜ በት/ቤቱ አካባቢ የሚኖሩ የአቅመ ደካሞችና የአረጋውያን ቤት ይጠገናል፣ ሰፈራቸው ይፀዳል፡፡ ለችግረኞቹም ድጋፍ ይደረጋል፡፡ ከዚህም የተነሣ አንዳንድ የአካባቢ ሰዎች እርዳታና ትኩረት እንዲያገኙ ለተማሪዎቹ ክበባት የሚያመለክቱበት ጊዜ አለ፡፡

በት/ቤቱ አዋሳኝ ያሉ መንገዶች በአረም፣ በቆጥቋጦና በቆሻሻ ተበክለው አይታዩም፡፡ ተማሪዎቹ ሁሉ በቅንነትና በታማኝነት የሚያከናውኑት የሥራ ድርሻ በድምር ውጤቱ አደራን የማክበርና ቃልኪዳንን የመፈፀም ክቡር ተግባር ሆኖ እንዲመሰገኑ አደርጓል፡፡ ስለዚህም፣ ለውጥና ውጤት የሚታይባት በመሆንዋ ምስራቅ ጮራ ት/ቤት የቃልኪዳን ሙዳይ እየተባለች ትጠራለች፡፡

**መልመጃ 3**

***ከላይ በቀረበው ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. አደራና ቃልኪዳን ያላቸውን ተያያዥነት አስረዱ፡፡
2. የምሥራቅ ጮራ ት/ቤት ተማሪዎች የግልና የጋራ ኃላፊነታቸውን የተወጡት እንዴት ነው?
3. በቅንነትና በኃላፊነት ስሜት በተማሪዎቹ የተሠሩትን ሥራዎች ውጤት ያስገኙትን ጥቅም ዘርዝሩ፡፡

ቃልኪዳን ማለት ኃላፊነትን መወጣትና አደራን ማክበር ማለት ነው፡፡ ቃልኪዳንን መፈፀም ግለሰባዊ ክብርና የመንፈስ ጥንካሬ መለኪያ ነው፡፡

ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ቃል ኪዳን ከሚገቡባቸው ሁኔታዎች መካከል፣ በሰዓቱ በት/ቤት በመገኘት መማር፣ የቤት ሥራዎችን ሠርቶ መምጣት፣ ለት/ቤቱ ሕግና ሥርዓት መገዛት እንዲሁም በት/ቤት ውስጥ የሥራ ተሣትፎ ማድረግ ከሚጠቀሱ ተግባራት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ትምህርትን በተመለከተ አጥጋቢ ውጤት ለማምጣት ለራሳቸው፣ ለቤተሰቦቻቸዉና ለት/ቤቱ ቃልኪዳን የገቡ ተማሪዎች በትጋትና በኃላፊነት ስሜት ይማራሉ፡፡

በዓመቱ መጨረሻም በውጤታቸውና በሥነ ምግባራቸው የተመሰገኑና ተሸላሚዎች ይሆናሉ፡፡ ለሌሎችም አርአያ ሆነው ይጠቀሳሉ፡፡ ቃልኪዳን አክባሪ ወጣቶች በልዩ ልዩ የአካባቢ ማኅበራት ውስጥ በመደራጀት እንደአቅማቸው የኅብረተሰቡን ችግር ለመፍታት ቃልኪዳን ይገባሉ፡፡ ይህም ኃላፊነትን እና አደራን መቀበል ነው፡፡

በዚሁ መሠረት ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን፣ ጽዳትንና ትምህርታዊ ቅስቀሳዎችን በማድረግ ለጋራ ጠቀሜታ የሚውሉ ውጤቶችን ያስመዘግባሉ:: ይህም የሚያሳየው የገቡትን ቃልኪዳን ማክበራቸውንና በውጤት ማስመስከራቸውን ነው::

ወጣቶች ሀገር ተረካቢ ኃይሎች እንደመሆናቸው መጠን ተማሪዎች የሚጣልባቸውን አደራ በአቅማቸው በቅንነትና በሀቀኝነት በመሥራት ኃላፊነትን መወጣት እንደሚችሉ የሚያረጋግጡት በየአካባቢያቸው በሚያሳዩት ተሣትፎ ነው:: ይህም የአካባቢ ልምምድ ደረጃውን ጠብቆ በማደግ ከፍተኛ ኃላፊነትንና አደራን ወደ መወጣት ብቃት ያሸጋግራል:: ስለዚህ አንቺም/አንተም ኅብረተሰቡ ለጋራ ጥቅምና ሕልውና ጉዳዮች መሟላት ለሚያደርገው ጥሪ የዜግነት ምላሽ በመስጠት ኃላፊነታችሁን መወጣት ይጠበቅባችኋል::

**መልመጃ 4**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. የሰዎች የዓላማ ጽናትና የመንፈስ ጥንካሬ የሚለካው በምንድን ነው?
2. አንድ ወጣት ለአካባቢው ዕድገት በቅንነት የሚያደርገው ተሣትፎ ምን መሆን አለበት?
3. አንድ ተማሪ ለራሱ የሚገባው ቃል ኪዳን ምንድን ነው?

## 6.3 የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች

- በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶ ችና ታሪካዊ ቅርሶች ዘርዝሩ::





*ሥዕል 6.2 የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል*

**የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች፣ ማለት በተፈጥሮ የሚገኙና ኅብረተሰቡ በኑሮ ሂደት የሚፈጥራቸው መለያዎቹ ናቸው::**

የአንድን ሕዝብ ማንነት የሚገልጹት እነዚህ ሀብቶችና ቅርሶች ለተለያዩ ጉዳቶችና ብክነቶች በመጋለጥ ላይ ይገኛሉ:: እነዚህ ሀብቶችና ቅርሶች ከብክነትና ከጥፋት መጠበቅ አለባቸው:: በየጊዜው እያደገ በመጣው የሕዝብ ቁጥር መጨመርና የከተሞች መስፋፋት የተነሳ ለቤቶችና ቁሳቁሶች መስሪያ እንዲሁም ለማገዶ አገልግሎት ሲባል ደኖች እየተጨፈጨፉ ከሚያሰጋ ደረጃ ላይ ደርሰዋል:: በተጨማሪም ለግል ጥቅምና ብልጽግና ሲባልም ሕገወጥ በሆነ አደን አራዊትን መግደል፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን ማውደም፣ ቅርሶችን መስረቅና መሸጥ በስፋት የሚታዩ ችግሮቻችን ናቸው:: ለተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች ብክነት መጉዳትና መዘረፍ ዋናዋናዎቹ ምክንያቶች:-

1. የትምህርት እጦትና የግንዛቤ ማነስ፣
2. ድህነትና ኋላቀር ኑሮ መኖር፣
3. ሀገራዊ ስሜት ማጣትና የግል ብልጽግናን ማስቀደም ናቸው::

እነዚህ እኩይ ተግባራት ሊከስሙ የሚችሉት በዋናነት በትምህርት የአስተሳሰብ ለውጥ ሲፈጠር ነው:: ለዚህም ት/ቤቶች ግንዛቤን በማዳበር በኩል ጠንካራ ሥራ ይጠበቅባቸዋል:: ከዚሁ በተጓዳኝም የመገናኛ ብዙሀን የጉዳዩን አሳሳቢነት ለሕብረተሰቡ በማሳወቅና በቀጥታ የሚመለከታቸው ተቋማትም ብሔራዊ ኃላፊነታቸውን በመወጣት የድርሻቸውን ማበርከት ይገባቸዋል::

ጥበቃውና እንክብካቤው የመንግሥት ወይም የአንድ ወገን ኃላፊነት ብቻ ተደርጐ መወሰድ የለበትም:: ጉዳዩ ሀገራዊ በመሆኑ የሁሉንም ርብርብ ይጠይቃል:: የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን ሕልውና መጠበቅ የራስን ጥቅምና ክብር እንዲሁም ታሪክን መጠበቅ መሆኑን በመገንዘብ ንብረቶቹንና ቅርሶቹን መጠበቅ የሁሉም የዜግነት ግዴታ መሆኑ መታወቅ አለበት::

**መልመጃ 5**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

1. የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን ስለመጠበቅ የብዙሀን መገናኛ ድርጅቶች ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል?
2. ስተፈጥሮ ሀብቶችና ቅርሶች ብክነት ወይም ጥፋት ምክንያቱ ምንድን ነው?
3. የተፈጥሮ ሀብቶችንና ቅርሶችን በመጠበቅ ረገድ ከዜጐች ምን አስተዋጽኦ ይጠበቃል?

## 6.4 ኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ




*ሥዕል 6.3 ልጃቸው በኤች አይ.ቭ/ኤድስ የሞተችባቸው እናት ሲለምኑ*

- ሥዕሉ ላይ የሚታዩትን አረጋዊት ኤች. አይ.ቪ../ ኤድስ የጐዳቸው እንዴት ነው?
- የታዘለው ሕጻን የወደፊት የሕይወት ዕጣው ምን ሊሆን ይችላል ?
- ራስን ከኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ መጠበቅ ጥቅሙ ለማን ነው?

ኤች. አይ.ቪ/ ኤድስ፣ ዕድሜና ጾታ፣ ዘርና ቀለም እንዲሁም የትምህርት ደረጃን ሳይለይ ያጠቃል:: የዚህ በሽታ መስፋፋት በዜጐችም ሆነ በሀገር ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ ላይ ነው:: በመሆኑም ሁሉም ሰው ይህን መፍትሔ ያልተገኘለትን በሽታ ለመከላከልና ለማጥፋት በሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉ ተሣትፎ በማድረግ የየበኩሉን ኃላፊነት መወጣት ይጠበቅበታል::

ማሕበራዊ ቀውስ በመፍጠር ላይ ያለው ይህ በሽታ ልጆችን ያለ ወላጅ፣ ወላጆችን ያለደጋፊና ጧሪ እያስቀረ መሆኑ በገሀድ እየታየ ነው:: ይህም በማሕበራዊ ኑሮ ሠላምና ደኅንነት ላይ አስፈሪ ጥላውን ጥሏል:: ያለሰብሳቢ የተበተኑ ህጻናት፣ ለምጽዋት እጆቻቸውን የሚዘረጉ አረጋውያንን ማየት የተለመደና እየጨመረ በመሄድ ላይ ያለ ክስተት ነው::

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በአሁኑ ወቅት በይበልጥ በማጥቃት ላይ ያለው ወጣቱን ነው:: የወጣቱ በዚህ በሽታ መጠቃት የአምራች ኃይል መቀነስን፣ የድህነት መባባስንና የኢኮኖሚ መቀጨጭን ያስከትላል:: ይህ አስደንጋጭ ሁኔታም በሀገራችን እየታየ ነው:: የልዩ ልዩ ሙያዎችና እውቀቶች ባለቤት የሆኑት ዜጐች በኤች.አይ.ቪ ሲጠቁ ሀገር እየተጐዳች ትሄዳለች::

አስተማማኙ የመከላከያ ዘዴ ከጋብቻ በፊት ወሲብ አለመፈፀም ነው:: ጋብቻንም በተረጋገጠ ምርመራ መመስረት ይገባል:: በሁለተኛ ደረጃም ከሌላ ሰው ደም ጋር ምንም ዓይነት ንክኪ እንዳይኖር መጠንቀቅ ነው:: ለዚህም ማንም ሰው በተጠቀመባቸው የስለት መሣሪያዎች አለ መጠቀም ያስፈልጋል::

“ሳይቃጠል በቅጠል” እንዲሉ ከዚህ ጠንቀኛ በሽታ ራስን መጠበቅ አማራጭ የማይሰጠው ተግባር ነው:: ይህም ለራስና ለሌሎች የመኖር ኃላፊነትን የመወጣት ክቡር የዜግነት ድርሻ ነው:: በዚሁ አኳያም፣ በአጋጣሚና ባለማወቅ በበሽታው የተያዙ ዜጐች የኅብረተሰቡ አካል በመሆናቸው ተገቢው ድጋፍና እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል:: በበሽታው ቢያዙም እነዚህ ወገኖች እንደማንኛውም ዜጋ በሙያቸውና በጉልበታቸው ለሀገር ዕድገት አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ስለሚገኙ የሞራልና የቁሳቁስ ድጋፎችን መስጠት ከሁሉም ዜጋ ይጠበቃል::

**መልመጃ 6**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩባቸው፡፡***

1. የምሁራንና ሙያተኞች በበሽታው መሞት በሀገር ደረጃ የሚያስከትለው ጉዳት ምንድን ነው?
2. ወጣቱ የኅብረተሰብ ክፍል ከዚህ ጠንቀኛ በሽታ ስመራቅ ምን ማድረግ አለበት?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የኃላፊነት ስሜት የዜግነት ድርሻውን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ድርጊትና ባህርይ ነው፡፡ ኃላፊነትን መወጣት፣ በቅንነትና በታማኝነት የግልም ሆነ የጋራ ተግባርን በማከናወን የሚገለጽ ቁም ነገር ነው፡፡ ልዩ ልዩ የሙያ ችሎታና የትምህርት ደረጃዎች እንዳሉ ሁሉ የኃላፊነት ዓይነቶችና ደረጃዎችም የተለያዩ ናቸው፡፡ ሆኖም በማንኛውም የኃላፊነት ደረጃ ላይ ያለ ዜጋ ተግባሩን በብቃት ካከናወነ ለኅብረተሰቡ የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡

ለራስና ለኅብረተሰብ ቃልኪዳን መግባት አንድን ተግባር ለማከናወን ወይም ላለማከናወን ቁርጠኝነትን መግለጽ ነው፡፡ ቃልኪዳን የቃል መተማመኛ ሲሆን ውጤቱ ተጨባጭ ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ ሁሉም ሰው እንደሙያውና ችሎታው ማኅበራዊ ለውጥ ለማምጣት ቃልኪዳን ሊገባና ይህንንም ቃልኪዳን በተግባር ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

በሌላም በኩል አንድ ዜጋ የሀገሩን ታሪክና ሀብት ጠንቅቆ ማወቅ እንዲችል በቂ ትምህርት መውሰድ አለበት፡፡ በመሆኑም በት/ቤት ሕይወት የሀገርን ሀብትና ታሪክ በሚገባ በመማርና በማወቅ የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች ከብክነትና ከጥፋት እንዲድኑ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ አለበት፡፡ የተፈጥሮ ሀብቶች፣ የሕይወትና የኑሮ መሠረቶች፣ ቅርሶችም የማንነት መገለጫና መግለጫ እሴቶች ናቸው፡፡ እነዚህን የሀገር ሀብቶች ማወቅ፣ ንዩኔን በሚል ስሜት መጠበቅና መንከባከብ፣ የሌሎችንም ንቃተ ህሊና በመቀየር ከጥፋት እንዲታቀቡ ማድረግ የዜግነት መብትና ግዴታ ነው፡፡

ከዚህ በበለጠ ጥንቃቄና ጥበቃ የሚያስፈልገው ደግሞ የዜጐች ጤናማ ሕልውና ነው፡፡ ሰው ተፈጥሮን በማልማትና በመቀየር ታሪክ መሥራት የሚችለው ጤናማ አቋምና ሞራል ሲኖረው ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የሰው ልጆች ፈተና ሆኖ የተጋረጠው ኤች.አይ.ቪ ኤድስ እየተዛመተና ጉዳት እያደረሰ በመሆኑ ሰለባ ላለመሆን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

| | |
|---|---|
| **የኃላፊነት ስሜት፣** | የዜግነት፣ የሙያ የማኅበራዊ ወዘተ. ኃላፊነቶችን ለመወጣት የሚያነሳሳ ፍላጐት፡፡ |
| **ኃላፊነትን መወጣት፣** | የዜግነት፣ የሞያ፣ የማኅበራዊ ወዘተ... ኃላፊነቶችን በውጤታማ የሥራ ክንውን መግለጽ፡፡ |
| **ትውስታ፣** | ያለፈ ሁኔታ፣ ታሪክ ወዘተ... ማስታወስ፡፡ |
| **የዜግነት ግዴታ፣** | የአንድ ሀገር ተወላጅ ለሀገሩ ዕድገትና ሕልውና የሚያከናውነው የግዴታ ወይም የውዴታ ፍሬያማ ተግባር |

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

***ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::***

## I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::

1. የኃላፊነት ስሜት ያለው ሰው የሥራ ድርሻውን በአግባቡ ያከናውናል::
2. ኃላፊነት ዓይነትና ደረጃ የለውም::
3. ቃልኪዳን የሚገባ ሰው አስቀድሞ አቅሙንና ችሎታውን ማገናዘብ አለበት::
4. የተፈጥሮ ሀብቶችንና የታሪካዊ ቅርሶችን ብክነት መጠበቅ ያለበት መንግሥት ብቻ ነው::
5. ራስን  ከኤች.አይ.ቪ. መጠበቅ ኃላፊነትን ከመወጣት ጋር ግንኙነት የለውም::

## II. በ “ለ” ሥር የተዘረዘሩትን በ “ሀ” ሥር ካሉት ሥር አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሚያስከትለው ችግር፣ | ሀ. ለወል ጥቅም የኅብረት ሥራ። |
| 2. ኃላፊነትን መወጣት፣ | ለ. የተናገረውን አፍራሽ። |
| 3. ሀቀኝነት፣ | ሐ. ወርቅ፣ ነዳጅ፣ ውሀ። |
| 4. የተፈጥሮ ሀብቶች፣ | መ. ሕክምና፣ ውትድርና፣ ግብርና፣ ዘበኝነት። |
| 5. ቃል አባይ፣ | ሠ. ውጤት ያለው ተግባር ማከናወን። |
| 6. የኃላፊነት ዓይነትና ደረጃዎች፣ | ረ. ጥሩ አገልግሎት መስጠት ወይም ተገቢ ውጤት ማሳየት። |
| 7. የጋራ ኃላፊነት፣ | ሰ. የኤኮኖሚ ድቀት። |

## III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::

1. የጋራ ኃላፊነትን መወጣት፤ ________
   ሀ. ሥራን ያጓትታል፣
   ለ. አጥጋቢ ውጤት የለውም፣
   ሐ. ለብዙዎች ጥቅም ይሰጣል፣
   መ. ጊዜ ያባክናል::
2. ዜጐች ሁሉ ኃላፊነት ቢኖርባቸውም፤ ________
   ሀ. እንደ ዕውቀትና ችሎታ ይለያያል፣
   ለ. ኃላፊነቶች ሁሉ እኩል ናቸው፣
   ሐ. ኃላፊነት በዕድሜ ይወሰናል፣
   መ. የማይመለከታቸው ዜጐች አሉ::

3. በት/ቤት አካባቢ ቃልኪዳንን ማክበር ማለት________ ማለት ነው፤
   ሀ. ለት/ቤት ድጋፍ የተስፋ ቃል መስጠት፣
   ለ. ከመማር ባሻገር ተሳትፎ አለማድረግ፣
   ሐ. በትምህርት ውጤታማ መሆንና በክበባት ተሳታፊ መሆን፣
   መ. በራስ መተማመንን ማዳበር፡፡

4. ታሪካዊ ቅርሶች፣ ________
   ሀ. የማንነት መገለጫ ናቸው፣ ሐ. የዘመን ማስረጃነት የላቸውም፣
   ለ. ለመዝናኛነት አያገለግሉም፣ መ. የገቢ ምንጭ አይሆኑም፡፡

5. ለተፈጥሮና ታሪካዊ ሀብቶች ብክነት ምክንያት የሚሆነው_________ ነው፤
   ሀ. የግንዛቤና የኃላፊነት ስሜት ማነስ፣ ሐ. በጥበቃ ሙያ አለመሰልጠን፣
   ለ. የቱሪዝም መስፋፋት፣ መ. የፓርክና ሙዚየም ማነስ፡፡

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ፡፡

1. ኃላፊነትን መወጣት_________________ ማክበር ነው፡፡
2. ራስን ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መጠበቅ_________________ መወጣት ነው፡፡
3. የማንነት መገለጫ የሆነና ከትውልድ የተላለፈ ሀብት__________ይባላል፡፡

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. ኃላፊነትን የመወጣት አስፈላጊነት ጥቅሙ ምንድን ነው?
2. የተፈጥሮ ሀብቶችን ማልማትና ቅርስን መጠበቅ የማን ሥራ ነው? እንዴት?
3. የብክነት መንስኤዎች ምን ምን ናቸው?

# ምዕራፍ ሰባት

# ጠንካራ የሥራ ባህል

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቂ/ ስታጠናቅቅ፤***

- ማንኛውም የሥራ መስክ መናቅ እንደሌለበት ትገነዘባለህ /ትገነዘቢያለሽ::
- የሥራንና የጊዜን ክቡርነት ትረዳለህ/ ትረጃለሽ::
- የሙያ ሥነ ምግባር ለምርታማነትና ለዕድገት መሠረት መሆኑን ትረዳለህ/ ትረጃለሽ::

## 7.1 የሥራ ባህልን ማዳበር

### 7.1.1 አንድ የሥራ መስክ ከሌላው የማያንስ መሆኑን ማመን

- አንድ ሥራ ከሌላው የማያንስ መሆኑን በምሣሌ አስረዱ::
- "ማንኛውንም ሥራ ሁሉ እኩል ማክበር አለብን" ሲባል ምንን ለመግለፅ ነው?

### የእንጨት ጥበብ፤

አምሳሉና አስማማው በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ መንግሥት በአሶሳ ከተማ የሚኖሩ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው:: እነዚህ ጓደኛሞች ሠፈራቸው ቅርብ ለቅርብ ስለሆነ እየተገናኙ ትም ህርታቸውን በጋራ ያጠናሉ:: ተስማምተው የዕ ረፍት ጊዜያቸውን በመወሰን ይጫወታሉ፣ ስለ ወደፊት ፍላጎታቸውም ይወያያሉ:: አምሳሉ ወደ ፊት የዕደ ጥበብ ባለሙያ አስማማው ደግሞ የዕ ፀዋት ምርምር ባለሙያ የመሆን ምኞት አላቸው::

አስማማው ሁልጊዜ ወደነአምሳሉ ቤት ለጥናት በሔደ ቁጥር ልዩ ደስታን ከሚሰጡት ትዕ ይንቶች አንዱ የአምሳሉ አባትና እናት በከፍተኛ ጥንቃቄና ጥበብ በጋራ የሚሠሯቸው የእንጨት ውጤቶች ነበሩ:: የአምሳሉ አባት እንጨቶችን እያለሰለሱ ሲያቀርቡ እናቱ ደግሞ በመፈልፈያ እየታገዙ በመቦርቦር የታሰቡትን ዕቃዎች ቅርፅ ቁልጭ አድርገው ያወጡ ነበር::

አስማማው በዕረፍት ጊዜው ስለጓደኛው እናትና አባት የእጅ ጥበብ በጣም በመደነቅ ቅርፅ መሽጫ ሱቁና በሳጠራ ዳስ ውስጥ የተደረደሩትን ዕቃ ዎች እየተዘዋወረ ይጎበኝ ነበር:: በጉብኝቱ ወቅት ዓይኑን ከሚስቡት የባህል ዕቃዎች መካከል የሙ ዚቃ መሣሪያዎች ማለትም ክራር፣ ማሲንቆ፣ በገና የመሳሰሉት ሲሆኑ ከታሪካዊ ቅርሳቅርሶች ደግሞ የጎንደር ፋሲለደስ ቤተመንግሥት፣ የአክ ሱም ሐውልትና ሌሎችም ይገኙበታል::

አስማማው በሕብረተሰብ ሳይንስ ትምህርቱ ውስጥ ስለ እነዚህ የሀገር ቅርሶች ታሪክ በማስታወስ ወደፊት ይህን ጥበብ ለመማር ፍላጎት አደረበት:: በዚህም የአምሳሉን አባት ስለዚህ ጥበብ እንዲ ያስተምሩት በጠየቃቸው መሠረት እሱን ብቻ ሳይሆን አምሳሉንና ሌሎች ጓደኞቹን ጨምረው ለማሠልጠን ፈቃደኛ ሆኑ:: አስማማው የእን ጨት ሥራ ዝቅተኛ ሙያ ነው ብሎ ሳይንቅ ለሥልጠና ራሱን በማዘጋጀቱ የአምሳሉ አባት ጠንካራ መንፈሱን አደነቁለት::

አስማማውና ጓደኞቹ ሥልጠናውን በማጠናቀቅ ከአምሳሉ ቤተሰብ ጋር ይህን የእንጨት ጥበብ ኢንዱስትሪ በአካባቢው ለማስፋፋት ዕቅድ አው ጥተው ከፍተኛ እንቅስቃሴ አደረጉ:: ከቀላል ሥራ የተነሱት እነአስማማው ከዓመታት በኋላ የአካባቢውን ዷሪ በዘመናዊ የእንጨት ጥበብ ማሠልጠን ጀመሩ:: የእንጨት ጥበብ ኢንዱስ ትሪም በጋምቤላ አካባቢ ለመስፋፋት ቻለ::

**መልመጃ 1**

***በምንባቡ መሠረት ለተከታዮቹ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፣***

?

1. አስማማው ወደ እንጨት ሥራ ጥበብ እን ዴት ሊገባ ቻለ?
2. የአምሳሉ አባት አስማማውን ያመሰገኑት በምን ምክንያት ነው?
3. በታሪኩ ውስጥ አንድ ሥራ በሴትም ሆነ በወንድ ሲሠራ መቻሉን የሚያስገነዝበው ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው? በደብተራችሁ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አንብቡላቸው::

አንድ የሥራ መስክ ከሌላው የማያንስ መሆኑን ማመን ስንል የማንኛውም ሥራ ዓላማና ግብ ራስን ከማስቻል አልፎ የሀገርን ልማት የማፋጠን ድርሻ ያለው መሆኑን ለማስገንዘብ ነው:: አንድ ሰው የአንድ የሥራ ዘርፍ ዝንባሌ እያለው በአጋጣሚም ይሁን በሥልጠና ባገኘው ችሎታ ምክንያት ወደ ሌላ ሥራ ሊሠማራ ይችላል::

በዚህ ሁኔታ ሁሉም ሠራተኞች በትክክል ሥራቸውን አክብረው ከሠሩ ራሳቸውን ከመጥቀም ባሻገር ሀገርንና ወገንን በእኩል የሚጠቅም ተግባር አከናወኑ ማለት ነው::

ስለዚህ እያንዳንዱ ዜጋ ሥራን ትንሽ ወይም ትልቅ ነው ብሎ ልዩነት ሳያደርግ ሥራን በማክበርና ጊዜን በአግባቡ በመጠቀም ሀገርና ወገን የሚጠብቁበትን የልማት አስተዋፆ ማበርከት አለበት::

**መልመጃ 2**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብቡና አጫጭር መልስ ስጡ፣***

1. የሥራ ትንሽ/ትልቅ የለውም የሚባለው ለምን ይመስላችኋል?
2. ሁሉም የሥራ ዓይነት ለሀገር ልማት ድርሻ ያለው መሆኑ በምን በምን ይገለፃል?
3. ካየሥራ ትንሽ/ትልቅ የለውም ሲባል የሥራ ልዩነት የለም ማለት አይደለምካ ይህን ሀሳብ በክፍል ውስጥ አንስታችሁ በቡድን ተወያዩ በት::



*ሥዕል 7.1 የተራቆተ መሬትን ደን የማልበስ ተግባር*

- ከሥዕሉ ምን ተገነዘባችሁ?
- ከዚህ በፊት በችግኝ ተከላ ተሳትፋችሁ ከሆነ ሒደቱን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው::
- ዛፍ በመትከል ስለሚገኙ ዋና ዋና ጥቅሞች አስረዱ::

## ዳገታማ ቀበሌ፤

ዳገታማ ቀበሌ በመተከል ዞን በቻግኒ ከተማ አዋሳኝ የሚገኝ ለምለምና ተራራማ የገጠር መንደር ነበር:: ቀበሌው በደን ሽፋን ከሚታወቁት የዞኑ ለም አካባቢዎች አንዱ ስለነበር ነዋሪው የዝናብ እጥረት አጋጥሞት አያውቅም:: ይህ ልምላሜ ግን እንዳለ ሊቀጥል አልቻለም:: ብዙዎቹ የአካባቢው ኗሪዎች የመንደራቸውን ለምነት እንዳለ ለማቆየት ጥረት ቢያደርጉም ለአካባቢው ደህንነት በማይጨነቁ ጥቂት ግለሰቦች በየጊዜው ዛፎች በመቆረጣቸው ደኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነ፣ የነበረው ልምላሜ እየቀነሰ ለም አፈሩም በውሃ እየታጠበ ሄደ::

ከሰላሣ ዓመት በፊት የዳገታማን ቀበሌ የመሬት ለምነትና ጥቅጥቅ ያለ ደን የሚያውቅ ሰው ዛሬ ተመልሶ አካባቢውን ቢመለከት እሳተ ገሞራ ያነደደው እስኪመስለው ድረስ ደኑ ተመናምኖና የአካባቢው ውበት ተገፎ ማየቱ እጅግ ሊያሳዝነው ይችላል:: ይህ ሁኔታ በዚህ እንዳይቀጥል ለማድረግ አስቸኳይ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ መሆኑን ነዋሪው ለመንግሥት አሳሰበ:: በዚህም መሠረት ዳገታማ ቀበሌን እንደገና በደን ለመሸፈን ምቹ በሆኑ አካባቢዎች የችግኝ ማፍያ ጣቢያዎች እንዲቋቋሙ ተደረገ::

የቀበሌው ሕዝብ ራሱን በቡድን በማደራጀት የሚሠራበትን የጊዜ ሠሌዳ በማውጣትና ራሱን ለእቅዱ ተግባራዊነት በማዘጋጀት ከመንግሥት ጋር ተቀናጅቶ በባለሙያ የታገዘ የችግኝ ተከላ ኘሮግራም አካሄደ:: የዳገታማን ልምላሜ እንደገና ለመመለስ ሕዝቡ በፍላጎትና በቁርጠኝነት ተንቀሳቀሰ:: የዝናብ ጊዜው ሳያልፍ የተራራው አናትና ግርጌ በዛፍ ችግኞች ተሸፈኑ::

ችግኞቹ በሚገባ ሥር እስኪይዙ ድረስም በፈረቃ በመጠበቅና በመንከባከብ ሁሉም በተሰጠው የጊዜ ሠንጠረዥ የሚጠበቅበትን ድርሻ ተወጣ:: ዘንድሮ ማንም በመንደሩ የሚያልፍ ሰው የዳገታማ ቀበሌን ልምላሜ በርቀት ሊመለከት ይችላል:: አሁን በተራራው አናትና ግርጌ የበቀሉት ሀገር በቀል ዛፎችና ቁጥቋጦዎች፣ በተራራው ሥር የሚፈሰው የምንጭ ውሃና በረባዳው መስክ የበቀሉት እፀዋት ለሰውም ሆነ ለእንስሳት ምቹ መሆን ጀምረዋል::

**መልመጃ 3**

*በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄ ዎችን መልሱ፡፡*

?

1. ከላይ ከቀረበው ታሪክ የጊዜ፣ የሥራና የልማት ግንኙነት በምን ሁኔታ ተገለፀ? በቡድን እየሆናችሁ ተወያዩ፡፡
2. የዳገታማ ቀበሌ ነዋሪዎች አሳሳቢ ችግር እንዴት ተፈታ?
3. አካባቢን በለምነት ጠብቆ ለማቆየት ሲደረጉ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎች ከጊዜ ጋር በማያያዝ ግለፁ፡፡

የጊዜ፣ የሥራና የልማት ግንኙነት በዕቅድና በዓ
ላማ ሲመራ አጥጋቢ ውጤት ያስገኛል፡፡ ጊዜ
የሰው ልጆች በተፈጥሮ የታደሉትና ገንዘብ የማ
ይከፍሉበት ሃብት ሲሆን ያለ አድልዎ ለሁሉም
ሰዎች በዕኩል የሚያገለግልና የማያቋርጥ የዕ
ድሜ ፍሰት ነው፡፡

ማንም ሰው ያለማንም ከልካይ ከሚያዝባቸው
ነፃ ሀብቶች መካከል አንዱ ጊዜ ሲሆን ሁሉም
በፈለገው ሁኔታ ሊጠቀምበት የሚችል በእጅ
ያለ ሀብት ነው፡፡ ሰው እንደ አካባቢውና እንደ
ወቅቶች ሁኔታ ጊዜን በመከፋፈል ለሥራ፣ ለዕ
ረፍትና ለመኝታ በሚል ይጠቀምበታል፡፡

"የአንድ ሀገር ዕድገት የሚወሰነው ሕዝቡ ለጊዜ
በሚሰጠው ግምትና አጠቃቀም ነው" የሚል የአ
ዋቂዎች አባባል አለ፡፡ ይህ በእርግጥም ሁሉንም
ሊያስማማ የሚችል ሃሳብ ነው፡፡ የጊዜን ክቡ
ርነት የተረዳ ሕብረተሰብ በጊዜ ተጠቅሞ ራሱን
ለመለወጥና ሀገሩን ለማልማት በቂ አቅም ይኖ
ረዋል፡፡

**መልመጃ 4**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

?

1. አንድ ተማሪ የጊዜ ዕቅድ ማውጣት አለ በት የሚባለው ስምንድን ነወ?
2. የጊዜና የሀገር ልማት ግንኙነት እንዴት ይገለፃል?
3. አንድ ዜጋ ጊዜን በአግባቡ ካልተጠቀመ የሀገርን ልማት የሚጎዳው እንዴት ነው?

## 7.1.2 የግልና የጋራ ሥራዎችን በሁሉም ሥፍራ በወቅቱና በጥራት ማከናወን



*ሥዕል 7.2 ሥራን በጋራ መሥራት ውጤታማ ያደርጋል*

- በሥዕሉ ላይ የሚታዩት ሰዎች ምን እየሰሩ ነው?
- የግል የሥራ ጥረት በጋራ ውጤት ላይ ምን አስተዋፅኦ አለው?

### ሥራና ጊዜ፤

ወ/ሮ አንበሴ የዕድገት በሕብረት የመጀመሪያ
ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህርት ሲሆኑ
በአስተዳደር ሥራቸውና በጊዜ አጠቃ ቀማቸው
አንቱ የተባሉ ናቸው፡፡ በግልና በቡድን ሥራ
የሚያምኑት ርዕሰ መምህርቷ ከሌሎች
መምህራንና ሠራተኞች ጋር በመሆን በትም
ህርት ቤቱ ለውጥ ለማምጣት ጠንክረው በመሥ
ራት ላይ ናቸው፡፡ ለጊዜ አጠቃቀም ከፍተኛ
ትኩረት ስለሚሰጡ አንድን ሥራ ከተመደበለት
ዕቅድና ጊዜ ቀድሞ መጨረስ የትምህርት ቤቱ
ባህልና መታወቂያ ከሆነ ቆይቷል፡፡

በጊዜ ሠሌዳው መሠረት ትምህርት ቤቱ የአ
ንደኛ መንፈቀ ዓመት የትምህርት በዓል የማክ
በሪያ ጊዜው ስለደረሰ ሁሉም በልዩ ልዩ የሥራ
ቡድኖች ተመድበው መንቀሳቀስ ጀምረዋል፡፡ የስ
ፖርት፣ የድራማ፣ የሥነ ፅሑፍ፣ የሠርቶ ማሳያ፣
የልጃገረዶች፣ የሙዚቃ ክበብ፣ የሽልማት ወ.ዘ.ተ
ሁሉም የሥራ ቡድኖች ዕለቱን ለማድመቅ ዝግ
ጅቶች እያደረጉ ናቸው፡፡

በዕለቱ ከአጎራባች ትምህርት ቤቶች፣ ከአካባቢው
ታዋቂ ግለሰቦች፣ ከወጣትና ከሴቶች ማህበራት

እንግዶች እንደሚገኙ ይጠበቃል:: ወ/ሮ አንበሴ በጋራ የተደረሰባቸውን ውጤቶችና ቀሪ ሥራ ዎችን ለመገምገም ስብሰባ በጠሩበት ወቅት ያረጋ ገጡት የሚከተለውን ነበር::

ይህም በግል የተሰጠን ኃላፊነት መወጣት ማለት ለጋራ ሥራ በጊዜ መከናወን መሠረት መሆኑን ነው:: በአሁኑ ወቅት የዕድገት በሕብረት ትምህ ርት ቤት መምህራንና ተማሪዎች በወጣው የጊዜ ሠሌዳ ተጠቅመው ዝግጅቱን በመልካም ሁኔታ ለማክበር በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ይገኛሉ::

**መልመጃ 5**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

?

1. የግል ሥራ በጋራ ሥራ ላይ ያለው ተፅዕኖ ምንድን ነው?
2. የግልንም ሆነ የጋራ ሥራን በወቅትና በጥራት ማከናወን ምን ጥቅም ይሰጣል?
3. ተማሪዎች በጋራ ሲሠሯቸው የሚችሏቸው ሥራዎች ምን ምን ናቸው? ሁለት ምሣሌ ስጡ::

የግልና የጋራ ሥራዎችን በሁሉም ሥፍራ በወ ቅቱና በጥራት ማከናወን ማለት ኃላፊነትን መወ ጣት ማለት ነው:: የማንኛውም ሥራ ውጤቱ የሚለካው በሥራ ጥራቱ ብቻ ሳይሆን በተያዘ ለት ጊዜ ውስጥ መጠናቀቁ ጭምር ነው::

በሥራ ሂደት ውስጥ የግል ሥራ በጋራ/በቡድን/ ሥራ ውጤት ላይ ከፍተኛ ድርሻ ያለው ሲሆን የግልንም ሆነ የጋራ ሥራን በወቅቱና በጥራት መሥራት ለሀገር ልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው::

ሥራ በግልም ሆነ በጋራ በወቅቱና በጥራት ሲሠራ የባለሙያውም ሆነ የመላው ሕዝብ ሕይ ወት ይሻሻላል:: ጊዜን በአግባቡ በመጠቀም ሥራን በወቅትና በጥራት የማከናወን ሌላው ጠቀሜታ ለሀገር ልማትና ለኢኮኖሚ እድገት የሚጫወተው ሚና ነው:: ሥራ የሁሉንም ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ማሕበራዊ እንቅስቃሴ ስለ ሆነ የግልና የጋራ ሥራዎችን በሁሉም የሥራ ቦታ በወቅቱ ማከናወን ጥራት ላለው ውጤት ያበቃል::

ሥራን በመጠንም ሆነ በጥራት የማከናወን ውጤት የሚመዘነው ያንን ምርት ለማምረት በፈጀው ጊዜና በተገኘው የምርት መጠን ነው:: አንድን ሥራ ከታቀደለት ባነሰ ጊዜ ማከናወን ማለት ራስን ለሌላ ተጨማሪ ሥራ ማዘጋጀት ማለት ስለሆነ ውጤታማነትን ማሳደግ ነው:: ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በግልም ሆነ በጋራ የምንሠራው ሥራ ውጤታማ ነው ለማለት በወ ቅትና በጥራት የተገኘ ምርት ሊኖር ይገባል::

ይህ ተግባራዊ እንዲሆን እያንዳንዱ ሠራተኛ ለሥራው ተገቢውን ትኩረት መስጠት ይኖር በታል:: ይህም ለሀገር ልማትና እድገት መሠ ረት ይሆናል::

**መልመጃ 6**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

?

1. አንድ ሥራ ውጤታማ ነው የሚባለው በምን በምን ምክንያት ነው?
2. የሥራ ውጤታማነት መመዘኛው ባነሰ ጊዜ ጥራት ያለው ምርት ማከናወን ነው የተ ባለው ለምን ይመስላችኋል?

## 7.2 ሳይሠሩ መኖር

### 7.2.1 ሳይሠሩ መኖር የኢኮኖሚ፣ የልማትና የዕድገት ፀር ነው

ከነውርም ነውር የልማት ጠላት፣
ሁልጊዜም ፀያፍ ነው ሳይሠሩ መብላት::

- ሳይሠሩ መብላት ፀያፍ የተባለው በምን ምክንያት ነው? ምክንያቶቹን ግለጹ?
- በግጥሙ መሠረት የልማት ጠላት የተ ባለው ምንድን ነው?

**ሰነፏ ልጅ፤**

ጻዲ ሥራ አትወድም። ሳትሠራ መኖር የምት ፈልግ ሰነፍ ልጅ ናት:: በቤት ውስጥም ሆነ በትምህርት ቤት ይህ የስንፍና ባህሪዋ እያደር እየባሰባት በመምጣቱ ቤተሰቧንና ትምህርት ቤ ቷን በጣም አሳስቧቸዋል:: የማይሠራ ሰው በማ ህበረሰቡ ዘንድ የተወገዘና የሌሎች ጥገኛ በመ ሆን ለሀገሩ ልማትና ዕድገት ፀር ሆኖ ስለ ሚቆጠር ከዚህ አደገኛ ባህሪ እንድትወጣ በተ ለይ አባቷ ከፍተኛ ጥረት አደረጉ::

ጻዲ ሥራ ባለመውደዷ የተነሳ የአደገኛ ሱስና የኀጺ ልማድ ሰለባ እንዳትሆንም መፍትሔ

ያሏቸውን ነገሮች ሁሉ ማሰላሰል ጀመሩ፡፡ በዚህም መሠረት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በግቢአቸው ውስጥ በጀመሩት የዶሮ ዕርባታ ሥራ ውስጥ ዳዲን ቀስ በቀስ ለመሳብ ያደረጉት ጥረት ሰመረላቸው፡፡

አንድ ቀዳሜ ጠዋት ዳዲን ጠርተው ዶሮዎቹ የጣሉትን እንቁላሎች እንድትሰበስብና እንድትቆጥር ኃላፊነት ሰጧት፡፡ እሷም ጥቂት በማቅማማት የተባለችውን አደረገች፡፡ በሁለተኛው ቀን ያዘዟትን ሥራ በተሻለ ስሜት ፈፀመች፡፡ ዳዲ ትናንትትናና ዛሬ የሠራችው ሥራ መልካም ስሜትን እንደፈጠረላት አስተዋለች፡፡

በሦስተኛው ቀን አስታዋሽ ሳያስፈልጋት በቀጥታ የዶሮዎቹን እንቁላሎች ከሰበሰበች በኋላ የማደሪያ ክፍላቸውን አፀዳች፡፡ ከዚያም አባቷን ጠርታ የጥናትና የመዝናኛ ጊዜ በመመደብ ኘሮግራም እንዲያወጡላት ጠየቀቻቸው፡፡ በሥራ ኘሮግራሟ ውስጥ በተለይ ለዶሮዎች ምግብና ውሃ መስጠትን፣ እንቁላሎቻቸውን ድመት እንዳይበላባቸው መሰብሰብን፣ እናት ዶሮዎችን ማስታቀፍንና አዳዲስ ጫጩቶችን አስፈልፍሎ መንከባከብን እንደመዝናኛም ቆጠረችው፣ እንዲሁም እንቁላሎችን ለነጋዴዎች ቆጥራ ማስረከብንና ሂሳቡን አስልቶ ለአባቷ ማሳወቅን እንደ አንድ የእለት ሥራዋ በመውሰድ ማከናወን ጀመረች፡፡

እናትና አባቷ በልጃቸው ለውጥ ከፍተኛ ደስታ ተሰማቸው፡፡ ዳዲ ሥራ ምን ያህል የመንፈስ ነፃነትንና በራስ የመተማመን ስሜትን እንደሚፈጥር በተጨባጭ እያረጋገጠች መጣች፡፡ ቀስ በቀስ ከሥራጠል ባህሪዋ ራሷን በማውጣት ኀበዝ ተማሪና ታታሪ ሠራተኛ ለመሆን ቻለች፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ባመጣችው የባህሪ ለውጥ ቤተሰቧ ብቻ ሳይሆን የክፍል ጓደኞቿና መምህራኖቿም ጭምር እጅግ ተደነቁ፡፡

**መልመጃ 7**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. ዳዲ በራስ የመተማመንን ስሜት ለማዳበር የቻለችው እንዴት ነበር?
2. ዳዲ ከሥራ ጠል ባህሪዋ እንድትላቀቅ የረዷትን ሁኔታዎች ዘርዝሩ፡፡
3. ሳይሠሩ መኖር የልማትና የዕድገት ፀር ነው የሚለውን የመወያያ ሃሳብ ይዛችሁ አንድ ባለሙያ በመጋበዝ ውይይት አድርጉ፡፡

ሳይሠሩ መኖር የኢኮኖሚ፣ የልማትና የዕድገት ፀር መሆኑን ለማጉላት ብዙ ሰዎች "የማይሠራ አይብላ" የሚል ጠንካራ አባባል ሲሰነዝሩ ይሰማል፡፡ ይህ ዕውነትና ትክክለኛ አባባል ነው፡፡ መሥራት የሚችል አቅም እያለው የማይሠራ ሰው መብላት የለበትም፡፡ ሥራ መንፈሰ ጠንካራ የመሆንና በተሻለ ሕይወት የመኖር ዋስትናን የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ የሰው ልጅ አዕምሮም ሆነ አካል ሊዳብር የሚችለው እጆች ለሥራ ሲዘረጉ ብቻ ነው፡፡ ሰው በሠራ ቁጥር የራሱንም ሆነ የሌሎችን ሕይወት ለመለወጥ አቅም ያገኛል፡፡ ሳይሠሩ መኖር የሚጎዳው ራስን ብቻ ሳይሆን ቤተሰብን፣ ሕዝብንና ሀገርን ጭምር ነው፡፡

ሳይሰሩ መብላትን በመፀየፍ ሁሉም ዜጎች ኑሮአቸውን በሥራ ለመለወጥ ጠንክረው ቢሠሩ የሕዝቡ ኑሮ ወደተሻለ ደረጃ ይሸጋገራል፡፡ ይህ ሂደት ጠንካራ የሥራ ባህል አስተማማኝ መሠረት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ሕዝብ በሥራ አደገ ማለት ደግሞ የሀገር ዕድገትና ልማት ባስተማማኝ ሁኔታ ተረጋገጠ ማለት ነው፡፡

**መልመጃ 8**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. የግለሰቦች ጠንክሮ መሥራት ከሕዝብና ከሀገር ልማት ጋር የሚያያዝባቸውን ሁኔታዎች አብራሩ፡፡
2. ከመምህራችሁ ጋር ተነጋግራችሁ ሳይሠሩ መኖርን ስለመፀየፍ በትምህርት ቤታችሁ አንድ መድረክ በማዘጋጀት መምህራንና ተማሪዎችን በጋራ አወያዩ፡፡

## 7.2.2 በኢ.ፌ.ዴሪ ሕገ መንግሥት የተደነገጉ የኢኮኖሚ መብቶች፣

- *በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የኢኮኖሚ መብቶችን ማስቀመጥ ለምን አስፈለገ?*

### ታታሪዋ አርብቶ አደር፤

ወ/ሮ ሐዋ አብደላ ከአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በጠንካራ ሠራተኝነታቸው ለሜዳሊያ ሽልማት ከበቁት አርብቶ አደሮች አንዷ ናት:: ከዛሬ ሦስት ዓመት በፊት በእንስሳት ዕርባታ ላይ ብቻ ተሰማርታ የቆየችው ይህች አርብቶ አደር ስለ ግብርና ትምህርት በልማት ጣቢያ ሠራተኞች አማካኝነት በቂ ግንዛቤ ካገኘች በኋላ ከከብት ዕርባታ በተጨማሪ አንድ ሄክታር መሬት ተቀብላ በማልማት ከፍተኛ ምርት አስመዘገበች በተሰጣት መሬት ላይ የተለያዩ አትክልቶችንና የፍራፍሬ ምርቶችን እንዲሁም ለከብቶቿ የሚሆን መኖ አመረተች:: በዚህም ጥሩ የገቢ ምንጭ ፈጠረች::

ከዚሁ ሥራዋ ጎን ለጎን ወደ ንግዱ ዓለም ለመግባት ባቀደችው መሠረት ለዚሁ አገልግሎት የሚውል ባለ ሁለት ክፍል ቤት በአሳይታ ከተማ በማስገንባት ላይ ናት::

*ምንጭ:-አዲስ ዘመን የካቲት 8/2000 ዓ.ም*

**መልመጃ 9**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

?

1. **ወ/ሮ ሐዋ አሁን ሳለችበት የተሻለ ሕይወት ያበቃት ምንድን ነው?**
2. **እንደ ወ/ሮ ሐዋ ያሉትን ጠንካራ ሠራተኞች ለሽልማት ማብቃት ምን ጥቅም አለው?**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት የተደነገጉት የኢኮኖሚ ነክ መብቶች ዋና ትኩረት የሕዝቡን መሠረታዊ ጓቁፌቶች በእኩልነት ላይ ተመሥርቶ ማሟላትና የሀገሪቱን ዕድገትና ብልጽግና ማረጋገጥ ነው:: ስለሆነም ሀገራችን የምታራምደው የልማትና የኢኮኖሚ ነክ ዓላማ ሕዝቦች በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆኑበትን፣ ከተመፅዋችነት የሚላቀቁበትንና ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በማረጋገጥ በሀገራችን የዳበረ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ የሚስፍንበትን ሥርዓት መገንባት ነው::

ነፃ የኢኮኖሚ ሥርዓት ማለት ዜጎች በሀገራቸው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ በሚፈልጉት የሥራ ዘርፍ የሚሠማሩበትና በሕብረተሰቡ ፍላጎትና በምርት አቅርቦት ላይ የተመሠረተ የገበያ ሥርዓት ማለት ነው። በኢፌዴሪ ሕገመንግሥት በግልጽ እንደተቀመጠው የዜጎችን ዕድገትና መሠረታዊ ፍላጎቶች በእኩልነት ለማሟላት በሕገመንግሥቱ የተደነገጉት የኢኮኖሚ መብቶች መረጋገጥ አለባቸው።

ሕገመንግሥቱ በአንቀጽ 41 “የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባሕል መብቶች” በሚለው ሥር የሚከተሉትን የኢኮኖሚ መብቶች ደንግጓል፤

- ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመሥራት መብት አለው፣
- ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያውን፣ ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው፣ መንግሥት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል፤ እንዲሁም በሚያካሂዳቸው የሥራ ዘርፎች ውስጥ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ኘሮግራሞችን ያወጣል፣ ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል፣
- መንግሥት ዜጎች ተጠቃሚ ሥራ የማግኘት ዕድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል::

እነዚህን የኢኮኖሚ መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የግብርና ኢኮኖሚን ማዕከል ያደረገ የልማት እንቅስቃሴ እየተካሄደ ሲሆን በሌሎች የሥራ ዘርፎችም ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል::

ከላይ የተጠቀሱትን የኢኮኖሚ መብቶች በግልፅ በማስቀመጥ ለውጤታማነታቸው ድጋፍ ከማድረግ ባሻገር እስካሁን የገጠሩ ሰፊ አርሶ አደር፣ አርብቶ አደርና የሠራተኛው ሕይወት እንዲሻሻል ልዩ ልዩ እርምጃዎች ተወስደዋል:: ገበሬዎችን፣ አርብቶ አደሮችንና ኢንቨስተሮችን ለማበረታታት ልዩ ልዩ ሽልማቶች ተበርክተዋል:: እነዚህ ሽልማቶች ሌሎች ገበሬዎችን፣ አርብቶ አደሮችንና ኢንቨስተሮችን ለተመሳሳይ ውጤት እንዲበቁ በማትጋት በኩል ከፍተኛ ድርሻ ይኖራቸዋል::

**መልመጃ 10**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩባቸው፡፡***

1. በሀገራችን ፈጣን ዕድገት ሊመጣ የሚችለው እንዴት ነው?
2. የሀገራችንን የኢኮኖሚ እድገት ለማረጋገጥ ከእያንዳንዱ ዜጋ ምን ይጠበቃል?

## 7.3 የሙያ ችሎታና ሥነምግባር

### 7.3.1 የሙያ ችሎታንና ሥነምግባርን ማሳደግ ምርታማነትን ከማሳደግ ጋር ያላቸው ግንኙነት

- *ሙያ ምንድነው? የሙያ ሥነምግባርስ?*

**እንዶድ የሣሙና ፋብሪካ፣**

*ያደኒ የምትሠራበት የእንዶድ ሣሙና ፋብሪካ በናዝሬት ከተማ ሰፊ ሕዝባዊ አገልግሎት ከሚሠጡ ፋብሪካዎች ቀዳሚው ነው፡፡ ያደኒ በፋብሪካው ከተቀጠረች 16 ዓመት ያሳለፈች ሲሆን ትጉህና ሥራ ወዳድ መሆኗን እንኳን ሠራተኛው ተጠቃሚው ሕብረተሰብም ያውቀዋል፡፡*

*የፋብሪካው ሠራተኞች ምርታማነታቸውን ከፍ በማድረግ የፋብሪካውን ገቢ በእጥፍ ለማሳደግ በወሰኑበት ጊዜ ሃሳቡን ከደገፉት ሠራተኞች መካከል ያደኒ አንዷ ነበረች፡፡ የምርት ሽያጭ ክፍል ኃላፊ የሆነችው ያደኒ መልካም ሥነምግባርን በመላበስ በጊዜ አጠቃቀም፣ ደንበኞችን በማስተናገድ ከሁሉም ጋር ተግባብቶ በመሥራት የተመሰገነች ሠራተኛ ናት፡፡*

*በእዚህ ፋብሪካ ሥራዋን የጀመረችው በቢሮ ፅዳት የነበረ ሲሆን ዕውቀቷን በማሳደግ ከአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ በንግድ ሥራ አመራር ዲኘሎማ ካገኘች ወዲህ ደረጃ በደረጃ ለዚህ የሙያ ብቃትና የኃላፊነት ቦታ በቅታለች፡፡ ድካምና መሰላቸትን የማታውቀው ያደኒ በትምህርት ያገኘችውን ሙያና ችሎታ በልምድ በማዳበር ፋብሪካው በውስጥም ሆነ በውጭ ያለው የንግድ እንቅስቃሴ በመልካም ሁኔታ ላይ እንዲገኝና ምርታማነቱ ከፍ እንዲል ትልቅ ሚና ተጫውታለች፡፡*

*የፋብሪካው የሙያ ማሕበር ሥራ አመራር አባል ሆና እንድትሠራ በሠራተኛው ሙሉ ድምፅ ከተመረጠች በኋላም የፋብሪካው የሥራ አመራርና ሠራተኞች የሥራ ችሎታንና የሙያ ሥነምግባርን ተላብሰው ተጠቃሚውን ሕዝብ በቅንነትና በታማኝነት እንዲያገለግሉ በማስተማር ላይ ትገኛለች፡፡*

**መልመጃ 11**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. የእንዶድ ፋብሪካ የምርት ውጤታማነት ምክንያት ምንድን ነው?
2. ያደኒን ለከፍተኛ ኃላፊነት ያበቃትን የሙያ ሥነምግባር ዘርዝሩ፡፡
3. ሕዝብን የሚያገለግል ባለሙያ የሙያ ሥነምግባር የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

*የሙያ ችሎታንና ሥነምግባርን ማሳደግ ምርታማነት መሠረት ነው፡፡ እንደሚታወቀው ሙያ አንድን ሥራ ለማከናወን በረጅም ጊዜ ልምድ ወይም በሥልጠና የሚገኝ ችሎታ ሲሆን የሙያ ሥነምግባር ደግሞ ሙያው ከሞያተኛው የሚፈልገው ባሕሪና ዝንባሌ ነው፡፡*

*ሰዎች እንደፍላጎታቸውና ዝንባሌአቸው በተለያየ ሙያ ላይ ይሰማራሉ፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች እንደተሰማሩበት የሥራ መስክ ሙያው የሚጠይቃቸው ሥነምግባሮች አሉ፡፡ የሙያ ሥነምግባር ማለት እያንዳንዱ ባለሙያ ተጠቃሚውን ለማገልገል አስቀድሞ መላበስ ያለበት የአገልግሎት አሰጣጥ ባህሪ ነው፡፡ ለምሣሌ ከመምህራን የሚጠበቅ የሙያ ሥነ ምግባር አለ፣ ከሕክምና አዋቂም የሚጠበቅ የሙያ ሥነ ምግባር አለ፡፡*

*ይሁን እንጂ ቅንነት፣ ታማኝነት፣ ታታሪነትና፣ ሰዓት አክባሪነት በሁሉም ባለሙያዎች ዘንድ ሊኖሩ የሚገቡ የመልካም ሥነምግባር መገለጫዎች ናቸው፡፡ ሙያና ሥነምግባር የማይነጣጠሉ የሙያ ብቃት ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡ ሥራ ሙያና የሙያ ሥነምግባርን በማጣጣም ካልተሠራ ውጤታማ ለመሆን አይቻልም፡፡*

**መልመጃ 12**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. ከሁሉም ባለሙያዎች ዘንድ ሊኖሩ የሚገባቸውን የመልካም ሥነምግባር መገለጫዎች ዘርዝሩ፡፡
2. አንድን ሥራ በውጤታማነት ለማከናወን የሙያ ችሎታ ብቻውን በቂ አይደለም የተባለው ለምንድን ነው?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ጠንካራ የሥራ ባህል ሊገለብት የሚችለው ጠንክሮ መሥራትን የሕይወት መመሪያው ያደረገ ሕዝብና ሠራተኛ ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ጠንካራ የሥራ ባህል ማለት እያንዳንዱ ዜጋ በግልም ሆነ በጋራ የተሰጠውን ኃላፊነት በጥራትና በዓይነት ለማሳደግ የሥራ ጊዜውን በአግባቡ ተጠቅሞ ጠንክሮ የመሥራት ልምድ ማለት ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች ትኩረት የሁሉንም ዜጎች ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡ የሀገር ልማትና ዕድገት እውን ሲሆን ሁሉም ዜጎች የተሻለ የኑሮ ደረጃ ይኖራቸዋል፡፡ ይህን የሀገር ልማትና ዕድገት ለመገንባት እያንዳንዱ ዜጋ ጠንካራ የሥራ ባህል ሊኖረው ይገባል፡፡

ምርትና ምርታማነትን ሳያሳድጉ ዕድገት ይመጣል ብሎ መመኘት ከድንጋይ ላይ የውሃ ምንጭ እንደ መጠበቅ ያለ የተዛባ አስተሳሰብ ነው፡፡ በሁሉም የሥራ መስኮች የተሠማሩ ሠራተኞች የሙያ ሥነምግባርን በመላበስ የሥራ ባህላቸውን ሲያዳብሩ የሀገር ልማት እውን ይሆናል፡፡

ከዚህም በላይ ሁሉም ዜጎች ሥራን ሳይንቁ በመሥራት፣ ሳይሠሩ መብላትን በመፀየፍና አንዱ ሥራ ከሌላው የማያንስ መሆኑን በመረዳት በሁሉም ሥራ ከተረባረቡ ሀገራቸውን ወደ ተሻለ ደረጃ እንደሚያደርሱ ጥርጥር የለውም፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

| | |
|---|---|
| **ፀር፣** | ጠላት፣ ተቀናቃኝ፣ ተቃዋሚ:: |
| **ሰለባ፣** | ጉዳተኛ፣ ተጠቂ:: |
| **ማቅማማት፣** | መወላወል:: |
| **ሳጠራ፣** | ከሸምበቆ ወይም ከቀርቅሃ ተክል የሚሠራ ወይም ለልዩ ልዩ ቁሳቁስ የሚያገለግል። |

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::*

## I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::

1. አንድ የተሟላ አገልግሎት ለተጠቃሚ ለመስጠት የሙያ ችሎታ ብቻውን በቂ ነው::
2. የሀገርን ልማት የጥቂት ግለሰቦችና መሪዎች ጉዳይ ብቻ አድርጎ መውሰድ ስህተት ነው::
3. ከሙያ ሥነምግባር መገለጫዎች አንዱ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ነው::
4. የሙያ ሥነምግባሮች ሁሉ ተመሳሳይ ናቸው::
5. የግል የሥራ ውጤት በጋራ የልማት ሥራ ላይ የማይናቅ ተፅዕኖ አለው::

## II. በ “ለ” ሥር የተዘረዘሩትን በ “ሀ” ሥር ካሉት ሥር አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሳይሠሩ መኖር፣ | ሀ. ሁሉንም ዜጎች በዕኩልነት ተጠቃሚ የማድረግ አቅጣጫ። |
| 2. የሙያ ሥነምግባር፣ | ለ. ጊዜን በአግባቡ ከፋፍሎ ለመጠቀም ያስችላል። |
| 3. የሥራ ዕቅድ፣ | ሐ. ፀያፍና የጥገኝነት ባህሪ ነው። |
| 4. ሥራን አለመናቅ፣ | መ. በሥራ እኩልነት ማመን። |
| 5. የኢኮኖሚክ ነክ ዓላማዎች፣ | ሠ. እያንዳንዱ ሠራተኛ ሊኖረው የሚገባ ባህሪ። |
| | ረ. የጋራ ሥራ:: |

## III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::

1. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች መካከል ለአንድ ባለሙያ አስፈላጊ የሆነው፤
   ሀ. በሙያውና በሥልጣኑ ራሱን መጥቀም፣
   ለ. በቢሮ ሥራ ላይ ብቻ መሰማራት፣
   ሐ. የሙያን ብቃትና የሙያ ሥነምግባርን መላበስ ፣
   መ. ሥራን መምረጥ።
2. ለሀገር ልማትና ለኢኮኖሚ እድገት እንቅፋት ከሆኑት መካከል፤
   ሀ. ሳይሠሩ መኖር፣ ሐ.ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም፣
   ለ. ልመናን እንደ ገቢ ምንጭ መቁጠር፣ መ. ሁሉም።
3. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ስለ ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት የኢኮኖሚ መብቶች ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ዜጎች በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መሳተፍ እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
   ለ. ለሥራ አጦች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ማውጣት፣
   ሐ. ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ሥራውንና ሙያውን መምረጥ የሚያስችለው መብት ማጎናጸፍ፣
   መ. ዜጎች በመንግሥት ሥራ ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ማድረግ።

4. ጠንካራ የሥራ ባህል መገንባትን የማይመለከተው ነጥብ የቱ ነው?
   ሀ. ሳይሠሩ በመኖር የሌሎች ጥገኛ መሆን፣
   ለ. የሥራ ድርሻን መወጣትና በጋራአብሮ የመሥራትን ባህል ማዳበር፣
   ሐ. አገልግሎት ፈላጊውን በአግባቡ ተቀብሎ የማስተናገድ ብቃት፣
   መ. ሴቶች በግብርናም ሆነ በአርብቶ አደርነት በእኩል እንዲሳተፉ ማድረግ::
5. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች መካከል ስለጠንካራ የሥራ ባህል ትክክል የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ሥራን ከታቀደው ባነሰ ጊዜ ውስጥ በጥራት ማጠናቀቅ፣
   ለ. ሥራን ትንሽ/ትልቅ ብሎ አለመናቅ፣
   ሐ. ልመናንና ሳይሠሩ መብላትን ማውገዝና ጠንክሮ መሥራት፣
   መ. ሁሉም ትክክል ነው::

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::

1. ______________ ሁሉንም የሀገሪቱ ዜጎች የልማት ተጠቃሚ ማድረግ ነው::
2. እያንዳንዱ ባለሙያ ሊላበሰው የሚገባ የሥራ ባህሪ የሙያ ______________ ይባላል::
3. በዚህ ምዕራፍ በተማራችሁት መሠረት ፀያፍ ተግባርና የማህበራዊ ችግር አንዱ ገጽታ ነው የተባለው ____________________ ነው::
4. ሀገር የምትለማው ሁሉም ዜጎች ጠንካራ___________________ ባህል ሲኖራቸው ነው::
5. አንድ ሠራተኛ ከሌሎች በላቀ ደረጃ ውጤታማ ሆኖ ሲገኝ ከመንግሥትም ሆነ ከመሥሪያ ቤቱ የሚሰጠው ማበረታቻ___________ ይባላል።

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ::

1. ጠንካራ የሥራ ባህልን እንዴት ማዳበር ይቻላል?
2. ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም በሀገር ልማት ላይ ምን ጉዳት ያደርሳል?
3. ልመናንና ሳይሠሩ መብላትን ለማስቀረት ምን ምን እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው ትላላችሁ?

# ምዕራፍ ስምንት

# ራስን መቻል

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቂ/ ስታጠናቅቅ፤***

- የጥገኝነትን አስከፊ ገጽታ ትገነዘባለህ/ ትገነዘቢያለሽ
- የራስን ችሎታ የማወቅን ጠቀሜታ ትረዳለህ/ ትረጂያለሽ፣
- ለሳቀ የሥራ ውጤት ክብር መስጠት እና ከሌሎች መማር በራስ ለመተማመን ያለውን ጠቀሜታ ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ

## 8.1 ራስን የመቻል ባህልን ማዳበር

### 8.1.1 ጥገኝነትን ማስወገድ



*ሥዕል 8.1 የምጽዋት ጥገኛ*



*ሥዕል 8.2.ራስን የመቻል ተግባር*

- ከሁለቱ ሥዕሎች ራስን የመቻል ጥረት የታየው በየትኛው ስዕል ላይ ነው?
- ጥገኝነት እንዴት ይወገዳል?

**ሳይቃጠል በቅጠል፤**

ወ/ሮ ሀዋ እና አቶ ሱለይማን ሳሎን ውስጥ ቁጭ ብለው ሻይ እየጠጡ ዜና በማዳመጥ ላይ ነበሩ፡፡ አቶ ሱለይማን የሚያውቁት ሰው ድንገት በቴሌቪዥኑ ውስጥ ታየ፣

"ሀዋ ይህ ሰው ፈለቀ ይባላል፡፡ አብሮ አደጌ ነው" አሉ፡፡ ወዲያውም ዜና አንባቢዋ፣

"አቶ ፈለቀ የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ በሕገ ወጥ መንገድ ለማግኘት ጉቦ ሲሰጥ እጅ ከፍንጅ ተይዟል። በዚህ ምክንያት ዛሬ በዋለው ችሎት የእስራትና የገንዘብ ቅጣት ተበይኖበታል" በማለት ተናገረች፡፡ አቶ ሱሌይማን በሰሙት ዜና ደነገጡ፡፡ ቀጥለውም፣

"አይ ትምህርት ቤት ሳለንም እንድናስኮርጀው ፓስቲ፣ ከረሜላ፣ ደብተርና እርሳስ ያመጣልን ነበር" አሉ፡፡

"አይ ለካስ ሳይቃጠል በቅጠል" "የሚባለው ለዚህ ነው"አሉ - ወ/ሮ ሀዋ፡፡

"እሱስ እውነትሽን ነው፡፡ ግን እኛም ጓደኞቹ ብንሆን ከምናስኮርጀው ይልቅ ተው ራስህን ቻል ይህ ጥገኝነት ይቅርብህ ልንለው ይገባ ነበር" አሉ - ትክዝ ብለው፡፡

በዚህ ጊዜ ወ/ሮ ሀዋ ብስጭት አሉና "እናንተስ ብትሆኑ የትምህርት ቤቱን ደንብ ጥሳችሁ ፓስቲና ከረሜላ፣ ስክሪፕቶና ደብተር እየተቀበላችሁ አይደል ታስኮርጁት የነበር፡፡ ታዲያ እናንተም እኮ በሕገ ወጥ መንገድ ጥቅም አግኝታችኋል፡፡ ጉቦ በልታችኋል። ስለዚህ እናንተም የኢኮኖሚ ጥገኛ ናችሁ" አሏቸው፡፡

**መልመጃ 1**

*ከላይ የቀረበውን ታሪክ በጥሞና አንብቡና የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሥሩ፡፡*

1. ወ/ሮ ሀዋ "ሳይቃጠል በቅጠል" ያሉትን ምሳሌያዊ አነጋገር ከታሪኩ በተገነዘባችሁት መሠረት ግለጹ?
2. አቶ ሱስይማን እና አቶ ፈስቀ በልጅነታቸው በትምህርት ቤት የፈፀሙት ዓይነት አፀያፊ ተግባር ዛሬም እናንተን ቢያጋጥማችሁ ምን ታደርጋላችሁ?

**የቡድን ሥራ፤**

ተማሪዎች በሦስት ቡድን ተቧደኑ፡፡ ከዚያም በየቡድናችሁ እንድታከናውኑት ቀጥሎ የተሰጧችሁን ተግባራት ያዙ፡፡ በመቀጠልም በመምህራችሁ አማካይነት በአቅራቢያችሁ ወደሚገኝ የማህበራዊ ጉዳይ መ/ቤት ሂዱ፡፡ እዚያም ለባለሙያዎች ቃለመጠይቅ አድርጉ፡፡ በዚህ መንገድ ያሰባሰባችሁትን ሀሳብ ክፍል ውስጥ እያቀረባችሁ ተወያዩበት፡፡

**ቡድን አንድ፡-** የማሕበራዊና የኢኮኖሚ ጥገኝነት የሚገለፅባቸውን ባህሪያት በዝር ዝር ጽፎ ያቅርቡ፡፡

**ቡድን ሁለት፡-** ይህ መጥፎ ባህሪ ያለባቸው ሰዎች በሕብረተሰቡ ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት በዝርዝር ጽፎ ያቅርብ፡፡

**ቡድን ሦስት፡-** ይህ መጥፎ ባህሪ ያለባቸው ስዎች የሚያጋጥማቸውን ችግር እና ጉዳት በዝርዝር ጽፎ ያቅርብ፡፡

ጥገኝነት በየትኛውም የእድሜ ደረጃ ላይ ያለ ሰው በአቅሙ መሥራት የሚችለውንና ለራሱ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በሌሎች እንዲሰሩለት መፈለግ ነው፡፡ በተለይም የወደፊት ማንነታችን የሚቀረፀው ከህጻንነታችን ጊዜ ጀምሮ ስለ ሆነ በቤታችን እና በትምህርት ቤታችን ውስጥ የምናሳልፈውን ጊዜ በጥንቃቄ መጠቀም ይኖርብናል፡፡ በልጅነታችን በአቅማችን መሥራት የምንችለውን ሳንሠራ ከቀረን ስናድግም ይኼው ባህሪያችን አብሮን ያድግና ለከፋ ውድቀት ይዳርገናል፡፡

ስለዚህ ጥገኝነት በራሳችን ተማምነን ራሳችንን እንዳንመራ እንቅፋት ስለሚሆንብን በአቅማችን መሥራት የምንችለውን ለመሥራት ጥረት በማድረግ ልናስወግደው ይገባል፡፡

**መልመጃ 2**

*የሚከተለውን ጥያቄ ሥሩ፡፡*

በቤት እና በትምህርት ቤት በአቅማችን ልናከናውናቸው የምንችላቸው ሥራዎች ምንድን ናቸው? እነዚህን ሥራዎች ባለመሥራት ጥገኝነት እንዴት ይገለጻል?

## 8.1.2. ጥገኝነትና የኮንትሮባንድ ንግድ



*ሥዕል 8. 3. ጉቦ አጸያፊ ተግባር ሲሆን፣ ኮንትራባንዲስቶችም ከሕግ አያመልጡም*

- ስለ ኮንትሮባንድ ከሥዕሉ የተገነዘባች ሁትን ግለጹ፡፡

## ፋይዳ ቢስ፤

ጨቡዴ ኮንትሮባንድ ነጋዴ መሆኑን የሰፈሩ ሰው ሁሉ ያውቃሉ፡፡ የሚሸጣቸው እቃዎች ሁሉ ሕግንና ደንብን ጥሰው ስለሚገቡ ቀረጥና ታክስ አይከፍልባቸውም፡፡ ንግድ ፈቃድ አውጥቶ በሕግ መሠረት ስለማይነግድ ግብር አይከፍልም፡፡

ከዚህም ባሻገር ደግሞ የሚሸጣቸው ዕቃዎች ወደ አገር ሲገቡ ጥራታቸው በተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በኩል ስለማይመረመሩ ጥራታቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ ሆኖም የሰፈሩ ሰዎች ስለ ኮንትሮባንድ ጉጂነት ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ ስለሆነ እቃዎችን በቅናሽ ዋጋ ለመግዛት ወደ ጨቡዴ ሱቅ ይሄዳሉ፡፡

ጨቡዴ በዚህ ሁኔታ እያጭበረበረ ሲኖር ጐረቤቱ የሆነ ቢያልፈው የተባለ ሰው ይከታተለው ነበር፡፡ ቢያልፈው ሀገራችን ድሀ እና ኋላቀር መሆኗ የሚያሳስበው ሰው ነበር፡፡ ስለዚህ ሕገወጥ ሥራዎችን ሁሉ ይጠላል፤ ያጋልጣል፡፡ ጨቡዴንም አጋልጦ ሕግ ፊት ለማቅረብ ስላሰበ ብዙ ጊዜ ዕቃ የሚገዛ እየመሰለ ወደ ሱቁ በመሄድ ይሰልላል፡፡

አንድ ቀን ጨቡዴ በስልክ ሲያወራ በጭነት መኪና የተጫኑ ኮንትሮባንድ እቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ በመግባት ላይ መሆናቸውን ሰማ፡፡ ወዲያው ለፖሊስ ጥቆማ ሰጠ፡፡ ዕቃዎቹም በፖሊስ ክትትል ተያዙ፡፡ ቤቱ ሲፈተሽም በጣም ብዙ ገንዘብ የሚያወጡ የኮንትሮባንድ እቃዎች ስለተገኙ ተወረሱ፡፡ ብዙ ዓመት ያጠራቀመውን ገንዘብ ሁሉ በአንድ ጊዜ አጣ፡፡ ከዚህም በላይ የሰባት ዓመት እስራት ተፈረደበት እና ወደ ማረሚያ ቤት ገባ፡፡

አቶ ቢያልፈው ኮንትሮባንድን ለመከላከል በአደረገው ጥረት የዜግነት ግዴታውን ከመወጣቱ በተጨማሪ በሕግ ላይ የተደነገገው የጠቋሚ አበል ተከፈለውና ብዙ ገንዘብ ማግኘት ቻለ፡፡

### መልመጃ 3

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. ከጨቡዴ ታሪክ ምን ተማራችሁ?
2. የኮንትሮባንድ ንግድ ለምን ፋይዳ ቢስ ነው ተባለ?
3. ከላይ የቀረበውን ታሪክ መሠረት በማድረግ በክፍላችሁ ውስጥ ድራማ አዘጋጁ እና አሳዩ፡፡ በመጨረሻም በጋራ ተወያዩ፡፡

ኮንትሮባንድ የአንድን ሀገር እድገትና መረጋጋት የሚያቃውስ ወንጀል ነው፡፡ ይህ የወንጀል ተግባር የመንግሥትን ኢኮኖሚያዊ አቅም በማዳከም ልማትን የማደናቀፍ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው፡፡ ዕቃዎችን በድብቅ ድንበር አዘልሎ በማስወጣት እና በማስገባት ሀገራችን ከወጪ እና ከገቢ ዕቃዎች ልታገኘው የሚገባትን ገቢ ያሳጣል፡፡

ኮንትሮባንድ ንግድ የገበያ መዋዠቅን በማስከተል ሕጋዊ ነጋዴዎችን ለውድቀት ይዳርጋል፡፡ በኮንትሮባንድ ንግድ የጦር መሣሪያዎች ድንበር ጥሰው በድብቅ ወደ ሀገር ውስጥ ይገባሉ፡፡ ከዚያም በሕግ ተመዝግቦ ባልተሰጣቸው ግለሰቦች ይዞታ ስር በመሆን ለሽብርና ለዝርፊያ አገልግሎት ይውላሉ፡፡

በሽብር ተግባርም ሕዝቡ በተረጋጋ መንፈስ በሠላም ሠርቶ እንዳይኖር ይሆናል፡፡ ሕይወቱ ለሰቀቀን፣ ለስጋት እና ለአደጋ ይጋለጣል፡፡ ከዚህም ባሻገር ሽብርተኝነት በጤናና ማሕበራዊ ሕይወት ላይም በርካታ ችግሮችን ያደርሳል፡፡

### መልመጃ 4

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. ኮንትሮባንድ በምን ምክንያት ለሀገር ሠላም፣ ማሕበራዊ ሕይወት እና ለጤና ጉጂ ተባለ?
2. እናንተስ በኮንትሮባንድ ንግድ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ቢያጋጥማችሁ ምን ታደርጋላችሁ?

## 8.2 ስላቀ የሥራ ውጤት ክብር መስጠት





*ሥዕል 8.4 በላቀ የሥራ ውጤት ተሸላሚ ጀግኖች*

በሥዕሉ ላይ ያሉትን ሰዎች ተመልከቱ እና ሌሎችን በተለያየ ሙያ ሽልማት ካገኙት መካከል የምታውቋቸውን ሰዎች ስም እየጠ ራችሁ ግለጹ፡፡

### ከወ/ሮ ሐዋ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ፤

ወ/ሮ ሐዋ በአፋር ክልል በአሚባራ ወረዳ ነዋሪ የሆኑ የሁለት ልጆች እናት ሲሆኑ፣ በቀበሌ ደረጃ ያደራጁት ማሕበር ሊቀመንበር ናቸው፡፡ የላቀ ሥራ ተሸላሚ ሆነዋል፡፡

***ጥያቄ፣ ለሽልማት የበቁት ምን ስላደረጉ ነው?***

ወ/ሮ ሐዋ፣ ከዚህ በፊት የአሚባራ ሴት አርብቶ አደሮች በደቦ ካልሆነ በስተቀር ተደራጅተው በማምረት ተግባር ላይ ተሠማ ርተው ትርፍ የሚያገኙበትና የሚጠቀሙበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ ብዙዎቹ በባሎቻቸው ላይ ጥገኞች ናቸው፡፡ ለሽልማት ያበቃኝ ትልቁ ነገር የነዚህን ሴቶች ኢኮኖሚያዊ አቅም ለማጠናከርና በራሳቸው እንዲተማመኑ ለማድ ረግ በማህበር ማደራጀቴ ነው፡፡

***ጥያቄ፣ ማህበሩን ለመመሥረት ምን አነሳሳዎ?***

ወ/ሮ ሐዋ፣ እኔ ማህበሩን ከማደራጀቴ በፊት ለራሴ ጥሩ እንቅስቃሴ ነበረኝ፡፡ ይኸውም ከል ማት ባቢያ ሠራተኞች ስለ ጓሮ አትክልት ልማት ስለዶሮ እርባታና ስለተለያዩ የግብርና ኤክስቴሽን ፓኬጆች ተምሬአለሁ፡፡ ነገር ግን በአካባቢዬ ያሉት ሴቶች ይህ ዕውቀት አልነ በራቸውም።

ሠርተውም እየተጠቀሙ አልነበሩም በመሆኑም እነርሱን አደራጅቼ በጋራ ብንቀሳቀስ ጥሩ ውጤት እንደምናገኝ እርግጠኛ ሆንኩኝ፡፡ ይህ ሃሳብ በአዕምሮዬ እንዳለ ወደ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የመሄድ አጋጣሚ አገኘሁ፡፡ እዚያ ክልል የኢትዮጵያ አርብቶ አደር ልማት ማሕበር የተሰኘ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ሴቶችን አደራጅቶ ከብቶች እንደሚሰጥ አረጋገጥኩ፡፡ ከዚያም ማሕበሩን አነጋግሬ 10 ጊደሮችና 4 ወይፈኖች ሰጡኝ፡፡ ከዚያም እነዚህን ጊደሮችና ወይፈኖች ይዤ መጥቼ ለሴቶች አከፋፈልኩ፡፡

*ጥያቄ፣ ማሕበሩን ለመመሥረት ምን ምን ችግሮች አጋጠመዎት? እንዴትስ ተወጡ?*

ወ/ሮ ሐዋ፣ ሥራውን ለመጀመር ብዙ ችግሮች ደርሰውብኛል፡፡ እሷ ሴቶቻችንን ወደ ውጪ አውጥታ ታበላሽብናለች በማለት ተሳልቀውብኛል፡፡ ባለቤቴም ደስተኛ አልነበረም፡፡ ለማደራጀት ስማቸውን የመዘገብኳቸውም ሴቶች ባሎቻችን ይቆጡናል ብለው ከእኔ ጋር ለመሥራት ዝግጁ አልነበሩም፡፡

በኋላ ላይ ግን የኢትዮጵያ አርብቶ አደር ልማት ማህበር የተባለው ድርጅት የሰጠኝን ጊደሮችና ወይፈኖች ሳከፋፍላቸውና ዓላማዬ የጋራ ልማት መሆኑን ሲረዱ በኔ ላይ የነበራቸው መጥፎ አመለካከት ተቀየረ፡፡ በዚህም በማህበር መደራጀት ጥቅም እንዳለው ተገነዘቡ፡፡

## መልመጃ 5

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሱ።*

?

1. ወ/ሮ ሐዋ ለሽልማት ያበቋቸው ሥራዎች ምን ምን ናቸው?
2. ሳለቀ የሥራ ውጤት ትምህርት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው መሆኑን ወ/ሮ ሐዋ እንዴት እንደገለፁት አስረዱ፡፡
3. መንግሥት ወ/ሮ ሐዋን ለማበረታታትና ሴሎች የሳቸውን አርአያ እንዲከተሉ ምን ምን እርምጃዎችን ወሰደ?
4. ወ/ሮ ሐዋን ብትሆኑ ሽልማቱ ምን ስሜት ያሳድርባችሁ ነበር?

ለላቀ የሥራ ውጤት መሠረቱ በተሰማራንበት የሥራ መስክ የሚኖረን ትጋት ነው፡፡ የምንሰራውን ሥራ ለምን እንደምንሠራው ካወቅን፣ እንዴት ብንሠራው የበለጠ ውጤት እንደምናገኝበት ተመራምረን ከደረስንበት፣ ከሌሎች ተሞክሮ ልምድ ከወሰድን፣ እንዲሁም በመማር እውቀታችንን ካዳበርን የሥራ ውጤታችን ከፍተኛ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የላቀ የሥራ ውጤት ፅንሰ ሐሳብ በውስጡ የውድድር መንፈስን የያዘ ነው፡፡ ከሌሎች ተሽሎ መገኘትን እና በሥራ ውጤት ራስን፣ ቤተሰብን እና ሀገርን መጥቀም መቻልን ያካትታል፡፡ ለምሳሌ የወ/ሮ ሐዋን ታሪክ ብናስተውል ትምህርት እና ችሎታቸውን በማዳበር የሌሎችን ልምድ በመካፈል እንዲሁም ተግተው በመሥራት የራሳቸውን ኑሮ ለውጠዋል፡፡

ከዚህም በላይ በአካባቢያቸው የሚኖሩ ሴቶችን በማህበር በማደራጀት ኑሯቸው እንዲሻሻል ማድረግ ችለዋል፡፡ እንዲሁም ለላቀ የሥራ ውጤት ክብር መስጠት፣ ለሌሎች ሰዎች ተግባራዊ ክንዋኔዎችና ውጤቶች እውቅና፣ ክብርና አድናቆት መስጠት እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ ለሰዎች ሥራ ክብር መስጠት ሥልጡን የመሆን ምልክት ብቻ ሳይሆን ውጤታማዎቹ ሰዎች እንዲበረታቱና የበለጠ እንዲሰሩ ያተጋቸዋል፡፡ ሰዎች የበለጠ በሠሩ ቁጥር ደግሞ የሀገር እድገት ይፋጠናል፡፡

## መልመጃ 6

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

?

1. የላቀ የሥራ ውጤት ለማስመዝገብ ምን ማድረግ አለባችሁ?
2. የላቀ የሥራ ውጤት በውስጡ የውድድር መንፈስ እንዴት ይኖረዋል? አብራሩ፡፡

## 8.3 በራስ መተማመን

### 8.3.1 በራስ መተማመን ላለቀ የስራ ውጤት ስመብቃት ያለው ወሳኝ ሚና

- በራስ መተማመን ላለቀ የሥራ ውጤት እንዴት ያበቃል?

**ባለ ራዕይ የትዳር ጓደኞች፤**

**አቶ ሙሉዓለም ብርሀኔ** በጉጃም ተወለዱ፡፡ መደበኛ ትምህርትን እስከ 12ኛ ክፍል ተከታትለዋል፡፡ አቶ ሙሉዓለም በ1967 ዓ.ም በወቅቱ በነበረው የዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻም ዘማች ነበሩ፡፡ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወስደው ውጤት አላገኙም፡፡

በዚህ ወቅት በደረሰባቸው ችግር ሳይደናገጡ ባላቸው የዕውቀትና የገንዘብ አቅም መሥራት የሚችሉትን ነገሮች ለይተው ገመገሙ፡፡ በዚያን ጊዜ ከቤተሰቦቻቸው የተማሩት የግብርና ሙያ እውቀት ነበራቸው፡፡ ይህንን እውቀታቸውን በቀሰሙት የዘመናዊ ትምህርት አዳብረው ቢሰሩ ጥሩ ውጤት እንደሚያመጡ ተገነዘቡ፡፡ ገጠር የሚኖሩ ወገኖቻቸውንም ከተለያዩ ኋላቀር አስተሳሰቦች ለማላቀቅና የአመጋገብ ሥርዓታቸውንም ማስቀየር እንደሚችሉ አመኑ፡፡

በወቅቱ በዚህ ውሳኔያቸው የሚያውቋቸው ሰዎች የተማረ ሰው ከተማ ውስጥ የቢሮ ሥራ ይሠራል እንጂ እንዴት ገበሬ ይሆናል ብለው አምተዋቸዋል፡፡ አቶ ሙሉዓለም ግን በአቋማቸው ጸንተው የግብርና ሥራቸውን ቀጠሉ፡፡ ቆይተው የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ገጠር ገብተው ከወላጆቻቸው ጋር የግብርና ሥራ በመሥራት ላይ ከነበሩት ከወ/ሮ ውብዓለም መንግሥት ጋር ትዳር መሠረቱ፡፡

አቶ ሙሉዓለም እና ወ/ሮ ውብዓለም ከመጀመሪያው አቅጣጫቸውን ገምግመው መሥራት በሚችሏቸው ነገሮች ላይ በራሳቸው ተማምነው ስለተነሱ በሥራቸው ውጤታማ ሆኑ፡፡ ለራሳቸው ለቤተሰባቸው እና ለአካባቢያቸው ከዚያም አልፎ ለሀገራቸው እጅግ ጠቃሚ ሥራዎችን በማከናወናቸው የተለያዩ ሽልማቶችን አገኙ፡፡

በተለይም በ1997 ዓ.ም በተደረገው የአረንጓዴው ዘመቻ ሽልማት በሀገር አቀፍ የሦስተኛ ደረጃ ተሸላሚ በመሆን ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዚዳንት እጅ ለመሸለም በቅተዋል፡፡ አሁንም አቅማቸውን በየጊዜው በማሻሻል የበለጡ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ናቸው፡፡

**መልመጃ 7**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. አቶ ሙሉዓለምና ወ/ሮ ውብዓለም በራሳቸው ስመተማመን ያስቻላቸው ምንድነው?
2. አቶ ሙሉዓለም እና ወ/ሮ ውብዓለም ወደ ገጠር የገቡበት ውሳኔ በትክክል የታሰበበት ነበር? እንዴት? ምክንያቱን አብራሩ፡፡

በራስ የመተማመን ባህሪይ ስንወለድ በተፈጥሮአችን ይዘነው የምንወለደው መለያችን አይደለም፡፡ ይልቅስ ከተወለድን በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች የምናዳብረው ባህሪያችን ነው፡፡

ማንኛውም ሰው ቢሆን ከተወለደ ጊዜ ጀምሮ ከወላጆቹ እና ከአካባቢው ጋር በሚኖረው ግንኙነት እንዲሁም በትምህርት ቤት ውስጥ በሚያገኘው መደበኛ ትምህርት ዕውቀትን ይቀስማል፡፡ በዕውቀቱ መሥራት የሚችላቸውና የማይችላቸው ነገሮች ይኖራሉ፡፡ አካላዊ ጥንካሬም እንደዚሁ በሕይወት ሂደት ውስጥ እየተለዋወጠ የሚሄድ የአቅማችን አንድ መገለጫ ነው፡፡

ስለዚህ የአንድ ሰው በራስ የመተማመን ስሜት እነዚህን አቅሞች እና ችሎታዎች ለይቶ ከማወቅ የሚመነጭ ነው፡፡ ጠንካራ ጐንን በማጐልበት፣ ደካማ ጐንን ደግሞ በማሻሻል በራስ የመተማመን ስሜትን ማሳደግ ይቻላል፡፡

**መልመጃ 8**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡*

?

1. በራስ የመተማመን ባህሪ እንዴት ይዳብራል?
2. በራሱ የሚተማመን ሰው ምን ምን ባህሪያት አሉት?

### 8.3.2 የሌሎችን አስተሳሰብና አመለካከት በግልጽነትና በአግባቡ በማስተናገድ የራስን አመለካከትና እምነት በጽናት ማራመድ

- *የራስን አመለካከት በጽናት ማራመድ ማለት ምን ማለት ነው?*

የሌላውን ሰው አስተሳሰብና አመለካከት በግልጽነት እና በአግባቡ በማስተናገድ የራስን አመለካከት እና እምነት በጽናት ማራመድ በራስ ከመተማመን ስሜት ይመነጫል፡፡ ይህ መሠረታዊ የሆነ ራስን የማወቅ ሂደት በሕይወት ስኬታማነት ውስጥ ወሳኝ ድርሻ አለው፡፡ ለምን ቢባል የብዙ ሰዎች ችግር ያላቸውን አቅም ለይቶ ያለማወቅ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በመደበኛ ትምህርት፣ ከሌሎች ጋር በሚኖረው ግንኙነት ወይም በልምድ ያካበተው የራሱ የሆነ ችሎታ አለው፡፡ ይህንን ፈትሾ ማወቅ ከቻለ በራሱ እንዲተማመን የሚያስችለው አቅም ይኖረዋል፡፡

በራሱ የሚተማመን ሰው ደግሞ ድክመቶቹን እና እጥረቶቹን ለይቶ ስለሚያውቅ እነዚህን ድክመቶች ለማሻሻል ይሠራል፡፡ በራስ በመተማመን ስሜት በመነጨም የበታችነት ስሜት ስለማይሰማው ግልፅ የመሆን ችሎታንም የተጐናፀፈ ነው፡፡

በሌላ በኩል የነዚህ ችሎታዎች ድምር ውጤት ሚዛናዊነትን ያስከትላል፡፡ ሚዛናዊነት በራስ መተማመንን ተከትሎ የሚከሰት ጤናማ የግንኙነትና የመደማመጥ ገፅታ ነው፡፡ በራስ መተማመንን ካዳበርን ከሌሎች ጋር ለመደማመጥ ትልቅ እንቅፋት የሚሆኑብንን የበላይነት እና የበታችነት ስሜቶችን እንዲሁም ትችቶችን የመፍራት ሥጋትን ማስወገድ እንችላለን፡፡ ምክንያቱም የሌላውን ሰው አመለካከት ለማክበር እና የራሳችንን አመለካከትም ለማዳበር የምንችለው በራሳችን የምንተማመን ሰዎች ስንሆን ነው፡፡

የራስን አመለካከት ለመገንባትና በፅናት ለመፈፀምም ሆነ የሌሎችን አመለካከት ለማዳመጥ፣ ሚዛናዊ ሆኖ ለመቀበልና ላለመቀበል በቅድሚያ በራሳችን የምንተማመን ዜጐች መሆን ይኖርብናል፡፡ በራስ የመተማመን ስሜትን ለማዳበር ትምህርት ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡ ትምህርት ዕውቀትን ያስጨብጣል፣ አስተሳሰብን ያጐለብታል፣ ራስን ማወቅ ያስችላል፡፡ ራሳችንን ካወቅን በራሳችን እንተማመናለን፡፡ በራሳችን ስንተማመን ሚዛናዊ እንሆናለን፣ ሚዛናዊ ስንሆን ደግሞ ሌሎችን በማዳመጥ መጠቀም እንችላለን፡፡ የሌሎችን

ሰዎች አስተሳሰቦች እና አመለካከቶች በአግባቡ ማድመጥ እና መመዘን ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ አስፈላጊውን ክብር መስጠት እና ተግባር ላይ ማዋል ተገቢ ነው፡፡ በሌላ በኩል የሌሎች ሰዎች አስተሳሰቦች እና አመለካከቶች ትክክል ሆነው ካልተገኙ በጽሞና ስህተት መሆናቸውን ማስረዳት እና ትክክል የሆነውን የራስን አቋም በጽናት ለሌሎች ማስረዳት ዘመናዊና የሠለጠነ ሰው ተግባር ነው፡፡

**መልመጃ 9**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

?

1. ከሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት ሚዛናዊ ስመሆን የሚያስችለን ምንድን ነው?
2. አንድ ሰው በራሱ ስመተማመን አቅሙን ማወቅ አለበት የተባለው ስምንድንነው? ተወያዩበት፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ራስን የመቻል ባህልን በማዳበር ከጥገኝነት ለመላቀቅ እና በራሳችን የመተማመን አቅማችንን ለማዳበር እንችላለን፡፡ ጥገኝነት በማንነታችን እንዳንኮራ፣ ሀሳባችንን ያለ ፍርሀት እንዳንገልጽ እንቅፋት እየሆነ በራስ የመተማመን አቅማችንን የሚሰልብ ችግር ነው፡፡

ኮንትሮባንድ ንግድም የጥገኝነት አስተሳሰብን ተከትሎ የሚመጣ ሀገርንና ሕዝብን የሚጐዳ ወንጀል ነው፡፡ ስለሆነም በመንግሥት እና በሕዝቦች የጋራ ጥረት ሊወገድ ይገባል፡፡

የጥገኝነት ጉጂነትን ተገንዝበን በቁርጠኝነት ከተከላከልነውና በራስ የመተማመን ስሜትን ካዳበርን ስላቀ ውጤት እንበቃለን፡፡ በራሱ የሚተማመን ሰው ለሌሎች የላቀ የሥራ ውጤት ክብር በመስጠት የበለጠ እንዲሠሩ ያበረታታል፡፡ በሌላ በኩል የሌሎችን አስተሳሰብና አመለካከት በግልጽነትና በአግባቡ በማስተናገድ የራሳችንን አመለካከትና እምነት በጽናት ማራመድ በራሱ የሚተማመን ሰው የሚፈጽመው ተግባር ነው፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

| | |
|---|---|
| **መዋዠቅ፣** | ከፍና ዝቅ ማለት። |
| **እጅ ከፍንጅ፣** | አንድን ወንጀለኛ ወንጀል በመፈፀም ላይ እያለ የመያዝ ሁኔታ። |
| **ችሎት፣** | የፍርድ ክርክር የሚካሄድበት መድረክ። |
| **ብይን፣** | ፍርድ። |

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ፡፡*

**I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ፡፡**

1. የላቀ የሥራ ውጤት በዘር ይወረሳል፡፡
2. ራስን የመቻል ባህል የረዥም ጊዜ ጥረት ውጤት ነው፡፡
3. ጠንካራ ሰው ጥረት ማድረግ ያለበት ሽልማት እስኪያገኝ ድረስ ብቻ ነው፡፡
4. የላቀ የሥራ ውጤት ለማምጣት ትምህርት የሚሰጠው እገዛ አነስተኛ ነው፡፡
5. የሌሎችን ሀሳብ ማስተናገድ የጥገኝነት መገለጫ ነው፡፡

**II. በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን በ "ሀ" ሥር ካሉት ሥር አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ጥገኝነትን ማስወገድ፣ | ሀ. ለላቀ የሥራ ውጤት የሚተጉ። |
| 2. ጥገኛ አስተሳሰብ፣ | ለ. ለላቀ የሥራ ውጤት የሚሰጥ ማበረታቻ። |
| 3. ለሀገር የሚጠቅሙ ዜጎች፣ | ሐ. በራስ መተማመንን ያዳብራል። |
| 4. ሽልማት፣ | መ. ለላቀ ውጤት መሥራት። |
| | ሠ. በራስ አቅም መሥራት የሚቻልን ከሌላ ሰው መጠበቅ። |

**III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. ራስን መቻል፤
   - ሀ. አካልን በስፖርት ማጠንከር ነው፣
   - ለ. ሌሎችን ማዘዝ ነው፣
   - ሐ. አቅም የሚችለውን በራስ መሥራት ነው፣
   - መ. ሁሉም መልስ ነው፡፡
2. የላቀ የሥራ ውጤት፤
   - ሀ. አንድን ሥራ ሌሎች ሊሠሩት ከሚችሉት አስበልጦ መሥራት ነው፣
   - ለ. በተሰማሩበት የሥራ መስክ ረዥም ጊዜ መሥራት ነው፣
   - ሐ. በልመናም ሆነ በሥርቆት ወይም በመሥራት ሀብታም ሆኖ መገኘት ነው፣
   - መ. ሀ እና ለ መልሶች ናቸው፡፡
3. የጥገኝነት አስተሳሰብ፤
   - ሀ. አብሮን የተወለደና እስክንሞትም አብሮን የሚቀጥል የተፈጥሮ ስጦታ ነው፣
   - ለ. ራስን በመቻል ይጎለብታል፣
   - ሐ. ለሀገርና ለወገን ቢጎዳም ለግለሰቦች ግን ይጠቅማል፣
   - መ. ግለሰብን እና ሀገርን ይጎዳል፡፡

4. ከሌሎች ለመማር ዝግጁ የሆነ ሰው፤
   ሀ. ጥገኛ ነው፣
   ለ. በራስ የሚተማመን ሰው ነው፣
   ሐ. የላቀ የሥራ ውጤት ለማምጣት ከፍተኛ ዕድል አለው፣
   መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው፡፡
5. ዕቃዎች በኮንትሮባንድ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ፤
   ሀ. መንግሥት መሠረተ ልማቶችን ለመሥራት እንዲችል ከግብር እና ቀረጥ የሚሰበስበውን ስለሚያጣ የልማት እንቅፋት ነው፣
   ለ. የዕቃዎችን ዋጋ ርካሽ ስለሚያደርግ ጠቃሚ ነው፣
   ሐ. የጦር መሣሪያዎች እና አደንዛዥ ዕጾች በድብቅ እንዲገቡ ስለሚያደርግ የሕዝቦችን ሠላምና ጤና እንዲቃወስ ምክንያት ይሆናል፣
   መ. ከ ለ በስተቀር ሁሉም መልሶች ናቸው፡፡

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ፡፡

1. ለራስ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በራስ አቅም መስራት __________________ ነው?
2. የላቀ የሥራ ውጤት ላመጡ ሰዎች የሚደረግ ማበረታቻ__________________ ይባላል፡፡

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. ራስ የመቻልን ጥረት በየትኛውም የእድሜ ደረጃ ላይ መጀመር ይቻላል? ለምን?
2. በላቀ የሥራ ውጤታቸው የተሸለሙ ሰዎች ምን ይጠበቅባቸዋል?
3. ኮንትሮባንድ በሀገር ኢኮኖሚና ማህበራዊ ሕይወት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ግለጹ፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ
# የቁጠባ ባህል

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቂ/ ስታጠናቅቅ፤***

- የተለያዩ የቁጠባ ዘዴዎች መኖራቸውን ታውቂያለሽ/ታውቃለህ::
- ራስንና ቤተሰብን በአቅም ልክ የማስተዳደርን አስፈላጊነት ትረጃለሽ/ትረዳለህ::
- በእቅድ በመመራት የቁጠባን ባህል የማዳበርን አስፈላጊነት ትገነዘቢያለሽ/ትገነዘባለህ::

## 9.1 የቁጠባ ዓይነቶች

- ቁጠባ ለምን ያስፈልጋል?

የተረጋጋና ሠላማዊ አኗኗር በዳበረ የቁጠባ ባህል ላይ ይመሠረታል፡፡ ስለሆነም ሰዎች ምን ጊዜም ቢሆን ስለቁጠባ ጥሩ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ቁጠባ ማለት ጊዜን፣ ጉልበትንና እውቀትን ተጠቅሞ ጠንክሮ በመሥራት በተገኘ ገቢ በአግባቡ እየተጠቀሙ ለወደፊት የሚሆን ንብረት በገንዘብ ወይም በዓይነት ማስቀመጥ ማለት ነው፡፡

ስለዚህ ለነገ ቆጥቦ የማስቀመጥ ልምድ፣ ለዛሬ በአግባቡ ጥቅም ላይ ከሚውሉ ወጪዎች ጋር እኩል ትኩረት ሊሰጠውና ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል፡፡ ከሚገኝ ገቢ ላይ አስፈላጊ ለሆነ ጉዳይ ብቻ አውሎ ለተቀማጭ ማሰብ ስስታምነት የሚመስላቸው ሰዎች አሉ፡፡ ይህ ትክክለኛ ግንዛቤ አይደለም፡፡

በተቃራኒው ደግሞ ስስትና ቁጠባን የሚያመሳስሉ ሰዎች አሉ፡፡ ስስት ማለት ያለን ገንዘብም ሆነ ንብረት አስፈላጊ በሆነ ወቅትም ጥቅም ላይ ላለማዋል መፈለግን ያመለክታል፡፡ ቁጠባ ግን አስፈላጊ ለሆነ ምክንያትና ጉዳይ ልንጠቀምበት እንድንችል ከሚገኝ ገቢ እየቀነሱ ማስቀመጥ፣ ያንንም ምክንያታዊ ባልሆነ ጉዳይ ላይ ላለማባከን አቋም መያዝ ማለት ነው። ስስታም ሰው ዛሬ እየተራበ ለማስቀመጥ ይሞክራል፡፡ ስስታም ሰው የራሱን አስቀምጦ የሌሎችን ለመካፈልም ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም ስስት በጎ ያልሆነ የሰዎች ባህርይ ነው። ጥሩ የቁጠባ ባህል ያለው ሰው ግን ራሱን፣ ቤተሰቡንና እንደ ሁኔታው ሌሎች የተቸገሩ ሰዎችን ሳይቀር ሊያስተምር ይችላል፡፡ ለእለት ኑሮ የሚያስፈልጉትን መሠረታዊ ነገሮች ሳያጓድል፣ ሳይቸገርም፣ ብኩን ሳይሆንም ራሱን ችሎ ይኖራል፡፡

ብዙ ሰዎች ስለቁጠባ ሲነገር የሚቆጠበው ገንዘብ ብቻ ይመስላቸዋል፡፡ ይህ አስተሳሰብም ትክክል አይደለም፡፡ የሚቆጠብ ገንዘብ ብቻ ቢሆን ኖሮ ስለቁጠባ ማውራት የሚቻለው ከሀብታሞችና ከነጋዴዎች ጋር ብቻ በሆነ ነበር፡፡ ነገር ግን የቁጠባ ጽንሰ ሐሳብ ከዚህም የሰፋ ነው፡፡ ሦስት የቁጠባ ዓይነቶች አሉ፡፡ እነሱም በዓይነት የሚደረግ ቁጠባ፣ በገንዘብ የሚደረግ ቁጠባና በጊዜ የሚደረግ ቁጠባ የሚባሉት ናቸው፡፡

**መልመጃ 1**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. ስስትና ቁጠባ አንድ ናቸው ወይስ አይደሉም? ለምን?
2. ለወደፊት ፍጆታ የሚሆን ንብረት እንዴት መቆጠብ ይቻላል?

### 9.1.1 በዓይነት የሚደረግ ቁጠባ

- በዓይነት የሚደረግ ቁጠባ ምን ዓይነት ነው?

**የመታሰቢያ ሀውልት፤**

የወ/ሮ ማንያህልሻል ሶስቱ ልጆቻቸው በጣም ታታሪዎችና ብልሆች ስለሆኑ በአካባቢያቸው ነዋሪዎች ዘንድ ይደነቃሉ፡፡ በምሳሌነትም በዚህ ዓመት ካከናወኗቸው ተግባራት አንዱ

ይጠቀሳል፡፡ ይኸውም ለጥናት የሚሆናቸውን ክፍል በግቢያቸው ውስጥ ባለው ባዶ ቦታ ላይ ያለምንም ገንዘብ ለመስራት ችለዋል፡፡ ለዚህም የተጠቀሙበት ከአራት ዓመታት በፊት በግቢያቸው ውስጥ የተከሏቸውን የባህር ዛፎች በመቁረጥና ግማሹንም በመሸጥ ነው፡፡ ከአራት ዓመት በፊት የባህር ዛፎቹን ችግኞች የተከሉት ይህንን ቤት ለመሥራት አቅደው አልነበረም፡፡ የአባታቸውን መሞት ምክንያት በማድረግ እርሳቸውን ለማስታወስ ለመታሰቢያ ብለው የተከሏቸው ናቸው፡፡ "የከተማ ሕዝብ በመቃብር ላይ የድንጋይ ሃውልት ሲያስገነባ እንሰማለን፡፡ እኛ ለምን ለአባታችን መታሰቢያ ችግኝ አንተክልም" በሚል ሀሳብ ያደረጉት ነበር፡፡ የባህር ዛፍ ችግኞችን እንዲተክሉ የመከሯቸው ደግሞ እናታቸው ናቸው፡፡

## መልመጃ 2

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተለውን ጥያቄ መልሱ፡፡***

?

በአካባቢያችሁ እንደ ወ/ሮ ማንያህልሻል ልጆች ምን ቋሚ ንብረት ልትገነቡ ትችላላችሁ? እንዴት?

በዓይነት የሚደረግ ቁጠባ በገንዘብ ሳይሆን ቋሚ በሆኑ ንብረቶች የሚገለጽ ነው፡፡ ለምሳሌ ውድ እቃዎችን እና የከበሩ ድንጋዮችን ገዝቶ በማስቀመጥ፣ እንስሳትን በማርባትና ቋሚ ተክሎችን በማጽደቅ ይገለጻል፡፡ ቤት መሥራት፣ ለረጅም ዓመታት ምርት የሚሰጡ እንደ ቡና የመሳሰሉትን መትከል በዓይነት የሚደረግ ቁጠባ ምሳሌዎች ናቸው።

በዓይነት የሚደረግን የቁጠባ ዘዴ በማንኛውም የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች ሊከተሉት የሚገባ ነው፡፡ ለምሳሌ በገጠር በአንዳንድ ቦታዎች የሚኖሩ ቤተሰቦች ልጆቻቸው ቁጠባንና የንብረት አጠቃቀምን እንዲለማመዱ የሚያደርጉት ከለጋ እድሜያቸው ጀምረው ነው፡፡ የእንስሳት ግልገሎችንና ጫጩቶችን በስጦታ መልክ በመስጠት ልጆቹ እነዚያን እየተንከባከቡና እየጠበቁ የራሳቸውን ንብረት ያቆያሉ፡፡ እንስሳቱ እየተዋለዱ በተበራከቱ፣ ልጆቹም በእድሜ ባደጉ ቁጥር የደስተኛነትና የባለንብረትነት ስሜት እየሰረጸባቸው ይሄዳል፡፡

በዚህ ሁኔታ ከወላጆቻቸው ያገኙትን ቅርስ በመጠበቅ በወጣትነት እድሜ ላይ ሲደርሱ የራሳቸውን የቁጠባ ዘዴ በልጅነታቸው በተማሩት መሠረት ያዳብራሉ፡፡ በከተሞች አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ንብረታቸውን እንዴት በዓይነት እንደሚያስቀምጡ ብንመለከት በርካታ ምሳሌዎችን ለመጥቀስ እንችላለን፡፡ ከነዚህም ውስጥ ቤት መሥራት፣ መኪና መግዛት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

## መልመጃ 3

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. በቀረበው ምንባብ መሠረት በዓይነት የሚደረግ ቁጠባ መሠረቶች ምን ምን ናቸው?
2. በአካባቢያችሁ ከገንዘብ ሌላ ሰዎች ባስፈለጋቸው ጊዜ እንደገቢ ምንጭ የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁሶች ወይም ንብረቶች ምን ምን እንደሆኑ ከሰዎች በመጠየቅም ሆነ በራሳችሁ ምልከታ መዝግባችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

## 9.1.2 የገንዘብ ቁጠባ

*"ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ፡፡"*

*"ወርቅ የተጫነች አህያ በሮች ሁሉ ይከፈቱላታል፡፡"*

- ምሳሌያዊ አባባሎቹን በመመርመር ስለገንዘብ የሚያስተላልፉትን መልእክት አስረዱ፡፡

### ከማልና ዮሴፍ፤

ዮሴፍና ከማል ለከፍተኛ ትምህርት ከደሴ ከተማ ወደ አዲስ አበባ የመጡት ከሁለት ዓመት በፊት ነበር። ከማል ቤተሰቦቹ በየወሩ የተወሰነ ገንዘብ ይልኩለታል። ይህንንም ገንዘብ የሚያውለው የትምህርት መሳሪያዎች ለመግዛት፣ አዲስ አበባ ወደሚገኙ ዘመዶቹ ሲሄድ የመጓጓዣ እና ጥቃቅን የስጦታ እቃዎች ለመግዣ ነው። ይህም ሆኖ ወላጆቹ የሚልኩለትን ገንዘብ በሙሉ አይጠቀምበትም። ይልቁንም የባንክ ሂሳብ ከፍቶ እየቆጠበ ያጠራቅማል።

የዮሴፍ ወላጆች ደግሞ የከማልን ቤተሰቦች ያህል በኢኮኖሚ የጠነከሩ አይደሉም:: ስለሆነም በዓመት አንድ ጊዜ የሚያስፈልጉትን ልብሶችና የትምህርት መሣሪያዎች ከመግዛት በስተቀር በየወሩ የሚልኩለት ገንዘብ የለም:: ዮሴፍ ግን ገንዘብ ሊያስፈልገው የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ አውቋል:: ስለሆነም አንድ ጥሩ ሀሳብ አፈለቀ::

የትምህርት ሰዓቱን ሳይነካ የራሱ የገቢ ምንጭ ለመፍጠር ሲያስብ አንዳንድ ሥራዎችን አገኘ:: ተማሪዎችን ማስጠናት፣ ለጋዜጦችና ለመጽሄቶች ለወጣቶች ማስተማሪያ የሚሆኑ ጽሁፎችን መጻፍና መስጠት የፈጠራቸው የገቢ ምንጮቹ ናቸው:: ይሁን እንጂ እነዚህን ሥራዎች የሚሠራው የትምህርት ጫና በሌለበትና ሰፋ ያለ ጊዜ በሚያገኝበት በመሆኑ ቋሚ የሆነ ወርሃዊ ወይም ሳምንታዊ ገቢ የለውም:: አንድ ጊዜ ሠርቶ ያገኘውን ገቢ በመቆጠብ ገንዘብ ለማግኘት በማይንቀሳቀስበት ጊዜ ሁሉ አብቃቅቶ ይጠቀምበታል::

በዚህም የተነሳ ዮሴፍም እንደከማል ሁሉ በየጊዜው ለሚያጋጥሙት ሁኔታዎች የሚያወጣው የራሱ ገንዘብ ሊኖረው ችሏል:: ዮሴፍና ከማል በዓመቱ መጨረሻ ትምህርታቸውን ጨር ሰው ወደ ቤተሰቦቻቸው ተመልሰው ለመሄድ ምንም ዓይነት የገንዘብ ድጋፍ አይፈልጉም:: ምክንያቱም ሁለቱም ከገቢዎቻቸው የተወሰነ ገንዘብ አጠራቅመዋል::

**መልመጃ 4**

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. ዮሴፍና ከማል በትምህርት ላይ ሳሉ ገንዘብ ያስፈለጋቸው ለምንድን ነው?
2. ዮሴፍ ገንዘብ ለማግኘት ሲል የሚሠራቸው ሥራዎች በትምህርቱ ላይ ችግር አይፈጥሩበትም? ለምን?

በአሁኑ ጊዜ አገልግሎትና ሸቀጥ ማግኘት የሚቻለው በገንዘብ አማካኝነት ነው፡፡ ገንዘብ በእለት ከእለት ኑሮ ውስጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ለዚህ ጠቀሜታ የሚውለው ገንዘብ በልዩ ልዩ ዘዴዎች ይገኛል፡፡ ጠንክሮ በመሥራት፣ በስጦታ፣ በብድርና በጡረታ አበል ክፍያ የሚሉት ለአብነት የሚጠቀሱ የገንዘብ ምንጮች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በእነዚህ ዘዴዎች የሚገኝን ገንዘብ በእቅድና በቁጠባ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ለእለታዊ ኑሮ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮች በርካታ ስለሆኑ የሚገኝን ገቢ አብቃቅቶ በመጠቀም ለተቀማጭም ማሰብ ተገቢ ይሆናል፡፡

ገንዘብን ለመቆጠብ የገንዘብ አጠቃቀምን ማወቅ ብቻ አይበቃም፡፡ ተቀማጭ ገንዘብ ተለይቶ የሚቀመጥበት ሥፍራም አስተማማኝ መሆን ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም አስተማማኝ ያልሆነ ቦታ የተቀመጠ ገንዘብ ሊሰረቅ፣ ሊበላሽ፣ ያለእቅድ በድንገት ሊባክን ይችላል፡፡ ከእነዚህ አስተማማኝ ማስቀመጫ ሥፍራዎች አንዱ የባንክ ቤት ነው፡፡

የባንክ ቤት ጠቀሜታ ገንዘብን በማስቀመጥ ረገድ ያለው አስተማማኝነት ብቻ አይደለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ገንዘብን በምስጢር ማስቀመጥ ያስችላል፡፡ ባለገንዘቡ ካልቀረበ በስተቀር የተቀመጠን ገንዘብ ሌላ ሰው ሊወስድ ወይም ሊያውቅ አይችልም፡፡

ገንዘብ አስቀማጮች በፈለጉት ጊዜ የሚያስቀምጡበት፣ ባስፈለጋቸው ጊዜ ደግሞ ለሚያስፈልጋቸው ጉዳይ አውጥቶ መጠቀም መቻላቸው ሌላው ጠቀሜታው ነው፡፡

### አዳነች፤

አዳነች በአዲስ አበባ ከተማ በቦሌ ክፍል ከተማ የምትኖር የ20 ዓመት ወጣት ናት፡፡ ከሁለት ዓመት በፊት የራሷ የሆነ የገንዘብ ምንጭ አልነበራትም፡፡ ታላቅ እህቷና ወንድሟ አንድ የሙያ ሥልጠና እንድትከታተል ለስድስት ወራት ወጪዋን በመሸፈን ረድተዋታል፡፡

በዚህ መካከል ሬዲዮና ቴሌቪዥን ስትከታተል ሠርተው ራሳቸውን መቻል ለሚፈልጉ ወጣቶች አዲስ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ተቋም ብድር እንደሚሰጥ ሰማች፡፡ ከዚህ በመነሳት አንድ እቅድ አወጣች፡፡ ይህም እቅድ ብድር ወስዳ ለመሥራትና የራሷን ገቢ ለመፍጠር ነው፡፡



*ሥዕል 9.1 ሠርቶ እራስን መቻል*

ከዚያም ወደ ተቋሙ በመሄድ የገንዘብ ብድሩን ተቀበለች፡፡ ሠርታ በተወሰነ ጊዜ የወሰደችውን ብድር ለመመለስም ቃል ገብታ ፈረመች፡፡ በወሰደችው ገንዘብ ዘመናዊ የወንዶች ጸጉር ማስተካከያ ቤት ከፈተች፡፡ አንድ ረዳት ባለሙያ በመቅጠር፣ ቤት ተከራይታ ሥራዋን ጀመረች፡፡ የምታገኘው ገቢም ጸጉር ለማስተካከል የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ለመግዛት፣ ለሥራ ባልደረባዋ ደመወዝ ለመክፈል፣ የተበደረችውን ብድር በየጊዜው ለመክፈል፣ ለራሷ የሚያስፈልጓትን ወጪዎች ለማሟላት እና ለተቀማጭ በማለት መደበች፡፡

ከአንድ ዓመት በኋላ የብድር እዳዋን ከፍላ ለመጨረስ አቅዳ በመስራት ላይ ነች፡፡ በየእለቱ የምታገኘውን ገንዘብ እያጠራቀመች በየሳምንቱ ወደ ባንክ ቤት በመሄድ ታስቀምጣለች፡፡

**የቡድን ሥራ፣**

1. "ሥራ የገንዘብ መሠረት ነው" በሚልና "ገንዘብ የሥራ መሠረት ነው" በሚሉ ሁለት ርእሶች ላይ በቡድን ተከፋፍላችሁ ክርክር አካሂዱ፡፡ ለዚህም መነሻችሁ ከላይ የቀረቡትን ሁለት ታሪኮች ይሆናሉ፡፡
2. በአካባቢያችሁ ወደሚገኝ የቁጠባ ተቋም በመሄድ ይህ ተቋም ለተገልጋዮቹ ምን ምን ዓይነት አገልግሎቶችን ወይም ጠቀሜታዎችን እንደሚሰጥ ጠይቃችሁ ያገኛችሁትን መረጃ በጽሁፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

## 9.1.3 የጊዜ ቁጠባ

ሀ/ "ካልተሳፈሩበት ቶሎ ተሸቀዳድሞ ጊዜ ታክሲ አይደለም አይጠብቅም ቆሞ"

ለ/ "ያበሻ ቀጠሮ"

- በተራ ፊደል «ሀ» እና «ለ» በቀረቡት አገላለጾች ላይ በመመሥረት ስለ ጊዜ ያላችሁን አስተያየት ስጡ፡፡

በሰዎች የእለት ከዕለት ሕይወት ውስጥ ጊዜ ትልቅ ሚና አለው፡፡ የጊዜን አጠቃቀም የማያውቅና ያልተረዳ ሰው አስቀድሞ እጁን ለድህነት ሰጥቷል ማለት ይቻላል፡፡ የወደፊት ሕይወቱም አንዳችም ተስፋ ሰጪ ራዕይ አይኖረውም፡፡ ለአብነት ያህልም ትምህርት ቤት አርፍዳችሁ በመድረሳችሁ ምክንያት ፈተና ቢያመልጣችሁ፣ በዚህም የተነሳ በትምህርታችሁ ልትወድቁና ትምህርታችሁን ልታቋርጡ ትችላላችሁ። ትምህርት በማቋረጣችሁም በወደፊት

ሕይወታችሁ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡

የጊዜ ቁጠባ በትንሽ ሰዓት ብዙ ሥራን ማከናወን ወይም ደግሞ አንድን ስራ በሚፈጀው ትክክለኛ ጊዜ መሥራት ማለት ብቻ አይደለም:: አንድን ሥራ በተገቢው ወቅት ማከናወንም ውጤታማ የሆነ የጊዜ አጠቃቀም ነው:: ለምሳሌ የተማሪዎች የትምህርት ቤት ምዝገባ የታወቀ መደበኛ ጊዜ አለው:: አንድ ተማሪ የምዝገባ ጊዜ ካለፈ በኋላ ልመዝገብ ብሎ ቢመጣ ወይም ብላ ብትመጣ ጥያቄው ወቅቱን ያልጠበቀ ስለ ሆነ ለመመዝገብ አይችሉም:: የእርሻ ወቅት፣ የሰብል መሰብሰቢያ ወቅት፣ ወዘተ...በተፈጥሮ የጊዜ ሂደት ላይ የተመሠረቱ ናቸው:: በበጋ ዝናብ ስለማይኖር ዘርን መዝራት አይቻልም::

እንደዚሁም በክረምት የጥራጥሬ ሰብልን ማጨድ አይታሰብም:: ስለሆነም ጊዜን ለመቆጠብ አንድ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚሠራን ስራ በተያዘለት የጊዜ ገደብና በጥራት መሥራት ያስፈልጋል፡፡ በጥራት ያልተሠራ ሥራ እንደ ገና መሥራትን ሊያስከትል ስለሚችል ጊዜ ያለአግባብ ባከነ ማለት ነው፡፡

**መልመጃ 5**

***በሚከተለው ጥያቄ ላይ ተወያዩ፡፡***

**?** የአንድ ሥራ በወቅቱ አለመሠራት ምን ጉዳት ያስከትላል? በምሳሌ አሳዩ::

የጊዜ ሰሌዳ አጠቃቀም ለጊዜ ቁጠባም ሆነ ሥራውን በተገቢው ጊዜ ለማከናወን እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው የእለትና የረጅም ጊዜ ሥራውን ለማከናወን የራሱ የሆነ የጊዜ ሰሌዳ ሊኖረው ይገባል፡፡ የጊዜ ሰሌዳ እንደአካባቢውና እንደሥራው ዓይነት ይለያያል:: ለምሳሌ በገጠር አካባቢ ያሉ ተማሪዎች በትርፍ ጊዜያቸው ከብት ሊጠብቁ፣ ከወላጆቻቸው ጋር ወደ እርሻ ቦታ ሊሄዱ፣ የጓሮ አትክልት ሊኮተኩቱ፣ በመስኖ በመጠቀም እርሻቸውን ሊያጠጡ ወይም ዋና ሊዋኙ ይችላሉ:: ስለሆነም የራሳቸው የጊዜ ሰሌዳ ሊኖራቸው ይገባል::

**የቡድን ሥራ፣**

የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የዓመቱን ብሔራዊ ፈተና በሚገባ እንዲያልፉ መምህራቸው ስለአጠናንና ስለጊዜ አጠቃቀም በቂ ግንዛቤ ሰጧቸው:: እያንዳንዱ ተማሪም የአንድ ወር የጊዜ አጠቃቀም ሰሌዳ እንዲያቀርቡ አዘዙ:: ከቀረቡት መካከል የሚከተሉትን ወስዳችሁ ከሠንጠረዡ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

| የሚፈጸሙ ተግባራት | የመደቡት ጊዜ | |
|---|---|---|
| | ተማሪ «ሀ» | ተማሪ «ለ» |
| ለጥናት | 1:00-2:00 ሰዓት ያህል | 2:00-3:00 ሰዓት ያህል |
| ለትምህርት ቤት ቆይታ | ከ6:00-7:00 ሰዓት ያህል | ከ6:00-7:00 ሰዓት ያህል |
| ለመኝታ | 10:00 | 8:00 |
| ለጨዋታ/ ለእረፍት | 3:00 | - |
| ለቤት ውስጥ ሥራ (ቤተሰብን ለማገዝ) | 1:00 | 3:00 |
| መጻህፍት ለማንበብ | 1:00 | 2:00 |
| ጋዜጣ፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ለመከታተል | 1:00 | 2:00 |

***ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

ሀ. በሠንጠረዡ ከተመለከቱት የሁለቱ ተማሪዎች የጊዜ ሰሌዳዎች የትኛው የተሻለ ነው? ለምን?

ለ. የትኛው ተማሪ የበለጠ ጊዜ ለጥናት ያውላል?

ሐ. የትኛው ተማሪ ከትምህርት ቤት ውጪ ሥራ ይበዛባታል?

መ. በተመለከታችሁት ሞዴል መሠረት የራሳችሁን የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት ለክፍል ውይይት አቅርቡ::

## 9.2 የቁጠባ ባህል

"በበጋ ጸሀይ ፈራ በክረምት ዝናብ ፈራ ልጄ እንጀራ ቢለው በጅብ አስፈራራ።"

- ከዚህ ባህላዊ ግጥም ምን ተገነዘባችሁ?

## በቁም ሳይኖር ስመቃብር፣

ሰውየው እናቱ ሲሞቱ የመቃብር ሥርዓት ማስ ፈጸሚያ ገንዘብ ያጣል። በሕይወት ሳሉም ቢሆን የሁለቱም ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ "የመንደሩ ሰዎች እንዳደረጉ ያድ ርጉ፣ አስከሬን አጠገባቸው ተቀምጠ ዝም ብለው አይመለከቱም" ብሎ ይሰወራል። ከሁ ለት ቀናት በኋላ ተመልሶ ቢጠይቅ የእናቱ አስከሬን እርሱን እየጠበቀ መሆኑን ይነግሩ ታል። በዚህ ጊዜ ኃላፊነቱ ከእርሱ ላይ እንዳ ልወረደ ይረዳል።

ተመልሶ ወደቤቱ ይገባና ገንዘብ ካላቸው ሰዎች በአራጣ ይበደርና ቀብሩን ያስፈጽማል። በሕይወት ሳሉ ለብሰውት የማያውቁትን አዲስ ኩታ ለቀብራቸው ሥርዓት ይገዛና አስከሬና ቸው ይለብሳል። በዚህ ጊዜ ሲያለቅስ ከዚህ የሚከተለውን ሙሾ አወረደ፡፡

ለብሳ የማታውቀውን ጃኖ ኩታ ለብሳ፣
ተመለሽስ ቢሏት በየት ተመልሳ።
ፍሰሽ እናቴ ፍሰሽ፣
እኔን በእዳ ለውሰሽ።

(ምንጭ፣ አዲስ አድማስ ጋዜጣ፣ 1992)

**መልመጃ 6**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. እናቱ የሞቱበት ሰውዬ ችግሩን እቤቱ አስቀምጦ መሰወሩ፣ ከዚያም የፈራው ችግር ሌሎች ጣልቃ ገብተው መፍትሄ አስ መፈለጋቸው ምንን ያመለክታል?
2. በአራጣ የተበደረውን ገንዘብ ለመክፈል በሚያደርገው ጥረት የራሱን የወደፊት ሕይወት በአግባቡ ለመኖር ይችላል ትላላችሁ? ለምን?

የአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ኑሮ የተመሠ ረተው በቤተሰብ እርስ በርስ መደጋገፍ ላይ ነው። ዜጎቻችን እንደአውሮፓውያን በእርጅና ዘመናቸው የሚደጎሙበት ማህበራዊ ዋስትና የላቸውም። አረጋውያን ቋሚ ቅርስ ወይም ተቀ ማጭ ገንዘብ ስለሌላቸው የሚጦሩበትና የል ጆቻቸውን ድጋፍ የሚሹበት ሁኔታ ብዙ ነው። ስለዚህ በድህነት የሚኖሩ ሰዎች እድሜያቸው ሲገፋ የልጆቻቸው ጥገኛ ይሆናሉ። ችግሩን የበ ለጠ የከፋ የሚያደርገው ደግሞ በሀዘንና በደ ስታ ጊዜ የሚከናወኑ ባህላዊ ሥርዓቶች ብዙ ወጪን የሚጠይቁ መሆናቸው ነው። ባህላዊ ሥርዓቶችን ለማክበርም ሆነ ችግርን ለመቋቋም የቁጠባ ዘዴን ማዳበር አስፈላጊ ነው። ይህም ሲባል የተቆጠበን ገንዘብ ወይም ንብረት በአ ንድ አጋጣሚ ብቻ ማውደም ተገቢ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት፡፡

### የቡድን ሥራ፣

በአካባቢያችሁ የተለመደውን የሀዘንና የቀብር ሥነ ሥርዓት ጠይቁ በመረዳት

ሀ) ለሥርዓቱ የሚያስፈልጉ ክንውኖችን
ለ) ለእነዚህ ክንውኖች የሚያስፈልጉ ዝግጅ ቶችንና ወጪዎችን በዝርዝር አሳዩ። በዝ ርዝሩ የተመለከቱት ነጥቦች ምን ያህል ከቁጠባ ጋር እንደሚቃረኑ ወይም እንደሚ ጣጣሙ አመልክቱ፡፡

የምጣኔ ሀብት ምሁራን እንደሚሉት ሰዎች የሚቆጥቡት በሚከተሉት ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ነው። እነዚህም

***ሀ. ለሚጠበቁና ለማይጠበቁ አጋጣሚዎች ወይም ችግሮች ለማዋል፡፡*** የሚጠበቁ ችግሮች የሰ ዎችን ማሕበራዊ ኑሮ መሠረትያደረጉ ሁኔ ታዎችን ተመርኩዘው የሚከሰቱት ናቸው። ሰዎች በየእለቱ ምግብና መጠለያ ያስፈል ጋቸዋል፡፡

ልደት፣ የመስቀል በዓል፣ ፋሲካ፣ የአረፋና መው ሊድ በዓላት ወጪዎች ያስወጣሉ። የትምህ ርት ቤት መመዝገቢያ፣ የቤት ኪራይ የመሳሰሉ ትም በወጪ መዝገብ የሚገቡ ናቸው። ሰዎች አስቀድመው ለእነዚህ የበዓላት የሚያወጡትን ወጪ ስለሚያዘጋጁ የሚጠበቁ ወጪዎች ናቸው። ሳይጠበቁ የሚያጋጥሙ ወጪዎች የሚ ባሉት ደግሞ አደጋ፣ ህመም፣ ሞት እና የመሳ ሰሉት ናቸው፡፡

ለ. ቋሚ ንብረት ለማፍራት፡፡ ሰዎች በተረጋጋ ኑሮ ውስጥ ካሉ ለረጅም ጊዜ የሚገለገ ሉባቸውንና ከዚያም ከራሳቸው አልፈው ለቀ ጣይ ትውልድ የሚሸጋገሩ ንብረቶችን ያፈ ራሉ:: ቤት መሥራት፣ ቡና እና እንሰት መት ከል፣ ደን ማልማት፣ የቤት እንስሳት ማር ባት፣ ድርጅት መክፈት... መኪና መግዛት እንደምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው::

**መልመጃ 7**

**?** ***በሚከተለው ዝርዝር ውስጥ የተመለከ ቱት ጉዳዮች የሚጠበቁ ወይም የማይጠ በቁ ወጪዎች መሆናቸውን በምክንያት እያስደገፋችሁ አመልክቱ::***

## 9.3 በእቅድ መመራት፤

| አጋጣሚ | የሚጠበቁ | የማይጠበቁ | ሁለቱም |
|---|---|---|---|
| ሠርግ | | | |
| ሞት | | | |
| አርባ/ተዝካር | | | |
| ማህበር | | | |
| እንግዳ | | | |
| የታሪካዊና ባህላዊ ቦታዎች ጉብኝት | | | |
| ልደት | | | |
| ሕክምና | | | |
| መዝናኛ | | | |
| እርዳታ (ለሰዎች የሚሰጥ) | | | |
| የተለያዩ ሱሶች | | | |

- ስለእቅድ ምንነትና አፈጻጸም የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ::

እቅድ አንድን ሥራ ለመሥራት፣ ወይም ውጤት ለማግኘት የምንጠቀምበት የአሠራር ሥልት መንደፍ ማለት ነው:: ያንን ያሠራር ሥልት በምንነድፍበት ጊዜ ለተግባራዊነቱ የሚጠቅሙን ሥልቶች ደግሞ ያስፈልጉናል:: ለእቅድ መሳካት እንግዲህ ሦስት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው::

እነዚህም ልናሳካ የምንፈልገው ተግባር፣ ያንን ውጤት ለማግኘት የሚረዱን ስልቶችና ለሥራ የሚያስፈልጉን መሣሪያዎች ናቸው:: ለምሳሌ የአንድ ሰው እቅድ ከሁለት ዓመት በኋላ መኪና መግዛት ነው እንበል። መኪና ለመግ ዛት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ደግሞ ገንዘብ እና የመኪና መንዳት ችሎታን ማጎልበት ይሆናል:: ገንዘብ ለማግኘት ማጠራቀም ይገ ባል:: መኪና ለመንዳት አስቀድሞ የመንጃ ፈቃድ መያዝን ግድ ይላል:: ቀጥሎ የቀረ በውን ምሳሌ በተጨማሪ እንመልከት::

ከላይ የቀረበውን እቅድ ለማስፈጸም የሚረዱ ሥልቶች ያስፈልጋሉ:: ለምሳሌ ገንዘብን በሚ መለከት እቁብ መግባል፣ አለበለዚያም ከመጀ መሪያው ዓመት ከሚገኝ ገቢ ላይ እየቆጠቡ በማስቀመጥ የስነልቡናዊ ዝግጅት ማድረግ::

**እቅድ፣ በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት ዲፕሎማ የሚያስገኝ ትምህርት መማር፣ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች፣**

- **ለትምህርት የሚከፈል፣ ለመጓጓዣና ለትምህርት መሳሪያዎች መግዣ የሚውል ገንዘብ ማዘጋጀት::**
- **ጊዜ መመደብ:: ሠራተኛ ከሆኑ እየሠሩ ለመማር ራስን ማዘጋጀት::**
- **ለጥናት የሚሆን ጊዜ መመደብ::**

ጊዜን በሚመለከት ትምህርት ቤት ለመሄድ በሚያስችለው ጊዜ የተለመዱ ሌሎች ተግባ ራት ካሉ እነርሱን መተው ይገባል:: ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች ከሥራ ሰዓት በኋላ በቡድን ሆነው በመዝናኛ ቦታዎች ጊዜያቸውን ማሳለፍ ያዘወትራሉ:: የእነዚህ ቡድኖች አባል የሆነ ሰው ጊዜውን ለትምህርት ማዋል ከፈለገ መዝ ናናቱን ሊተው ይገባል::

ጊዜያቸውን በቤት ውስጥ የሚያሳልፉ ሰዎችም የቤት ውስጥ ተግባሮቻቸውን የሚፈጽሙበት ሌላ ጊዜ በመመደብ ማስተካከል ይኖርባቸዋል:: ለጥናት የሚውል ሰዓት በቀን ከሌላቸው ደግሞ ከሌሊት እንቅልፋቸው ሰዓት በመቀነስ ሊጠቀሙ ግድ ይላቸዋል::

**መልመጃ 8**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. እቅድን ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻለው በምን ዓይነት ዘዴ ነው?
2. ቀጥሉ ከቀረቡት ሁለት ጥያቄዎች አንዱን ብቻ በመምረጥ መልሱ::
   ሀ. አንድ ሰው የመኖሪያ ቤት ለመሥራት ቢፈልግ አስቀድሞ ምን ምን ተግባሮችን መፈጸም ይኖርበታል?
   ለ. ከአንድ ዓመት በኋላ ምን መሆን ትፈልጋላችሁ? ይህንን እቅዳችሁን ለማሟላት የሚያስፈልጓችሁን ነገሮች፣ እነዚህንም አስፈላጊ ግብአቶች ልታገኙ የምትችሉባቸውን መንገዶች ግለጹ::

### 9.3.1 በአቅም ልክ አለመመራት የሚያስከትሏቸው ችግሮች

- አቅምን በማወቅና አቅምን ባለማወቅ መካከል ያሉትን ልዩነቶች ምሳሌ በመስጠት ግለጹ::

**አቅምን አለማወቅ፤**

በአንድ መንደር ውስጥ የሚኖሩት አቶ ግርማ ሁለት ዓይነት የገቢ ምንጮች ነበሯቸው:: ወፍጮ ቤትና የጡረታ አበል:: ሰውየው በመንደሩ የሚታወቁት በዓመት ውስጥ የተለያዩ ድግሶችን ደግሶ ሰዎችን በማብላት ነው:: ለምሳሌ የልጃቸውን ልደት ሲደግሱ ጎረቤቶቻቸው በቀላል ወጪ የሚያደርጉትን ድግስ እሳቸው ግን አንድ ሙክት አርደው፣ ጠላ አስጠምቀው፣ ዳቦ አስደፍተው፣ መንገደኛውን ሳይቀር ያበላሉ:: የመደገሻ ገንዘብ አስቀድመው ያዘጋጃሉ:: በሰፈሩ የተለያዩ የእቁብ ማህበራት አሉ:: እርሳቸው የሁለት እቁብ አባልም ናቸው:: ሰሞኑን የወፍጪቸው ሞተር ተበላሽቶ ሥራ አቁሟል:: ለመንደሩ የመንገድ ሥራ መዋጮም ተጠይቀዋል:: እርሳቸው ግን ለዚያ ቅድሚያ የሚሰጡ አይመስሉም:: እርሳቸው ዘንድ ተቀምጣ የኮሌጅ ትምርቷን ስትማር የነበረችው የእህታቸው ልጅ ሰኔ ወር መጨረሻ ላይ ትመረቃለች:: የምረቃ ድግስ እንደሚደገስላት ተስፋ አላት::

ገጠር ከሚኖሩት ወላጆቿ ምንም ገንዘብ እንደማታገኝ ታውቃለች:: አቶ ግርማ ግን ለእህታቸው ልጅ ምረቃ የተሰማቸውን ደስታ ለመግለጽ የእቁብ ገንዘብ ስለማይበቃቸው ከሰፈሩ አራጣ አበዳሪ ለመበደር ደጅ መጥናት ጀምረዋል:: ለድግሱ ያወጡትን ገንዘብ ወደፊት ሥራ ስትጀምር እንደምትከፍላቸው ነግረዋት እርሷም የጊዜው ደስታዋ እንዳይቀርባት ተስማምታለች:: ያላስቀመጡትን ገንዘብ በማለም ከፍተኛና ብዙ ወጪ የሚጠይቁ በጊዜያዊ ደስታና ፈንጠዝያ ላይ ያተኮሩ ዝግጅቶችን ለማዘጋጀት ላይና ታች እየተሯሯጡ ይገኛሉ::

**መልመጃ 9**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መለሱ::*

1. አቶ ግርማ የሚከተሉት የቁጠባ ዘዴ አለ? ካለ ይህን ዘዴያቸውን በአግባቡ ተጠቅመውበታል ወይስ አልተጠቀሙበትም? እንዴት?
2. የአቶ ግርማ በአቅም ልክ ለመኖር አለመዘጋጀት የሚያስከትላቸውን ችግሮች ዘርዝሩ::

ብልህ ሰዎች የጭልፊቶችን ዓይነት ኑሮ መምራት ይችሉበታል:: ጭልፊቶች መላ ክረምትን የሚያሳልፉት በጎጆዎቻቸው ውስጥ ነው:: በወቅቱ የሚመገቡትም በበጋ ወራት ከእለት ምግባቸው በላይ እያደኑ ያስቀመጡትን ምግብ ነው::

ብዙ ሰዎች ሀብትና ንብረት ባላቸው ጊዜ ለችግር ጊዜ የሚሆናቸውን ነዋይ ያላግባብ ያጠፉና የወጣትነት ዘመናቸው አልፎ አረጋውያን ሲሆኑ ይቸገራሉ:: ይህ በእቅድ አለመመራት ከሚያስከ

ትላቸው ሁኔታዎች ዋነኛው ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በእቅድ እየተመሩ ጥሩ የቁጠባ ባህል ማዳበር የሚሰጣቸው ጠቀሜታዎች ወይም የሚ ያስገኛቸው ውጤቶች አሉ፡፡

የቁጠባ ውጤቶች ማለት አንድ ሰው ከሚያ ገኘው ገቢ ላይ እየቆጠበ በማስቀመጥ ከአጭ ርና ከረጅም የጊዜ ሂደቶች በኋላ የሚያገኛቸውን ጠቀሜታዎች ለማመልከት ነው፡፡ ሁለት ዓይነት የቁጠባ ውጤቶች አሉ፤

**በአጭር ጊዜ የሚታይ የቁጠባ ውጤት፣** በሰዎች እለታዊ ኑሮ ውስጥ የሚከሰትን ለውጥ ይመ ለከታል፡፡ ለምሳሌ መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸው ተጓድለውባቸው የነበሩ ሰዎች በልዩ ልዩ የሥራ ጥረት ተጨማሪ ነገሮችን ሊገዙ ሲችሉ ማለት ነው፡፡ ቀያሬ ልብስ ያልነበራቸው እነዚህን ሲያ ሟሉ፣ በድህነት ሳቢያ ትምህርታቸውን ማሻሻል ያልቻሉ ሰዎች በቆጠቡት ገንዘብ መማር ሲችሉ፣ በቁጠባ ሥልት በአጭር ጊዜ ተጠቃሚ ሆኑ ለማ ለት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በአጭር ጊዜ የሚታይ የቁጠባ ውጤ ት ለመኖር አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ነገሮችን ማሟላት ማለትም መራብንና መታረዝን ማስ ወገድ ነው፡፡

**በረጅም ጊዜ የሚታይ የቁጠባ ውጤት፣** ይህ ኛው የቁጠባ አይነት ውጤቱ የሚታየው ከረጅም ጊዜ በኋላ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሰዎች መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ከማሟላት አልፈው ቋሚ ንብ ረት ማፍራት መቻላቸውን ያመለክታል፡፡ ቤት ያልነበራቸው ቀስ በቀስ ቆጥበው ቤት መሥራት ሲችሉ፣ አንድ በሬና አንድ ላም ብቻ የነበራቸው የብዙ ከብቶች ባለቤት ሲሆኑ የቁጠባን መሠረታዊ አስፈላጊነት መረዳታቸውን ያመለክታል፡፡

ልጆችን በአግባቡ ማሳደግም የቁጠባ ሌላው ገጽታ በመሆኑ የወደፊት ሀብትን በታዳጊዎች አእምሮ ውስጥ እንደማከማቸት ይቆጠራል፡፡ የተማሩና ጥሩ ደረጃ ላይ የደረሱ ልጆች ራሳቸውን ከመ ቻል አልፈው ቤተሰቦቻቸውንና ሀገራቸውን ይጠ ቅማሉ፡፡

**መልመጃ 10**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተከራከሩ፡፡***

?

1. ከተማረ የሰው ኃይልና ከተፈጥሮ ሃብት የትኛው የበለጠ ለሀገር እድገት ይጠቅ ማል? የሚለውን በክርክር መልክ ተዘጋ ጅታችሁ ተነጋገሩበት፡፡
2. በክርክሩ ላይ በመመርኮዝ ልጆቻቸውን ከሚያስተምሩና ከማያስተምሩ ወላጆች የት ኞቹ ድህነትን በመዋጋት ሂደት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ አስተያየት ስጡበት፡፡

### 9.3.2 በእቅድ አለመመራት የሚያስከትላቸው ችግሮች

- እቅድ ማለት ምን ማለት ነው? የእቅድ ማስፈጸሚያ ስልቶችስ ምንድን ናቸው?

**የቆጠቡ ተጠቀሙ ያልቆጠቡ ተለቀሙ፤**

በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሁለት ጎረቤታሞች አሉ፡፡ ሁለቱም የአንድ ፋብሪካ ሠራተኞች ናቸው፡፡ አንደኛው አቶ ዘለለው ስድስት ልጆች አሏቸው፡፡ አቶ ዘለለው ደስተኛ ኑሮ አይኖሩም፡፡ ሰካራም በመሆናቸው በቤተሰባቸው ውስጥ ሠላም የለም፡፡ ወደ መዝናኛ ክበብ እየገቡ ከረንቡላ የሚባል ጨዋታ በገንዘብ ይጫወታሉ፡፡

ብዙ ጊዜ ገንዘባቸውን በዚህ ምክንያት ያባክ ናሉ፡፡ እንዲያውም በአራጣ ብድር እዳ ምክንያት የቤተሰባቸው መገልገያ የነበረች ብስክሌት ሳት ቀር በእዳ ተይዛለች፡፡ ስለዚህ ልጆቻቸውን እን ኩዋን ለማስተማር በአግባቡ ለመመገብ ያልቻ ሉ ሰው ናቸው፡፡ ባለቤታቸው በተደራረበ ወሊድ ምክንያት አቅመ ደካማ ሆነዋል፡፡

ሁለተኛው አቶ ከፍያለው ይባላሉ፡፡ ባለቤታቸው የማታ ትምህርት ይከታተላሉ፡፡ አራት ልጆች አሏቸው፡፡ የመሥሪያ ቤታቸው የቁጠባ ሕብረት ስራ ማሕበር አባል በመሆን በወር የደመወዛቸ ውን ሶስት በመቶ ይቆጥባሉ፡፡ ይህ ማሕበራ ቸው በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ለልጆቻቸው የት ምህርት ቤት ወጪ ስለሚሸፍንላቸውና እርሳ ቸውም በሚያደርጉት ጥረት ሁሉም ልጆቻቸው ይማራሉ፡፡

**መልመጃ 11**

***ከላይ በቀረበው ምንባብ መሠረት የሚከተለውን ጥያቄ መልሱ፡፡***

?

**በአቶ ከፍያለውና በአቶ ዘለለው መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ከሁለቱ ጎረቤታሞች መካከል ቆጣቢ ማነው?**

**በዕቅድ አለመመራት በግላዊም ሆነ በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ጉዳት ያመጣል፡፡ ዕቅድ ገንዘብን፣ ጊዜንና ጉልበትን በአስፈላጊ ሁኔታዎችና አግባብነት ባላቸው ተግባራት ላይ ለማዋል ተጠንቅቆ መጓዝ ነው፡፡ ይህን አለማድረግ ሥራን በአግባቡ እንዳይሠራ፣ ጠቀሜታ በሌላቸው ጉዳዮች ላይ ገንዘብ እንዲባክን ያደርጋል፡፡ በመሆኑም በግል ኑሮ መሻሻል ላይና በቤተሰብ ውስጥ ሠላምና መረጋጋት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡**

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ሰዎች ዛሬ ላይ ሆነው ስለነገ ማቀድ የሚችሉ ብቸኛ ፍጡሮች ናቸው፡፡ የሚያገኙትን ገቢ ለኑሯቸው ለሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ብቻ በማዋል ለወደፊት እቅዳቸው ማስፈጸሚያ መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡ ሦስት የቁጠባ ዓይነቶች አሉ፡፡ አንዱ በዓይነት የሚደረግ ነው፡፡ ሁለተኛው በገንዘብ የሚደረገው ቁጠባ ሲሆን ሦስተኛው ደግሞ የጊዜ ቁጠባ ነው፡፡

ሰዎች ለነገ ሕይወታቸው ዋስትና ሲኖራቸው የሚችለው በጊዜ፣ በገንዘብና በንብረት አጠቃቀም አግባብ ያለው አሠራር ከተከተሉ ብቻ ነው፡፡ ሥራን በተወሰነለት ጊዜና ወቅት ማከናወን፣ በእቅድ መመራት ለእድገት ወሳኝ የሆኑ ነገሮች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች ጥሩ ውጤት ለማምጣት፣ ገበሬዎች ውጤታማ ሆነው ረሀብን የሚዋጉት ጊዜያቸውንና ወቅቱን በአግባቡ ተጠቅመው ከሠሩ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ በዚህ መልኩ የሚደረግ ቁጠባ ብዙ ዓይነት ውጤቶች አሉት፡፡ ለምሳሌ በአጭር ጊዜ ውስጥ ኑሮን ማሻሻል ይቻላል፡፡ ከዚህም አልፎ ለትውልድ የሚተላለፍ ሀብት ማፍራት ይቻላል፡፡

ለመጪው ትውልድ ማሰብና የኑሮ ዋስትና ማቆየት የሰዎች አጠቃላይ ኃላፊነት ነው፡፡ ስለሆነም ከግለሰብ አንስቶ የሀገር ህልውና የሚረጋገጠው በቁጠባና በእቅድ ላይ የተመሰረተ የአኗኗር ዘዴ ካለ ብቻ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ብዙ ሰዎችን ለድህነት የሚዳርጉ ኃላቀር ልማዶች በርካታ ናቸው፡፡ የእነዚህ ልማዶች አጠቃላይ መገለጫ ብኩንነት ነው፡፡ ያለእቅድ መኖር፣ ድግስ ማብዛት፣ ጥሪት አላግባብ በጊዜያዊ ፍጆታ መጨረስ ከብኩንነት መገለጫዎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ስለዚህ ሰዎች ከወጣትነት እድሜያቸው ጀምሮ የሚያገ ኙትን ገቢ በአግባቡ መጠቀም፣ ለመጪ ሕይወታቸውም እያሰቡ መኖርን መልመድ ይኖርባቸዋል፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

| | |
|---|---|
| አራጣ፣ | ትርፍ፣ ወለድ፣ የወለድ ገንዘብ፡፡ |
| ስስት፣ | ንፍገት፣ እያስ የለም ማለት፡፡ |
| የከበሩ ድንጋዮች፣ | ውድ የሆኑና በቀላሉ የማይገኙ፡፡ እንደ አልማዝና ልዩ ልዩ ማእድናት የመሳሰሉ፡፡ |
| ፍጆታ፣ | ጥቅም ላይ የሚውል፣ ለምግብ፣ ለልብስ፣ ለመሳሰሉት፡፡ |
| ንዋይ፣ | ገንዘብ፡፡ |
| ግብአት፣ | አንድን ነገር ለመሥራት የሚያስፈልጉ ወይም የሚጠቅሙ መገልገያዎች፡፡ |
| አረጋውያን፣ | በእድሜ የገፉ፣ ረጅም እድሜ ያሳለፉ ሰዎች፣ ጡረተኞች፡፡ |
| ከእጅ ወደአፍ፣ | ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ፣ ያገኙትን ለእለት ምግብ ብቻ ማዋል፡፡ |

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

***ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ።***

**I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ።**

1. *መቆጠብ ማለት አሁን ከሚያስፈልገን በመቀነስ ማስቀመጥ ማለት ነው።*
2. *የሕዝብንና የመንግሥት ንብረት በአግባቡ መጠቀም የቁጠባ አካል ነው።*
3. *ስስትና ቁጠባ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው።*
4. *በአጭር ጊዜ የሚታይ ቁጠባ በረጅም ጊዜ ለሚታየው ቁጠባ መሠረት ነው።*
5. *የተፈጥሮ ሀብት ካለ ድህነት የለም።*

**II. በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን በ "ሀ" ሥር ካሉት ሥር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. *በጊዜ ሂደት የሚታይ፣* | *ሀ. በአይነት የሚደረግ ቁጠባ።* |
| 2. *ወጪና ገቢን ማስላት፣* | *ለ. ወፍጮ ቤት።* |
| 3. *የጊዜ ሰሌዳ፣* | *ሐ. የስራ መመሪያ።* |
| 4. *የጉተራ እህል ክምችት፣* | *መ. የገንዘብ አጠቃቀምን ማወቅ።* |
| 5. ባንክ ቤት፣ | *ሠ. የገንዘብ መቆጠቢያ።* |
| | *ረ. የረጅም ጊዜ ዕቅድ።* |
| | *ሰ. የገቢ ምንጭ።* |

**III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ።**

1. *ከሚከተሉት ውስጥ የዓይነት ቁጠባ ያልሆነው የቱ ነው?*
   *ሀ. መኪና፣* *ለ. እንቁ፣* *ሐ. እንስት፣* *መ. እውቀት።*
2. *ጊዜ ወርቅ ነው ማለት ምን ማለት ነው?*
   *ሀ. ጊዜ እንደወርቅ በገንዘብ ይመነዘራል ማለት ነው፣*
   *ለ. ጊዜ ከሌሎች ሰዎች ልንበደረው የምንችለው ነው ማለት ነው፣*
   *ሐ. ጊዜ ብልጭልጭ ነው ማለት ነው፣*
   *መ. መልሱ አልተሰጠም።*
3. ስስት ከቁጠባ የሚለየው፤
   *ሀ. ራስን በመጉዳት መርህ ላይ ስለሚመሠረት፣*
   *ለ. ከመጠን ያለፈ ራስ ወዳድነት ስለሚንጸባረቅበት፣*
   *ሐ. አዘውትሮ መሥራትን ስለማያነቃቃ፣*
   *መ. ሁሉም መልሶች ናቸው።*

4. ገንዘብ በእጅ ከማስቀመጥ የተሻለና አስተማማኝ የማስቀመጫ ዘዴ፤
   ሀ. በባንክ ማስቀመጥ፣
   ለ. የመድህን ዋስትና መግባት፣
   ሐ. በቋሚ ንብረት ላይ ማዋል፣
   መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ።

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ።

1. በኑሮ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን በቅደም ተከተል አዘጋጅቶ መሥራት ___________________ ይባላል።
2. ሰዎች የሚቆጥቡባቸው ሁለት መሠረታውያን ምክንያቶች___________________ እና ___________________ ናቸው።

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ።

1. ገንዘብን ከማስቀመጥ ይልቅ ሥራ ላይ ማዋል ትርፋማነትንና ቆጣቢነትን ሊያሳይ የሚችልበትን መንገድ አሰረዱ።
2. የቁጠባ ዓይነቶችን በምሳሌ እያቀረባችሁ ዘርዝሩ፡፡

# ምዕራፍ አሥር

# ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቂ/ ስታጠናቅቅ፤***

- በአካባቢያዊና በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ትረዳለህ/ትረጃለሽ።
- የሲቪክ ማሕበራት ሚናዎችን ትገነዘባለህ/ ትገነዘቢያለሽ ።
- በሲቪክ ማሕበራት መሳተፍ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ታውቃለህ/ታውቂያለሽ።

## 10.1 በአካባቢ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ

### 10.1.1 በአካባቢ የልማት ዘመቻ በንቃት መሳተፍ



*ሥዕል 10.1 አካባቢያችንን በጋራ እናልማ*

- ፎቶግራፉ ምን እንደሚያሳይ አጠር በማድረግ አሰረዱ።
- በፎቶግራፉ ላይ የሚንቀሳቀሱት ሰዎች ሥራውን በምን አኳኋን እንደሚያካሂዱ ግለጹ።

### የመንዴራ ጉብኝት፤

የገልሞሌ ወረዳ ትርፍ አምራች የምትባል በተፈጥሮ በጣም የለማችና የበለፀገች አካባቢ ነች። መሬቱ የሰጡትን ሁሉ የሚያበቅል እን ደደቹ ያሉ ወንዞች ዓመቱን ሙሉ በከንቱ የሚ ፈሱባት፣ እንደማንጉሬ ያሉ ደኖች በርካታ የዱር እንሰሳትና አእዋፍን አቅፈው የያዙባት ወረዳ ነች። ሕዝቡ በግብርና የሚተዳደር ሲሆን በዓመት አንዴ ለቀለቡ ጤፍና ስንዴ በማምረት ከእጅ ወደአፍ የሆነ ኑሮውን እንደአባቶቹ ይገፋል። መሠረተ ልማት የሚባል አይታወቅም። ማኀበራዊ ተቋማት የሉም። ሕፃናት በእረኝነት ይኖራሉ፤ ሰዎች በቀላል በሽታዎች ይጠቃሉ፤ ይሞታሉ። እናቶች በወሊድ ምክንያት በብዛት ይረገፋሉ። ችግሩ ተነግሮ አያልቅም። ሕዝቡ መንግሥት ምንም አላደረገልንም እያለ ይወቅሳል። ሀሉንም ማሟላት ያለበት መንግሥት እንደሆ ነም ያምናል። ሕዝቡን ለልማት የሚያነሳሳ ሲመጣም አጥብቆ ይቃወማል።

ዛሬ ከገልሞሌ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ሰዎች፣ የወጣቶችና የሴቶች ተወካዮች የተውጣጣ የልዑካን ቡድን ሁለት የጭነት መኪናዎች ለጉብኝት ወደ መንዴራ ወረዳ እየተጓዘ ነው። አባላቱ የወረዳቸውን ልምላሜ በኩራት እየቃኙ አቋርጠው ወደ መንዴራ ገሠገሡ።

መንዴራ የምትታወቀው ድርቅ የሚፈራረቅባትና ሕዝቧ በእርዳታ ስንዴና ዘይት በመኖሩ ወጣቱም እየተሰደደ በተለያዩ ከተሞች ወይም በውጪ ሀገር በመኖሩ ነበር። ተራሮቿ ከዕፅዋት አልባሳቷ ተጋልጠው፣ ድንጋዮቿ አፍጠው ስለሚታዩ ያዝኑላት ነበር። የልዑካን ቡድኑ አባላት ጉብኝቶቹን ካከናወኑ በኋላ ግን ስለመንዴራ የነበራቸው ስሜትና አመለካከት በፍፁም ተለውጧል።

*መንዴራን ያገኟት በልጆቹ መነሳሳትና ንቁ ተሳትፎ እየተለወጠች ነበር፡፡ የመንዴራ ድንጋዮች በአቅራቢያውና በሩቅ ላሉ ከተሞች የህንፃዎቻቸው መዋቢያ ውድ ጌጦች ሆነው ተገኙ፡፡ የመንዴራ ተራሮችና ሜዳዎች ከእንሰሳት ንክኪ እየተከለሉ በመጠበቃቸው በእፅዋት፣ በልዩ ልዩ ሳሮችና በአበቦች ማሸብረቅ ጀመሩ፡፡ ይዘውት የቆዩትን የቀንድ ከብቶች፣ የበጐችና የፍየሎች እርባታ እንዲሁም የንብ ልማት ልማድ ወደ ዘመናዊ ሥርዓት በማሸጋገር የቆዳና የቁም እንሰሳት አምራቾች ሆኑ፡፡ ይህን ለማስፋፋት በወረዳው የሚገኙትም ሆኑ ተሰደው በየቦታው የሚማስኑት የመንዴራ ልጆች እጆቻቸውን አስተባብረው ተነሱ፡፡ ይህን የሕዝብ መነሳሳት የተመለከተው መንግሥትና ሌሎችም የልማት ኃይሎች እገዛ አደረጉ፡፡*

*መንግሥት መንገዶችንና የመገናኛ አውታሮችን ዘረጋላቸው፡፡ እንዲሁም የእንስሳት የሕክምና ማዕከላትና የገበሬዎች ሙያ ማሠልጠኛዎችን ከፍቶላቸው ባለሙያዎችም አሰማራላቸው፡፡ በሕዝቡ መገንባት የተጀመሩትን የትምህርትና የጤና አገልግሎት ማዕካላትንም አጠናከረላቸው፡፡ በልማቱ የተሳቡ ባለሀብቶችም ሁለት የቆዳ ፋብሪካዎችና አንድ የሥጋ ማቀነባበሪያ እንዲሁም የማር ምርት ማደራጃ ፋብሪካዎችን ገነቡ፡፡*

*እነዚህን ሁሉ የተመለከተው የገልሞሌ የልዑካን ቡድን ለማመን አስቸገረው፡፡ አባላቱ ሁሉንም መንግሥት ይስራልን እያሉ አንጋጠው መጠበቃቸው አስቆጫቸው፡፡ በባከነው ጊዜ እልህና ቁጭት ይዟቸው የተመለከቱት ሁሉ በነሱም ውስጥ የተስፋ ብርሃን ለኰሶ ሕዝባቸውን ወደንቁ ተሳትፎ ለማነሳሳት በመጣደፍ የመልስ ጉዟቸውን ማድረግ ቀጠሉ፡፡*

## መልመጃ 1

***እራሳችሁን በአራት ቡድን አደራጁ፡፡ በየቡድናችሁም በመሆን ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡ በማስከተልም የደረሳችሁባቸውን መልሶች ለክፍሉ አቅርቡ፡፡***

1. የገልሞሌ ሕዝብ አንዱ ዋና ችግር የጥገኝነት ስሜት ነበር ቢባል ትስማማላችሁ? ለምን?
2. እናንተ የገልሞሌ ነዋሪዎችና የልዑካን ቡድኑ አባላት ብትሆኑ ከጉብኝቱ መልስ ምን ታደርጉ ነበር፡፡ ቡድናችሁን እንደልዑኩ በመቁጠር ምክሩና የምታከናወኑትን ለክፍሉ አቅርቡ፡፡
3. በመንዴራ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ያስገኘው ውጤት ነበር? ምን እንደሆነና እንዴት እንደተገኘ አስረዱ፡፡

በአካባቢ የልማት ዘመቻ ላይ በንቃት መሳተፍ ዜጎች የሚፈለግባቸውን ዓይነት አስተዋጽኦ የሚያደርጉበት ተግባር ነው፡፡ ይኸውም በራስ ተነሳሽነትና በሙሉ ፈቃደኝነት የሚፈፀም ነው፡፡ ለጋራ አካባቢያዊና ሀገራዊ ጥቅም ዜጎች ይህን ማከናወን ያለበት መንግሥት ነው በሚል በጥገኝነት አመለካከት ሳይገደቡ በየበኩላቸው የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ መሠረት ነው፡፡ ሕዝባዊ ተሳትፎ በገንዘብ፣ በጉልበት፣ በእውቀት፣ በሐሳብ አስተዋጽኦና በሌሎችም መንገዶች ሊከናወን ይችላል፡፡

ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ነው የሚያስኙት ዋና ዋና ነገሮች ሰዎች ውጤታማ የሆነ ተግባር ማከናወናቸው ብቻ አይደለም፡፡ ከሱ ጎን በጋራ የሥራ ስምሪት ጊዜንና ሥርዓትን አክብረው ተግባሩን ማከናወናቸው፣ በተናጠል ሳይሆን በተደራጀ መልክ መንቀሳቀሳቸው፣ እንዲሁም ተግባራቱ ቀጣይነት እንዲኖራቸው መደረጉን ይጨምራል፡፡

## መልመጃ 2

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ሰዎች የሚያደርጉት ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ምን ምን በማበርከታቸው ሊገለጽ ይችላል?
2. በማናቸውም የልማት ተግባር ላይ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ በርግጥም ተረጋግጧል ሊያሰኙ የሚችሉትን አራት ተግባራት ዘርዝሩ፡፡

## 10.1.2 ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ማጠናከር



ሥዕል 10.2 የልማት ኮሚቴ አመራር ስብሰባ



ሥዕል 10.3 ዴሞክራሲያዊ ምርጫ

- ከዚህ በላይ ካሉት ሥዕሎች የተገነዘባችሁትን ግለጹ፡፡
- ምርጫ በዴሞክራሲያዊ መንገድ መካሄድ አለመካሄዱ በምን ይታወቃል?

### የሙጭሌ ከተማ፤

ሙጭሌ በርካታ ነዋሪዎች ያሉዋት ግን ጽኑ የውሀ ችግር የሚያሰቃያት ነባር ከተማ ነች፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የውሀ ችግሯ መቃለሉ ነው ተብሎ ተስፋ ተደርጎ ነበር፡፡ ይኸውም ከሦስት ዓመት በፊት በተካሄደ ምርጫ ሐላፊነቱን የተረከበው የከተማይቱ የልማት ኮሚቴ ለችግሩ ቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራ ስለነበር ነው፡፡ በተለይም ሊቀመንበሩ አቶ ዋችሶ በግል ጥረታቸው ከአንድ ለጋሽ ድርጅት ከፍ ያለ ገንዘብና አንድ የቆየ የከተማዋን የውሃ ፕሮጄክት ጥናት ሰነድ ለማግኘት ችለዋል፡፡ ፕሮጄክቱ ከብዙ ዓመታት በፊት ከፍተኛ ወጪ ተደርጎበት የተሠራ ሲሆን በልዩ ልዩ ምክንያት ተግባራዊ ሳይደረግ የቆየ ነበር፡፡ ሊቀመንበሩ እነዚህን ይዘው ለኮሚቴው በማቅረብ ሊያስወስኑ ሲሉ ከአንድ አባል ትልቅ ተቃውሞ ደርሰባቸው፡፡

ለተቃውሞው ምክንያት ውሀው የሚገኝበት ሥፍራ የአካባቢው ነዋሪዎች ቀደምት ትውልዶቻቸው የሚያመልኩበትና የዚሁ መንፈስ ያላቸው ቤተሰቦች የመቃብር ቦታ በመሆኑ መቆፈር የሌለበት ነው በሚል ነበር፡፡ አቶ ዋችሶ ግን ይህ ባዕድ አምልኮ ከመሆኑ ሌላ አሮጌ አስተሳሰብ በመሆኑ ሕዝብ እንደማይቀበለው በማስረዳት የተገኘውን የጥናት ሰነድና ከፍተኛ ገንዘብ መጠቀም ይገባል በማለት የቀሩትን የኮሚቴ አባላት አሳመኑ፡፡ በድምጽ ብልጫም አስወሰኑ፡፡ ከዚህ በኋላ ፕሮጄክቱ በጨረታ ላሸነፈ ድርጅት ተሰጥቶ ግንባታው ላለፉት ሁለት ዓመታት ሲካሄድ ቆየ፡፡

በአሁኑ ጊዜ ሥራው በመገባደድ ላይ ቢሆንም ተቃውሞው ግን በከተማው ሕዝብ ዘንድ እየሰፋ መጥቶ ሥራውን እስከማስተጓጎልና አቶ ዋችሶንም በሕዝብ ፊት እስከማስጠየቅ ደረሰ፡፡ እንዲያውም በአብላጫ ድምጽ ከኃላፊነታቸው እንዲወርዱ አስደረጋቸው፡፡

ፕሮጀክቱም ከፍ ያለ ገንዘብ ቢፈስበትም ወደ መገባደድ ላይ እያለ እንዲቋረጥ ይብሱንም ጉድጓዱ እንዲደፈን ተደረገ፡፡ የሙጭሌ ከተማም የውሀ ችግር ባለበት መቀጠሉ ግድ ሆነ፡፡

**መልመጃ 3**


***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ለደረሰው ከፍተኛ ኪሳራ ተጠያቂ መሆን ያለበት ማነው?
2. አቶ ዋችሶ ያሰቡትን ከፍተኛ የልማት ሥራ ከስኬት ለማድረስ ያልቻሉት ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ለማረጋገጥ ስላልቻሉ ነው ቢባል ትስማማላችሁ? ለምን?
3. በዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ስለንቁ ህዝባዊ ተሳትፎ ወሳኝነት ከምንባቡ ምን ትምህርት ለመቅሰም ቻላችሁ?

### 10.1.3 በኢትዮጵያ ውስጥ ፈጣን የልማት ዕድገት ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት በሕዝባዊ ተሳትፎ ማገዝ




*ሥዕል 10.4 በመንንዣ ችግር አዙሪት ውስጥ*




*ሥዕል 10.5 ከመንንዣ ችግር አዙሪት ውስጥ መውጣት*

- ሥዕሎቹ የሚገልጹትን ሐሳብ በአጭሩ አብራሩ::
- በሁለቱም ውስጥ ዕድገት ያለ ቢሆንም እድገቶቹ እጅግ የተለያየ ደረጃ እንዳላቸው ግልጽ ነው:: የደረጃውን ልዩነት ግለጹ::

**የነአወል ቤተሰብ፤**

አወል ለትምህርት ከሄደበት ከተማ ለእረፍት ተመልሶ ከቤተሰቦቹ ጋር ይገኛል:: በዚህ ምሽት የቤተሰቡ አባላት ሁሉ የተሰባሰቡበት ወቅት ነው:: በፋኖሱ ብርሃን እርስበርስ እየተያዩ ሞቅ ያለ ቁምነገር እያወሩ ነበር:: አወል አባቱ የሚሉት ትክክል አይደለም እያለ ቢከራከርም የቤተሰባቸው መሻሻል እንዳለ ግን አልካደም::

ሆኖም ይህ መሻሻል በሕይወታቸው ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ አላመጣም ባይ ነው:: ሌሎቹ አባታቸውን እየደገፉ ይከራከራሉ:: በነሱ አስተያየት በቤታቸው አባታቸው ለቀለባቸው የተሻለ ምርት መሰብሰብ መቻላቸው፣ ቤተሰቡ ከዓመት እስከ ዓመት ጠግቦ መብላቱ፣ ከቤተሰቡ ተርፎ በሚሸጠውም ለሁሉም ልብስ ስለሚገዛ እንደድሮው አለመታረዛቸው፣ የጨውና የሳሙና ችግር መወገዱ፣ የሰው እጅ ያለማየታቸው፣ ወንዶቹ ልጆች ሁሉ ትምህርት ቤት መግባታቸው፣ ዋና ዋናዎቹ ለውጦች ናቸው:: ለወደፊትም አወል ተምሮ ሲጨርስ እንደከተሜዎች እንደሚያኖራቸው ተስፋ ያደርጋሉ:: አወል ለነዚህ ለውጦች ተገቢ ግምት ሊሰጥ እንደሚገባም ይከራከራል::

አወል አሁንም በክርክሩ እንደጸና ነው:: ድሮም በከፍተኛ ድህነት ውስጥ ነበርን ዛሬም ከከፍተኛው ድህነት አዙሪት ውስጥ አልወጣንም በማለት ይከራከራል:: ከከፋው ድህነት የሚያስወጣ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት ነው ያለብን ሲል ለሚያቀርበው ክርክር በምሳሌነት አብሮት የሚማረውን የአንጁሎን ቤተሰብ ያቀርባል::

ይህ ቤተሰብ እንደነሱ በከፋ ድህነት በግብርና ይኖር የነበረ ነው:: አሁን ግን የተሻለ መጠን ያለው ምርት ማምረት ብቻ ሳይሆን ብዙ ገንዘብ የሚያስገኝና ገበያው የሚፈልገውን ዓይነት ምርት ለይቶ ያመርታል:: ያንን በከፍተኛ ዋጋ ሸጠ ቀለብም ሆነ ሌላ የሚያስፈልገውን ነገር ይገዛል:: በሠፈር ከሚፈሰው ከዳኮታ ወንዝ ውሀ ለመስኖ ይጠቀማል:: ከዚህም ሌላ የአንጀሎ

አባት ንብ ያንባል፣ ከብቶችና በጎችን እያረባና እያደለበ ከተማ ወስዶ ይሸጣል:: ዛሬ ከተማ ገብቶ ቤት ለመሥራት፣ ወንዶቹንም ሆነ ሴቶቹን ልጆች ለማስተማር ችሏል:: ትምህርቱ ያልሆነላትን አንዷን ልጁ እዚያው እንድትነግድ አድርጓል። የአንጀሎንም ታላቅ ወንድም አንድ የጭነት መኪና ገዝቶ በትራንስፖርት ዘርፍ እንዲሠራ አድርጓል::

ታዲያ የአንጅሎ እናትና አባት ኢንቬስተር ሆነው ለልጆቻቸው የሥራ እድል አልፈጠሩም? እነዚህ የቤተሰብ አባላት መሠረታዊ ለውጥ በማምጣታቸው አስከፊውን የድህነት አዙሪት በግልጽ ሰብረው እየወጡ ነው:: አወል እንዲህ ዓይነት መሠረታዊ ለውጥ በማምጣት ከነበርን በት የአስከፊ ድህነት አዙሪት በማያዳግም አኳኋን ሰብረን ልንወጣ ይገባል ነው የሚለው::

ሁሉም በአወል ብስለት ተደነቁ:: ተስፋም አደረጉበት:: ለጊዜውም ክርክሩ በዚህ ተቋጨና ወደ የመኝታቸው ሄዱ::

ቁልናና ኋላቀርነት በአስተማማኝ ሁኔታ አውጥቶ ዕድገቷን እንድትቀጥል ሊያደረጋት አይችልም::

ዛሬ በሌሎች ሀገሮች እንደሚታየው በመጠነኛ ለውጥ ኢትዮጵያ ልትጓዝ አትችልም:: በመሆኑም የሚመጣው ለውጥ ፈጣን ሊሆን የግድ ነው:: በጣም ፈጣን ለውጥ በማካሄድ የድህነቱንና የኋላቀርነቱን አዙሪት ሰብሮ መውጣት ያስፈልጋል:: በሕዝቡ እለታዊ ኑሮ ላይ ጉልህ፣ ተጨባጭና መሠረታዊ ለውጥ በአንጻራዊነት በአጭር ጊዜ ውስጥ ማምጣት አማራጭ የሌለው ነገር ነው::

ይህ እውን እንዲሆን ካስፈለገ ደግሞ ሕዝቡም በልማቱ ሥራ ያለምንም ማመንታት ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎውን ማጠናከርና ባለማሰለስ አስተዋጽኦ ማበርከት ይኖርበታል:: ፈጣን ልማትን ለማረጋገጥ፣ ሕዝቡ የተደላደለ ሕይወት እንዲኖር ለማድረግ፣ ሀገሪቱም ከኋላቀርነት እንድትላቀቅ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ዋና መሣሪያ ነው::

**መልመጃ 4**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

?

1. የነአወል ቤተሰብ የኑሮ ሁኔታ ለውጥ በየትኛው ዓይነት አዙሪት ሲገለጽ ይችላል? ለምን? የአንጅሎ ቤተሰብስ?
2. ይህ በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል የታየው የእድገት ልዩነት በሁለት ሀገሮች መካከል የሚታይ ለውጥ ቢሆን እንዴት ሲገለጽ ይችላል?
3. የድህነቱ አዙሪት ሲሰበር የሚችለው በፈጣን ልማት ነው ቢባል ትስማማላችሁ? ለምን?

ሀገራችን የምትገኘው እጅግ ዝቅተኛ በሆነ የድህነትና የኋላቀርነት ደረጃ ላይ ነው:: ሆኖም መላው ሕዝብ ቆርጦ ከተነሳና ጠንክሮ ከሠራ ይህ ሁኔታ የማይለወጥበት ምክንያት አይኖርም:: ይሁን እንጂ የምንገኝበት የድህነት ደረጃ አስከፊ በመሆኑ መጠነኛ ለውጥና እድገት መመዝገቡ ብቻ ሀገሪቱን አሁን ከምትገኝበት ጉስ

**መልመጃ 5**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::***

?

1. ኢትዮጵያ አስከፊ በሆነ የድህነትና የኋላቀርነት ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች በሚለው ሀሳብ ላይ ተወያዩ::
2. ሀገሪቱ ከዚህ አስከፊ ሁኔታ ልትወጣ የምትችለው በሕዝቡ የነቃ ተሳትፎ የተደገፈ ፈጣን ልማት ከተረጋገጠ ብቻ እንደሆነ ይገልፃል:: በዚህ ሐሳብ ትስማማላችሁ?

## 10.2 የሲቪክ ክበባት/ማሕበራት ተግባራት

### 10.2.1 የሲቪክ ማሕበራት መጠናከር ለንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ መጎልበት የሚኖረው ጠቀሜታ፣



*ሥዕል 10.6 ዓመታዊ የቀይ መስቀል ቀን*

- ቀይ መስቀል ምን ምን ተግባራትን ያከናውናል?
- ቀይ መስቀል የሕዝብን ንቁ ተሳትፎ በመጠቀም ሊያከናውን የሚችላቸውን ተግባራት ግለጹ::

#### በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች.አይ.ቪ ኤድስ ምርመራ፣

በዞናችን ኤድስን በመከላከል ረገድ የሚሰጠው ትምህርት እየተጠናከረ መጥቷል:: ስለዚህ በፈቃደኝነት ምርመራ የሚያደርጉት ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ሄዷል:: የኤድስ መከላከያና ማሕበራዊ አገልግሎት ቅርንጫፍ ባለፈው ዓመት አገልግሎቱን በነጻ ለመስጠት በአካቢያችን የደም ምርመራ ላብራቶሪ አቋቁሞ ነበር::

ያኔ በመጀመሪያው ስድስት ወራት የኤድስ ምርመራ በፈቃደኝነት ያካሄዱት ሰዎች 300 ብቻ ነበሩ:: በኋላም ስለበሽታው የሚሰጠው ትምህርት በተለያዩ ወገኖችና በተለያዩ ሥፍራዎች እየተጠናከረ እንዲሄድ ተደርጓል:: በመሆኑም በሁለተኛው ስድስት ወራት ምርመራ ያደረጉት ሰዎች ብዛት ወደ 1700 አድርጓል:: ለዚህም ዋናው ምክንያት ድርጅቱ በሕብረተሰቡ ዘንድ ያለው ግንዛቤ እያደገ እንዲሄድ በማድረጉ ነው::

ለረዥም ጊዜያት በዞኑ በሚገኙ አድባራትና ገዳማት ለሚያገለግሉ በርካታ ምዕመናን ስለኤድስ መከላከል ትምህርት ተሰጥቷል:: ከወጣት ማሕበሩ ጋር በመተባበር የወጣቶች የአቻ ለአቻ መወያያ ማዕከሎች ተቋቁመዋል:: በነዚህም አማካኝነት ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ ተጀምሯል::

ድርጅቱ ስለበሽታው መከላከል የሚሰጠውን የወጣቶች የአቻ ለአቻ ትምህርት ለማጠናከር በየትምህርት ቤቱ የሚኒ ሚዲያ ክበባት እንዲቋቋሙ አስደርጓል:: በክበባቱም አማካኝነት ተማሪዎች ስለበሽታው ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል:: ከትምህርት ቤት ውጪ ለተደራጁት ማዕከላትም የልዩ ልዩ ቁሳቁሶችና የፅሕፈት መሣሪያዎች ድጋፍ ተደርጓል::

በተጨማሪም ለ565 የሚኒ ሚዲያ ክበባት ተጠሪ ተማሪዎችና የማዕከላት አስተባባሪዎች ለመምህራንና ለሀገር ሽማግሌዎች በኤች አይቪ/ኤድስ መከላከል ዙሪያ አጫጭር ሥልጠናዎች ተከናውነዋል:: ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩና ደጋፊ ለሌላቸው ሃያ አምስት ሰዎችም ከኅዳር ወር ጀምሮ ለያንዳንዳቸው በየወሩ ብር 150 በእርዳታ እየተከፋፈለ ነው::

ይህ ሁሉ ያስገኘው ድምር ውጤት ከፍተኛ ነው:: እጅግ ብዙ ተማሪዎች በክበባት ዙሪያ ከመደራጀታቸው ሌላ በሚኒ ሚዲያውም በብዛት መጠቀም ጀምረዋል:: በመኖሪያ አካባቢዎች በየማዕከላቱ ወጣቶች በማሕበራት እየተደራጁ መንቀሳቀስና በበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች እየተሰማሩ ደካሞችንና ህሙማንን መርዳት ጀምረዋል::

በአጠቃላይ የሕዝቡ ግንዛቤ በማደጉ ራሱን ከበሽታው በመጠበቅ፣ ከአድሎና ከማግለል ድርጊቱ በመታቀብ ረገድ ጉልህ ለውጥ እያሳየ ይገኛል:: ሕሙማን በነዚህ ሁሉ በመበረታታት የመኖር ተስፋቸውን ማሳደግና ሠርተው በጉልበታቸው ፍሬ ለመኖር ጥረት ማድረግ ጀምረዋል::

*(አዲስ ዘመን ግንቦት 7/95 ዓ.ም)*

**መልመጃ 6**

***ከላይ የቀረበውን መረጃ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

?

1. **በምንባቡ ውስጥ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የነበሩትን የሲቪክ ማሕበራት ስም ጥቀሱ:: እያንዳንዳቸው ምን ምን አስተዋጽኦ አድርገዋል?**
2. **የሲቪክ ማሕበራት የሕብረተሰቡ አባላት ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያስችል ሁኔታ እደሚፈጥሩ የሚያሳይ ምሳሌ ከጽሑፉ አቅርቡ::**
3. **በመረጃው ውስጥ ከተጠቀሱት የሲቪክ ማሕበራት መካከል እናንተስ በየትኛው መሳተፍ ትፍልጋላችሁ? ምን ዓይነት ተሳትፎስ ለማድረግ ትችላላችሁ?**

## የቡድን ሥራ፣

ቀጥሎ ስድስት ስድስት አባላት ያላቸውን ቡድኖች ትመሠርታላችሁ:: በያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ግማሹ በአንድ ወገን የቀረው ደግሞ በሌላ ወገን እየሆናችሁ ከታች ከቀረቡት አከራካሪ አርእስቶች መካከል አንዱን በመምረጥ እርስ በርስ ትከራከራላችሁ::

ከክርክሩ በኋላም እያንዳንዱ ቡድን ከክርክሩ ያገኘውን ቁምነገር ለክፍሉ አባላት በአንድ ተወካይ አማካኝነት ያቀርባል:: በክፍሉም ውይይት ተካሂዶ የክርክሩን ቁም ነገሮች በመለየት ክርክሩ ይቋጫል::

***የክርክር አርእስት፣***

1. የሲቪክ ማሕበራት የሚጠቅሙት ሕብረተሰቡን ነው ወይንስ የራሳቸውን አባላት?
2. በሲቪክ ማሕበራት ውስጥ መሳተፍ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?

የሲቪክ ማሕበራት በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች በገዛ ፈቃዳቸው በጋራ የሚመሠርቷቸው ድርጅቶች ናቸው:: በሌላ አገላለፅ አባላቱ የገዛ ጉልበታቸውን ገንዘባቸውን እውቀታቸውንና ጊዜያቸውን ሰውተው የሚያቋቁማቸው ማሕበራት ናቸው:: ከዚያ በኋላ ከሌላ አካል ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ:: ለህብረተሰቡ የሚሰጡትም አገልግሎት የአትራፊነት መርህ የማይከተል ሲሆን አገልግሎት ለማበርከት በተለያዩ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዩች ይሠማራሉ::

የሲቪክ ማህበራት ከማንኛውም ሃይማኖታዊ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ተጽእኖ ነፃ መሆን አለባቸው:: እነዚህ አካላት የሀገሪቱን ሕገ መንግሥትና አግባብ ያላቸውን ሌሎች ሕጎች አክብረው በሕግ መሠረትም ታውቀውና ተመዝግበው የሚሠሩ ነጻ ማህበራት ናቸው::

የሲቪክ ማህበራት የሕዝቡን ንቁ ተሳትፎ በማሳደግ በኩል ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አላቸው:: ጠንካራ የሲቪክ ማህበራት የሕብረተሰቡን ፍላጎት መሠረት አድረርገው ስለ ሚንቀሳቀሱና ሕዝቡንም በእንቅስቃሴዎቻቸው ውስጥ በቀጥታ ስለሚያሳትፉ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎን ያሳድጋሉ:: ቀደም ሲል እንደተገለፀው የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ መጎልበት ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ለመልካም አስተዳደር መስፈን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል::

**መልመጃ 7**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

?

1. **የሲቪክ ማህበራት ከሚያገለግሉት ሕብረተሰብ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ሲኖራቸው ይገባል?**
2. **የሲቪክ ማህበራት ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎን በመፍጠርና በማሳደግ ረገድ ያላቸው ሚና ምን ይመስላል?**

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማለት በሕብረት ለአካባቢያዊና ለሀገራዊ ጥቅም ግለሰቦች በጋራ በፈቃደኝነትና በራስ ተነሳሽነት የተለያዩ አስተዋጽኦዎችን ለማድረግ የሚያካሂዱት እንቅስቃሴ ነው፡፡ እንቅስቃሴው ውጤታማ ይሆን ዘንድ በሕብረት መከናወኑ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም መደራጀት ያሻል፡፡

በግል ተነሳሽነት የሚቋቋምና ከፖለቲካ፣ ከሃይማኖትና ከወታደራዊ ተጽእኖ ነፃ የሆነ፣ ለትርፍ ሳይሆን ሕብረተሰቡን ለማገልገል የሚቋቋም ድርጅት የሲቪክ ማሕበር ይባላል፡፡ እነዚህ የሲቪክ ማሕበራት ሕዝቡን ለበጎ ተግባር በማስተባበር ለራሱ ማህበራዊ ጥቅሞች እዲንቀሳቀስ ያደርጋሉ፡፡ ፍላጎቱን ይዘው በውስጡ በመንቀሳቀስም ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ እንዲያደርግ ያነሳሳሉ፣ ያለማምዱሉም፡፡ በዚህ መልክ መልሰው ለንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ መጎልበት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

የተጀመረው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲጠናከርና ሀገራችን ከምትገኝበት ከፍተኛ የድህነትና የኋላቀርነት ደረጃ በፈጣን እድገት እንድትወጣ የሕዝቡ ንቁ ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ የሲቪክ ማሕበር በሚንቀሳቀስበት የልማት ተግባር ንቁ ተሳትፎ ብናደርግ ለአካባቢያችንና ለሕብረተሰባችን ጠቃሚ ነገር ልናበረክት እንችላለን፡፡ በዚህም በሕብረተሰባችን ዘንድ እየሰፋ ያለውን ዴሞክራሲን ማጎልበትና ለእ ድገትም አስተዋጽኦ ልናደርግ እንችላለን፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**የአካባቢ ልማት፣** የሰፈርን ወይም የቀበሌን ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የሚያሻሽሉ እንቅስቃሴዎች ውጤት፡፡

**እቅድ፣** አንድን ተግባር በላቀ ውጤት ለማከናወን ሰዎች ያላቸውን የገንዘብ፣ የቁሳቁስ፣ የሰው ኃይል፣ የጊዜና የመረጃ ሀብት አቀናጅተው ወደተግባር የሚያስማሩበት ንድፍ፡፡

**ግምገማ፣** አንድ በእቅድ የተከናወነ ተግባር የታለመለትን ውጤት በሚፈለገው ደረጃ ማስገኘቱን የመመዘንና ለቀጣዩ እቅድም ካለፈው ተሞክሮ ትምህርት የሚቀሰምበት ሂደት፡፡

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::*

## I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ::

1. የአካባቢ ልማት ላቅ ያለ ማሕበራዊ ጠቀሜታ ያስገኝ ዘንድ በንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ሊደገፍ ይገባዋል::
2. በአንድ ሀገር በተለያዩ ደረጃዎች ለሚከናወኑ የአካባቢ የልማት ሥራዎች ብቸኛው ባለቤትና ተዋናይ ሕዝቡን የሚወክለው መንግሥት ነው::
3. በአካባቢ የልማት ተግባር ተሳታፊዎች በሚፈለጉበት ጊዜ ወቅቱን አክብረው የማይገኙ ከሆነ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ይተጓጎላል::
4. የሲቪክ ማሕበራት ከመንግሥት ተጽእኖ ነፃ እንደመሆናቸው በማንኛውም መንግሥታዊ ተቋም መመዝገብና መታወቅ አያስፈልጋቸውም::
5. ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ለአካባቢ ልማት መጎልበት እንጂ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጠናከር አስተዋጽኦ አይኖረውም::

## II. በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን በ "ሀ" ሥር ካሉት ሥር አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የንግድ ማሕበር፣ | ሀ. ለተመሳሳይ ዓላማ በማሕበር መሰባሰብ። |
| 2. የወጣቶች ማሕበር፣ | ለ. በሰፈር የሚከናወን ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባር። |
| 3. መደራጀት፣ | ሐ. የእውቀት አስተዋጽኦ። |
| 4. የአካባቢ ልማት፣ | መ. በአንድ ሙያ ዙሪያ የተሰባሰቡበት። |
| 5. ከንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ መገለጫዎች አንዱ፣ | ሠ. የሲቪክ ማሕበር ያልሆነ ድርጅት። |
| | ረ. የሲቢክ ማሕበር አንድ ምሳሌ። |
| | ሰ. ሰዎች ተሰብስበው በጋራ ውሳኔ የሚያከናውኑት ማንኛውም ነገር። |

## III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::

1. የሲቪክ ማሕበራት ከመንግሥት ተጽእኖ ነፃ በመሆናቸው፣
   ሀ. ለሕገመንግሥቱ የመገዛት ግዴታ የለባቸውም፣
   ለ. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት መመዝገብና ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል፣
   ሐ. ከአካባቢ ልማት ጋር አዋህደው ፖለቲካዊ ወይም ሃይማኖታዊ ዓላማዎቻቸውን ማራመድ ይችላሉ፣
   መ. መልሱ አልተሰጠም::

2. የአካባቢ ልማት ሥራ ሕብረተሰቡን አግልሎ ለመንግሥት ብቻ መተው የሌለበት ምክንያት፣
   ሀ. ሕዝቡ በልማቱና በልማቱ ውጤት የባለቤትነት ስሜት እንዲኖረው ለማድረግ ሲባል ነው፣
   ለ. በሕዝቡ ዘንድ የጥገኝነት ስሜት እዲያድግ ለማድረግ ነው፣
   ሐ. የአካባቢ ልማት ዘላቂነት ወይም ቀጣይነት የሚረጋገጠው መንግሥት ብቻ ካከናወነው ነው፣
   መ. ሁሉም ትክክል ናቸው::

3. በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ካለ ከሚከተሉት በአንዱ ሊገለጽ ይችላል፤
   ሀ. በአካባቢ ልማት እንቅስቃሴ ወቅት በአካል በመገኘት፣
   ለ. በአካባቢ ልማት እንቅስቃሴ ወቅት የጉልበት አስተዋጽኦ በማድረግ፣
   ሐ. በአካባቢ ልማት እንቅስቃሴ ወቅት በሥፍራው ተገኝቶ በማበረታታት፣
   መ. ሁሉም ትክክል ናቸው::
4. በአንድ ማሕበራዊ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የአባላቱ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ መታየት ያለበት በየትኛው ደረጃ ነው?
   ሀ. በእቅድ አወጣጥ፣ ለ. በእቅዱ ትግበራ፣
   ሐ. በእቅድ አፈጻጸም ግምገማ፣ መ. ሁሉም ትክክል ናቸው::
5. በአንድ የአካባቢ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አለ ሊያሰኙ ከሚችሉት ነገሮች መካከል አንዱ ----------ነው፤
   ሀ. በተደራጀ መልክ ሳይሆን በተናጠል መከናወኑ፣
   ለ. በተሰማሩት ሰዎች ቁጥር መብዛት፣
   ሐ. ሥራው በመከናወኑ ብቻ ሳይሆን ውጤታማ በመሆኑ፣
   መ. ሁሉም ትክክል ናቸው::

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::

1. በሕብረተሰቡ ውስጥ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎን የሚያጎለብትና ከመንግሥት ተጽዕኖ ነጻ የሆነ ድርጅት __________ ተብሎ ይጠራል::
2. የአካባቢ ልማት ዘላቂነቱ ይረጋገጥ ዘንድ የሕብረተሰቡ ንቁ ተሳትፎ ሊኖርበት ስለሚገባ ሥራው ለ __________ ብቻ መተው የለበትም::

## V . የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ::

1. አንድን የአካባቢ የልማት እንቅስቃሴ በእርግጥም ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ታይቷል ለማለት የሚያስችሉ ሦስት ነገሮችን ጥቀሱ::
2. አንድ የሕብረተሰብ አባል በአካባቢው የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማድረጉን ከሚያሳዩ ተግባራት አራቱን ጥቀሱ::

# ምዕራፍ አሥራ አንድ

# ዕውቀትን መሻት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቂ/ ስታጠናቅቅ፤***

- ዕውቀት ለልማት፣ ለምርምርና ለፈጠራ መሠረት መሆኑን ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ።
- የመረጃን አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ትረዳለህ/ ትረጃለሽ::
- የመረጃ ምንጮችን፣ የመረጃ አያያዝንና የአጠቃቀም ዘዴዎችን ታውቃለህ/ቂያለሽ::

## 11.1 ሣይንሳዊ ጠቀሜታ

### 11.1.1 የሣይንሳዊ ዕውቀቶች ጠቀሜታ



*ሥዕል 11.1 ምርምር በላቦራቶሪ*



*ሥዕል 11.2 የአርኪኦሎጂ ምርምር*

- ከሥዕሎቹ ምን ትረዳላችሁ?
- በቤተሙከራ ውስጥ የሚታየው ሥዕል ስለ ሳይንሳዊ አመለካከት ምን ያመለክታል?



*ሥዕል 11.3 መምህርት በክፍል ውስጥ*

**የሌሊት ወፍ፤**

በድሮ ጊዜ የሌሊት ወፍ በምትኖርበት አካባቢ አስጨናቂ ረሐብ ገባ:: በአካባቢው የሚኖሩት አእዋፋትና ሌሎችም እንስሳት በረሐቡ ክፉኛ ተጠቁ:: ረሐቡን ለመቋቋም የሌላቸው ካላቸው እየተበደሩ ይበሉ ጀመር:: ከተበዳሪዎቹም አንዷ የሌሊት ወፍ ነበረች፣ ከተለያዩ ወፎች ብዙ ተበድራ ነበር:: ክፉው ቀን ካለፈ በኋላ ሌሎቹ ወፎች ሁሉ ያለባቸውን ብድር መክፈል ሲችሉ የሌሊት ወፍ ግን ተበድራ የበላችውን መመለስ አቃታት::



*ሥዕል 11.4 የሌሊት ወፍ*

ጨረሻም አበዳሪዎቿ ሁሉ አጥብቀው ይፈልጓት ጀመር:: እሷ ግን በመደበቅ ማምለጥን መረጠች:: ከዚህም የተነሳ እንደሌሎቹ ወፎች ቀን መብረሯን አቁማ ምግቧን ለማግኘት ሌሊት መብረር ግዴታዋ ሆነ፣ በዚህም የሌሊት ወፍ ተባለች::

*(ከቃላዊ ትረካ የተገኘ)*

**መልመጃ 1**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሱ፡፡***

?

1. "የሌሊት ወፍ" የሚለው ጽሑፍ በተጨባጭ ዕውነታ ላይ ተመሥርቶ የቀረበ ነው? ለምን?
2. ስጥያቄ ቁጥር አንድ ከሰጣችሁት መልስ በመነሳት ሳይንሳዊ ስላልሆነ አመለካከት ምን ተረዳችሁ?

**ግመል፤**

ግመል ከፈረስ ይበልጣል:: በአካሉም ከሌሎች እንስሳት ግዙፍ ነው:: ሲጫንና ሲራገፍ ይንበረከካል:: ሲቆምም ባሰበ ጊዜ መጀመሪያ የኋላ እግሮቹን ያነሳል:: ሰው ተቀምጦበትም ግመሉ ሲነሳ ሰውየው አጥብቆ ካልያዘው ወደግመሉ ራስ ሊወረወርና ሊወድቅ ይችላል:: ግመል ጠንካራ ከመሆኑ የተነሳ ከባድ ዕቃ ለመሸከም ይችላል::

ግመል በሰሜን ሕንድ፣ በአረብ አገሮችና፣ በአፍሪካ በረሃማ አካባቢዎችም ጭምር ከፍተኛ ጥቅም አለው:: ውሃ ሳይጠጣ ብዙ መጓዝና ከአራት እስከ አምስት ቀናት መቆየት ይችላል:: የተወሰኑት የግመል ዝርያዎች በጀርባቸው ላይ አንድ፣ ሌሎች ደግሞ ሁለት ሻኛ አላቸው:: ሻኛው የሰባ ነው:: ግመሉ ሳይበላ ለብዙ ቀናት በሚቆዩበት ጊዜ ሻኛው እየሟሸሸ እንደ ምግብ ያገለግለዋል::



*ሥዕል 11.5 ግመል*

የግመል እግሮች ትልልቅ፣ ሰፊና ለስላሳ ሆነው በወፍራም ቆዳ የተያያዙ ናቸው:: በበረሃ ውስጥ በሞቀ አሸዋ ላይ በቀላሉ እንዲራመድ ይረዱታል:: ግመል ሲራመድ በቀስታ ነውና ባጠገባችን ቢያልፍ አንሰማውም::

የግመል አፍንጫ ጠባብ ስንጥቅ ኖሮት በቀላሉ መዘጋትና መከፈት የሚችል ነው:: አሸዋ በነፋስ ሲቦን ግመሉ ይተኛና አፍንጫውን ዘግቶ ራሱን በአሸዋው ውስጥ ይቀብራል:: አፍንጫው ከርቀት የውሃ ሽታ ለመሳብ ይረዳዋል:: አንዳንዴ መንገድን በማሳበር በአቋራጭ ይሄድና ውሃው ካለበት ሥፍራ ይደርሳል:: በዚህ ሁኔታ መንገደኞች በቀላሉ ውሃ ካለበት እንዲደርሱ ያግዛቸዋል::

*(ከበደ ሚካኤል፣ ተሻሽሎ የተወሰደ)*

**መልመጃ 2**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

?

1. "ግመል" የሚለውን ጽሑፍ ያቀረበልን ጸሐፊ የሚነግረንን ሐሳብ እውነተኛነት ማረጋገጥ ይቻላል? እንዴት?
2. እስካሁን ካስተዋላችሁት ሁኔታ ተነስታችሁ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ሲባል ምን ገባችሁ? በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ:: የደረሳችሁበትን ማጠቃለያም በክፍል ውስጥ አቅርቡት::

ዕውቀትን መሻት የሰው ልጅ የተፈጥሮ ባሕርይ ነው:: ዕውቀት ሲፈለግ ታዲያ በሳይንሳዊ አስተሳሰብ ላይ የመመሥረት ሂደት አለው:: ሳይንሳዊ አስተሳሰብ፣ ስለራሳችን ስለአካባቢያችንና ስለዓለም የምንመሠርተው ተጨባጭ ግንዛቤና ዕውቀት ነው::

ይህም አስተሳሰብ በተለያዩ መንገዶች በምናገኛቸው መረጃዎች ስፋትና ጥበት እዲሁም ቅለትና ጥልቀት ይወሰናል:: ይህም ሲባል ከዕድሜያችን፣ ከልምዳችንና ከትምህርት ደረጃችን በምናገኘው መረጃ ላይ ተመሥርቶ የሚያድግ የሕሊና ሀብት ይሆናል ማለት ነው:: በሌላ አነጋገር የሳይንሳዊ አስተሳሰባችን ጥንካሬ ባለን ትክክለኛ መረጃና ተግባራዊነት ልክ የሚመዘን ነው ማለት ይቻላል፡፡

ጥልቅ የሆነ ዕውቀት መገብየታችን ትክክለኛ ውሳኔ ለመወሰን፣ የፈጠራ ችሎታችንን ለማበልጸግ፣ ልማትን ለማፋጠንና ራስንም ለመቻል ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው:: አንድ ሰው በአንድ ነገር ዙሪያ ጥልቅ ዕውቀት ከቀሰመ በዚያ ጉዳይ ላይ ተገቢ ውሳኔ ለመወሰን አይቸገርም:: ለምሣሌ ከፍ ሲል ባቀረብናቸው ሥዕሎች ላይ የምንመለከታት የቤት ሙከራ ተመራማሪ የተለያዩ ኬሚካሎችን በሳይንሳዊ መንገድ ከፈተሸች በኋላ፣ እነዚያ ኬሚካሎች ለመድኃኒትነት ወይም ለሳሙና ምርት መቀመሚያ መዋል መቻል ወይም አለመቻላቸውን በቀላሉ መወሰን ትችላለች ማለት ነው::

በዕውቀት መጎልመስ ሙያን ከማሳደግ በተጨማሪ፣ ለተለያዩ የሥራ ተነሳሽነት ስለሚጋብዝ ሰዎች ሌሎች በሠሩት ከመጠቀም አልፈው አዳዲስ ነገሮችንም እንዲፈጥሩ ይረዳቸዋል:: ለምሳሌ በምሕንድስና ሙያ ከፍያለ ዕውቀት ያለው ሰው ሰዎች የሠሯቸውን የቤት እቅዶችን ከመጠቀም ይልቅ የራሱን አዳዲስ የቤት ፕላኖችን ሊፈጥር ይችላሉ::

ሀገር ልትለማ የምትችለው ሕዝቧ በሚገባ ሲማር ነው:: ዜጎች ከፍ ወዳለ ዕውቀት ተሸጋገሩ ማለት አዳዲስ ግኝቶች መጡ፣ የሰውን ሕይወት የሚለውጡ ልማዶች ተመሠረቱ እንዲሁም ዜጎች በስፋት ወደ ሥራ ተሠማሩ ማለት ነው:: ያኔ ቴክኖሎጂ ያድጋል፣ ቴክኖሎጂ ሲያድግ የማምረቻ ሥርዓት የተቀላጠፈ ይሆናል፣ ያኔ ምርት ያለጥርጥር ያድጋል:: ያኔ ሀገር ለማች፣ ዜጎችም በለጸጉ ማለት ይቻላል::

**መልመጃ 3**

***ከሚከተሉት ርእሶች መካከል በሳይንሳዊነቱ መቀበል የሚቻለው የትኛውን ነው? ለምን ሳይንሳዊ ወይም ኢሳይንሳዊ እንዳላችሁ ከእያንዳንዱ ነጥብ አንጻር ምክንያታችሁን አቅርቡ::***

?

1. ጨረቃ የራሷ ብርሃን የሌላት አካል ናት::
2. መሬት ክብ ሳትሆን ጠፍጣፋ ቅርጽ ያላት ፕላኔት ናት::
3. በጥገኛ ሕዋሳት ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ለመከላከል ፈልቶ የቀዘቀዘ ውሃ መጠጣት ፋይዳው ዝቅ ያለ ነው::
4. የውሻ በሽታን ለመከላከል ውሾችን ተከታትሎ ማስከተብ ተገቢ ይሆናል::
5. መብረቅ እግዜር ሰይጣንን ሲገል የሚተኩሰው ጥይት ነው::

## 11.2 የመረጃ ምንጮችና አጠቃቀም

### 11.2.1 መረጃ ከየት ይገኛል?



*ሥዕል 11.6 ከሞባይል ይገኛል*



*ሥዕል 11.7 መረጃ ከመፃሕፍት ይገኛል*



*ሥዕል 11.8 መረጃ ከጋዜጦች ይገኛል*

- ከላይ የምትመለከቷቸው ሥዕሎች ስለመ ረጃ ምን ፍንጭ ሰጧችሁ?
- በሥዕሉ የተመለከቱትን የመረጃ ምን ጮች እንደጠቀሜታው ልናስቀምጣቸው ብንፈልግ፣ የትኛው ቀድሞ ይመጣል? የትኛውስ ይቀጥላል? በመጨረሻ የሚመ ጣውስ የትኛው ነው ትላላችሁ? ለምን ይህን መሰል ደረጃ ልትሰጡ ቻላችሁ?

እዚህ ላይ አስቀድመን አንድ ልብ ልንለው የሚ ገባን ነጥብ አለ:: መረጃ ስንል ጠበብ አድርገን ማየት የለብንም:: ስለትምህርታችን በቂ የሆነ ማመሳከሪያ ጽሑፍ ወይም ማጣቀሻ መጽሐፍ እንፈልጋለን:: መረጃ አስፈለገን ማለት ነው:: ት/ቤት መቼ እንደሚከፈት፣ እያንዳንዱን ትምህ ርት ማን እንደሚያስተምረን፣ ፈተና መቼ እንደ ሚሰጥ መረጃ ያስፈልገናል::

ስለአካባቢያችን የአየር ሁኔታ፣ ስለዞናችን ወይም ስለክልላችን እንዲሁም ስለሀገራችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ በቂና ሐቀኛ የሆነ መረጃ ማግኘት ይኖርብናል:: ለዚህም እንደ ስልክ፣ እንደጋዜጣ፣ እንደሬዲዮና ሌሎችንም ዘዴዎች እንጠቀማለን:: ሰፊና ጠለቅ ያለ የትምህርት መረጃ ስንሻ ግን በበለጠ የሚ ረዱን መጻሕፍት ስለሆኑ ወደ ቤተመጻሕፍት መሄድ ሊኖርብን ይችላል:: የሚኖረን መረጃ ከራሳችን ተሞክሮ፣ ከትምህርት ገበታ፣ ከልዩ ልዩ ንባብ፣ ከሬዲዮና ከቴሌቪዥን እንዲሁም ከሰ ዎች የሚገኝ ይሆናል::

ባጭሩ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ራሳችን በአምስቱ የስሜት ሕዋሳታችን አማካኝነት ከምንደርስባ ቸው እንዲሁም ሌሎች በትክክል ተመልክተው ወይም በጥናት ደርሰውበት ከሚያሳውቁን ዕውነ ታዎች ሊገኝ የሚችል የተጨባጩ ዓለም ነጸ ብራቅ ነው ማለት እንችላለን::

ከራሳችን ተሞክሮ የምናገኘው መረጃ ብዙውን ጊዜ ኢመደበኛ የሆነ ነው:: ይህም ሲባል ት/ቤት ሳንገባ ወይም መረጃን ለማግኘት የግድ ሳንቀ ሳቀስ በአካባቢያችን ያሉ ሰዎችን፣ የአየር ሁኔ ታን፣ እንስሳትን ወይም ዕፅዋትን ስንመለከት፣ ስንዳስስ፣ ስናሸት፣ ስንቀምስ ወዘተ... የምናገኘውን መረጃ የሚጠቁም ነው:: እንዲህ ያለ መረጃ ብንፈልገውም ባንፈልገውም የግድ ልናገኘው የም ንችለው ዓይነት ነው:: ምክንያቱም በሕይወት እስካለንና እስከተንቀሳቀስን ድረስ ከነገሮችና ከሰ ዎችም ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት እስከኖረን ድረስ መረጃ እናገኛለን::

ከመገናኛ ብዙኋን የምናገኘው መረጃ ደግሞ ስን ዝናና ወይም ዜና ስንከታተል ወይም የተለያዩ የጋዜጦችንና የመጽሔቶችን አምዶች አፈላልገን ስናነብ የሚገኝ መረጃ ነው:: ከመገናኛ ብዙኋን የምናገኛቸውን መረጃዎች ለየት የሚያደርጋ ቸው ብዙውን ጊዜ አዳዲስ መሆናቸውና ከዓለም ዙሪያ ከተገኙ እውነታዎች ጋር የሚያገናኙን መሆናቸው ነው::

የበለጠ አስተማማኝና እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው ግን በትምህርት ቤት የምናገኘው መረጃ ነው:: ይህም በሁለት ምክንያት ነው:: በአንድ በኩል በትምህርት ሥራ ላይ የሚ ሠማሩት መምህራን በሙያቸው የሠለጠኑ መሆናቸው የሚገኘውን መረጃ አስተማማኝ ያደርገዋል:: በሌላ በኩልም የሚቀርበው ትምህርት የተማሪዎችን የዕድሜ፣ የዕውቀትና የአኗኗር ዘይቤ መሠረት አድርጎ የሚዘጋጅ በመሆኑ መረጃውን እርግጠኛና አቅ ምንም የመጠነ አድርጎት ይገኛል:: በዚያ ላይ ለሚፈለገው መረጃ መሠረት የሚሆኑ መጻሕ ፍት ተዘጋጅተው መቅረባቸው የማይቀር ነው:: ስለሆነም ለትምህርት ቤት መረጃዎች በቂ ትኩ ረት መስጠት ያስፈልጋል::

### 11.2.2 መረጃ እንዴት በሥራ ላይ ይውላል?

- በየዕለቱ የምታገኟቸውን መረጃዎች በምን መልክ ትይዟቸዋላችሁ?
- በተለያዩ አጋጣሚዎች በማስታወሻ የያዛችኋቸውን መረጃዎች እንዴት ትጠቀሙባቸዋላችሁ?

በዘመናዊ አነጋገር “መረጃ ሕይወት ነው!” የሚል ብሒል አለ:: ምክንያቱም መረጃ ለዘመናዊ ሰው ወሳኝ ሚና ስላለው ነው:: ምክንያቱም ዛሬ በተ ራራቀ ቦታና ሁኔታ የሚኖሩ ሰዎችም ሕይ ወታቸው እርስ በርሱ የተሳሰረ ነው:: ለምሳሌ ኢትዮጵያና ቻይና በተራራቀ የዓለም ክፍል

የሚገኙ ሁለት ሀገሮች ናቸው:: የንግድ፣ የፖለቲካ፣ የማሕበራዊና የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ላይ አብረው መሥራት ይገባቸዋል::

ስለሆነም የዕለት በዕለት መረጃ ልውውጥ ይሻሉ:: ባጭሩ በተሻለ ሕይወት ለመኖር፣ ጠቅላላ ሰብእናችንን የተሟላ ለማድረግና ለሀገራችን ጠቃሚ ዜጎች ለመሆን መረጃን በበቂ ደረጃ ማግኘት አስፈላጊ ነው::

ሆኖም መረጃ ማግኘቱ ብቻውን በቂ አይደለም:: የምናገኛቸውን መረጃዎች በተመለከተ ሦስት አጠቃላይ ጥንቃቄዎችን ማድረግ አለብን:: አንደኛው ማንኛውንም መረጃ በሰነድነት ለማቆየት መጣር ነው:: ለምሳሌ እናንተ በት/ቤታችሁ ውስጥ ያሉትን ተማሪዎች በጾታ፣ በዕድሜና በትምህርት ደረጃ መዝጋባችሁ ይዛችኋል? የአካባቢ ያችሁን የአየር ሁኔታስ እየተከታተላችሁ ትመዘግባላችሁ?የራሳችሁንና የቤተሰባችሁን የጤንነት ሁኔታስ በየጊዜው ማስታወሻ ትይዛላችሁ? እነዚህ ሁሉ በጣም ጠቃሚ መረጃዎች መሆናቸውን አትርሱ::

ሁለተኛው ቁምነገር፣ መረጃዎች ስንወስድ ከተገቢ ምንጭ ማግኘታችንን እርግጠኞች መሆን አለብን:: ለምሳሌ የዘንድሮው የዞናችን የአየር ሁኔታ ምን ሊመስል እንደሚችል ማወቅ ስንፈልግ የምናገኘው ከሜትሮሎጂ ባለሙያ መሆኑን መገንዘብ ይገባል። አንዳንድ ሰዎች በግምት “ዝናብ ሊዘንብ ይችላል” ቢሉን እውነት ነው ብለን ልንቀበል አይገባም::

ስለትምህርታችንም ቢሆን መጻሕፍትን ስንጠቀም በቂ ዕውቀት ያላቸው ምሁራን የጻፏቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ይሆናል:: ምክንያቱም አንዳንድ ሰዎች ለንግድ ብለው የሚያሳትሟቸው ሥራዎች አስተማማኝ ዕውቀት ሊሰጡን የማይችሉ ሊሆኑ ይችላሉ::

ሦስተኛው ነገር ያገኘናቸውን መረጃዎች ባግባቡ መያዝንና በሥራ ላይ ማዋልን ይመለከታል:: በራሳችን ጥረት ከልዩ ልዩ ምንጮች የምንሰበስባቸውንም ሆነ ሌሎች አጠናቅረው ያቀረቡልንን መረጃዎች ሥርዓት ባለው መንገድ መያዝና መጠበቅ አለብን:: መረጃዎቹ በምሥጢር መያዝ ያለባቸው ሆነው ከተገኙም ምስጢሩን ለመጠበቅ ታማኞች መሆን ይገባናል:: ሊሰረቁ ወይም ሊባክኑ ስለሚችሉ አቀማመጣቸውን በተመለከተ ማሰብ ያስፈልገናል::

ለዚህም ከጽሑፍ የምናገኛቸውን መረጃዎች በልዩ ማስታወሻ ላይ ምንጫቸውን እየጠቀስን ማስፈር ተገቢ ነው:: በቃለ መጠይቅ መልክ ያገኘናቸው ከሆኑም በመቅረጸ ድምጽ ወይም በቪዲዮ ካሴት ቀርጸን በሰነድነት መያዝ ይኖርብናል:: ስለሆነም አንድ ጨዋና ኀበዝ ተማሪ መረጃዎችን በጥንቃቄ ማግኘት የሚገባው ሲሆን የሚያገኛቸውን መረጃዎች በጥንቃቄ መያዝ ይገባዋል።

**መልመጃ 4**

*ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶች ስጡ::*

1. መረጃዎችን ከምን ከምን ምንጬች ማግኘት ይቻላል? በበለጠስ መረጃ ለማግኘት የሚያስችለን ቦታ የት ነው?
2. መረጃዎችን ከማግኘት ጎን ለጎን ማድረግ የሚገባን ጥንቃቄ ምንድን ነው?
3. መረጃ በዘመናዊ አኗኗር ውስጥ ወሳኝ የሚሆነው ለምንድን ነው?

## 11.3 ኋላቀር አስተሳሰብና ትምክህተኛ አባባሎች

### 11.3.1 በአካባቢ የሚነገሩ ኋላቀርና ትምክህተኛ አባባሎች

- አንድን ሰው ኋላቀር አስተሳሰብ አለው ስንል ምን ማለታችን ነው?
- በአካባቢያችሁ የምታስተውሏቸው ኋላቀር አመለካከቶች ያሏቸው ሰዎች አሉ? እነዚህ ኋላቀር ያላችኋቸው አመለካከቶቻቸው በምን በምን መንገድ የሚንጸባረቁ ናቸው?

### ፊታውራሪ መሸሻና ወይዘሮ ጥሩዓይነት፣

ፊታውራሪ መሸሻና ሚስታቸው ወይዘሮ ጥሩ ዓይነት በዘር ያክለናል ይመስለናል የማይሉት ሰው ልጃቸውን ለጋብቻ ሲጠይቅ እንኳን ለመ ስጠት መጠየቃቸውን እንደ ውርደት እየቆጠሩ እጅግ ያዝኑ ነበር።

"ወዬው ጉድ ጆሮ አልሰማም አይልምኮ!" ይላሉ ፊታውራሪ።

"ዛሬ ደግሞ ምን ሰሙ ጌታዬ?" ሲሉ ይጠይቃሉ ባለቤታቸው።

"ቀኛዝማች እገሌ ሰብለወጌልን ለልጁ ለመነኝ"
"ቀኛዝማች እገሌ የማን ልጅ ነው?" በማለት ባለቤታቸው ይጠይቃሉ።
"አባቱን እንኳዋን እኔ እሱም አያውቀው።"
"ትልቅ ድፍረት ነው!" በማለት ይቆጣሉ ወይዘሮ ጥሩዓይነት።
በሌላ አጋጣሚ ደግሞ ፊታውራሪ፣ "ግራዝማች እገሌ ልጅህን ስጠኝ አለኝኮ ጥሩ!" ይላሉ።
"የማን ልጅ ነው ጌታዬ?"
"አባቱ ሰው አይደለም፤ ገበሬ ነው!"
"ምነው ይህን ሳልሰማ በሞትሁ!" በማለት ጥሩዓይነት ያማርራሉ።



*ሥዕል 11.9 ባልና ሚስት በውይይት ላይ*

"ባላምባራስ እገሌ ልጅህን ስጠኝ ብሎ አማላጅ ላከብኝኮ፣ ሀ .. ሀ... ሀ ... ወይ ጊዜ!"
"የማን ልጅ ነው?" በማለት ጥሩዓይነት ይጠይ ቃሉ።
"አባቱ ብዙ ላም የነበረው ባለጌ ባላገር ነበር። እሱ ላሙን ሁሉ አውርሶት ሞተ። አሁን አን ቱን እየጠጣ ሆዱ ሲነፋ ጊዜ ከሰው እኩል የሆነ መስሎት ይኼዋ የኛን ልጅ ይለምን ጀመር።"

"ይበለን፣ ኧረ ይበለን ሲያንሰን ነው፣ ሲያንሰን ነው፤ እንደታሰርን ሁሉ ይህን አገር መልቀቅ አቅቶን የባላገር መጫወቻ ሆንን።" ይላሉ ወይ ዘሮ ጥሩ ዓይነት።

"ታዲያ ለነዚህ ልጄን ልስጥ? የእሌኒን፣ የገላውዴዎስን ልጅ ለገበሬ፣ ለነጋዴ ልስጥ? እነሱ ባያዩ ባይሰሙ አጥንታቸው አይከሰኝም? አይወቅሰኝም?" ይላሉ ፊታውራሪ።

"እርስዎም ልስጥ ቢሉ እኔን መቃብር ሳይጫነኝ ልጄ አጥንተ ሰባራ አታገባም። እንዲያውም አላቻዋ አግብታ ዘር ከምታበላሽ የሚያክላት-የሚመስላት አጥታ ሳታገባ ቀረች ቢባል ክብሯን ይጨምረዋል።"
"እውነትሽ!" ይላሉ ፊታውራሪ።

*(ፍቅር እስከ መቃብር፣ ገጽ 86-87 በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ)*

**መልመጃ 5**

***በምንባቡ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄ ዎች ተገቢ መልሶችን ስጡ።***

1. በገጸባሕርያቱ ንግግር ውስጥ የኋላቀር አስተሳሰብን የሚያንጸባርቁት የትኞቹ አገላለጾች ናቸው? እንዴትስ ኋላቀር ሊባሉ ይችላሉ?
2. በፊታውራሪና በወይዘሮ ጥሩዓይነት አስተ ሳሰብ ውስጥ የሴትን ልጅ መብት የሚጋፋ የትምክተኝነት አቋም ይታያል? እንዴት?
3. እነፊታውራሪ እንደሚሉት ከሆነ፣ በሰው ልጆች መካከል የዘር መበላለጥ አለ ማለት ይቻላል?

ኋላቀር አስተሳሰቦች ብዙውን ጊዜ ከነባሩ ባህልና እምነት በቃልና በተግባር እየተወራረሱ ይሸጋ ገራሉ። ይህም ማለት አያቶች ወይም ከእነሱ በፊት የነበሩ ትውልዶች በዘመናቸው ያምኑብ ትና ይመሩበት የነበረውን የሕይወት ፍልስፍና ወይም ሕዝባዊ አመለካከት በሚቀጥለው ትው ልዳቸውም ውስጥ እንዳይሻር አድርገው በቃልና በድርጊት ያወርሳሉ።

እነዚያ በዚያ ዘመን በብዙኃኑ ተቀባይነት ያገኙ የሚመስሉት አመለካከቶች ግን በቀጣዮቹ ትውልዶች አፍራሽ ስለሚሆኑ ላይሠሩ ይችላሉ:: ለምሳሌ ከፍ ሲል ያየነው የፊታውራሪና የባለቤታቸው የሕይወት ፍልስፍና በጥንት ዘመን በሕዝቡ ላይ ተጭኖ ሲኖር እውነት መስሎ ይታይ ነበር:: ነገር ግን የሰዎች ንቃተ ሕሊና እየጨመረና አስተሳሰቡም እየተለወጠ ሲመጣ፣ የቀደመው አመለካከት ፍጹም ኋላቀርና በትምክህት የተሞላ ይሆናል::

አሁን ባለንበት ዘመን ሴት ልጅ በቤተሰቧ ፍቃድ ለባል መሰጠት የለባትም እንላለን:: ትምህርቷን ያለተጽዖኖ የመማርና ትምህርቷን ስትጨርስም የማንም ግዴታ ሳይጫናት ዕድሏን መወሰን ትችላለች:: በዘመናችን የዘር ምርጫም የትም አያደርስም:: ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በሕግ ፊትም ዕኩል ነው:: ሙያውም የተከበረ ነው::

በየአካባቢያችን በርካታ ኋላቀር አመለካከቶች መኖራቸውን አስቀድመን ማስተዋል ይገባናል:: ይህም ጥንቃቄ እንድናደርግ ብሎም እንድናርማቸው ዕድሉን ያሰፋልናል:: እነዚህ በአካባቢያችን የሚኖሩት ኋላቀር አመለካከቶች ሕሊናዊ መልክ ቢኖራቸውም፣ የሚንጸባረቁባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ::

በተለይ የሚንጸባረቁት በምሳሌያዊ ንግግሮች፣ በተረቶች፣ በፌዝ መሰል አነጋገሮች፣ በቀልዶች እንዲሁም በእምነቶች ውስጥ ነው:: ዘርን ከዘር የሚያበላልጡ እንደ "የትልቅ ሰው ዘር"፣ "የልዑላን ቤተሰብ"፣ የመሳሰሉት አገላለጾች ዛሬም ቢሆን ይስተዋላሉ:: በዘር መካከል ያለውን ልዩነት የሚጠቁሙ መሆናቸውን ልብ ማለት ያሻናል:: አንዳንድ ሰዎች መልክ፣ ሀብት ወይም ዕድል ከሰዎች መካከል ለተወሰኑ ዘሮች ብቻ በጸጋ የሚሰጡ እንደሆኑ ዛሬም ያምናሉ::

ስለሥራም ቢሆን እንዲሁ የተዛቡ አመለካከቶች በብዛት አሉ:: የተወሰነ የሰው ዘር ብቻ ገበሬ ወይም ነጋዴ ሊሆን እንደሚገባ፣ የትልቅ ሰው ዘር ግን እነዚህ ሙያዎች እንደማይመጥኑት የሚናገሩ፣ የሚተርቱ ወይም የሚቀልዱ ሰዎች ይስተዋላሉ:: እነዚህ ሁሉ የትምክህት አመለካከቶች ታዲያ ምንም ሳይንሳዊ መሠረት የሌላቸው ናቸው፤ ወደ ትውልድ እንዳይተላለፉ መወገድ አለባቸው::

ምክንያቱም አመለካከቶቹ በሕዝቦች መካከል ሊኖር የሚችለውን ፍቅርና መቻቻል ይጎዳሉ:: ፍትሐዊ አመለካከትንም ያበላሻሉ:: በሂደትም የሀገርን ሠላም የሚያናጉና አንድነትን የሚሸረሽሩ መጥፎ ሁኔታዎችን ሊፈጥሩ ይችላሉ:: በመሆኑም አስቀድመን ልንዋጋቸውና ልናስወግዳቸው ይገባል::

**መልመጃ 6**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::*

?

1. ኋላ ቀር አስተሳሰቦች በሕዝቦች ሠላም ላይ ምን ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ?
2. ሰዎች በኋላቀር አመለካከት የሚጠቁት ከምን የተነሳ ነው?
3. በሳይንሳዊ አስተሳሰብ መጎልበት ከኋላ ቀር አስተሳሰቦች ለመላቀቅ እንዴት ይረዳል?

## 11.4 የተለያዩ መጻሕፍትን ማንበብ

### 11.4.1 የንባብ ልምድን ማበልጸግ

- ንባብ ምንድን ነው?

ንባብ የዕውቀት መሣሪያ ነው:: መምህራን የሚነግሩንን ብቻ ሳይሆን፣ በየበኩላችን ብዙ አንብበን ዕውቀትን የምናዳብርበት መሣሪያ ነው:: በዚህ መሠረት ሰፊ የንባብ ልምድ ሊኖረን ይገባል::

ንባብ የራሱ የሆነ ሳይንስ አለው:: ማንበብ የሚገባን የምንማረውን ትምህርት ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ ማጣቀሻ መጻሕፍትንም ማንበብ ይጠበቅብናል:: ለምሳሌ መምህራችን ስለሰላም ጥቅም አስተምረውን ከሆነ ከክፍል ስንወጣ ስለ ሰላም የተጻፉ ሌሎች መጻሕፍትን ፈልገን ማንበብ አለብን፣ ያኔ ዕውቀታችን ሥር የሰደደ ይሆናል::

ጋዜጦችንና መጽሔቶችንም ማንበብ አለብን:: ለንባብ ጊዜና ቦታ መወሰን አስፈላጊ ቢሆንም፣ እነዚህን ነገሮች አመካኝቶ ከንባብ መዘናጋት ግን አያስፈልግም:: የማንበብ ልምድ ካለን በማንኛውም

ቦታ ማንበብ እንችላለን:: ለምሳሌ በዛፍ ሥር፣ በታክሲና በአውቶቡስ ላይ፣ በሳሎን ውስጥ፣ በመኝታ ቤታችንና በሌሎችም ሥፍራዎች ማንበብ እንችላለን:: ታላላቅ የምንላቸው የሀገራችንና የዓለም ሰዎች ለዚህ ታላቅነታቸው የበቁት ብዙ ከማንበብና ነገሮችን በጥልቀት ከመመርመር ነው:: እናንተም ሀገራችሁን ለማስጠራት የማንበብ ልምድ ማዳበር አለባችሁ::

**መልመጃ 7**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::*

?

1. ንባብ የዕውቀት መሣሪያ ነው ሲባል ምን ማለት ነው?
2. የንባብ ልምድን ለማዳበር ምን መደረግ አለበት?

### 11.4.2 የትምህርት አጠናን ሥልቶችን መቀየስ

- እናንተ ጥናታችሁን የምታካሂዱት እንዴት ነው?

**የግርማይ የአጠናን ብልሃት፤**

ግርማይ የሚባለው ተማሪ ዘወትር ለረጅም ሰዓታት ያጠናል:: አንዳንድ ቀን ሌሊቱን በሙሉ ነው የሚያጠናው:: ሆኖም "እንዲህ እያጠናሁ ለምን በጣም ጥሩ ውጤት አላመጣም" እያለ ዘወትር ይበሳጫል:: ዓላማው አንደኛ በመውጣት የሚበልጡትን የክፍል ጓደኞቹን ማስቀናት ነበር ግን አልሆነለትም::

በኋላ ግን ግርማይ የአጠናን ሥልቱን መቀየር አሰበ:: እንደበፊቱ በአንድ ቀን በርካታ ሰዓታት አንድ ትምህርት ብቻ ማጥናቱን ትቶ፣ የጥናት መርሐግብር አወጣና እያንዳንዱን ትምህርት በየጊዜው ለተወሰነ ጊዜ ማጥናቱን ቀጠለ:: በጥናት መርሐግብሩ መሠረትም ለእሱ ከበድ ለሚሉት እንደ ሒሳብና ሳይንስ ላሉት ትምህርቶች በመጠኑ ሰፋ ያለ ጊዜ መደበ::

ከዚህም አልፎ እነዚህን ትምህርቶች በየቀኑ ለተወሰኑ ጊዜያት የግድ ማጥናት እንዳለበት አቋም ያዘ:: በተለይ የሒሳብ ትምህርቱን ገና ከት/ቤት እንደመጣ ወይም ከክፍል እንደወጣ መከለስ እንዳለበት ወሰነ:: ግርማይ በዚህ ሂደት በማጥናቱ እነሆ ያሰበውን አሳካ። በአንደኛው መንፈቀ ዓመት አንደኛ በመውጣቱም በጣም ተደስቷል::

**መልመጃ 8**

*በምንባቡ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶች ስጡ::*

?

1. ከግርማይ የጥናት ሂደት ምን ትማራላችሁ?
2. አንድን ትምህርት ብቻ ለደቶ ማጥናት ወይም በአንድ ቀን ለብዙ ጊዜያት ማጥናት ውጤታማ ያደርጋል ትላላችሁ? ለምን?
3. የጥናት መርሐግብር ማውጣት ጥቅም ይኖረዋል? እንዴት?

ስለጥናት ስንነጋገር አስቀድመን ማንሳት ያለብን ጥቅሙን ነው:: የጥናት ዋናው ጥቅሙ ላቅ ያለ ዕውቀት የሚያጎናጽፍ መሆኑ ነው:: ላቅ ያለ ዕውቀት ያለው ሰውም በትምህርቱ ትልቅ ደረጃ ላይ ይደርሳል:: ያኔም ሀገሩንና ራሱን በሚገባ ይጠቅማል::

ራሱን ይጠቅማል ስንል በትምህርቱ ውጤታማ ይሆናል፤ ጥሩ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ሊይዝ ይችላል ማለታችን ነው:: በሌላ በኩል ሀገሩንም የሚጠቅም ጠንካራ ሐኪም ወይም ታዋቂ መምህር ወይም ሕዝቡን የሚወድ የፖለቲካ መሪ ሊሆን ይችላል:: በዕውቀት ለመበልጸግ ታዲያ ዋናው ጉዳይ ጠንክሮ ማጥናት ነው:: ጥናቱም በዘፈቀደ የሚከናወን ሳይሆን በዕቅድ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። ጠቅላላ ዕውቀትንና መረጃዎችን ለማግኘት የምናነበው ንባብና የጥናት ንባብ መጠነኛ ልዩነት አላቸው::

ለጠቅላላ ዕውቀት ወይም መረጃ ወስደን ለመሔድ ስናነብ የተለየ መርሐግብር ማውጣት የግድ አይደለም:: ለጥናት ንባብ ግን የጥናት መርሐግብር መዘርጋት አለብን:: መርሐ ግብሩንም ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልገናል:: ባጠቃላይ ስለጥናት ስናስብ ነገሮችን ከልዩ ልዩ አቅጣጫ ማጤን ይኖርብናል:: የምናጤናቸውን ነገሮች ቀጥሎ እንመልከት::

1. **የጊዜን ፋይዳ ማወቅ፣** ምሁራን እንደሚ መክሩት ጥናታችንን ስናስብ የሚያመችንን ጊዜ መምረጥ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ እንቅልፍ ወይም መሰላቸት በሚሰማን ወቅት ማጥናት እንደሌለብን ይመከራል፡፡ ስለሆነም የእንቅልፋችንን መደበኛ ሰዓት ለይተን ማወቅና በዚያ ሰዓት መተኛት ተገቢ ነው። ጥናት በአዲስ መንፈስ መካሄድ አለበት። ከዚሁ ጋር መታየት ያለበት የምናጠናበት የጊዜ ርዝመት ነው፡፡ ለረጅም ጊዜ ስላጠናን ብቻ ትምህርት ሊገባን አይችልም፡፡

2. **ከሰዎች ጋር መሥራት መልመድ፣** በጥንድ ወይም በቡድን ሆኖ መወያየትና መከራከር ለጥናት በጣም ጠቃሚ እንደሆነ የስነልቡና ምሁራን ይመክራሉ፡፡ እኛ ለጓደኞቻችን ስናስ ረዳ ወይም ጓደኞቻችን ሲያስረዱን ዕውቀት የተሻለ ተጨባጭና ግልጽ ይሆናል፡፡

3. **አመች የጥናት ሥፍራ መምረጥ፣** በግል የም ናጠና ከሆነ ጸጥታ ያለው ቦታ ተመራጭ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው አንዳንድ ነገሮች ቀልባችንን እንዳይሰርቁት ነው፡፡ ይሁንና በማ ንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆነን ስናጠና ሥዕ ሎች ባሉበት ቦታ ወይም የተለየ ጠንካራ ሽታ በሚሰማን ቦታ መቀመጥ እንደሌለብን ይመከራል፡፡ እንዲህ ያሉ ነገሮች የማይመ ረጡት ስሜትን ስለሚበታትኑ ነው፡፡ የምና ጠናበት፣ ቦታ በቂ ብርሃን ያለበትና ንጹሕ አየር የሚዘዋወርበት ሊሆን ይገባል፡፡ አለባ በሳችንም ቢሆን ለብርድ ወይም ለኃይለኛ ሙቀት የሚያጋልጥ እንዳይሆን ማድረግ አለብን፡፡ የምንቀመጥበት መቀመጫም ደረቅና ቀጥ ብለን እንድንቀመጥ የሚያስችል መሆን ይገባዋል፡፡

4. **መርሐግብር ማውጣት፣** የጥናት መርሐግብር ለጥናት ሥራ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ ይህም ጥናታችንን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ነገሮችን ለመቆጣጠር ያስችለናል፡፡ እንደገናም ለየት ኛው ትምህርት ሰፋ ያለ ጊዜ መስጠት እንዳ ለብን መንገድ ይመራናል፡፡ መቼም ሁሉንም ትምህርት እኩል ጊዜ ሰጥተን ማጥናት አንች ልም፤ ጠንከር ለሚሉብን ትምህርቶች በመ ጠኑ ሰፋ ያለ ጊዜ መመደብ አለብን፡፡ ይህን ለማድረግ መርሐግብራችን ይረዳናል፡፡

5. **በጥናት ወቅት የሚኖሩ ሂደቶችን መገንዘብ፣**

   **5.1 የገረፍ-ገረፍ ንባብ፣** ጥናት ስንጀምር መጀመሪያ የትምህርቱን ጠቅላላ ይዘት ገረፍ-ገረፍ አድርገን እንመለከተዋለን፡፡ ይህም ሁኔታ ምን ምን መሣሪያዎችን ማዘጋጀት እንዳለብንና ምን ተጨማሪ ነገሮችን ማሟላት እንደሚገባን አቅ ጣጫ የሚሰጠን ነው፡፡

   **5.2 ጥያቄ ማንሳት፣** የትምህርቱን ይዘት ገረፍ-ገረፍ ስናደርግ፣ በዚህ ጥናት ውስጥ ለዚህ ጥያቄ መልስ ማግኘት አለብኝ ብለን መነሻ ሊኖረን ይገባል፡፡ ያንንም ጥያቄ እስከምንመልስ ድረስ ጥናታችንን አናቆምም፡፡

   **5.3 ወደንባብ መግባት፡-** አሁን ወደዋናው የጥናታችን ሥራ ገብተናል ማለት ነው፡፡ ወደ ንባብ መግባት፤ አሁን ወደ ዋናው የጥናታችን ሥራ ገብተናል ማለት ነው፡፡ ይህ ደረጃ የተለያዩ ጭብጦችን እየቀሰምን የምንገሰግስበት ነው፡፡ እናም በጽሞና ሆነን ፍሬ ነጥቦችን መቅሰም እንሞክራለን፡፡

   **5.4 ተግባራዊ አቅጣጫን ማየት፣** ፍሬ ጉዳዮ ቹን በምንቀስምበት ወቅት ይህን ትም ህርት በሕይወታችን ውስጥ እንዴት በተግባር ልንገለገልበት እንደሚገባን ማሰብ ጥሩ ነው፡፡ ለምሳሌ የምናጠ ናው ስለጓሮ አትክልት ቢሆን እኛም በግቢያችን ውስጥ በሳይንሳዊ መንገድ እንዴት አትክልት ልናለማ እንደም ንችል ማሰብ ለትምህርቱ ጥልቀት በጣም ይረዳል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ደረጃ ላይ ትምህ ርቱ ምን ያህል እንደገባን ራሳችንን በመገ ምገም ጥናቱን ከተግባር ጋር ለማጣጣም እንሞክራለን፡፡

**መልመጃ 9**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ጠንክራችሁ በመማር ሂደት ውስጥ ንባብ ያለው ድርሻ ምንድን ነው ትላላችሁ?
2. ለማንበብ የተወሰነ ቦታ መምረጥ የግድ አስፈላጊ ነውን? እንዴት?
3. በጥናት ውስጥ የጊዜን ፋይዳ ማወቅ ሲባል ምን ማለት ነው?
4. እስከዛሬ ከትምህርታችሁ ወጣ ያሉ ጉዳዮችን የተመለከቱ ነገሮች አንብባችሁ ታውቃላችሁ? እነሱን በማንበባችሁስ ምን ጥቅም አገኛችሁ?
5. በምታጠኑበት ጊዜ በሚከተሉት ደረጃዎች ላይ ምን ማድረግ ይኖርባችኋል?
   ሀ. ገረፍ-ገረፍ ንባብ፣
   ለ. ጥያቄ ማንሳት (ጥየቃ)፣
   ሐ. ተግባራዊ አቅጣጫን ማየት፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ሳይንሳዊ አስተሳሰብ በተለይ ከት/ቤት፣ ከንባብ፣ ከምልከታ፣ ከምርምር ምንጮች የሚገኝ ነው፡፡ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ራሳችንንና አካባቢያችንን ለመለወጥ የሚያስችለን ትልቅ መሣሪያ ነው፡፡

ተጨባጭ ባልሆኑ ግምቶችና ልማዶች መመራት ለኋላቀር አመለካከት ተገዥ እንደሚያደርገን ሁሉ፣ ዘርን ወይም የመደብ ክፍልን ወይም ሙያን መነሻ አድርገን ከሁሉ እንደምንበልጥ ወይም እንደምናንስ ማሰብም ተገቢ አይደለም፡፡ እንዲህ ያለ አመለካከት ካለን ራሳችንን ለመለወጥና ሀገራችንን ለማልማት የምናደርገውን ጥረት ያሰናክልብናል፡፡

ጥናት ተገቢውን ዕውቀት በወቅቱ ለመጨበጥ የሚያስችል ሂደት ነው፡፡ ለጥናት ውጤታማነትም ዕቅድና ግብ ያስፈልገዋል፡፡ ለጥናት የሚያስፈልጉንን ነገሮች ማሟላትንም ይጠይቃል፡፡ ጥናቱን ስንጀምር አስፈላጊ ሁኔታዎችን ሁሉ ማሟላት ይጠበቅብናል፡፡ ጥናታችንን ስናጠናቅቅ ደግሞ በልዩ ልዩ መልክ የራሳችንን አጠቃላይ አቋምና ያጠናነውን ትምህርት ፋይዳ መገምገም አለብን፡፡ እንዲህ ስናደርግም ትምህርቱን ወደተግባር ማሸጋገርና በእሱም መገልገል እንችላለን፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

| | |
|---|---|
| **ሳይንስ፣** | በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሠረተ ዕውቀት የሚገኝበት የፍተሻ መስመር፡፡ |
| **ኢመደበኛ መረጃ፣** | ት/ቤት ሳንገባ፣ ሥርዓተ ትምህርት ሳይኖረው በየአጋጣሚው ከተለያዩ ምንጮች የምናገኘው መረጃ። |
| **ትምክህተኛነት፣** | በዘር ወይም በመደብ ከሌሳው ሁሉ እበልጣለሁ፤ ከእኔ የሚስተካከል የለም ብሎ የመኮፈስ ሥነልቡና፡፡ |
| **ፍተሻ፣** | ነገሮችን፣ መረጃን፣ ዕውቀትን እየመሳለሱ የመመርመርና እርግጠኝቱን የማረጋገጥ ሂደት፡፡ |
| **ጥናት፣** | ንድፈ ሐሳቦችን በጥልቀት *ለመረዳት* የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን እየፈተሹ-እየመ ረመሩ በማጤን ጽሞናን የተሳበሰ ዕውቀት የማካበት ሂደት፡፡ |
| **የገረፍ-ገረፍ ንባብ፣** | ከሚጠናው ትምህርት ጋር የመተዋወቂያ ንባብ ማድረግ። |

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ።*

## I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ።

1. ከኋላቀር አመለካከቶች መካከል አንደኛው ትምክህተኝነት ነው።
2. ሳይንስና ዕውቀት ሲስፋፋ የትምክህተኝነት አመለካከትም ሥር እየሰደደ ይሄዳል።
3. ሕይወትን በተሻለ መንገድ ለመምራት ሳይንሳዊ የሆነ ዕውቀት ያስፈልጋል።
4. ንባብ ግማሽ የሚሆነውን የሰብእናችንን ክፍል የሚገነባ ክሂል ነው ለማለት ይቻላል።
5. አንድ ትምህርት ብቻ በማጥናት ብዙ ሰዓትን ማጥፋት ተገቢ አይደለም።

## II. በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን በ "ሀ" ሥር ካሉት ሥር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የሳይንሳዊ አመለካት ዋናው ምንጭ፣ | ሀ. ሴት ልጅን ማስተማር ጥቅሙ የሁሉም ነው። |
| 2. የገረፍ-ገረፍ አጠናን ፋይዳ፣ | ለ. የትምህርቱን ባሕርይ የመተዋወቅ ሥራ ነው። |
| 3. የጥናት መርሐ ግብር፣ | ሐ. የትምህርቱን ባህርይ ለመቃኘት ይረዳል። |
| 4. ገረፍ-ገረፍ ማድረግ፣ | መ. የጥናት ጊዜን ባግባቡ ለመጠቀም ያግዛል። |
| 5. የዘመናዊ አባባል ምሳሌ፣ | ሠ. ትምህርት በትኩረት የሚነበብበት ሂደት። |
| | ረ. ትምህርት ቤት። |

## III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ።

1. ትምክህተኛ አስተሳሰቦች ሊቀየሩ የሚችሉት መቼ ነው?
   - ሀ. ትውልድ በሳይንሳዊ አስተሳሰብ ሲታነጽ፣
   - ለ. ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሲበለጽግ፣
   - ሐ. ትምህርት ቤቶች ሲስፋፉ፣
   - መ. ሁሉም።
2. ስለጥናት መርሐግብር ትክክል የሆነው የትኛው ነው?
   - ሀ. የጥናት መርሐ ግብር ማውጣት ያለብን በትምህርት ቤት ብቻ ለማጥናት ነው፣
   - ለ. ለትምህርት መዘጋጀት ያለበት የፈተና ሰሞን ነው፣
   - ሐ. ትምህርቶቻችንን ከሥር-ከሥር ልናጠና የሚያስችለን መሆን አለበት፣
   - መ. ከጓደኞች ጋር የማጥናት ልምድን ማካተት የለበትም።
3. ከሚከተሉት መካከል ሰፋ ያለ የጥናት የመረጃ ምንጭ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?
   - ሀ. ቴሌቪዥን ለ. ሬዲዮ ሐ. ቤተ መጻሕፍት፣ መ. ጋዜጣ

4. በጥናት ጊዜ ማስታወሻ የመያዝ ጥቅም ምንድነው?
   ሀ. ያልገቡንን ጉዳዮች ለውይይት ለማቅረብ፣
   ለ. የድርሰት ችሎታን ለማሻሻል፣
   ሐ. ትምህርቱን ምን ያህል እንደተረዳን ለመገምገም፣
   መ. ሀ እና ሐ
5. ከሚከተሉት መካከል የትምክህተኝነት አስተሳሰብ የሚስተዋልበት የትኛው ነው?
   ሀ. ወይ ካለው ተወለድ ወይ ካለው ተጠጋ፣
   ለ. ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ፣
   ሐ. ሴትን ልጅ ማስተማር ሁሉንም ይጠቅማል፣
   መ. ሀ እና ለ

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ፡፡

1. __________ተገቢውን ዕውቀት በወቅቱ ለመጨበጥ የሚያስችል ሂደት ነው፡፡
2. _______ ፣ __________ ፣ _________ እና __________በጥናት ወቅት የሚኖሩ ሂደቶች ናቸው።

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. የሳይንሳዊ ዕውቀት መሠረታዊ ጥቅሞች ምንድንናቸው?
2. ኋላቀር አስተሳሰብ ለሀገር ሠላም ጎጂ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?
3. በጥናት ሂደት ወቅት ጥየቃ ምን ፋይዳ አለው?
4. ኋላቀር አመለካከቶችን ለማስወገድ ወጣቶች ሊጫወቱ የሚችሉት ሚና ምንድን ነው?